# እመጓ



ዓለማየሁ ዋሴ እሸቴ

3ኛ ዕትም 2008 ዓ.ም.

# እመጓ

ዓለማየሁ ዋሴ እሸቴ (ዶ/ር)

3ኛ ዕትም 2008 ዓ.ም

Brought to you by: Ethiopian Bookstore
https://t.me/etbookstore

© ዓለማየሁ ዋሴ እሸቱ

2008 ዓ.ም.

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

ALL RIGHTS RESERVED

አድራሻ

ዓለማየሁ ዋሴ እሸቱ (ዶ/ር)

☎ +251 0935 86 02 67

E-mail:- Emegua2015@gmail.com

ባሕር ዳር

ኢትዮጵያ

ለሲሳይና

ለሙኒት

# ምዕራፍ አንድ

ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ስደረስ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ተኩል ሆኖ ነበር። ከመኪና እንደወረድኩ ሻንጣዎቼን አውርጄ ለእነርሱ በተዘጋጁ ጋሪዎች ላይ አድርጌ እየገፋሁ ወደ ውስጥ በፍጥነት ገሰገስኩ። ከዚህ በፊት ዓለም አቀፍ በረራ አድርጌ የማላውቅ እስከሚመስል ድረስ ከነበርኩበት የመቸኮልና ግራ የመጋባት ስሜት ውስጥ የመለሰኝ ‹‹አንተን እኮ ነው! አትሰማም እንዴ ትኬትክን አሳይ እኮ ነው የምልህ!›› የሚለው ቁጣን ያዘለ የአንድ ሴኩሪቲ ንግግር ነበር። ከሃሳቤ በፍጥነት ተመልሼና ደንገጥም ብዬ ይቅርታ ጠይቄ ትኬቱን ከፓስፖርቴ ጋር በአንድነት ሰጠሁት።

‹‹እያዳመጥክ አትሄድም እንዴ! ምን ሆነሃል›› አለኝ።

በማፈር ስሜት ውስጥ ሆኜ ይቅርታ ስጠይቀው ትኬቱን በፓስፖርቴ ውስጥ አድርጎ ፊት ፊቴን አተኩሮ እያየ መለሰልኝ። ምን ሆኜ ነበር እያልኩና ራሴን እየወቀስኩ ስገባ ነበር ቦሌ ድረስ ያደረሰኝን ተክሌን እንኳ ሳልሰናበተው እንደገባሁ ያስታወስኩት። ከሀሳቤ ራሴን እንደ ምንም አረጋግቼ የበር ላይ ፍተሻውን አልፌ ወደ ውስጥ በመዝለቅ ካሉት የመንገደኞች ማስተናገጃ ዴስኮች ወደ አንዱ ወረፋዬን ጠብቄ ጠጋ አልኩ።

“ጤና ይስጥልኝ? ወዴት ነው የሚሄዱት!” አለችኝ ወጣቷ የአየር መንገድ ሠራተኛ።

“ወደ ዋሽንግተን ነው” አልኩኝና ፓስፖርቴንና ትኬቴን ሰጠሁ። ቪዛና ትኬቴን ከመረመረች በኋላ የኮምፒውተሩን ቁልፍ እየነካካች፣

“የት ነው የሚያርፉት?” አለችኝ

“ለጊዜው ማረፊያዬን አላወኩትም፤ እዛው ስደርስ ሆቴል ፈልጌ ነው የማርፈው” አልኩኝ።

“ከጉዞው በፊት ማረፊያዎትን ካላወቁ ሲስተሙ መሳፈሪያ ቅጽ Boarding Pass/ ለማውጣት አይችልም” አለችኝ።

“እንዴ! ታዲያ ያላዘጋጀሁትን አሁን ባለቀ ሰዓት ምን አደርጋለሁ?” አልኳት።

“አዝናለሁ ምናልባት ዘመድ ወይም ጓደኛ ዋሽንግተን ካለዎት ስልክ ደውለው አድራሻ መቀበል ይሻላል” አለችኝ።

“ኧረ እኔ የማውቀው ማንም የለኝም፣ ስም ባስታውስም ስልክ የለኝም”።

“ባውቅስ ድንገት ደውዬ ልመጣ ነው የቤትህን አድራሻ ስጠኝ ብል ምን ይባላል?” አልኩኝ በሃሳቤ።

እዛው እንደቆምኩ በሃሳብ መንጉዴን አይታ፡-

“ይቅርታ ሌላ መንገደኛ ማስተናገድ ስላለብኝ ቦታውን ቢለቁልኝ?” አለችኝ በታላቅ ትሕትና።

እሺ አልኩና ቀልጠፍ ብዬ ወደ ኋላ አፈገፈኩ።

ወዲያው አንድ ዘዴ መጣልኝ። በእጄ ያለው ሞባይል ሽቦ አልባ ወይም መደበኛ ስልክ ባለበት አካባቢ ኢንተርኔት ማየት ያስችላል። ወዲያው "Washington + Hotel" የሚል ፃፍኩና ጉግልን እንዲፈልግ ገፋሁት። ወዲያው በርካታ ሆቴል እስከ አድራሻው ይዞ ብቅ አለ። አንዱን መረጥኩና ወደ ካውንተሩ ጠጋ ብዬ አንዱን አድራሻ ነገርኩ:: የኮምፒውተሩን ቁልፍ ስታንቋቋ ቆየችና፦

"ሻንጣዎን እዛ ጋ ያድርጉት?" አለችኝ። እኔም እንደ ዘንዶ እየተሳበ ከሚሄደው ሽራ መሰል ንጣፍ ላይ አስቀመጥኩ።

"መልካም በረራ" ብላ የመሳፈሪያውን ቅጽ ከጉዞ ሰነዶቼ ጋር መለሰችልኝ።

የእጅ ሻንጣዬን ይዤ ለበረራ ወደምጠባበቅበት ውስጠኛው ክፍል እያመራሁ፥ "አሁን ኢንተርኔት ባይኖር እውነት ሊያስቀሩኝ ኖሯል?! አልኩ ለራሴ። "እንዳው ይህ ኮምፒውተር የሚባል የፍጥነቱን ያክል እጅግ ቀሽም ነው" አልኩ አሁንም ለራሴ። ነገሩ ኮምፒውተሩ ምን አደረገ? እንዲህ እንዲሠራ ወይም እንዳይሠራ ያደረጉት ፕሮግራመሮቹ ናቸው። በቃ ይሄ የሠለጠነው ዓለም ከቴክኖሎጂው ጋር ከንአሠራር ድክመቱ እኛም ጋር ሰተት ብሎ ገባ ማለት ነው? የኅሊና ውስጥ ጥያቄ ነበር። በምዕራቡ ዓለም ቴክኖሎጂውና የሠለጠነ አሠራሩ እንዳለ ሆኖ እንዲህ ዓይነት የሰብአዊነት ዕሴቶችን ማጥፋቱ ግን ከባድ ዋጋ እያስከፈላቸው ነው። አሁን በዚህ ፕሮግራም መሠረት ኮምፒውተሩ ሰዎችን የሚያውቃቸው እንደ ቁጥር ነው። የሚጠይቀውን ስሰጠው ይፈቅድልኛል፤ ካጣም ይከለክለኛል፤ አለቀ በቃ። ሰው ቢሆን ወይም ሰብአዊ ዕሴቶች ባያጠፋ ነሮ ግን ሆቴል ቀድሜ ስለመያዜ ብቻ መንገዴን ሊከለክለኝ አይችልም ነበር።

እርሷስ እንዴት ደውለህ ጠይቅ ትለኛለች? የእጅ ሻንጣየን እየጎተትሁ አመስግና ከሸኘችኝ አስተናጋጅ ጋር በሃሳቤ ሙግት ገጠምሁ። ለምን በሌላ መንገድ አድራሻውን ለመሙላትና ለመርዳት አላሰበችም? በቃ ሰውም እንደ ኮምፒውተር ሰብአዊነቱን ሊተወው ነው ማለት ነው? ምዕራቡ ዓለም የተጎዳው እንዲ በዚህ ነው። አሸባሪዎች ሳይቀር የኮምፒውተር ፕሮግራሞቻቸውን ውሱንነት ስለሚያውቁ ልክ እኔ እንዳደርኩት ከበይነ መረብ አስሰውና ኮምፒውተሩ የሚጠይቃቸውን ሰጥተው አልፈው የሚፈልጉትን አደጋ ለማድረስ የሚችሉት የዘመናዊና ቴክኖሎጂ አገዝ ሥራዎች ሰብአዊ ዕሴት ማጥፋታቸውን እንደ በጎ አጋጣሚ በመጠቀማቸው ነው። ታዲያ ይህ አሠራር እንዳለ እኛ ጋር እየተገለበጠ መምጣቱስ ምን አደጋ ይኖረው ይሆን? ከቀጥታ አደጋቸው ደግሞ ሰውን ራሱ ሰብአዊ ዕሴቱን እያጠፉ መሔዳቸው የበለጠ እያሳሰበኝ ቀሽምነቱንም ከኮምፒዩተሩ ወደ ሰዎች አስተላልፌ ወደ ውስጥ ገባሁ።

የውስጠኛውን ፍተሻ አልፌ ወደ መቆያ ክፍሉ እንደደረስኩ የመሣፈሪያ ጊዜያችን ደርሶ ስለነበር ግቡ ተባልን። ጉዞው የተጀመረው በሰዓቱ ነበር። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ቦይንግ 767 አውሮፕላን እኮብኩቦ ሲነሳ ምንም መንገጫገጭ ሳያሰማ እንደ ነብር ብድግ ብሎ እንደ ንስር መስስ አለ። ከዚያም ከፍታውን በፍጥነት እየጨመረ የግራ ክንፉን ወደ ታች የቀኝ ክንፉን ወደ ላይ አሰደፎ ተንደርድሮ ከተነሳበት ሰሜን ምሥራቅ አቅጣጫ ቀስ በቀስ ወደ ግራ ዘወር በማለት አንዳች የደስደስ ስሜት እየለገሰን ደመናውን እየሰነጠቀ የሰሜን አቅጣጫን ይዞ ወደ ባሕርዳር ከዚያም በካርቱም አድርጎ ወደ ሮም ይከንፍ ጀመረ።

ወደ ተለያዩ ሀገሮች በብዙ አየር መንገዶች ተጉዣለሁ። በኢትዮጵያ አየር መንገድ ስጓዝ ግን የሆነ ደስታና ኩራት ይሰማኛል። በተለይም የአብራሪዎቹ ብቃት፣ ምንም እንኳ እንደኔ ያለ ለአውሮፕላን በረራ ግምገማ ማይም የሆነ ሰው አስተያየት ሊሰጥ የሚችለው ሊያርፍና

ሲነሳ ለተሳፋሪዎች ከሚሰጠው ምቾትና ድምጽ ያሳለፈ ቢሆንም እርሱ እራሱ በአብራሪዎቹ ብቃት ላይ ከፍተኛ መተማመን ስለሚፈጥርብኝ ሁልጊዜም ደስታና ክብር ይሰማኛል። አንዳንዱ እኮ ሲያስነሳው መንጭቆና አፈገምግሞ ስለሆነ ከተነሣም በኋላ ተጋጭቶና ነጥሮ እንደሚመለስ ኳስ ከፍ ዝቅ ሲያደርገው በአየር ላይ ሳይሆን በኮርኮንች መንገድ ላይ የሚነዳ አሮጌ መኪና ያስመስለዋል፤ ሲያሳርፈው ደግሞ የባሰው ሁሉ ይመስላል። በኢትዮጵያ አየር መንገድ አብራሪዎች ግን እንዲህ ያለ ነገር አጋጥሞኝ ስለማያውቅ ሁሌም ደስታ ይሰማኛል። አንዳንድ ጊዜማ በሌላው ሞያና ሥራ ያጣነውን ሙያን በብቃት መፈፀም እነርሱ ያካካሱልኝ ሁሉ ይመስለኛል። በተለይ ከሠለጠነው ዓለም ጋር ተናብበውና በዚያው መጠን የሚያስቡና የሚሠሩ የተለያዩ ባለሞያዎች በግለሰብ ደረጃ ቢኖሩም በተቋም ደረጃ ሠራተኛውን ሁሉ በዚህ አግባብ የሚቀርጽና ሀገራዊ መልክ ያለው ሲታይና አርአያ ሊሆን የሚችል ተቋም የሌለንና የእኛ ሀገር አሰራር ሊሻሻል እንደማይችል ለሚከራከሩኝ አንዳንድ ምዕራባውያን ጓደኞቼ ሁልጊዜም ማሳያዬ ይኼው አንድ ለእናቱ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ነው። ውስጣዊ አሠራሩን ቀርበን ለማየት እድል ባይኖረንም አየር መንገዳችን እንደ ምሳሌ ሲነሣ ግን ብሎዎቹ ከከርከራቸው ጋብ ስለሚሉ ያስደስተኛል።

ረጅም የአውሮፕላን ጉዞ ሳደርግ በተቻለኝ መጠን ዘና ለማለት እሞክራለሁ። እንደ እውነቱ ከሆነ በጣም ዘና የምልበት አጋጣሚ ቢኖር የአውሮፕላን ጉዞ ላይ ነው። ፊልም አያለሁ፣ መጠጥ እጠጣለሁ፣ ምናልባትም ዘና ብዬ ሰው በተሰበሰበት ቦታ አልኮል መጠጥ የምጠጣበት ቦታ ቢኖር በአውሮፕላን ጉዞ ላይ ነው። የአሁኑ ጉዞ ግን ሀሳብ በማውጣትና በማውረድ፣ እንቆቅልሽ ለመፍታት በመታገል የተሞላ ስለሆነ ጉዞዬ እንደ ሁልጊዜው አስደሳች አልሆነልኝም። የምግብና የመጠጥ ፍላጎቴም ጭምር የተዘጋ ነበር። ፊልም ለማየት፣ መጽሐፍ ለማንበብም ብሞክር አሰልቺ ሆነብኝ።

ከግራ ጎኔ በኩል የተቀመጠች ኢትዮጵያዊት ወጣት ዲሲ ደርሷት ለጉሮ ወደ አሜሪካ የምትጓዝ ስለነበረች ከእርሷ ጋር ለማውራት ሞከርኩ። የእርሷን የደስታ ስሜት፣ የህልም እንጀራና ተስፋ ሳዳምጥ ደግሞ "አቤት ሰው መሆን ያለው ፈተና!" አልኩ። ሰው እንጀራ፣ ፍትህ ወይም ሰላም ፍለጋ ሀገሩን ጥሎ ቢሰደድ አያስገርምም። ነገር ግን ሰው እንዴት የትውልድ ሀገሩን ጥሎ ሲሰደድ ያን ያክል ይፈነድቃል። ብቻ ዕድለኛ መሆኗን እየሰበከችልኝ በደስታ ስትቃኝ ከእርሷም ጋር ለመነጋገር ያደረኩት ሙከራ ቁራሽ ያቅለሸልሸኝ ጀመር።

በሀሳብ እየነጎድኩ በምናብ ዓለም ውስጥ ከገባሁበት ክርክርና ውይይት ወጥቼ ፤ ከመጽሐፍ ንባብና ከፊልም ተለይቼ ምን አልባት የተሻለ ይሆናል ብዬ ከጎኔ ከተቀመጠችው እህቴ ጋር የጀመርኩት ውይይት እንዲህ ሲያስጠላኝ መንገዱን የበለጠ አሰልቺ አደረገው። ልረሳው የምፈልገው በውስጤ ያዘልኩትና ገና ኤርፖርት ስደርስ ጀምሮ በሀሳብ ባሕር ያሰጠመኝ ሀሳብም እንደ ናፍቆት ወዳጅ ፊቴ እየመጣ ድቅን ይል ጀመር። እንዲሁ ከራሴ ጋር ስታገል ከአዲስ አበባ ከተነሳን የአምስት ሰዓታት ጉዞ በኋላ አውሮፕላኑ ሮም ሊዮናርዶ ዳቬንቺ አውሮፕላን ማረፊያ አረፈና ትንሽ መለስ አደረገኝ። ከ45 ደቂቃ ቆይታ በኋላም ጉዞአችንን ወደ ዋሽንግተን ዲሲ አደረግን።

ከሮም ከተነሳን ከስምንት ሰዓታት በረራ በኋላ አትላንቲክን አቋርጠን ዋሽንግተን ዲሲ ዳላስ ኢንተርናሽናል ኤርፖርት ደረስን። በሀገሩ ሰዓት አቆጣጠር ከጠዋቱ ስምንት ሰዓት ተኩል ነበር። ግዙፉ አውሮፕላን መሬት ላይ ሳይሆን ውሃ ላይ እንዳረፈ ሁሉ ሳይንገጫገጭ አስፓልቱ ላይ ተንደርድሮ ቆመ። ተሳፋሪው እንደተማከረ ሁሉ አንድ ላይ አጨበጨበ። ከአውሮፕላኑ ስንወርድ በሀሳብ ሲወጣ ሲወርድ የደከመ ሰውነቴን ከውስጤ በተደበቀው ጉጉት አጠንክሬ ብዙም ፓስፖርትና ቪዛ ለማሳየት እረጅም ሰልፍ ጠበቅን። ወረፋዬ ደርሶ ወደ ካውንተሩ ጠጋ ብዬ ፓስፖርቴን ሰጠሁ።

ነጭ ወጣት ነው"ለምን ጉዳይ ነው የመጣህ?" አለኝ።

እራሱን እንደ ገነት በር ጠባቂ የቆጠረ መሰለኝ!

"ለንግድ ሥራ" አልኩት።

"ምን ዓይነት ንግድ?" አለኝ

"የአበባ ንግድ" አልኩ

" እው! ወደ ኔው አርሊያንስ ነዋ የምትሄድ" አለኝ

"አዎን!" አልኩና ገርሞኝ "እንዴት አወቅህ? አልኩት

ፈገግ ብሎ"መረጃው አለኝ፣ ለምን እንደመጣህም አውቅ ነበር" አለ።

"ዓለምን መረጃ ከትንሽ እስከ ትልቁ እየቃረማችሁ መቼም መከራ ሳያመጣባችሁ አይቀርም" አልኩ በልቤ። አሻራዬን ከወሰደና ፎቶግራፍ ካነሳኝ በኋላ መልካም ቀን ይሁንልህ ብሎ ፓስፖርቴን መለሰልኝ።

የጉዞዬ መዳረሻ ግን ገና ነው። በዋሽንግተን አድርጌ ወደ ሉዚያና ግዛት መሻገር ነውና። አሜሪካዊው የደኅንነት ባለሞያ እንዳለው ጉዞዬ ከጓደኞቼ ጋር የኢትዮጵያን የአበባ አትክልትና ፍራፍሬ ምርት በኒው አርሊያንስ (ሉዚያና) ላይ በሚያካሄደው ዓለም አቀፍ ኤግዚቢሽን በማቅረብ ለዓለም ማስተዋወቅና ገበያ ማፈላለግ ነበር። እኔ ግን ተጨማሪ ትልቅ የጉዞ አጀንዳ፣ ዓላማም ነበረኝ።

በፍጥነት ተራምጄ ሻንጣዬን ከመረከቢያው ላይ አነሳሁና ወደ መንገደኞች መረጃ መቀበያ ዴስክ አመራሁ። "ሆቴል መያዝ፣ ከዚያም በፍጥነት ስልክ መደወል አለብኝ" አልኩ ለራሴ ። ከዛው መረጃ ዴስኮች ወደ አንዱ ጠጋ አልኩ። በግምት ወደ ሰባ ዓመት የሚሆናቸው ወንድና ሴት አዛውንት አገኘሁ።

“What can I help you Gentleman?” “ምን ልርዳዎት ጌታዬ” አለኝ ሴቷ አዛውንት በሠለጠነ የመስተንግዶ ትሕትና።

“ለአንድ ቀን ማረፊያ ሆቴል ነበር የምፈልገው” አልኩ፣ በሥነ-ሥርዓታቸው ውስጤ እየተገረመ።

“እዚህ ኤርፖርት አካባቢ ነው ወይስ ዋሽንግተን ዲሲ መኻል ከተማ?” አለኝ።

“ገና ተጓዥ ስለሆንኩ እዚሁ አካባቢ ቢሆን ደስ ይለኛል” አልኩ።

“እሺ! በርግጥ አሁን የሚያስፈልግህ እንቅልፍና ዕረፍት ነው” አለኝ። ከዚያም ሆቴሎችን ከኮምፒውተራቸው ላይ አዩና፣

“አንድ ሆቴል አለ፤ ዋጋው 100 ዶላር ሲሆን እዚሁ መጥተው ሊወስዱህ ይችላሉ። ዋጋው ይስማማህ ይሆን?” አለኝ።

“Fair enough” አልኩኝ፤ መስማማቴን ለመግለጽ። አሮጊቷ ሴት ሙሉ ፈገግታ አሳይተውኝ ሲያበቁ፡

“በ6ኛው በር ትወጣና 2ኛው መንገድ ላይ 24 ከሚለው ፌርማታ ላይ ሂድና ቁም። በ10 ደቂቃ ውስጥ መኪና ይልካሉ። መኪናው ይህ ነው” አሉና የሆቴሉን አድራሻና የመኪናውን ፎቶ ግራፍ የያዘ ወረቀት ሰጡኝ። አመስግኜ በፍጥነት ወደ ተባለው ቦታ አመራሁ። ልክ በቆምኩ በ12 ደቂቃ መኪናው ከተፍ አለ።

“አይ አሜሪካ፤ አይ ሥራ ማክበር!” አልኩኝ በልቤ።

ወደ ሆቴሉ ደርሼ የመግቢያ ፎርማሊቲ ከሞላሁ በኋላ ወደ ክፍሌ ከሩጫ ባላነሰ እርምጃ ተጓዝኩ። ቦታ የማደርገው ነገር ቢኖር በፍጥነት ለአንድ ሰው ስልክ መደወል ነበር።

“አይደናሉ ይሆን? ለመገናኘት አይፈቅዱ ይሆን?” እላለሁ።

ሻንጣዬን ወርውሬ ስልኩን አነሳሁ።

"ሃሎ" የሚል የአሜሪካዊ ወንድ ድምጽ ሰማሁ።

"Good morning! May I speak to Professor David Ramisfield?" (እንደምን አደራችሁ! ፕሮፌሰር ዴቪድ ራምስፊልድን ማነጋገር እችል ይሆን) አልኩ።

"David speaking!" (ዴቪድ ነኝ) አለኝ።

"ጤና ይስጥልኝ ፕሮፌሰር!" አልኩና ስሜንና ከኢትዮጵያ መምጣቴን ተናገርኩ።

"Oh Well Come, I was expecting your call" (እሺ! እንኳን ደህና መጣህ! ስልክህን እየተጠባበቅሁ ነበር) አለና

"እንደምትመጣና እኔን ማግኘት እንደምትፈልግ ዶ/ር ሻሮን ነግራኝ ነበር" አለኝ።

የዶ/ር ሻሮንን ስም ስሰማ ደስታና በራስ መተማመን አደረብኝ። ዶ/ር ሻሮን ሉውማን የ58 ዓመት አሜሪካዊ ሳይንቲስት ስትሆን እጅግ ብዙ የምርምር ሥራ የሠራች ታዋቂ የብዝሀ ሕይወት ባለሙያ ናት። በወቅቱ የካሊፎርኒያ የሳይንስ አካዳሚ ዋና ዳይሬክተር ሆና ትሠራ ነበር። እኔ ጋር ከተዋወቅን ከሰባት ዓመት በላይ ሲሆነን ሰፊ የምርምር ሥራዎችን በጋራ እንሠራለን። በምሰራው ዓለም የምፈልገው ጉዳይ ካለኝ ዶ/ር ሻሮን ለእኔ የበሩ መክፈቻ ቁልፍ ናት። ቀደም ብዬ ማወቅ የምፈልገው ጥብቅ ጉዳይ እንዳለኝና ፣ አሜሪካ ውስጥ ሊረዳኝ የሚችል ሰው እንዳለ ሳማክራት በተለመደው አነጋገሯ፣

"I will see if I can find someone" ( ማግኘት የምችል ከሆን እስኪ ልሞክር) ብላኝ ነበር።

በዚህ መሠረት ነው የፕሮፌሰር ዴቪድ ራምስፈልድን የስልክ አድራሻ ያገኘሁት። ፕሮፌሰሩ ስለ ጉዞዬ ከጠየቁኝ በኋላ "ታዲያ ምን ልርዳህ?" አሉኝ።

በደፈናው አንድ የምርምር ሥራ እየሠራሁ እንደሆነና የርሳቸውን ድጋፍ የሚጠይቅ ጉዳይ ስላጋጠመኝ በአካል ላገኛቸውና ላወያያቸው እንደምፈልግ ነገርኳቸው።

"You well come!" (ትችላለህ) አሉኝና "የት ነው ያረፍከው? ምን ያክል ቀንስ ትቆያለህ?" አሉኝ።

በበነጋው ወደ ሉዚያና እንደምሄድ፣ ከዛም ስድስት ቀን እንደምቆይና እሑድ እንደምመለስ፤ እርሳቸውን ግን ሰኞ ማግኘት እንደምፈልግ ነገርኳቸው።

"ጥሩ ነው እሑድ እንደገባህ ያረፍክበትን ሆቴል ትነግረኝና ሰኞ ጠዋት መጥቼ ወደ ቤቴ እወስድሃለሁ" አሉኝ።

"እርስዎ መምጣት የለብዎትም፣ አድራሻዎን ከነገሩኝ በታክሲ መምጣት እችላለሁ" አልኩኝ በኢትዮጵያዊ ይሉኝታ።

"That is alright, you are my guest!" (ምንም አይደል፣ እንግዳዬ እኮ ነህ) አሉኝ።

ተሰነባብተን ስልኩን ዘጋሁ። እጅግ በጣም ደስታና እፎይታ ተሰማኝ። ወዲያው ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወሰደኝ።

# ምዕራፍ ሁለት

በማግስቱ የሆቴል ሂሳቤን አወራርጄ ያም ስለነበረ ቁርስ ሳያስፈልገኝ ወደ ኤርፖርት ተጓዝኩ። ከዳላስ ኢንተርናሽናል ኤርፖርት ከተነሣን ከሁለት ሰዓት በረራ በኋላ ከቀኑ በስምንት ሰዓት ሉዚያና ግዛት፣ ኒው ኦርሊያንስ ከተማ፣ ኒል አርምስትሮንግ ኢንተርናሽናል ኤርፖርት ደረስን።

ኒው ኦርሊያንስ በሚሲሲፒ ወንዝ ዳርቻ የተመሰረተች ከተማ ስትሆን አብዛኛው የከተማው ክፍል ከባሕር ወለል በታች በመሆኑ በጣም ሞቃታማ የአየር ንብረት አላት። የአየሩ ወበቅ ለብ ያለ ውሃ በሰውነትህ ላይ የተደፋብህ ያክል እንዲሰማህ ያደርጋል። ሀገሬ ረግረግ ምድር የበዛባት ስትሆን አሊጌተር (አዞ መሳይ ተሳቢ የውሃ ውስጥ እንስሳ) በብዛት የሚገኝባትም ናት። ፈረንሳዮች በቅኝ ግዛት ይዘው ያስተዳድሯት የነበረ በመሆኑ እስከ አሁን ድረስ French Quarter (ፈረንሳይ መንደር) የሚባለው አካባቢ ትልቅ የቱሪስት መስህብ ሆኗታል። ኒው ኦርሊያንስ በሚሲሲፒ ወንዝ ዳርቻ የተመሰረተች በመሆኗ በርካታ ጥቁር አሜሪካውያን ይኖሩባታል። ከአፍሪካ በባርነት እየተፈነገሉ የተጓጓዙት ጥቁሮች ሰፋፊ ፣ የስኳርና የጥጥ እርሻዎችን እንዲያለሙ የሰፈሩባት ከተማም ናት። የጃዝ ሙዚቃ መፈጠሪያ መሆኗም ይነገርላታል። ባሪያዎቹ በሳምንት አንድ ቀን እሁድ ብቻ ዕረፍት እንዲያደርጉ ይፈቀድላቸው ነበር። የያኔው መሰብሰቢያ ቦታቸው አሁን አደባባይ ሆኖ ቱሪስት ይጎበኘዋል።

ታዲያ በወቅቱ እንጨት ሲቆርጡ ፣ ድንጋይ ሲፈልጡ ለማስተባበር ከሚያወጡት ድምጽ በመነሳት ከበሮ ቢጤ እየመቱ ራሳቸውን ለማዝናናት ይጫወቱ ነበር። "በዚህ መልክ እዚህ ቦታ ነው የጃዝ ሙዚቃ የተፈጠረው" ይላሉ አስጎብኚዎች። ኒው ኦርሊያንስ በሀሩር አካባቢ በሽታዎች ህክምና ዘርፍ (Tropical Medicine) ዓለም አቀፍ እውቅናን ያተረፉ ዩኒቨርሲቲዎችና የምርምር ተቋማት ባለቤት ናት።

ከተማዋ ማታ ማታ ቀልቧን ታጣለች። ምግብ፣ መጠጥ፣ ዘፈን፣ ዝሙት፣ ቢቃ!!! እብደት ነው። አብረን ከሄድነው ልዑካን መካከል አንዱ በመገረም፣

"ይህች ከተማ እኮ ማታ ማታ ነካ ናት" አለ።

"አይይ...!! ነካ እንኳን ከጥፋቷና ከእብደቷ ተምራ ተመልሳለች። ይህች ማን እንደ ሰዶምና ገሞራ ናት" አለኙኝ። ከ10 ዓመት በፊት ከተማዋ ካትሪና በተባለ ከባድ ውሽንፍር ተመትታ ብዙ ውድመት ደርሶባታል። በ10 ሺ የሚቆጠር ሕዝብም አልቆባታል። እሷ እቴ! ያን ሁሉ ረስታ እርቃኗን ውላ፣ እርቃኗን ታድራለች፡፡ ሰው እንደፈረስ ወይም እንደ አሳማ ያለማቋረጥ ሲበላ የሚውልበት ሀገር ቢኖር ኒው ኦርሊያንስ ነው።

ከተማዋ ለሥነ-ምግባርም ሆነ ፈጣሪን ለመፍራት ግድ ያላት አትመስልም። ከአንድ ሱቅ ላይ "May the curse be with you!" (እርግማኑ በእርስዎ ላይ ይሁን) ተብሎ ተጽፎ አይቼ "ወይ ጉድ!" አልኩ። ሰማንያ በመቶ የሚሆነው ሰው በውፍረት ታስሯል። አንዳንዶቹማ የሰውነት ቅርጻቸው በውፍረት ተውጦ ከውሃ የወጣ ጉማሬ ይመስላሉ። ለሚያያቸውም "ወይ! ምነው?" ያሰኛሉ።

ለአራት ቀን የሚቆየው ዓለም አቀፍ የሆርቲካልቸር ኤግዚቢሽን በከተማዋ ኧርነስት ሚሞሪያል ኮንቬንሽን ሴንተር ተጀምሯል። የአዳራሹ ስፋት ፈረስ ያስጋልባል ከሚባለው ይልቅ በእኛ አገር የአንድ ከተማ ቀበሌ ስፋት ያክላል። አሜሪካ ሁሉ ነገር ትልቅ ነው።

ትልቅ አዳራሽ፣ ትልቅ ኤርፖርት፣ ትልልቅ ድልድይ፣ ሰፋፊ መንገድ፣ ትልልቅ መኪና፣ ትልልቅ ሆምበርገር፣ በቃ ትልልቅ ነገር ያለባት ሀገር ናት። ምናልባትም ትልቅነትን በትውልዳቸው ከሚቀርጹባቸው መንገዶች አንዱ ይሄው ትልቅ ነገሮችን ማሳየት ማለማመድና መስተዋወቅ ሊሆን ይችላል። እስቦ መሥራት ካለ ምን ችግር አለ፤ ሁሉንም ነገር ማስተማሪያ፣ ሥነ ልቡናዊ ማንነት መገንቢያ አድርጎ መጠቀም ይቻላል።

በኤግዚቢሽኑ ላይ ከላቲን አሜሪካ፣ ከአውሮፓ፣ ከዩኤስ አሜሪካና ከካናዳ የመጡ ገዥዎችና ሻጮች ተገኝተዋል። የገረመኝ ነገር ቢኖር የመክፈቻው ቀን ኤግዚቢተርስ (ምርታቸውን የሚያስተዋውቁ) ሁሉ ወደ አዳራሹ እንዳይገቡ መከልከሉ ነው። ከመክፈቻው ቀን በፊት ኤግዚቢተርስ ያላቸውን ምርት በተሰጣቸው ቦታ ላይ ያምራል፣ ገዥ ይስባል ባሉት መልክ አሰናድተዋል። ስለዚህ የመክፍቻው ቀን ገዥዎች በነጻነት ያለ ወከባና ማግባባት ምርቱን እንዲያዩ ሲባል ነው የተከለከለው። ነጻ ገበያ!

የኢትዮጵያ የሆርቲካልቸር ምርት በተለይም የአበባ ምርት ይዘን በዚህ ኤግዚቢሽን ላይ መገኘታችንን ብዙ ጎብኝዎች በመገረምና በአድናቆት ያዩት ነበር ።

"Ethiopia...Flowers?!" (አበባ ከኢትዮጵያ?) ይላሉ በመደነቅ።

ይዘን የሄድነው ጥራት ያላቸውን የተለያዩ የአበባ ዓይነቶችን ስለነበረ በቃ በጣም የሚያስደንቃቸው ነገር ሆነ። በተለያዩ ኤግዚቢሽኖች ተሳትፈ እንደታዘብኩት የአበባ ምርት ለኢትዮጵያ ከሚያስገኘው የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ይልቅ የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ለማስተዋወቅ የሚያደርገው አስተዋጽኦ እጅግ ግዙፍ ነው። በሥልጡነው ዓለም አበባ የውበት፣ የፍቅር፣ የሰላም ተምሳሌት ነው። ኢትዮጵያ አበባ አምርታ ለዓለም ገበያ አቀረበች ሲባል እንደ ተአምር የሚሆንባቸውም ለዚህ ነው። ምክንያቱም ለእነርሱ ኢትዮጵያ ማለት የደረቀች ምድር፣

ሰላም የራቃት፣ የተራቆቱ ደሀ ሕዝቦች መኖሪያ ብቻ ናት። ከዚህች ምድር የአበባ ምርት እንዴት ይጠበቃል? "ወይ ነዶ!" ያስብላል።

ኢትዮጵያ የሰባት ትላልቅ ወንዞችና ተፋሰሶች ባለቤት፣ ውስጡ አረንጓዴ የሆነ አፈር ያለባት ምድር፣ እንኳን ተክል አውራ ጣት አፈር ውስጥ ቢገባ የሚበቅልባት ሀገር መሆኗን መግለጽ ጉንጭ ማልፋት ነው። ኢትዮጵያ ያላትን በረከት እንኳን የውጭ ሰዎች ዜጎቿም የተረዱት አይመስልም። እንደኛው አሜሪካዊ ጎብኝ በአድናቆት አበቦቹን ሲያይ ቆይቶ ወደ እኔ ጠጋ ብሎ

"May I ask you something?" ( አንድ ነገር ልጠይቅህ እችላለሁ) አለኝ

"Sure please" (በደንብ! ይቻላል!) አልኩት። ሌሎች ጓደኞቹ ሌሎች እንግዶችን እያነጋገሩ ስለነበር እኔ ነጻ ነበርኩ።

ወደ እኔ ጠጋ ብሎ፣ "ምን ተአምር ነው ኢትዮጵያን እንዲህ የቀየረ?" አለኝ።

ሁለት ምክንያቶችን ለመጥቀስ ሞከርኩ፣

1ኛ. የምዕራቡ ዓለም ሚዲያ በአንድ ወቅት በኢትዮጵያ በተወሰነ አካባቢ የተፈጠረን ረሀብ እጅግ አጋንኖ በማቅረቡ በዓለም ሕዝብ ዘንድ የተፈጠረው ግንዛቤ የተዛባ በመሆን

2ኛ. ሕዝቡ ድህነትን ለማሸነፍ ቆርጦ በመነሣቱ ነው አልኩት። ከዛ በላይ መንግሥት የተቻለውን ሁሉ ለማድረግ ይጥራል ብዬ ደሰኮርኩ።

"በእኔ ግምት የሀገራችሁ ለውጥ እንደ ተአምር የሚቆጠር ነው" አለኝ።

እቡባ እምርቶን ወደ ዓለም ገበያ ይዘን መቅረባችን ትንሽ ግንት የታከለበት መልካም ሥዕል እየፈጠረ መሆኑ ተሰማኝ። እቡባ የሚያመርቱ፣ የምግብ ሰብልና ሌሎች የግብርና ምርቶችን እትረፍርፈው ነው የሚል ግንዛቤ የፈጠረ መሰለኝ። ለማንኛውም ከሰውየው ጋር የነበረኝን ቀይታ ጨርሼ ስራፍት ለማድረግ ከእዳራሹ እቅራቢያ ወደሚገኘውና River Walk (ሪቨር ወክ) ወደሚባለው ስፍራ ሄድኩ።

ሪቨር ወክ በሚሲሲፒ ወንዝ ዳርቻ የተገነባ በጣም ትልቅ የገበያና የሬስቶራንት ማእከል ነው። ወንዙን በሰፊው የሚያሳይ ሰገነት አለው። ቡና እየጠጣሁ ፊቴን ወደ ወንዙ እድርጌ ቁጭ አልኩ። ወራጅ ወንዝ ሳይሆን ሐይቅ የሚመስለው ሚሰሲፒ ፀጥ ብሎ ተኝቷል።

"አይ ሚሲሲፒ!

"ጥቁር አፍሪካውያን ከአንተ ውሃ እየቀዱ ከማንባራቸው ላብ እያንጠፈጠፉ ጥጥና ሸንኮራ አልምተው የአሜሪካን የሀብትና የሥልጣኔን መሠረት ጣሉ። አንተም በረጅሙ ታሪክህ የጥቁር ሰው ልጅን ግፍና መከራ ታዘብክ። እድሜም ሰጥቶህ ጥቁር ይህችን ሀገር ሲመራ፣ በአቅራቢያህ ያለው መሬት በሰው ጉልበት ሳይሆን በረቀቀ ሜካናይዝድ ቴክኖሎጅ ሲለማ ተመለከትክ። አንተ እድለኛ ነህ። ድህነት በብልጽግና፣ ባርነት በነጻነት ሲተካ፣ ታሪክ በበጎ ሲቀየር ለመመልከት በቃህ።"

"ምንአለ! ዓባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ሸበሌ፣ ባሮ፣ አሞና ጊቤ፣ ዳዋና ገናሌ እንዳንተ ታሪክ ሲቀየር ባዩ። ሲዘፈንባቸው እንጂ ሲለማባቸው ሳያዩ፣ ለም አፈር ደለል ተሸክመው ወደ ባዕዳን ሲጓዙ፣ ውሃቸው አንድም ቀን ሳይነጠፍ ሀገር በድርቅ ሰበብ፣ በረሀብና በድህነት መልኳና ታሪኳ ጥላሸት ሲቀባ፣ ያገር ልጅ በጠኔ ሲቆራመድ ማየት እጣቸው ባይሆን። የኋላዮሽ ጉዞ ታዛቢ ሆኖ ከመኖር ቢወጡ!" እያልኩ በጥልቅ ምሬት እጉረመረምኩ።

# ምዕራፍ ሦስት

የቀጠሮዬ ሰዓት ከጠዋቱ ሁለተ ሰዓት ተኩል ቢሆንም ከሁለት ሰዓት ጀምሮ ዋሽንግተን ዲሲ ከሀረፍኩበት ሆቴል እንግዳ መቀበያ አካባቢ ወደ ዋናው መግቢያ በር ትይዩ ትልቅ ሶፋ ላይ ቁጭ አልኩ። በአሜሪካዊ ሰዓት አክባሪነት ባህል መሠረት ልክ 2:31 ላይ አንድ አዛውንት የሆቴሉን በር አልፈው በዓይናቸው ቃኝት አድርገው ወደ እኔ እያመለከቱ፡

"ሲሳይ?" አሉኝ

"ፕሮፌሰር ዴቪድ?" አልኩ በበኩሌ።

ከዛም የእጅ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ከሆቴሉ በር ወደ አቆሟት መኪናቸው ወሰዱኝ። ስለ ኒው ኦርሊያንስ ሲጠይቁኝ ከቆዩ በኋላ "መኖሪያ ቤቱ ዋሽንግተን ዲሰ አቅራቢያ ሆና ቨርጂኒያ ስቴት ነው" አሉኝ። ከሃያ አምስት ደቂቃ ጉዞ በኋላ መኖሪያ ቤታቸው ደረስን። ባለቤታቸውን አስተዋውቀውኝ፣ ቡና ተቀድቶልኝ የጥናት ክፍላቸው ውስጥ ተከታትለን ገባን።

ፕሮፌሰር ዴቪድ ራምስፌልድ የ72 ዓመት አዛውንት ናቸው። ፊታቸው ሰፋ ያለ ሲሆን ጉንጫቸው በሁለት ረድፍ ታጥፎ ለንቦጭ ፈጥሯል። አንገጫቸው ሥር ትልቅ ጭምድድ ያለ ኩልኩልት አላቸው። ፊታቸው ላይ ጺም የሚባል ነገር የላቸውም።

የራስ ፀጉራቸውን ወደኋላ አበጥረው አስተኝተውታል። ፕሮፌሰር ዴቪድ በሀዋርድ ዩኒቨርሲቲ (የነገረ መለኮት ትምህርት) School of Divinity የመካከለኛው ምሥራቅ የጥንት ቋንቋዎች ፕሮፌሰር የነበሩ ሲሆን አሁን በጡረታ ላይ ናቸው። ከጥናት ክፍላቸው ውስጥ ያሉ መጻሕፍት ብዛት እንድ መለስተኛ ኮሌጅ ያስከፍታል። በአግባቡ የተደረደሩት መጻሕፍት ሲያዩዋቸው ዝም ብለው እውቀት የሚጭኑ ይመስላሉ። ከጥናት ጠረጴዛቸው አቅራቢያ ካሉት ሁለት ወንበሮች በአንዱ ላይ እንድቀመጥ ጋብዘውኝ እርሳቸው በኮምፒውተራቸው ትይዩ ተቀመጡ።

"እሺ! ምንድን ነበር እንድረዳህ የፈለግኸው?" አሉኝ

ከመጓጓቴ የተነሣ መግቢያና መውጫ ሳላበዛ፣

"የሁለት ቃላት ትርጉሞችን እንዲፈልጉልኝ ነበር" አልኳቸው።

"የየትኛው ቋንቋ ቃላት ናቸው?" አሉኝ

"ተጽፈው ያገኘኋቸው በግዕዝ ፊደላት ቢሆንም የአርማይክ ቃላት ይመስሉኛል" አልኩ።

"እንዴት አወቅህ? ማለቴ እንዴት አርማይክ መሆኑን አወቅህ?" አሉኝ

"እይ የእኔ ግምት ነው" አልኩኝ ።

"ለግምትህስ መነሻ አለህ?" አሉኝ

"እዎን ባለታሪኩ ሶርያዊ ክርስቲያን ስለሆነ ያው ቋንቋውም አርማይክ ይሆናል ብዬ ነው" አልኳቸው ዝርዝር ውስጥ ሳልገባ።

"ደኅና ነው" አሉኝና ቃላቱን እንድነግራቸው ጠየቁኝ።

ከግእዙ ፊደላት ወደ እንግሊዘኛው ፊደላት የገለበጥኩበትን ወረቀት ሰጠኋቸው።

"ለካስዋ በኮሳ"

"LKASWA BEKOSA"

ወረቀቱን ተቀብለው ቃላቶችን ለማንበብሞከሩና "የቃላቱ ድምፅት እንደገመትከው አርማይክ ይመስላል" ብለው ትንሽ ቆዩና

"ችግር ሊሆን የሚችለው መጀመሪያ ከአርማይክ ወደ ግእዝ ሲወሰድ ፣ አንተ ደግሞ ከግእዙ ወደ እንግሊዝኛው ስትቀይረው ሊቆነጸል ወይም ሊጎተት ከቻለ አለበለዚያ ደግሞ አላስፈላጊ እናባዚ ከገባበት ነው፤ይህ ደግሞ የቃሉን ትርጉም ሊያዛባው ይችላል" አሉኝ።

የእነዚህን ቃላት ትርጉም ከሳትኩ በቃ ሰዳከር መኖሬ ነው አልኩ በሃሳቤ።

"እ… ታዲያ እንዴት ነው የተሻለና የቀረበ ትርጉም ማግኘት የሚቻለው?" አልኳቸው በተማጽኖ ድምጽ።

"አይ እንድትረዳው አነሳሁት እንጅ ይህን ችግር የሚቀርፍ እራሱን የቻለ የሥነ ልሳን የኮምፒውተር ፕሮግራም አለኝ" አሉና ኮምፒውተራቸውን ለማስነሳት ቁልፉን ተጫኑ።

"እሮይ!" አልኩ።

ፕሮፌሰር ዳቪድ የዕብራይስጥን፣ የዐረብኛን ቋንቋዎች ጠንቅቀው የሚያውቁ ሲሆን አርማይክ ላይም ሰፊ ጥናትና ምርምር አድርገዋል። ዶ/ር ሻሮንን፣ የአራማይክ ቋንቋ ላይ ምርምር ያደረገ ሰው እፈልጋለሁ ሰላት ነበር በተለመደው ሰፊ ኔትወርኳ እኚህን ሰመጥር ፕሮፌሰር ያገናኘችኝ።

ፕሮፌሰር ዲቪድ ኮምፒውተራቸውን ለሥራ ዝግጁ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ ስለ ሶፍት ዌሩ ገለፃ ጀመሩልኝ።

"የአንድ ቃል ትርጉም እንዲፈልግ ሲነገረው የተለያዩ የቃላት ትርጉም አማራጮችን ያቀርባል። በእያንዳንዱ አማራጭ ስር

የቃሉን መሠረት ወይም ግስ

ቃሉ በተለያየ ቦታና ቁጥር ሲገለጽ

ቃሉ ስም ወይም ቅጽል መሆኑን

በተለያየ አካባቢ ያለውን አነባበብ

እንዲሁም ከጥንታዊ መጻሕፍት ጠቅሶ አገባቡን በምሳሌ ያስቀምጣል፡፡ማለትም ሃይማኖታዊ ቃል ከሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ወይም ከቁርዓን ጥቅስ አምጥቶ ተቀራራቢ ትርጉሙን ያስቀምጣል። ጥሩ ነገሩ ደግሞ ከቀረቡት አማራጮች የራሱን ትንታኔ (Analysis) ሰርቶ ተፈላጊው ቃል ከቀረቡት አማራጮች ጋር ያለውን ተቀራራቢነት በፐርሰንት አስልቶ ያስቀምጣል። ለምሳሌ በአማራጭ አንድ ላይ ከቀረበው ጋር 55% ሆሮት አማራጭ ሦስት ላይ ካለው ጋር 90% ሊሆን ይችላል። ይህ ማለት የቃሉ ትርጉም ወደ 3ኛ አማራጭ የቀረበ ነው ማለት ነው" በማለት ገለጻ አደረጉልኝ።

" አይ ምርምር! እንደዚህ ነው እንጅ ቁልጭ ብሎ መገለጽ ሲቻል፤ በተጨባጭ ችግር ሲፈታ ደስ ይላል!" አልኩና በልቤ "ለካ የሥነ ልሳን ቋንቋ ትምህርት ውስጥም አሐዛዊ (Statistics) ስሌትን መሠረት ያደረገ የተቀራራቢነት ስሌት አለ!" ብዬ ስደነቅ ፕሮፌሰር ዲቪድ ፈገግ አሉ።

በዚህም መሠረት የመጀመሪያውን ቃል በአረማይክ ፊደል በድምፁ መሠረት ተየቡና ፈልግ የሚለውን የኮምፒዩተራቸውን ቁልፍ ተጫኑ። ኮምፒውተሩ ትንሽ ከማሰነ በኋላ ብዙ አማራጮችን አቀረበ። ስሌትህን ከቃሉ ጋር አዛምድ "Match analysis" የሚለውን ቁልፍ እንደገና ሲነኩት ሲጥወለወል ቆይቶ በረድፍ ይዞ ብቅ አለ። ከፍ ያለው ፐርሰንት 94% ሲሆን ይህን ትርጉም ወስደው በስፋት እንዲያቀርብ የሚያደርገውን ቁልፍ ነኩ።

ቃሉ ቅጽል (Adjective) መሆኑን ፣ ነጠላ ቁጥር መሆኑን እና ከመጽሐፍ ቅዱስ ቲቶ1፡8 ፣ ሐዋ 2፡27፣ 3፡14 የሚሉትን ጥቅሶች ከዘረዘረ በኋላ የቃሉን ትርጉም ጎላ አድርጎ አሳየ።

"Holy" ይላል፣ "ቅዱስ" ማለት ነው።

ወዲያው አባ ተወልደ መድኅን ስለ አባ አድሪል የነገሩኝ ቃላት ትዝ አሉኝ። "ምንድን ነበር የሚፈልገው?" ስላቸው "ቅዱሱን ቅርስ ነዋ" ነበር ያሉኝ። እስኪ ምናለበት "ቅዱሱን ቅርስ" ከሚሉኝ ዝርዝር አድርገው ነግረውኝ ቢሆን ኖሮ ይህን ያክል በሀሳብ ውጣ ውረድ አልኖጥም ነበር አልኩኝ።

እንዲያው እኛን የአሁን ዘመን ልጆች ምሥጢር መያዝ የማንችል ዝርው፡ ወናፍ ሲያደርገን እነዚያን የኢትዮጵያ ገዳማውያንን የምሥጢር ሙዳይ ያደረጋቸው ምን ይሆን?! እንዴት ነው ሰው ምሥጢር መያዝ የሚችለው? ለእኔ ምሥጢር ውሃ በእፍኝ እንደመያዝ ነው፤ እየተንጠባጠበ የሚያልቅ።

ለማንኛውም ወደ ልቤ ተመልሼ ሳስብ የመጀመሪያው ቃል "ቅዱስ" መሆኑን ማወቁ ብዙም አስደናቂና ጠቃሚ አለመሆኑ ታወቀኝ። በገዳም አካባቢ ያለ ነገር ሁሉ ቅዱስ የሚል ቅጽል መያዙ አዲስ አይደለም። ዋናው ቁልፍ ያለው ሁለተኛው ቃል ላይ ነው አልኩና በሀሳቤ ሁለተኛውንና ለፍለጋዬ ወሳኝ ነው ብዬ የአመንኩበትን ቃል ፕሮፌሰሩ እንዲተይቡ በትሕትና ጠየቅሁ።

እንደ ቅድሙ የተለያዩ አማራጮች ቀረቡ። ሰፍ ብዬ አማራጮችን ሳይ አንድም ስሜት የሚሰጡ ቃላት አልቀረቡም። እንዲያውም እንዳቸውም የሃይማኖት ወይም የቅርስ ይዘት ያላቸው ቃላት አልነበሩም።

"It doesn't make any sense!" (ምንም ስሜት አይሰጥም) አልኳቸው ተስፋ በቆረጠ ስሜት፡

"Yaa, I agree, but that is what it is!" (እውነትክን ነው፣ ግን የሆነው መሆን የሚችለውን ነው) አሉኝ።

"ምን አይነት ጣጣ ነው!" አልኩኝና ሁለት እጆቼን ከግንባሬ አንስቼ ራሴን ጥምድድ አድርጌ ይገፎ ኮምፒውተሩ ላይ አፈጠጥኩበት። የሆነ አረንጓዴ መብራት ኮምፒውተሩ ቁልፍ (Key board) ላይ ሲበራ አየሁ።

"ፕሮፌሰር?" አልኳቸው በድንገት።

"አቤት" አሉኝ በመገረም እያዩኝ።

"ፕሮግራሙ ፊደላት በትልቁና በትንሹ በመጻፋቸው ፍለጋው ላይ ለውጥ ያመጣል?" አልኳቸው።

"Yes it is case sensitive" (አዎ በፊደሉ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው) አሉኝ።

"ታዲያ እኮ ኪቦርዱ ካፕስ ሎክ (Caps lock)" ሆኗል አልኳቸው፣

"What? Oh Shit!" (ምን? እኸ! አሳዛኝ) አሉ።

ለካ የመጀመሪያውን ቃል ትርጉም ለእኔ ለማሳየት ስክሪኑን ወደ እኔ ሲያዞሩት አብረው ኪቦርዱን ነክተውት ኖሮ ፊደላቱ በካፒታል ብቻ እንዲፃፍ አድርጎት ኖሯል።

"በፍለጋው ላይ እናባቢውን እንደ ተነባቢ ወይም አገላብጦ በመውሰድ ትርጉም ሊያዛባ ይችላል" አሉኝ።

እንደገና ቃላቱን በአግባቡ ተነባቢውን በካፒታል እናባቢውን በስሞል ሌተር አድርገው ጻፏቸው።

"This time we should get the right meaning!"( አሁን ትክክለኛውን ትርጉም እናገኘዋለን) አሉ በራስ መተማመን ስሜት።

ከሴኮንዶች በኋላ የኮምፒዩተሩ ስክሪን እንደተለመደው በአማራጮች ተሞልቶ ቀረበ። 92% ቀረቤታ ያለውን ቃላት ሙሉ መግለጫ እንዲያመጣ አዘዙት። ፕሮፌሰሩ እንደመገረም፣ እንደመደንቅም ብለው፡-

"Have a look what we got!" (ያገኘነውን ተመልከት) ብለው የኮምፒውተሩን ስክሪን ወደ እኔ ዘወር አደረጉት። ብዙ መግለጫ ከሰጠ በኋላ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ማቴ 26+27 እና ማር 9+41 ጠቅሶ ቃሉን በትልህ አስፍሮታል።

መብረቅ የመታኝ ያክል ደንግጬ "እ! አምላኬ" አልኩኝ።

ፍዝዝ ብዬ ቀረሁ። ረጅሙን ጉዞዬን ሳስበው ያለ አቅሜ ተጎትቼ እንደገባሁበትም ተረዳሁ።

ፕሮፌሰሩን "That is it! Thank You!" (ይኸው ነው፤ አመሰግናለሁ) አልኳቸው።

"My pleasure!" (በደስታ ነው) ካሉኝ በኋላ

"ከእናንተ አገር እንኳን ይገኛል ብዬ ገምቼ አላውቅም ነበር!" አሉኝ በመደነቅ

"ለምን?" አልኳቸው።

"በብዙ አጥኚዎችና ተመራማሪዎች እንዲሁም ባለቅኔዎች የሚነገረውና የሚታመነው በጣም የተለየ ስለሆነ" አሉኝ።

እርሳቸውን ላለማስቸገር ታክሲ እንዲመጣልኝ ስልክ ከደወልኩ በኋላ ቡና እየጠጣን ሰፊና አስገራሚ ታሪክና ማብራሪያ ሰጡኝ። በጥንቃቄና በተመሰጠ እያዳመጥኩ ማሳታዎሻ ያዝኩ። ታክሲው መጥቶ ለመሳፈር ወደ በር ሳመራ

"የሚያስፈልግህ ነገር ሲኖር በኢሜል ጠይቀኝ። የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ" አሉኝ። ቀጥለውም ብልሁ ፕሮፌሰር " ፍሊጋህ እስደሳች እንዲሆን የጀርመናዊዩን ባለ ቅኔ የምልፍራምን ፓርዚቫል ማንበብ ያስብህ ይመስለኛል" አሉኝ።

ፈገግ ብዬ "እሺ!" አልኳቸው።

"መጽሐፉን ማግኘት ካልቻልክ እስካን አድርጌ ልልክልህ እችላለሁ" አሉኝና እጃቸውን ትከሻዬ ላይ ጫን አድርገው።

"እየፈለግኸው ያለው ነገር ከበድ ያለ ነገር መሆኑን እረዳለሁ። እንደዚህ ያሉ ጥንታዊና ሃይማኖታዊ ቅርሶች ብዙ ጊዜ ከምናውቀውና ከተለመደው እጅግ ወጣ ባለ ምሥጢራዊ ኃይል ይጠበቃሉ። አንዳንዶም ቅርሶቹም ራሳቸው ልዩ ኃይል ሊኖራቸው ይችላል። በሃይማኖት ሰዎች ከሚሰጠው የመለኮታዊ ሃይል አምክንዮ ውጪ የፊዚክስ ምሁራን እንደነዚህ ያሉ ጥንታዊ ቅርሶች ራዲዮ አክቲቭ ከሆኑ ንጠረ ነገሮች በተሠሩ ሳጥኖች ወይም ቦርሳዎች ስለሚሸፈኑ ያለ ጥንቃቄ ወደነዚህ ቅርሶች መቅረብ በጨረር መጠቃትን ሊያስከትል ይችላል የሚል ትንታኔ ይሰጣሉ። ያም ሆነ ይህ ወደነዚህ ምሥጢራዊ ቅርሶች መቅረብ የሕይወት ዋጋ ሊያስከፍል ይችላል። Take care!!" (በጥንቃቄ!) አሉኝ።

የተሸከምኩት ሓላፊነት እጅግ ከባድና አደገኛ እንደሆነ እኔም ሆነ እርሳቸው ተረድተነው ነበር። ሞቅ ያለ ምስጋና አቅርቤላቸው ተሰናብቼ ወደ ታክሲው ስገባ እጅግ ከባድ ሸክም እንደተሸከመ ሰው ትልበቱ ገለ ነበር። "To Holiday Inn" (ወደ ሆሊዴይ ኢን) አልኩት ባለታክሲውን።

# ምዕራፍ አራት

በማግስቱ ረፋዱ ላይ ምቾት እንደጋበኘ በሚያጉናጽፈው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ድሪምላይነር አውሮፕላን ከዋሽንግተን ወደ አዲስ አበባ ለመብረር ቢዝነስ ክላስ ውስጥ በመስኮት በኩል ባለ መቀመጫ ለረጅም ጉዞ ራሴን አደላድዬ ቁጭ አልኩ።

ከጎኔ ዕድሜያቸው በግምት 70 ዓመት የሚሆናቸው ሽማግሌ ፈረንጅ ተቀምጠዋል። ረዘም ያለ ቁመና ሲኖራቸው ፀጉራቸው ሙሉ በሙሉ ሸብቷል በረዶ ይመስላል። በሥርዓት የተቀረጸው ጺማቸው ግርማ ሞገስ አላብሷቸዋል። ግንባራቸውና ዐይናቸው አካባቢ ቆዳቸው የተሸበሸበ በመሆኑ አባውንት መሆናቸውን ያሳብቃል። በተረፈ ንቁና ደስተኛ ይመስላሉ።

በሚገርም አማርኛ "እንደምን አረፈድክ፣ እንድረው ባርነስ እባላለሁ" አሉኝ የመቀመጫ ቀበቶቸውን አስረው ሲጨርሱ እጃቸውን ለሰላምታ እየዘረጉ።

"እግዚአብሔር ይመስገን እንደምን አረፈዱ፣ እኔም ሲሳይ እባላለሁ" አልኩኝና በሁለት እጆቼ ጨብጥኳቸው።

"ጥርት ያለ አማርኛ ነው የሚናገሩት፣ ከየት ተማሩት?" አልኩ።

"ነጃም ደብረ ማርቆስ ለአራት ዓመታት ያክል ኖሬያለሁ። በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ነው። የአሜሪካ የፒስ ኮር አባል ሆኜ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ለማስተማር ነበር እ.አ.አ. በ1969 የመጣሁት" አሉ።

የበረራ አስተናጋጆች በበረራ ላይ መወሰድ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች የሚሰጡትን በድምፅና በምስል የተቀናበረ የተለመደ መግለጫ በጽሞና በማዳመጥ ቆየን። አውሮፕላኑ አየር ላይ  አቅጣጫውንና ከፍታውን አስተካክሎ የመቀመጫ ቀበቶ እሠሩ የሚለው ምልክት ሲጠፋ ፊቴን ወደ ሚስተር እንድሪው ዘወር አድርጌ ራሴን ለወሬ ዝግጁ አደረግሁ።

ጨዋታውን ለማስቀጠል በሚያመላክት ዐይን ዐይናቸውን አተኩሬ እያየሁ፦ "የኢትዮጵያ ቆይታዎ እንዴት ነበር ታዲያ?"

"በሕይወቴ ልዩ ቦታ የምሰጠው ነገር ቢኖር ኢትዮጵያ ውስጥ ያሳለፍኩትን ጊዜ ነው።" እርሳቸውም አቀማመጣቸውን እያስተካከሉ ጨዋታቸውን ቀጠሉ፤

"ወደ ኢትዮጵያ ከመጓዛችን በፊት በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት አስተባባሪነት ኢትዮጵያን ቀደም ብለው በጎበኙ የአሜሪካ ባብቲስት ሚሲዮን አባላት ገለጻ ተደርጎልን ነበር።" ብለው ፈገግ አሉ።

"የሚገርመው ኢትዮጵያ ስንደርስ ያጋጠመኝ ሁኔታና ከገለፃው በመነሣት በአእምሮዬ ሥዬው የነበረው በጣም የተራራቀና የተቃረነ ነበር" አሉ፤ ራሳቸውን እየነቀነቁ።

"እንዴት?" አልኳቸው በጉጉት።

"በሚስዮናውያኑ የተሰጠን ገለጻ ፈጽሞ ኢትዮጵያን የሚወክልና የሚገልጽ አልነበረም። ምስኪንና በጣም የተጎሳቆለ ሕዝብ፣ የተራቆተና ምንም ጸጋና ውበት የሚባል ነገር የሌለባት ተስፋ ቢስ ሀገር እንደሆነች አድርገው ነበር የሳሉብን።"

"እና እርስዎና ጓደኞችዎ ኢትዮጵያን በወቅቱ እንዴት አገኛችኋት?"

"በርግጥ በወቅቱ የከፋ ድህነት ነበር። ይሁን እንጅ ደግ፣ በራሳቸውና በታሪካቸው የሚኮሩ ሕዝቦች መኖሪያ ፣ ውብና ማራኪ መልክአ ምድር ያላት፣ ሊለማ የሚችል ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት የታደለች ሀገር ሆና ነበር ያገኘኋት።

በተለይ ከአንድ ሳምንት የአዲስ አበባ ቆይታ በኋላ ወደ ደብረ ማርቆስ ሄጄ መኖር ስጀምርና ከሕዝቡ ጋር እየተዋወቅሁ ስሔድ ሕይወትን እንደ ብዬ የጀመርኩ መስሎኝ ነበር። ሁሉም ሰው ሚስተር እንድሪያስ እያለ ነበር የሚጠራኝ" አሉና ዐይናቸውን ከፊት ለፊት ካለው መቀመጫ ተክለው ብዙ ቆዩ።

"በተለይ ሁለት የማልረሳቸው ገጠመኞች አሉኝ" አሉና ለማዳመጥ መጓጓቴን ተመልክተው ትረካቸውን ቀጠሉ። አማርኛቸው መቸም ግሩም ነው። ቃናው የጎጃም አማርኛ እንደወረደ ነው።

"ደብረ ማርቆስ ሦስት ወር እንደቆየን እኔና አንድ ሌላ አሜሪካዊ የፒስ ኮር አባል ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ በጭነት መኪና ጋቢና ውስጥ ተሳፍረን ጉዞ ጀመርን። ደጀን ከመድረሳችን በፊት መንገዱ በድንጋይ ተዘግቶ አገኘን። ሪዳቱ በፍጥነት ወርዶ ድንጋዩን በማንሳት ላይ እያለ ሁለት የጦር መሳሪያ የታጠቁ ሰዎች ደረሱ። ሁሉንም ሰላም ካሉ በኋላ ሁለታችንን ከመኪናው እንድንወርድ ጠየቁን። እንደወረድን ሹፌሩን መንገዱን እንዲቀጥል አዘዙትና እኛን በእጅ ምልክት እንድንከተላቸው አሳይተው ወደ መንደር ጉዟቸውን ቀጠሉ። በወቅቱ የተሰማኝን የድንጋጤ መጠን አሁን ልገልፀው አልችልም። በቃ ወደ ሞት የሚወስዱን ሽፍቶች መሆናቸውን አምነን ነበርና" አሉና ዝም አሉ።

"እንዴ! ከዚያስ ምን ሆናችሁ? ማን አስለቀቃችሁ?" ጥያቄዎቼን አዥጎደጎድኩባቸው።

ፈገግ አሉና" ከሰፈር ስንደርስ ሰፊ ድግስ ተደግሶ ሥጋ፣ ጠጅ፣ ጠላ ቀርቦ ተጋባዥ በደስታ ላይ ሆኖ ደረስን። እኛን ሲያዩ ሽማግሌዎቹ ከመቀመጫቸው ተነሥተው ካስቀመጡን በኋላ በልግስና ይጋብዙን ጀመር። እኔና ጓደኛዬ ደንግጠን ስለነበር ግብዣው የበለጠ ግራ አጋባን። ወደ ሰው ስንመለከት ግን ሁሉም በፈገግታና በአድናቆት ነው የሚመለከተን። እናም አስጊ ነገር እንደሌለ ቀስ እያልንም ቢሆን ተረዳን። ትንሽ ቆይተን ተረጋጋንና ምግብ በልተን ጠጅ መጠጣት ጀመርን። የሚገርምህ ጥሬ ሥጋ ለመጀመሪያ ጊዜ የበላሁት ያን ጊዜ ነው" አሉና ሳቁ።

"ከዚያስ?"

"አንድ ሁለት ሰዓት እንደቆየን ያመጡን ሰዎች እንደገና እየመሩ ወደ መንገዱ ወስደውን መኪና መጠበቅ ያዙን። ከአንድ ሰዓት ቆይታ በኋላ መኪና መጣ። አንደኛው የያዘውን ጠበንጃ ወደ ላይ አቃንቶ ሲያሳየው ሾፌሩ መኪናውን አቆመ። በዚህ ሁኔታ አሳፍረውን ተመለሱ አልሃለሁ።"

"የሚገርም ነው፤ ለምንድን ነው እንዲህ ያደረጉትት?" እየተገረምኩ ጠየኳቸው።

«ይገርምሃል ዓላማቸው እንግዶችን በተለይም እኛን መጋበዝ ነበር። በዚያን ጊዜ በጎጃም እንግዳ መጋበዝ የትልቅነት ምልክት ተደርጎ ይቆጠር ነበር። አሉ።

በሀገራችን በተለይም በከተማውና በምሁሩ አካባቢ ከፍተኛ የማኅበራዊና ባህላዊ አስተሳሰብ ለውጥ የመጣ ቢሆንም እንግዳን የማክበር ባህል በገጠሩ አካባቢ አሁንም እንዳለ የእኔ ገጠመኞች በእምርዩ እየተነባበሩ ይመሰክሩልኝ ጀመር።

«አንድ ሌላ የሚያስቀውን ገጠመኜን ደግሞ ልንገርህ» አሉ፤ እንደገና ፈገግ ብለው።

«በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኢምባሲ ቆንስላው ግቢ ውስጥ ግብዣ አዘጋጅቶ ሁላችንን የፒስ ኮር አባላትን ጠራን። ያን ጊዜ አማርኛ መናገር የጀመርኩ ቢሆንም ቃላት ይምታቱብኝ ነበር።

ታዲያ በዚህ ግብዣ ላይ ሚኒስተሮች፣ ዲፕሎማቶች፣ ልዑላን የንጉሡ ቤተሰቦችና ታዋቂ ሰዎች ተጋብዘው ነበር። በአጋጣሚ አሁን ስሟን እረሳሁ አንድ እንደኛዋ የጃንሆይ ልጅ ልዕልት በግብዣው ላይ ተገኝታ ነበር። ወጣትና በጣም ቆንጆ ነበረች በወቅቱ።

ያው እንደምትገምተው ወጣትነት አለ፣ በዚያ ላይ የመጠጥ ሞቅታ ተደምሮበት ግማሽ ይደንሳል፤ ግማሹ ቆሞ እየጠጣ በነጻነት ያወራል። በዚህ መኻል ሰብሰብ ብለን ከቆምንበት የጃንሆይ ልጅ ልዕልት ወደ እኛ ቀረብ ብላ ሰላምታ ሰጥታን በኢትዮጵያ ቆይታችን ተደስተን እንደሆነ ወይም እንዳልሆን፣ በአጠቃላይ ያየነውንና የታዘብነውን እንድንነግራት ጥርት ባለ እንግሊዘኛ ጠየቀችን።

ሁላችንም የተሰማንን በአድንቆት ስንነግራት ቆይተን በመካከል አማርኛ መቻሌንና ለእርሷ ያለኝን አድናቆት ለመግለጽ ፈልጌ 'ቂጥሽ በጣም ቆንጆ ነው' አልኩ።»

ፊቷ በአንድ ጊዜ ልውጥውጥ አለ። ወዲያው ‹Nice to meeting you› (ስለተዋወቅን ደስ ብሎኛል) ብላን ሄደች። የሆነ ቦታ ላይ እንደተሳሳትኩ ገመትኩና በራሴ ሽምቅቅ አልኩ።

አብሮን የነበረው ኢትዮጵያዊ ዲፕሎማት በድንጋጤ "ምን ነካህ?" አለኝ በእንግሊዝኛ።

ምንድነው? ምን አጠፋሁ? አልኳት እኔም ደንግጬ።

'እንዴት የጃንሆይን ልጅ ቂጥሽ ቆንጆ ነው ትላለህ?' ብሎ በእንግሊዝኛ ሲነግረኝ በድንጋጤ ልወድቅ ምንም አልቀረኝም ነበር። እሱና በሚነግሩኝ ሰዓትም ወደዚያው ስሜት ሲመለሱ አሁን ድረስ ድንጋጤያቸውና ኃፍረቱ የለቀቃቸው አይመስልም።

በነገሩ ተገርሜ እየሳቅሁ፣ «ምንድን ነበር ለማለት የፈለጉት?» አልኳቸው።

እኔማ "ጉንጭሽ በጣም ቆንጆ ነው ለማለት ነበር፤ በርግጥም በጣም ያምር ነበር። በዚያው እያደነቅሁ የኢትዮጵያውያን የአፍንጫ፣ የከንፈርና አጠቃላይ የፊት ቆዳና ቅርጽ ከሌላው አፍሪካዊ ይለያል በማለት ለእርሳቸውም ለሀገሬውም ያለኝን አድናቆት ለመግለጽ ነበር" አሉ እየሳቁ።

የተለመደውን የፈረንጆችን ከእውነታዊ ጎን በመጀመር ሌሎች ስለእነርሱ ያላቸውን ገጽታ አወንታዊ አድርጎ የማዘጋጀት ችሎታ በልቤ እያደነቅሁና በአጋጣሚ አለመሳካቱን አስቤ እየሳቅሁ፣ «ከዚያስ?» አልኳቸው።

«ከዚያማ በኋላ» ረጅም ሳቅ እየሳቁ፣ «በአንድ ጊዜ ወሬው ተዳረሰና መሳቂያ መሳለቂያ ሆንኩ እልሃለሁ» አሉና በትዝታ እንደገና ተመሰጡ። አብረን በንሰት የቆየን እስከማይመስል ድረስም በቅጽበት በየፊናችን በዝምታ ውስጥ ተዋጥን።

ፊቡን ብዙ ከዝምታ ተመለሰኩና ጨዋታችን እንዲቀጥል መፈለጌን በሚያሳይ ሁኔታ «አሁን ለምን ተግባር ነው ወደ ኢትዮጵያ የሚሄዱት?» አልኳቸው።

«እንደነገርኩህ ኢትዮጵያን ሁልጊዜ በመልካም ትዝታ ሳስባት ቆይቻለሁ። አሁን እድሜዬ እየገፋ ስለሆነ ረጅም የውጭ ሀገር ጉዞ ከማቆሜ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ ለማየት ነው። ወዳጆችም ስላሉኝ እነርሱንም እጠይቃለሁ። በዚያውም በሀገሪቱ ያለውን ለውጥ አያለሁ። ብቻ ኢትዮጵያን መጎብኘቴ የሆነ ሰላም እንደሚሰጠኝ ዕረፍት እንደሚያጎናጽፈኝ አምኛለሁ» አሉ፤ ከረጅም ዓመታት በኋላ ወደ ቤተሰብ በናፍቆት የሚመለስ ሰው በመምሰል።

«ጉብኝትዎ የተሳካና አስደሳች እንዲሆን ከልብ እመኛለሁ» አልኩና አክብሮቴንና ደስተኛ መሆኔን ገለጽኩላቸው።

«አመሰግናለሁ» አሉና ዝም አሉ።

ትንሽ ቆየት ካሉ በኋላ ግን የእርሱንስ ለምን አልሰማም በሚል ስሜት «አንተስ ወደ አሜሪካ ለምን መጣህ? ነው ወይስ እዚሁ አሜሪካ ኗሪ ነህ» አሉኝ።

"ኗሪ እንኳን አይደለሁም፤ ኢትዮጵያ ነው የምኖረው። ለአጭር ጊዜ ለሥራ መጥቼ ነው" አልኳቸው።

«ምን ዓይነት ሥራ ነው? ቢዝነስ ነው ወይስ የዲፕሎማሲ ሥራ?» አሉ፤ አትደብቀኝ እንጂ በሚመስል ተማጽኖ። እኔም በጨዋታችን ደስተኛ ከመሆኔ በላይ ለኢትዮጵያ ያላቸውን ፍላጎትና ክብር አስቤ ዋናውን ጉዳይ ላጫውታቸው ፈለግሁና፡

«የመጣሁበት ሰበብ ቢዝነስ ነው» አልኩና ከዘረዘርኩላቸው በኋላ «ዋናው ዓላማዬ ግን ዋሽንግተን ዲሲ ሆዋርድ ዩኒቨርሲቲ ካሉ ምሁር ጋር በመገናኘት አንድ የእንቅቅልሽ መፍቻ ቁልፍ ለማግኘት ነበር" በማለት የማዳመጥ ፍላጎታቸውን ለማወቅ ሞከርኩ።

"የምን እንቆቅልሽ?" ሲሉ እርሳቸውም በከፍተኛ ጉጉት ከመቅጽበት መለሱ።

"አይ ታሪኩ ረጅም ነው" አልኩና ራሴን እንደ ማከክ እያደረግሁ እንደ ብዙዎቹ ፈረንጆች በጉዞ ላይ በዝምታና በንባብ ከማሳለፍ ይልቅ እንደኛ በጨዋታ ማሳለፍ የሚፈልጉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ስል ተረጋጋሁ።

"አታላንቲክ ውቅያኖስን አቋርጠን፣ በአውሮፓ ሰማይ ላይ አልፈን፣ የሚዲትራንያን ባሕር ተሻግረን፣ አለልችውን የሲቢያንና የሱዳንን በርሃ ቁልቁል እያየን በመንገዝ አዲስ አበባ ለመድረስ ከሀሥራ አምስት ሰዓታት በላይ አየር ላይ እንቆያለን። ስለዚህ የምናወራው ረዥም ታሪክ ያስፈልገናል" በማለት ሥጋቱን አርቀው በፈገግታ ፍላጎታቸውን ገለጹልኝ።

"እንዳሳሰለቸዎት ብዬ ነው እንጅ" አልኩ በድጋሚ።

"ፈጽሞ ! ይልቅስ ዝርዝር አድርገህ እንድትነግረኝ እፈልጋለሁ። እንቆቅልሽ የሆኑ ታሪኮችን መስማት ደስ ይለኛል" አሉ።

"ካሉ እሺ እንግዲህ" አልኩና ተመቻችቼ ትረካዬን ጀመርኩ።

# ምዕራፍ አምስት

ይገርመዎታል! ዕለቱ ሐሙስ በወርኃ ሚያዝያ እንደ ሁልጊዜው በጠዋት ቢሮ ገባሁ። ልማድ ሆኖብኝ ቢሮ ከጠዋት 12፡30 እስከ 1፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ መግባት ደስ ይለኛል። ብዙ ጊዜ ቀርስ አልበላም። ቤቴንም በጠዋት ለቅቄ ሠራተኛ ከመግባቱ በፊት ቢሮ ገብቼ መጀመሪያ አጭር የኀሊና ጸሎት ማድረስ ደስ ይለኛል። ቀጥሎም በኢንተርኔት የዓለምንና የሀገር ውስጥ ዋና ዋና ዜናዎችን አያለሁ። ከዚያም የኢሜል መልእክቶችን አይቼ መልስ የሚያስፈልገው ካለ ከሰጠሁ በኋላ በተለይ የምርምር ሥራዎቼን ጽሑፍ ሥራ እከናውናለሁ። ቀጥሎ መደበኛ የመሥሪያ ቤት ሥራዬን እሠራለሁ። ይህ ከእሑድ በስተቀር የማይቋረጥ በአብዛኛው የሚከናወን ልምዴ ነው።

በዚሁ ቀንም እንደተለመደው የዕለቱን ተግባሬን በማከናወን ላይ እያለሁ ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ተኩል አካባቢ የሞባይል ስልኬ ጮኸ።የሞባይል ስልኬ ሲጮህ ሰላም አይሰማኝም። ለምን እንደሆነ አይገባኝም። ሞባይልም ሆነ ሌሎች የመገናኛ ቴክኖሎጅዎችን ያለ እነርሱ መኖር አስቸጋሪ እየሆነ በመምጣቱ ለመጠቀም ብገደድም ብዙም ደግሞ አያስደስቱኝም። ለማንኛውም ስልኬን አንስቼ

"ሃሎ" አልኩኝ

"ሲሳይ ነህ ? " አለ የወንድ ድምጽ

"እምን ነኝ፤ ማን ልበል?" አልኩ

"ከናዳ ማርያም አበምኔት ከአባ መርሐ ጽድቅ ተልኬ ነው" አለኝ።

ከአባ መርሐ ጽድቅ ጋር የቀረበ ግንኙነት ባይኖረንም አውቃቸዋለሁ። በሰሜኑ ኢትዮጵያ ከሚገኙ ሊቃውንት አንዱ ሲሆኑ በምናኔ ሕይወታቸውም የተመሰገኑ አባት እንደሆኑ እሰማ ነበር።

"ምነው አባታችን ደኅና አይደሉም?" አልኩት

"ኧረ ደኅና ናቸው" አለኝ።

"ገዳሙ፤ ማኅበረ መነኮሳቱስ ? " አልኩት

"ሁሉም ሰላም ናቸው" አለኝ።

"አባ ናቸው መልእክቱን ንገር ያሉኝ"

"ለማን? ለእኔ ? " አልኩ

"እምን ለአንተ"

"እና ምን ነበር መልእክቱ ?" አልኩት ብዙም ጉጉት በሌለበት ስሜት

"ኧ .." አለና መልእክቱ እንደጠፋበት ሁሉ "እ.. አባ እንዳሉህ ታመሐል፤ ታመሐል እኛ የገዳም አባቶችህ ደግሞ መድኃኒቱ አለን እና ሳይበረታብህ ሳትውል ሳታድር ብቅ በል ብለውሃል" አለኝ።

"እንዴ ምን ዓይነት መልእክት ነው?" አልኩት በመገረም

"ንገር የተባልኩት መልእክት ይኸው ነው" አለኝ።

"በል እግዜር ይስጥልኝ ደኅና ዋል" ብዬ ስልኩን ዘጋሁ።

ስልኩን ዘግቼ በመገረም ብዙ ሳስብ ቆየሁ።

"ታመሐል ማለት ምንድን ነው?" እኔ እንደሆን ባለፉት ዐሥር ዓመታት እልፍ እልፍ በምግብ ለውጥና በሥራ ጫና ከሚሰማኝ የጨጓራ መጠነኛ ሕመም በስተቀር ሙሉ በሙሉ ጤነኛ ነኝ ማለት ይቻላል። ጨጓራዬም ቢሆን ለስሙ እንግሁት እንጂ ምቾት ከመንሣት ያለፈ ሕመም ሊባል በሚችል ደረጃ ሊገለጽ አይችልም።

በወጣትነት ዘመኔ በተለይም ከዐሥራ ስድስት እስከ ሃያ ሁለት ዓመት እድሜዬ ከፍተኛ የሆነ የሕመም ስቃይ ደርሶብኛል። በዚህም ምክንያት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ለአንድ ዓመት ሙሉ በሙሉ አቋርጬው ሁሉ ነበር። ሕመሜ እጅግ ስቃይ የበዛበት ነበርና። የሚያሳዝነው ደግሞ ተገቢ ሕክምና ካለማግኘቴም በላይ እስከፊ የሥነ ልቡና ጫናዎችንም አሳልፌያለሁ። አሁን ያለሁበትን ጤንነቴን ሳስበው ምናልባት "የመከራ ሂሳቤን አወራርጃለሁ ማለት ነው" እላለሁ። በቃ በጤናዬ በጣም ደስተኛ ነኝ። እንደልቤ እንቀሳቀሳለሁ፣ እሩቅ መንገድ በእግሬ መሄድ እችላለሁ፣ ያገኘሁትንና የቀረበለኝን እበላለሁ እጠጣለሁ፣ በቂ እንቅልፍ እተኛለሁ፣ እለቀ። ታዲያ በዚህ መካከል "ታመሐል" ብሎ መልእክት መላክ ምን ይባላል? አልኩና ነገሩን ለማጣጣልም፣ ለመርሳትም ሞከርኩ።

ነገር ግን "ሰው እኮ ሥጋው ብቻ አይደለም ጤነኛና በሽተኛ የሚባል፣ ነፍስም አእምሮም ወይም አስተሳሰቡም ጭምር እንጅ" የሚል ሁሊም የማውቀው ሃሳብ ይታገለኝ ጀመር። በርግጥም ሰው እንደ እንስሳ ሥጋ ብቻ አይደለም ነፍስም ጭምር እለው። ሰው ኃጢአት ሲሠራ ከእግዚአብሔር ሲርቅ ነፍሱ ታመመች ሊባል ይችላል። ይሁን እንጅ በተቻለ መጠን እግዚአብሔርን በመፍራትና በማመስገን ስለምኖር ያን ያክል ከተቀደሰ ገዳም፣ ከተከበረ የገዳም አባት መልእክት ሊያስልክ የሚችል ሕመም ምን ተገኘ በማለት ደግሞ እንደገና ማሰብ ጀመርኩ።

እሁንም እንደገና ውስጤ "ሰው ለለነፍሱ ጤንነት እርግጠኛ መሆን የሚችል አይደለም። እንዲያውም የመንፈስ ሕመም እኮ ለባለቤቱ አይታወቅም" የሚል ሙግት አመጣብኝ። ሳምንቱን ሙሉ ምንም ሥራ ሳልሠራ በዚህ ሀሳብ ስብጠበጥ "ምን ማለት ነው? ልሂድ ወይስ ልቅር" እያልኩ ሃሳብ ስፈትል ስተረትር፤ ስቋጥር ስፈታ አሳሳፍኩት። ለወትሮው ሌሊት የማያስቸግረኝ እንቅልፌም እልም ብሎ ጠፋ።

"ታመሐል ብሎ መልእክት መላክ ምንድን ነው? መድኃኒቱም ከእኛ አለ ማለትስ?" እንዳይሰነበት የለም አንድ ሳምንት ያለ እንቅልፍ አሳለፍኩ። እንደተለመደው ቢሮ በጠዋት እየተነሳሁ ብገባም የተረጋጋ ስሜት አጣሁ። እዚህ ሁኔ ከምበጠበጥ ሂጄ የሚሉትን ልስማ፤ ሌላው ቢቀር ትልቅ መንፈሳዊ አባት ናቸው፤ በታውን ተሳልሜ ከሳቸው ተባርኬ ብመጣ ምን የማጣው ነገር አለ?። አለመሄድ የሀሳብ እንግልቱን ሲጨምር መሄዱ ግን ሰላምን የሚሰጥ መሆኑ ተሰማኝና ለመሄድ ወሰንኩ።

# ምዕራፍ ስድስት

በሳምንቱ ዐርብ ከሰዓት በፊት ባለው ጊዜ የቢሮ ሥራዬን አጠናቅቄ ከሰዓት በኋላ ወደ ተጠራሁበት ቦታ ለመሄድ ከቢሮ ተሰናብቼ ወጣሁ። ምሳ እንደነገሩ ከበላሁ በኋላ መልእክቱን ላደረሰኝ ወጣት ደውዬ የገዳሙን አቅጣጫና እንዴት መሄድ እንደምችል ጠየኩት። በበጋ የመኪና መንገድ ከገዳሙ ድረስ የሚደርስ መኖሩንና በየትኛው አቅጣጫ መሄድ እንዳለብኝም ሙሉ መረጃ ሰጠኝ።

ከቀኑ 8፥30 አካባቢ የተከራየሁትን ሃርድ ቶፕ ቶዮታ ላንድ ክሩዘር የመስክ መኪና ይዤ ከባሕር ዳር ወደ አዲስ አበባ በሚወስደው መንገድ ወደ ዳንግላ ተፈተለኩ። መቼም በመንገዱ ሁሉ አእምሮዬን ወጥሮ የያዘው ነገር ቢኖር "ታመሐል" የሚለው ነበር። እንዴት "ታመሐል" ይሉኛል? ሊላኛው ስሜቴ ደግሞ "ታመሐል" ስላሉህ ይሆን ያክል የተረበሸክ "ሞተሐል" ቢሉህ እንዴት ልትሆን ነው እያሉ በእኔው ውስጥ ሁለት አሳቦች ወርነት ያካሂዱብኝ ጀመር።

ዳንግላ ከተማ ደርሼ ሰዓቴን ሳይ በሃሳብ ማዕበል እየተናጥኩ ከመጠን በላይ በፍጥነት እንደነዳሁ ታወቀኝ። "እውነትም ታምሚያለሁ" አልኩኝ ለራሴ። ዳንግላ ከተማ የገዳሙን አቅጣጫና መንገዱ መኪና የሚያስኬድ መሆኑን አረጋግጬ አንዳንድ ምልክቶችን መዝግቤ ጉዞዬን ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ አድርጌ ፍጥነቴን ተቆጣጥሬ መንዳት ጀመርኩ።

ከዳንግላ ከተማ ሁለት ኪ.ሜ. ጉዞ በኋላ ያለው የመሬት አቀማመጥ፣ የአፈሩ ለምነት፣ የውሃው መብዛት፣ የሰዕዋቱ ልምላሜ፣ ባስተዋለው "የአማልእክት አምላክ የሚኖረው እዚህ ነው" ያስብላል። አፈሩን አይቶ ምርት የሚያሳፍስ ብቻ ሳይሆን የሚታየው "ዝም" ብሎ በውሃ አቡክቶ ጋገር ለመብላት ፤ ወይም እንኩቶ ለመግመጥ፣ ወይም እንደ በሶ በጥብጦ ለመጠጣት የሚያስጎመጅ ነው። "አቤት አፈር! የጸጋ የውበት ምድር። እንዲያው እንደዚህ ያለ ሀገር ይዞ መቸገርና መራብ ይገርማል" እያልኩ ስደነቅ የቴዎድሮስ ካሳሁን ዘፈን ትዝ አለኝ።

"አፈር ይዞ ውስጡ አረንጓዴ

ለምን ይሆን የራበው ሆዴ?"

እንዲህ በአድናቆትና በተመስጦ በመጠኑም ቢሆን ዘና ብዬ ጉዞዬን ቀጠልኩ። 16 ኪ.ሜ. እንደተጓዝኩ የአማራ ክልል የገጠር መንገድ ሥራ ድርጅት የሠራው የበጋ መንገድ አገኘሁ። በአካባቢው የሚያርሱ ገበሬዎችን ከገዳሙ ለመድረስ የቀረኝን ርቀትና መንገዱ ወደፊት ያስኬደኝ እንደሆን ወይም እንዳልሆን ጠየቅሁ። ከገዳሙ የቀረኝን ርቀት በእግር ጉዞ ስሌት ሲነግሩኝ ስድስት ኪ.ሜ. እንደቀረኝ ተረዳሁ። መንገዱ ከገዳሙ አካባቢ ምናልባት ኃርሶ ሊሆን ይችል እንደሆን እንጅ እስከዚያ ድረስ ግን በእርሻዎች መካከል የተከለለ ጥርጊያ መንገድ እንዳለም ነገሩኝ፣ መግቢያ መንገዱንም አስጀመሩኝ። ባስጀመሩኝ መንገድና አቅጣጫ መኪናውን እየነዳሁ ሳይሆን እንደኳስ እያንጠርኩ በሚመስል ሁኔታ ጉዞዬን ቀጠልኩ።

ሦስት ኪ.ሜ. እንደተጓዝኩ ከደጋማው ሰከላ ወረዳ ግሽ ዐባይ ከተማ ተነሥቶ ወደ ጣና የሚገሰግሰው ከጣና በኋላ ዐባይ ተብሎ የሚነግሠው እስከዚያ ድረስ ግን የልጅነት ጊዜውን በአማልክት ምድር እንዳሻው እንዲቦርቅ የተፈቀደለት የሚመስለው ግልገል ዐባይ ፀሐይ ሊሞቅ ተገልብጦ የተኛ ዘንዶ መስሎ ከፊቴ ድቅን አለ። ጉድ ፈላ! ድልድይ የለ፣ ግልጽ መሻገሪያ የለ!

መኪናውን አቁሜ በእግሬ ብሔድ ከዐርባ ደቂቃ በላይ አይፈጅብኝም። ግን መኪና ሜዳ ላይ ጥሎ መሔድ ደግሞ አሳሰበኝ። ለመሻገር መሞከር ደግሞ አደጋው ታየኝ። ከመኪናው ወርጄ ከብት የሚጠብቁ እረኞችን ፍለጋ ተዘዋወርኩ። ከወንዙ ወዲያ ማዶ ከብቶች ታዩኝ። ለመጣራት ስሞክር ከአንድ ትልቅ ዋርካ ሥር በርከት ያሉ ልጆች "ኪሳራ" የሚባለውን ባህላዊ ጨዋታ ሲጫወቱ አየኋቸው።

"ኪሳራ" ማለት በዱላ ጫፍ ልክ በተሰራ ጉድጓድ በግምት ሁለት ሜትር ርቀት ላይ ቆሞ ቱሉፍ ወይም ድባ ወይም ዛጐል የተባሉ ጠጠር መሳይ የባሕር ጌጦችን፣ ወይም ደግሞ ያኔ ምንነታቸውን የማናውቃቸው የስማቸውም ትርጉም የማይገባኝ ወርቃ ወርቅ እያልን ስንጠራቸው የነበሩ የከበሩ ማዕድናት ስብርባሪዎችን እልሞ በመወርወር የሚጫወቱት ተወዳጅ ቁማር ቀመስ ጨዋታ ነው።

በገጠር ያሳለፍኩት የልጅነት ዘመኔና ሕይወቱ ድንገት ድቅን አለብኝ።‹‹ወርቃ ወርቅ›› የወርቅ ዘር ወይም ዓይነት ለማለት እንደሆነ እንኳ አሁን ነው የገባኝ። ያኔ ሳናውቅ ገደል ውስጥ እየወረወርን የተጫወትንባቸው፣ ዛሬ የከበሩ ድንጋዮች (Gemstones) መሆናቸውን ሳውቅ ደግሞ እነርሱ የሉም። አልማዝ ቢሆን ወርቅ፣ ሲሳም ማዕድን ያን ጊዜ ከጫካ ተለቅሞ ተወርውሯል፤ ጨዋታውም ሲያልቅ በዚያው ይቀራል፤ ዛሬ ደግሞ ምንነቱ ሲገባን ብንፈልግ አናገኘውም። እርሱን እያሰብኩ አሁንስ ከዚህ መውጫታችን በምን ያታወቃል? የሚል ጥያቄ ድንገት ወደ ኅሊናዬ መጣ። እዎ! ዛሬም እንደዚያ ጊዜው ባለማወቃችን መጫዎቻ ያደረግናቸው ትልልቅ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። የዘርመል (ጀኔቲክስ) ሀብታችን በኅሊናዬ መጣ፤ እንኳን ዝበሬው የተማረውስ እየተጫወተበት አይደል? ብረሳው ይሻላል እልኩና ወደ ጨዋታው ተመለስኩኝ።

አቤት! ስንት ዓይነት ጨዋታ ነበረን። ቀልሞ ሞሞ፣ እንኳል. እንኳል፣ ዙሮ ገብ፣ ውሻ ውሾሽ፣ ገና የሚባሉት ግልጽ ሕግ ያላቸው የቡድን ጨዋታዎች ነበሩ። በጣም የሚገርመኝ እነዚህ ጨዋታዎች አሜሪካ ውስጥ ተወዳጅ ከሆኑት ራግቢ፣ ክሪኬት፣ አሜሪካን ፉትቦል፣ ሆኪ ከሚባሉት ጋር መሠረታዊ ቅርርብ ያላቸው መሆኑ ነው። ልዩነቱ የእኛዎቹ ጨዋታዎች በአግባቡ ሳይጠኑና ሳያድጉ ባሉበት የቀሩና እየተዘነጉ ያሉ መሆናቸው ነው። ሕፃናትንና ልጃገረዶችን በማካተት ወጣቶችን በማዝናናት ተመራጭ የነበሩት መደዳውን ተሰልፈን በቁጠራ መልክ የምንጫወታቸው ብዙዎች ነበሩ። አባር መገንብር፣ አንዱ ብራንዱ፣ አዲና ወላዲና፣ አጃ ቆሎ ሰንዱ ቆሎ፣ የሚባሉት በአግባቡ ተጠንተውና አድገው ቢሆን ኖሮ ለዐፀደ ሕፃናትና አንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ጨዋታን ያካተቱ የአካል እንቅስቃሴ የተሞሉ የራሳችን የሆነ ልዩ ማስተማሪያ በኖረን ነበር። እነዚህ ሁሉ ከተማዊነት እያጠፋቸው መሄዱ ያሳዝናል። በእኛ ሀገር ከተማዊነትና ከተሜነት ምዕራባዊነት ሆኗልና።

ገጠሩን ሳስብ ሌላም ነገር ትዝ አለኝ። እናቶች ሕፃናት ልጆቻቸውን አባብለው ለማስተኛት የሚጠቀሙበት ዜማና ግጥም። በቁመታቸው ልክ ተሰክቶ ከታች በኩል አንድ ክንድ የሚሆን ድረስ በቀጭኑ ተተልትሎና በእያንዳንዱ ትልታይ ዛጎል የተባለ የባህር ሼል በታሰረበት ከቆዳ በተሰራ ማዘያ (እንቀልባ ይባላል) ሕፃኑን ታዝላለች። እናትዬዋ ስትወዛወዝም ሆነ ስትራመድ ዛጎሉ እርስ በርስ እየተጋጨ እንዳች ሥርዓት ያለው የሚመስል ድምፅ ያወጣል። በአንድ እጇ የሕፃኑን መቀመጫ እየጠበጠበች በልዩ ዜማ

እሽሩሩ.....እሽሩሩ...እምቡቡ..ቡ

የማሙሽ/የማሚት እናት የት ሄዳለች

ማርና ወተት ልታመጣ ሄዳለች፣ እያለች ታንጎራጉራለች።

የዜማው ይዘት ሕፃኑን እያባበለ የሚያስተኛ በመሆኑ እፍታ ሳይቆይ ሕፃኑን እንቅልፍ ይወስደዋል። ከዚያም ወደ ሌላው ሥራዋ ትገባለች። በአውሮፓ ከዚህ ጋር የሚቀራረቡ ዜማዎች ተደርሰው ለስላሳ የማጀቢያ ሙዚቃ ታክሎባቸው በሲዲ ታትመው ለእናቶች በገበያ ይቀርባሉ። እናቶችና አሳዳጊዎችም ልጆቻቸውን ማስተኛት ሲፈልጉ ሕፃኑን አልጋ ላይ አጋድመው ሲዲውን ያጫውታሉ። ሕፃኑ/ኗ በፍጥነት እንጎላችቶ ይተኛል። በመሠረቱ ከእኛ የገጠር እናቶች ዜማ መርሕ ጋር በእጅጉ የተቀራረበ ነው። ልዩነቱ የእኛ እናቶች ዜማና ድርሰት ሙያዊ እገዛና በሙዚቃ መሳሪያዎች እጀባ አግኝቶ ሳያድግ ቄስ እንደገዘተው ጋኔን ባለበት ቆሞ መቅረቱ ነው።

ከስመጥኩበት የትዝታ ባሕር ወጥቼ ሎክ ብዬ ስሥሀ ከጨዋታቸው ቀና፣ መለስ ብለው ከተሜ መሆኔንና መኪና መቆሙን ሲያዩ ተንጋግተው ወደ ወንዙ መጡ። እኔ በግርግሙ ፈርቼ ዳር የቆምኩትን ግልገል ዐባይን ከምንም ሳይቆጥሩ እየተሯሯጡ መሐል ለመሐል አቋርጠውት ወደ እኔ ሲመጡ ፍርሃቴን አስታውሼ ራሴን ታዘብኩት። እንደገመትኩት ግን ጥልቅ አልነበረም።

ከመካከላቸው አንዱ፡

"ጋሼ ምን እምታረግ ሁነህ መቶህ ነው?" አለኝ ከሕጻንነት ቅላጼው ጋር በሚያምር ዜማዊ ንግግሩ።

"ናዳ ማርያም ልሄድ ነበር። ወንዙ መኪና ያሻግር ይሆን?" አልኳቸው

"አዎን እንጂ። ሁልስትና ውሃ እምታበጀው መሙቅላይቱ መኪና አልፋበት የለ" አለኝ

ከዚያም እየተሻሙ መኪናውን ያሻገሩበትን መስመርም ጠቆሙኝ። መኪናውን እስነስቼ መንቀሳቀስ ስጀምር ሁሉም በአንድ ድምጽ

"ጋሸ ስቀለኝ ፣ ኧረ ስቀለኝ፣ እማ፣ አስቅለን እንጅ!" ይሉ ጀመር።

የመኪናውን የኋላ በር ከፍቼ ሁሉንም ጫንኩኝና የልጆቹን የቀሀንትና ፈጣሪን እምነ በመኪናው ወደ ወንዙ ገባሁ። ውሃው ጥልቅ ባይሆንም የዓለቱ ወጣ ገባነት እጅግ አንገላቱኝ እንደምንም ተሻገርኩ።

"በሉ በቃችሁ ውረዱ" አልኳቸው መኪናውን አቁሜ።

"ኧረ ትንሽ ውሰደን" አሉ በአንድነት የተማከሩ ይመስል።

"እንዴ ከብቶቻችሁን ማን ይጠብቅላችኋል? አልኳቸው በመገረም።

"ምን እማሆን ናቸው?" አሉ እየተቀባበሉ። ንግግራቸው ሁሉ የሆነ ደስ የሚል ዜማ አለው።

"በሉ ውረዱ ፤ወላጆቻችሁ ይቆጣሉ" ብዬ ከስተር ስል ሁሉም ቅር እያላቸው ከመኪናው ወረዱ።

ከዚያ በኋላ አካባቢውም በበልግ እርሻ ተሞልቶ መንገዱ እጅግ እየጠበበ መጥቶ በመጨረሻም ጭራሽ በትክክል እርሻ ተዘግቶ ቆመ። በአካባቢው ያገኘሁትን አርሶ አደር ስጠይቀው ከገዳሙ መድረሴን አረጋገጠልኝ።

"የመኪና ማቆሚያ የቀበሌ ገበሬ ማኅበር ጽሕፈት ቤት ወይም ትምህርት ቤት አገኝ ይሆን ?" አልኩት

"ተዚያው ተገዳሙ እማታቆመው ምንን ሆነህ?" አለኝ

"እርሻህን እንዳልጠቀጥቅ ብዬ ነው እንጂ" አልኩት

"ኧረ! እንግዳ መስለኸኛን፤ ና ዝም ብለህ እለፍ " አለኝ።

ገበሬውን አመስግኜ አምስት መቶ ሜትር እንደተጓዝኩ በሀገር በቀልና በፍራፍሬ ዛፎች የተከበበችውን ናጻ ማርያምን እስከ ግርማ ሞገሷ በአመሻሹ የፀሐይ ብርሃን እያበራች አየኋት።

ገዳሟ ከዳንግላ ከተማ በስተምሥራቅ 22 ኪ.ሜ. ላይ በምዕራብ ጎጃም ዞን በሜጫ ወረዳ የምትገኝ ጥንታዊት ገዳም ናት፤ ፈለገ ብርሃን ናጻ ማርያም።

# ምዕራፍ ሰባት

መኪናዬን ከአንድ ጥግ አቁሜ ቀላልሌ ወረድኩ። በጎዳሙ ሁለት ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናት አሉ። የጎዳሙ መጠሪያ የሆነችው ታሪካዊቷ ናዳ ማርያምና በቅርቡ የተሠራው የቅዱስ ላሊበላ ሕንጻ ቤተክርስቲያን። የማኅበረ መንክሳቱ መኖሪያና የእንግዳ ማረፊያው ከቅዱስ ላሊበላ ቤተክርስቲያን አካባቢ ስለሆነ ወደዛው አመራሁ። ወደ ቤተክርስቲያኑ ደጃፍ ሰላም ጠጋ ብዬ ጸሎት ከአደረስኩ በኋላ ወደ እንግዳ ማረፊያው ሄድኩ።

የእንግዳ ማረፊያው ከአበምኔቱ መኖሪያ አቅራቢያ ሲሆን የአበምኔቱ መኖሪያ ደግሞ ከእንጨት የተሠራ ባለአንድ ደርብ ቤት ነው። ከሥሩ ዳስ መሰል ሰቀላ ቤት ሲኖር የጉባዔ ቤት እንዲሁም የእንግዳ መቀበያ ሆኖ ያገለግላል። በአንድ ዲያቆን አማካኝነት ሰሜን ተናግሬ ከዳሱ ውስጥ አንድ ጥግ ይዤ ቁጭ አልኩ። ወዲያው አባ መርሐ ጽድቅ የሥራ ልብስ ለብሰው መጡ። ፊርጠም ያለው አካላቸው፣ ቆፍጣናው ቁመናቸውና አለባበሳቸው ሁዳድ ሲያርስ የዋለ የገጠር የመሬት ባላባት አስመስሏቸዋል። ገና ሲያዩኝ በአባታዊ ፈገግታ ተቀብለው ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ወደ ቤት ይዘውኝ ገቡ። እንደ ገዳሙ የእንግዳ አቀባበል ልማድ ውሃ ቀርቦ ዲያቆኑ እግሬን አጠበኝ። የሚጣፍጥ አሬት በነጭ ሽንኩርትና ተልባ ተቀምሞ በተሠራ ሽሮ ወጥ በእንጀራ ከጠላ ጋር ቀረበልኝ። እኔ ራቴን እየበላሁ አባ ስለ ቤተሰቤ፣ ስለ ሥራዬ፣ እንዲሁም ሌሎች የተለመዱ ጥያቄዎችን ሲጠይቁኝ ከቆዩ በኋላ

"መንገዱ ስላልተጠረገ በጣም እንገላታለህ እንደሚሆን አገምታለሁ። እዚህ ገዳሙ ድረስ መኪና ሲመጣ የአንተ የመጀመሪያው ሳይሆን አይቀርም። ለማንኛውም ስለደከመህ ሂድና እረፍ በሉ" ብለው ማረፊያ እንዲያዘጋጁልኝ ዲያቆኑን አዝዘውት የጉባዔ ሰዓት መድረሱን ነግረውኝ ወጥተው ሄዱ።

የተወሰነ ሰዓት ጉባዔውን ለመከታተል ሞከሬ መንገዱ በጣም አንገላቶኝ ስለነበረ በዛውም ሳምንቱን ስላልተኛሁ እንቅልፍ ሲታገለኝ ጊዜ ለመተኛት ወደ ማረፊያዬ ሄድኩ። ለራሴ ግን

"ሕመም ስለተባለው ነገር ምን አልባት በሕልሜ ይገለጽልኝ ይሆናል" አልኩት።

ከቤቱ ይዤው በመጣሁት የመኝታ ከረጢት (ስሊፒንግ ባግ) ተጠቅልዬ፣ ተገንገጮ ማለት ይቀላል በሳር ተደልድሎ ከዛፍ ላይ ቁርበት ከተነጠፈበት መደብ ላይ ጋደም አልኩ። እፍታም ሳልቆይ እንቅልፍ ሲያንገላብጠኝ ታወቀኝ። የት እንደወደቅሁ ሳላውቀው ጠዋት ዐሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ ነቃሁ። እንኳን ሕልም ቅዥትም የለ፤ በቃ ሰላማዊ ድብን ያለ እንቅልፍ ነበር የወሰደኝ። ሕልም እያለሁ ብዬ ያሰብኩት ግን ፍርሃቱን አልፎ ከመጣው ከግብዝነቱ የመነጨ በመሆኑ ራሴን ታዘብኩት፤ "የኛ ዮሴፍ" ብዬ ተረብኩት።

በፍጥነት ተነሣሁና ወደ ቤተክርስቲያን ሄጄ የጠዋት ጸሎት አደረስኩ። እኔ ቤተ ክርስቲያን ስደርስ የኪዳን ጸሎት አልቆ ማኅበረ መነኮሳቱ ወደ የሥራ ምድባቸው ተበታትነው ነበር። አባ መርሐ ጽድቅ ከአካባቢው ከመጡ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ጋር ባልና ሚስት መሰሉኝ ቆመው ሲነጋገሩ አየኋቸው። ንግግራቸውን እንዳላቋርጥ ነገር ግን በአቅራቢያው መኖሬን እንዲያውቁ በሚያስችለኝ በታ ላይ ራቅ ብዬ ቆሞ አልኩ። አባ ከሰዎቹ ጋር ያላቸውን ውይይት እንደጨረሱ በሙሉ ፈገግታ ታጅበው ወደ እኔ መጡ።

"እንደምን አደሩ አባ?" አልኳቸው ተሽቀዳድሜ።

ሰላምታዬን መልሰው መስተል ካሳለሙኝ በኋላ "መቼም መኝታው ጉርብጦህ ነው የሚሆን፡ ቁንጫውም እኮ መከራ ነው" አሉኝ።

"ኧረ የት እንደወደኩ እንኳን ሳላውቅ ነው የነጋው አባ! ጥሩ እንቅልፍ ነው የተኛሁት" አልኳቸው።

"ደኅና ነው። ባይመችህም የገዳሙ በረከት ከምንም በላይ ነው" አሉና

"እስኪ በል ና ገዳሙን ላሳይህ" አሉኝ።

እኔም እንግዲህ በጉብኝቱ ወቅት በምሳሌም፣ በተረትም ወይም በቀጥታም ሊነግሩኝ ይችላሉ ብዬ በንቃት ተከተልኳቸው።

ጉብኝታችንን የጀመርነው ከጥንታዊቷ የናዳ ማርያም ሕንፃ ቤተክርስቲያን ነው። ናዳ ማርያም መጀመሪያ በዐፄ ሠርፀ ሦስተኛው ከፍለ ዘመን ወደ ጣና ሃይቅ ዳጋ እስጢፋኖስ በመጡትና በታውንም ባቀኑት በአቡነ ሂሩተ አምላክ እንደተተከለች፣ ጽላቱንም ያመጡት ከጣና ቂርቆስ እንደሆነ፣ በኋላም በአጼ ፋሲል ዘመነ መንግሥት ርስት ተሰጥቷት ሕግ ተሰርቶላት እንደተገደመች ነገሩኝ። ከውጥ የጽድ እንጨት የተሠራው ግዙፉና ባለግርማው የቤተክርስቲያኑ በር ተከፈተና ሥዕሞቼን ከአወለቅኩ በኋላ ወደ ውስጥ ዘለቅን። የቤተ መቅደሱ ግድግዳ በሥዕል ተውቦ ከሚያውደው የዕጣን መዓዛው ጋር የሆነ ስሜትን ሰክን የሚያደረግ ሃይል አለው።

"የመጀመሪያውና በአጼ ፋሲል ዘመን የተሳለው ሥዕል በእሳት አደጋ ወድሞ ስለነበረ ይህኛው ሥዕል የጥንቱን ይዘት ጠብቆ በ1975 ዓ.ም ነው እንደገና የተሳለው" አሉና፡-

"የጥንቱ ሊቃውንት ሥዕሎች ቤተ መቅደሱን ከማስዋብ በዘለለ ትልቅ ማስተማሪያና የታሪክ መዛግብት ሆነው እንዲያገለግሉ በማሰብ ሲሳሉ ወጥ የሆነ የቦታ አቀማመጥና የአሳሳል ሥርዓት ተሠርቶላቸዋል። ሁል ጊዜ በስተምሥራቅ በኩል ባለው የቤተ መቅደሱ ግድግዳ ላይ የሚሳሉት ሥዕሎች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረጋቸውን ተዓምራት የሚያሳዩ ሲሆኑ፣ በስተምዕራብ በኩል ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በምድር ላይ ተገልጦ በተመላለሰበት ዘመን የፈጸማቸውን መጽሐፋውያንም ትውፊታውያንም ታሪኮች፣ ለምሳሌ ከብሥራት እስከ ዕርገት ያለውን፣ በስተሰሜን በኩል የቅዱሳንና የሰማዕታትን ተጋድሎ የሚያሳዩ ሲሆኑ፣ በስተደቡብ ደግሞ የድንግል ማርያምን ስደትን የሚያመላክቱ ይሳላሉ" እሉና እየዞርኩ በትኩረት እንዳያቸው ጋበዙኝ።

ሁሉም ሥዕሎች ክብ ፊት፣ ትልልቅ ዓይኖችና ጥቁር ፀጉር አላቸው። በአንድ ወቅት የድኅረ ምረቃ ጥናቴ አማካሪ ፕሮፌሰሬ ከነበረ ሆላንዳዊ ወዳጄ ጋር ጣና ሃይቅና ዘጌ የሚገኙ ገዳማትን ስንጎበኝ ሥዕሎቹን በአድናቆት ሲመለከት ከቆየ በኋላ የተናገረኝም ትዝ አለኝ።

"ከሥዕሎቹ ጥንታዊነትና ውበት በላይ የአስገረመኝ ሁሉም ሥዕሎች ራሳችሁን ኢትዮጵያውያንን እንዲመስሉ ተደርገው መሳላቸው ነው። ይህም በራሳችሁ የምትተማመኑ ሕዝቦች መሆናችሁን ያስረዳል" ነበር ያለኝ።

እኔም በውስጠ ወይራ ንግግር "እኛን ነበርን" ብዬ ነበር የመለስኩለት።

በሰሜን አቅጣጫ በኩል ስንደርስ አባ መቋሚያቸውን ወደ ላይ ከፍ አድርገው፣

"ይህን ሥዕል ተመልከተው ግማሽ ፊቱ ከአንድ ዐይኑ ጋር ብቻ ነው የተሳለው። እንደዚህ ሲሆን ባለታሪኩ ኃጥኣን፣ ከሃድያን፣

አረማዊያን ናቸው ማለት ነው። ምክንያቱም በሰማዕታቱና በቅዱሳኑ ያን ሁሉ መከራ ያደረሱባቸው በተፈጥሮ የተሰጣቸውን በጎነትና በሙሉነት የማስቢያ ጭንቅላት ስላልተጠቀሙበትና አስተሳሰባቸውም ሆነ ድርጊታቸው ሰብአዊነትን ለቅቆ ከእንስሳም ከፍቶ አውሬነት የታየበት ስለሆነ በሙሉ ሰውነት አይሳሉም። ከዚህ በተቃራኒው የጌታ፣ የእመቤታችን ፣ የቅዱሳንና የሰማዕታት ግን ሙሉ ፊታቸው ከሁለት ዐይኖቻቸው ጋር ራሳቸው አካባቢ የብርሃን ክበብ ኑሮበት ይሳላሉ" አሉ። "ምክንያቱም ደግነታቸውና በጎነታቸው፣ አዛኝነታቸውና ርኅራኄያቸውም ለገዳዮቻቸውም ጭምር ስለሆነና በሚገደሉበት ሰዓት እንኳ በገዳዮቻቸው ላይ ቂምም ሆነ በቀል ስለሌላቸው አምላካቸውንም ስለሚመስሉት ሙሉነታቸውን፣ እድሎም የሌለባቸው መሆኑን፣ ቅድስናቸውንና ክብራቸውን ስለመግለጥ ባለሙሉ ገጽ ባለ ክብ ዐይን (ሁሉንም እኩል የሚያይ ማለት ነው) ሆነው ክብራቸውና ጸጋቸውም በራሳቸው ላይ ባለው የብርሃን ክበብ ተወክሎ ይሳላሉ" ሲሉ እኔ በመገረም፣ እንዚህ ሠዐሊያን ኖረው የእኛን ዘመን ሰው በሥዕል አሳዩ ቢባሉ ያለ ዐይን ይስሉን ይሆን? የሚል የጎሊና ጥያቄ ሲመጣብኝ ፈገግ ካልኩ በኋላ አባ ያዩኝ መሰለኝና ደነገጥሁ።

የቤተክርስቲያን ሥዕሎችን እያየሁ ያደኩና የኖርኩ ብሆንም እንደዚህ የራሱ ሥርዓትና ፈርጅ ያለው፣ በአግባቡ ሳንጠይቅና ሳናውቅም እንዲሁ ልንናገርለት የማንችል መሆኑን ግን አስተውየው አላውቅም ነበር። አባ መርሐ ጽድቅ ከሚናገሯቸው ቃላት መካከል የመጣሁበትን ዓላማ የሚገልጽ ነገር ለመፈለግ ሰል በአእምሮዬ ሳውጠንጥን ገለጻቸውን አልፎ አልፎ በመሳቴ እራሴን ወቀስኩት። "መርፌ ፈላጊ ማረሻ ቢያንቅፈው አያያውም" የተባለው ተረት በእኔ ደረሰ አልኩ።

አባ አብሮን የነበረውን ዲያቆን ከመቅደሱ ውስጥ አንድ ሥዕል እንዲያመጣላቸው አዘዙት። እርሱም በወንዶች መቋሚያ በኩል ወዳለው በር ሲሔድ አባ፦ "ና በዚህ በቅዳሴና በጸሎት ጊዜ እንጂ

እንዳሁኑ ሲሆን ግን በዚህ በምዕራቡ በር መግባትም ይቻላል" ሲሉት ዲያቆኑ ጋቢውን አደግድጎ ሲያበቃ ሦስት ጊዜ ሰግዶ የመቅደሱን የበር ደፍ (የታችኛው ጠርዝ) ከተሳለመ በኋላ ወደ ውስጥ ገባ።

እኔም የእርሱን ድርጊትና የአባን መመሪያ የከተማው አገልጋዮች ከሚያደርጉት ጋር እያነጻጸርኩ በከተማው እንዲህ ጥንቃቄ ሲደረግ አላየሁም፤ አያስፈልግም ብለው ነው ወይስ ሥርዓቱን አያውቁትም እያልኩ ሳስብ ዲያቆኑ አንድ ሜትር በአንድ ሜትር በሆኑ እንጨቶች የተወጠረ ጥንታዊ ሥዕል ይዞ ብቅ አለ። አባም ሥዕሉን ተቀብለው፤

"ይህች የእመቤታችን ሥዕል ከእሳት አደጋ የተረፈች የጥንቱ ሥዕል ቅሪት ናት። እንደምታየው የፈለኩበት ምክንያት የዚህች ሥዕል እድሜ ከበሬት መቶ ዐመት በላይ በመሆኑ ነው። አሁን መቅደሱ ላይ የምታየው ሥዕል ግን በሠላሳ ዓመት ውስጥ መደብዘዝ ጀምሯል። በተሳለበት ወቅት ደማቅ ነበር" አሉ። ቅሬታቸው ከገጻቸው ላይ በግልጽ ይታያል። የሥዕሎቹ የውበት ልዩነት ቁልጭ ብሎ ስለሚታይ ለምን ቅር እንዳላቸው ተረዳሁ።

"ለመሆኑ የጥንቶቹ ሥዕሎች ውበታቸውን እንደያዙ ረጅም ዘመን የመቆየት ምሥጢር ምን ይሆን?" አልኳቸው።

"የጥንቶቹ ሥዕሎች ቀለማቸው የሚዘጋጀው ከዕፅዋት ሥር፣ ቅጠል፣ ቅርፊት፣ አበባና ፍሬ፡ ከእህል ዘር፡ ከጥቃቅን ነፍሳት፣ ከከሰልና ከጥቀርሻ ሲሆን በየመልካቸው ተቀምመው ረጅም ጊዜ መሬት ውስጥ ተቀብረው እንዲብላሉ ይደረጋሉ። አጠቃላይ ዝግጅቱም ትዕግሥት ይጠይቃል። ያሁኑ ቀለሙ የፋብሪካ ስለሆነ ችኩላ እየበዛበት ይመስለኛል" አሉና የገዳሙን የመሬት ይዞታ ለማሳየት ወደ ውጪ እየመሩ ይዘውኝ ወጡ።

በወቅቱ ስላለው የገዳሙ የመሬት ይዞታ፣ በጎርፍ ተቦርቡሮ ከጥቅም ውጭ የነበረውን በረባር መሬት ከአካባቢው መስተዳድር ተረክበው ልዩ ልዩ የአፈርና ውሃ መጠበቂያ ሀዳጎችን ሠርተውና አድነው ያለሙትን ደን፣ የፍራፍሬ ምርታቸውንና መንገድ ስላልገባ ገበያ ስለማጣታቸው በቁም ነገር ገለጻ አደረጉልኝ። እውነትም ለዐይን የሚያስጎመጅ የበሰለ የፓፓዬ ፣ የአቮካዶ፣ የማንጎና ሌሎች ፍራፍሬዎች የትሬሳ ቀለብ ሆነው ግማሹም ሜዳ ላይ ፈርጦ ሲታይ በጣም ያሳዝን ነበር።

በመቀጠልም የመድኃኒትነት ባሕርይ ያላቸውን ዕፅዋት እያሳዩኝ ለምን በሽታ ፈዋሽነት እንደሚያገለግሉ፣ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ በግልጽነትና በለጋሥነት ያብራሩልኝ ጀመር። የደንና የሥነ ምህዳር ሳይንስ ሙያዬ በመሆኑና በተለይም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ተጠብቀው በቆዩት ዕፅዋቶች ላይ ሰፋ ያለ ምርምር ሳደርግ የቆየሁ በመሆኑ የአባ ገለጻ ብዙም አዲስ አልሆነብኝም። ምናልባት ግልጽነታቸው ካልሆነ በስተቀር። የሆኖ ሆኖ የእኔ ዋና ዓላማ በዚህ ጉብኝት ወቅት መታመሜን የሚገልጽ ወይም የሚያመለክት ነገር አለ ወይ? የሚለው ነው። ነገር ግን ምንም ነገር ሳገኝ አልቻልኩም።

ለሁለት ሰዓታት ያክል የገዳሙን ውጫዊና ውስጣዊ ይዞታ ካስጎበኙኝ በኋላ ወደ ማረፊያቸው ወስደው ቁርስ እንዲቀርብልኝ አስደረጉ። ከፊቴ ቁጭ ብለው ከላይ ከላዩ በትንሹ ቁርስ እያደረጉ እየቀመሱ እንድበላ ይጋብዙኝ ጀመር። እንደ እውነቱ ከሆነ የመብላት ፍላጎት ጨርሶ አልነበረኝም። የቀረበልኝን ምግብ እንደምንም ጨርሼ ገበታው ከተነሳ በኋላ

" አሁን ነው ሰዓቱ!" አልኩኝ በልቤ።

አባ ጺማቸውን እያፍተለተሉ ሩቅ የሚያዩ መስለው በሀሳብ ነጐዱ። የተወሰኑ ደቂቃዎች አለፉ፤ ልቤ ከጉሮሮዬ መጥታ የተወተፈች መሰለኝ።እንደዚህ ለማወቅና ለመስማት የጓጓሁለት ነገር በሕይወቴ ከዚህ በፊት መኖሩን አላስታውስም። አባ ከሀሳባቸው ተመልሰው ለመናገር መዘጋጀታቸውን ለማሳወቅ ይመስል "እህ እህ" ብለው ጉሮሮአቸውን ጠረጉ።

"ስማ የኔ ልጅ! ጥሪያችንን አክብረህ ስለመጣህ ደስ ብሎናል። ብዙ ሥራ እንዳለብህ አውቃለሁ። በረጅሙ ጉዞ እግዚአብሔር ይርዳህ፤ የቅዱሳን በረከት አይለይህ!" ብለው መረቁኝና

"አሁን የበልግ ዝናብ እየጣለ ስለሆነ ግልገል ዐባይ ወደ ማታ ሊሞላ ይችላል፤ መንገዱም ጭቃ ሊሆንብህ ስለሚችል በጠዋት መሄድ አለብህ" አሉና

"የገዳሙ በረከት ለልጆችህ እንዲደርሳቸው ይሁን ትወስዳለህ" ብለው ፓፓዬ፣ ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ካዝሞራ ተቀርጦ በቅርጫት ተሞልቶ የተዘጋጀ አሳዩኝ። ከዚያም መደናገሬን ከምንም ሳይቆጥሩ ጸሎት ለማድረግ ተነሡ።

"እኔ እኮ አባ ....." ጠፋብኝ የምለው። እንደምንም ታግዬ፣

"አባታችን ከዚህ የመጣሁት በላኩብኝ መሠረት ሕመሜን ለማወቅና እ..... እ..... እንዳሉትም መድኃኒትም ካለ እንዲሰጡኝ ነው" አልኳቸው።

በጸጥታ ሲያዳምጡኝ ከቆዩ በኋላ ልዩ የሆነ ፈገግታ አሳዩኝ። ይህ ፈገግታ ለልጅ ወይም ለጅል የሚያሳዩት ዓይነት ሆኖ ተሰማኝ። 'በቃ ከዚህ በኋላ መጠየቅ ልጅ ወይም ጅል መሆን ነው። እኔ ደግሞ ሁለቱንም አይደለሁም" አልኩ በልቤ።

አባ የመሰናበቻና የጉዞ ጸሎት ካደረሱልኝ በኋላ፦

"ዕርፍ ይዞ ወደ ኋላ የሚል የለምና በርታ! አባ መዝገበ ሥላሴ የሚባሉ በሥራ ትጋታቸው የሚታወቁ ጻድቅ ነበሩ" ሲሉ ታሪክ ጀመሩ። "ፈጣሪ ተገልፆ እንዲህ አላቸው ‹ከዚህ ዓለም ድካም መሰናበቻህ ደርሷልና በመጪው ሐምሌ ትሞታለህ ቢላቸው፣ ‹ፈጣሪዬ በማረሻዬ፣ በመንልኅያዬ፣ በመዝሪያዬ በዋናው የሥራ ጊዜማ መሞት አልፈልግም። የምዘራው ሲያብብና ሲያፈራ በጥቅምት፣ በህዳር ልሙት እንጅ› አሉት። ፈጣሪም ጥያቄአቸውን ተቀብሎ በጥቅምት አረፉ። አንተም አንድ ቁም ነገር ሳትሰራ የጀመርከውን ዳር ሳታደርስ ሞት ቢመጣብህ እምቢ በለው !!" እያሉ ትከሻዬን መታ መታ አደረጉትና ወጥተው ሄዱ።

"በቃ! የመጣሁበት መልእክት ምሥጢር ሆኖ ሊመለስ ነው?!" አልኩ።

ለበረከት የተሰጠኝን ፍራፍሬ ከመኪናዬ ላይ ጭኜ ሲረዳኝ የቆየውን ዲያቆን አመስግኜና ተሰናብቼ በተስፋ መቁረጥና በመደናገር ስሜት ገዳሙን ለቅቄ ጉዞዬን ጀመርኩ። የገዳሙን ክልል ለቅቄ መውጣት እንደ ጀመርኩ ትናንት በእርሻው ላይ አቋርጬው እንዳልፍ የፈቀደልኝን ገበሬ በእርሻው ዳር ቆሞ በእጁ "የቁም" ምልክት ሲያሳየኝ አየሁት።

መኪናውን አቆሜ

"እንደምን አደርክ? የገዳሙ ቆይታዬን ጨርሼ እየተመለስኩ ነው፤ ያው ላስቸግርህ ነው። አቋርጬ ማለፍ አለብኝ" አልኩት።

"አይ! በሰላሙ ይበላሽብኛል" ሲል

ቱግ ብዬ "ምንድን ነው የምትለው፤ ወይ ትናንት አላሳልፍም ብትል ጥሩ ነበር፤ አሁን መኪናውን ከዚህ ጥዬ እንድሄድ ነው የምትፈልገው?!" አልኩት።

መቼም በአንድ ጊዜ የጋለ ብረት ድስት ላይ የተጣደ ሽሮ ይመስል ራሴ በራሴ ተንተከተከኩ።

"በዚያ በኩል እኮ ማለፊያ አለ" አለና ከገዳሙ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ወሽመጥ የሚመስል ያልታረሰ መሬት አሳየኝ።

"ኧረ በዚያ በኩል ብታልፍ ምን ችግር አለው?" አለኝ ደግሞ።

እየተመናጨኩ መኪናውን መከራውን በሚያባላ ፍጥነት አዙሬ ወደ ያሳየው አቅጣጫ በረርኩ። ውስጤ ግን ዝም ብሎ ይንተከተካል።

"እንዴት እንዲህ ይቀልድብኛል? ስንት ሥራ እያለኝ ና ብሎ ሂድ ይባላል እንዴ?!" እላለሁ። ያ ወሽመጥ የሆነው የማር መሬት በመጠንኛ ዛፎች የተሞላ ኮረብታ ላይ ደርሶ ቆመ። በቃ ወዴትም እንደማይወስደኝ ተረዳሁ። መኪናውን አቁሜ አካባቢውን ለመቃኘት ወደ ሜካው ጠጋ ስል ሁለት ሴት መነኮሳይያት እንጨት እየለቀሙ (መሰለኝ) አየኋቸው።

"ደኅና አደርክ የኔ ልጅ ?" አሉኝ አንደኛዋ በእድሜ ገፋ ያሉት።

"ደኅና እግዜር ይመስገን።" አልኩ በእልህና በቁጣ ስሜት ፤ ፊቴን ከእርሳቸው ዘወር አድርጌ።

"የደብረ አሮን መንገድ እኮ በዚህ አይደለም" አሉኝ።

"እማሆይ እኔ የደብረ አሮንን መንገድ አይደለም የምፈልገው። ወደ ዳንግላ ከዚያም ወደ ባሕርዳር የሚያደርሰኝን ነው" አልኳቸው።

ንግግሬ ከቁጥጥሬ ውጭ በሆነ ሁኔታ ከትሕትና የራቀ ሆነ።

"አይ የኔ ልጅ! ባሕር ዳርም፣ ደብረ አሮንም መንገዱ ያውም አይደል?!" አሉ። ከዚያ ሌላኛው መነኮሲት እንገታቸውን ወደ መሬት ሰበር አድርገው

"እ... ደብረ አሮን መሄድህ አይቀርም ብለው ነው" አሉኝ።

"ምንድን ነው የሚያወሩት!" አልኩ ለራሴ።

"ለማንኛውም የባሕር ዳርም ሆነ የደብረ አሮን መንገዱ በየት በኩል ነው?" አልኳቸው። ወደ መጣሁበት አቅጣጫ አመለከቱኝ። ቁጣዬ እንደገና ገነፈለ።

"ብዚያ በኩልማ አንድ ገበሬ ትናንት አሳልፎኝ ሲያበቃ ዛሬ ከለከለኝ" አልኳቸው።

"ግዴለም ተመልሰህ ሂድና፣ ሩቅ መንገደኛ ነው ብለውሃል ቆለኞቹ እማሆይ በለው" አሉኝ።

በወጉ ሳልሰናበታቸውና ሳላመሰግናቸው እየተቆናጠርኩ ያንን የፈረደበትን መኪና በአፍጢሙ እየደፋሁ ወደ እርሶ አደሩ እርሻ እቅጣጫ ሂድኩ። ስደርስ ከነበረበት ቦታ ቁሞ አገኘሁት። እንገቴን እውጥቼ "አሳልፈው ተብለሃል" አልኩት። ትዕቢት ነገር ያለብኝ መሰለኝ።

"ምን? እንዴት? " አለኝ ነቃ ኮስተር ብሎ።

"አሳልፈው ብለውሃል እዛ አካባቢ ያሉ መነኩሳት" አልኩት።

"አይ ጌታው እርጋታ ይጎድልሃል፣ ይችን ቁራጭ የእርሻ መሬት ለማለፍ የሚያስፈልግህ ትዕግሥት በእጅህ ነው" አለኝ። በጣም ስሜታዊ እንደሆንኩ ተሰማኝና ሐፍረት ያዘኝ። ስለሆነም ከመኪናው መሪ ላይ እራሴን ደፋሁ

"እንደጤዋ ሰው የመጣሁት ገዳም ነው፣ በቃ መጣሁ፣ ተመልሰኩ። ምን አጣሁ?" ብዬ እራሴን አረጋጋሁና መነኩሳቱ የነገሩኝ ነገር ቁም ነገር ያለው መሆኑን ለማስተዋል ቻልኩ። ስለዚህ ቃል በቃል ለገበሬው መንገር እንደሚገባኝ ተረዳሁ።

"ይቅርታ የኔ ወንድም ሩቅ መንገደኛ ነው ፣ አሳልፈው ነው ያሉህ" አልኩት።

"ማናቸው?" አለኝ

ቀጥሎ ያለው ብዥ አለብኝ።

"በረኸኛዋ እማሆይ  ያሉኝ መሰለኝ" አልኩት።

ትንሽ ፈገግ ብሎ " በረኸኛዋ እማሆይ አይደለም፣ ቆለኛዋ እማሆይ ነው" አለኝ።

"እምን እንደዛ ነው" አልኩት እንደ ማፈር ብዬ።

"ብዙ ነገር ለማወቅ ትሞክራለህ፣ የማለፈያህን ትንሽ ነገር ግን ማስታወስ ካቃተህ ጉዞህ ሳይከብድህ አይቀርም። ነገርህ ሁሉ ግርድፍ አይሁን፣ በል ና እለፍ" አለኝ።

የገበሬው አነጋገር ከበድ ማለት ብቻ ሳይሆን ግርምም አለኝ። አደብ ገዛሁና በትሕትና  አመስግኜ የእርሻ መሬቱን አቋርጬ ከመንገድ ስገባ የሆነ ቅንብር የሚመስል ነገር እንዳለ ተሰማኝ።

"ደብረ አሮንን ምን አመጣው?!" ፣ "ሩቅ መንገድንስ?!" ፣ "ቆለኛዋ እማሆይ! የሚለውስ?!"

"ሂድ በለው!" የሀሳብ ማዕበል መጣ።

"ለመሆኑ ምንድን ነው እያደረኩ ያለሁት?"

"መድኃኒት ፍለጋ ወይስ በሽታ ፍለጋ?"

"ታምሚያለሁ ወይስ አልታመምኩም?"

"ለምን ከዚህ የአእምሮ  ጨዋታ ውስጥ ገባሁ?!"

"ደብረ አሮን፣ ሩቅ መንገድ ፣ ቆለኛዋ እማሆይ!!!"

"ቹ በለው! የሀሳብ ፈረሴን ከመኪናዬ በበለጠ ፍጥነት እጋልበው ጀመር"። እንደገና ሊላ የሀሳብ ባሕር ውስጥ ዘፍቀውኝ በማዕበሉ እየተገፋሁ እነርሱን እየራቅሁ ነጎድኩ።

# ምዕራፍ ስምንት

ከናዳ ማርያም ተመልሼ አንድ ወር ቆየሁ። የሥራዬ ጠባይ ውጥረት የተሞላበትና ብዙ ሰዓት ሥራ ገበታ ላይ ማሳለፍን የሚጠይቅ ቢሆንም ናዳ ማርያም የሄድኩበትን ጉዳይና፣ ያጋጠሙኝን ነገሮች ማብሰልሰሌ አልተረም። ቢታ ሀሳቡ ኅሊናዬን ይወተውተው ጀመር። የጉዞዬ ዓላማ ምን እንደሆነ ባይገለጽልኝም ደብረ አሮን ክረምቱ ከመግባቱ በፊት መሄድ እንዳለብኝ ተሰማኝ።

ደብረ አሮንን ከሀሥራ ስድስት ዓመት በፊት ሄጄ አይቸዋለሁ። በወቅቱ የተጓዝኩበት ምክንያት በሀገራችን ካሉ ጥንታውያን አስደናቂ ገዳማት አንዱ በመሆኑ ከቦታው በረከት ለማግኘት ነበር። ደብረ አሮን በሰሜን ወሎ ዞን መቄት ወረዳ ውስጥ ከወረታ ወልድያ በሚወስደው መንገድ ደብረ ዘቢጥ ከተባለች ከተማ በስተሰሜን በስምንት ኪ.ሚ. ርቀት ላይ ከትልቅ ተራራ እናት ላይ የሚገኝ ገዳም ነው። በዐፄ ዐምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት በታላቁ ኢትዮጵያዊ ጻድቅ አቡነ አሮን የተመሠረተው ይህ ገዳም ቤተ መቅደሱ ከዓለታማው ተራራ ጫፍ ላይ በዋሻ መልክ ተፈልፍሎ የተሠራ ነው። ዋሻው ቤተ መቅደስና ቅኔ ማኅሌቱን ጨምሮ አምስት ክፍሎች፣ ሁለት በሮችና ሰባት መስኮቶች ያሉት ሲሆን ዓለታማ የሆነውን ጣራ የሚሸከሙ ዐሥራ ዐራት ዓምዶች ተሠርተውለታል።

የቅኔ ማኅሌቱ ጣሪያ በግምት ሁለት ሜትር በአንድ ሜትር የሆነ ቀዳዳ ሲኖረው በዚህ ቀዳዳ የፀሐይ ብርሃን ቢገባም ዝናብ ግን ወደ ውስጥ አያስገባም። ይህም ለአቡነ አሮን መታሰቢያ የተሰጣቸው ቃል ኪዳን ምልክት ሆኖ ይቆጠራል። "ወዳጄ አሮን ሆይ አንተን የሚመስልህ የለም። አንተ የተጋደልክበትን ቤተ መቅደስ እንኳን ዲያብሎስ ዝናብ አይደፍረውም" በማለት ፈጣሪ ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል ይላሉ መነኩሳቱ። በዚህ ተራራ በርካታ ቅዱሳን በተጋድሎ አለፈውበታል።

ደብረ አሮን ለመጓዝ ከባሕር ዳር ከተማ ከጠዋቱ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ተነሣሁ። መኪና የማሽከረከረው እኔ እራሴ በመሆኑና ሌላ ተጓዥ አብሮኝ ስላልነበረ ጉዞው ሀሳብ የተሞላበት እንደሚሆን ገምቻለሁ።

"ለምንድን ነው ደብረ አሮን የምሄደው? ምንስ ነው የምፈልገው?"

"ምናልባት ደብረ አሮን ከመሄዴ በፊት ማጣራት ያለብኝ ነገር ይኖር ይሆን?"

ተጨማሪ ሀሳብ በመጣልኝ ቁጥር እንደ ኳስ እየነጠረ መልሶ እኔን ከማስጨነቅ በስተቀር የተረፈኝ ነገር የለም። "በቃ ዝም ብሎ ደብረ አሮን መሄድ፣ ምልክት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን በጥሞና መከታተልና መመዝገብ፣ መተንተን ነው፤ ሌላ ምርጫ የለም" እላለሁ።

እንዲህ በሀሳብ እየተንገላታሁ የፎገራ ሜዳን አቋርጬው ጉና ተራራን ፊት ለፊት ከርቀት ወደ ቅርበት እያየሁ ፣ ጨጨሆ መድኃኔዓለም ደረስኩ።

እዚህ ሰፍራ ደርሶ ጨጨሆ መድኃኔዓለምን ሳይሳለሙ ማለፍ የማይታሰብ ነው። መኪናዬን አንድ ጥግ አቁሜ ተሳለምኩና ለአፍታ አካባቢውን ቃኘሁት። ይህ ቦታ በአሁኑ አጠራር በደቡብ ጎንደርና በሰሜን ወሎ ድንበር ላይ የሚገኝ የተራራ ሠንሰለት አካል ነው።

በስተምዕራብ በኩል ያለው የላይ ጋይንት ወረዳና በስተምስራቅ በኩል ያሉት የመቄትና ላስታ ወረዳዎች በግምት ሦስት ኪ/ሜ ጥልቀት ባለው ሸለቆ የተለያዩ ሲሆን ጨጨሆ መድኃኔዓለም ላይ ግን ሃምሳ ሜትር በላይ በማይረዝም የተራራ ሠንሰለት ተገናኝተዋል። በ1971 ዓም ቻይናዎች እዚህ ሰፍራ ላይ አስደናቂ ድልድይ መሳይ መንገድ ሰርተውበታል። የሰሜን ወሎዎቹ ደጋ መቄትና ላስታ ከጎንደሬዎቹ ጋይንቶች ጋር እንዲገናኙበት ተፈጥሮ ያበጀችው የሕዝቦች የፍቅር መገናኛ ሰፍራ ነው፤ ጨጨሆ መድኃኔዓለም። እናም የአካባቢው ሕዝብ የጎንደር፣ የላስታና የመቄት ሥነ ልቡናና ባህል ሕብር ውጤት ነው።

ለዚህ ይመስላል እንጋፋዋ ድምፃዊት አስቴር አወቀ

“እናቱ ከላስታ አባቱ ከጎንደር

ተወለደ ሸጋ ከጨጨሆ መንደር”

ብላ የተቀኘችው። ግጥም ባህልን ከመልክአ ምድር ጋር ማስተሳሰር ሲችል ዋጋው ከፍ ይላል።

ጨጨሆ መድኃኔዓለምን ከተሳለምኩ በኋላ መኪናዬን አስነስቼ ጉዞዬን ቀጠልኩ። ከባሕር ዳር ከተነሳሁ ከሦስት ሰዓት ጉዞ በኋላ መቄት ወረዳ ደብረ ዘቢጥ ደረስኩ። መኪናዬን ከነዋሪዎቹ ለአንዱ አደራ ሰጥቼ ኮተቴን በጀርባዬ አዝዬ ቁልቁል በረሃውን መውረድ ጀመርኩ።

እንደ እቅዴ ከሆነ ከሰዓት ከገዳሙ በመድረስ ሁለት ሦስት ቀን ከመነኩሳቱ ጋር ስጨዋወት ሰንብቼ፤ በዚያውም ለሚያንገላታኝ እንቆቅልሽ መፍቻ ፍንጭ አገኝቼ ለመመለስ ነው። ለአንድ ሰዓት ያክል ቁልቁል ከወረድኩ በኋላ እንደገና ቀጥ ያለ ዳገት ለአንድ ሰዓት ከሃያ ደቂቃ ያክል ተጓዝኩ። ጉልበቴ እየተብረከረከ ሰውነቴ በላበት ተዘፍቆ፣ እንዳይደረስ የለም ደብረ አሮን ደረስኩ።

ሁሉም እንግዳ ብርቅ የሚሆንባቸው ገዳማውያኑ በፍቅርና በፈገግታ፣ ለድካሜም ሐዘኔታቸውን በመግለጽ ተቀበሉኝ። ማንነቴንና ከየት እንደመጣሁ ስነግራቸው ብዙም እንግዳ እንዳልሆንባቸው ተገነዘብኩ። መምጣቴን የሚጠብቁ መሰለኝና ደስ አለኝ። እግሬን አጥበው፣ ገዳሙ ያፈራውን እህል ውሃ አቅርበው፣ ከበው እንደ ብርቅ ያነጋግሩኝ ጀመር። የገዳማውያንን ደግነት ሁልጊዜ ሳስብ፣

"በዚህ ዘመን ሰው ይህን ያክል የዋህ ይሆናል!" እላለሁ።

ለአንድ ሰዓት ያክል ካረፍኩ በኋላ በአባ ተወልደ መድኅን መሪነት ገዳሙን እየተዘዋወርኩ ለማየት ወጣሁ። የጉብኝቴን ዓላማ የሚገልጥ ነገር ይናገራል ብዬ ነገሮችን ሁሉ በጥንቃቄ በመመልከትና አባ የሚናገሩትንም ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቼ በመስማት ከዚህ በፊት ያየሁትን ገዳም እንደ አዲስ ማየት ጀመርኩ።

አባ ተወልደ መድኅን የደብረ አሮን ሊቃው የተአምራት መገለጫ ናቸው። ዐይነ ሥውር ሆነው ሳለ ዙሪያውን ጭው ያለ ገደል ባለበት ተራራ ጫፍ ላይ በተገደመ ቦታ ዐይናማ ሲንቀሳቀስ አዞርት ለመውደቅ በፍርሃት በሚረድበት ቦታ እግራቸውን ያዝ ሳያደርጋቸው በፍጥነት ከቦታ ቦታ እጥፍ እጥፍ እያሉ ሲራመዱ ማየት በራሱ ተአምር ነው። "መንክራዊ አቡነ አሮን እዚህ እንድኖር ነው የፈቀዱልኝ፤ መንገዱ ሁሉ በእርምጃዬ ቁጥር ልኬታ በፍጥነት የማየት ያክል አውቀዋለሁ" ይላሉ።

መቼም አቡነ አሮንን አንስተው አይጠግቧቸውም። በሰፊ የዘመን ልዩነት የኖሩ ሳይሆን በአካል ያሳደጓቸውና የሚያውቋቸው ያክል ነው ስለሳቸው የሚናገሩት። "በአምስትና በድስት መቶ ዓመት ዘመን ልዩነት ኑረው አንደኛው በዐጸደ ሥጋ ሌላኛው በዐጸደ ነፍስ ሆነው ይህን ያክል የሚያቀራኛቸው ምሥጢር ምን ይሆን?" እያልኩም እደነቃለሁ።

"አባታችን መንክራዊው አሮን በዐፄ ሰይፈ አርእድ ከፍተኛ ግፍና ስደት ደርሶባቸዋል" አሉ አባ በሐዘኔታ።

"እንዴ ለምን? ዐፄ ሰይፈ አርእድ ክርስቲያን የሆኑ የክርስቲያን ንጉሥ አልነበሩም እንዴ?" አልኳቸው በአግራሞት።

"የመንግሥቱ ወራሽ ትሆናለች ትባል የነበረችው የንጉሡ ልጅና የሥራዊቱ አዛዥ ይሆናል ይባል የነበረው የንጉሡ ወንድም በአባታችን በመንክራዊዉ አሮን ትምህርት ተማርከው ደብረ አሮን መጥተው በመመንኰሳቸው ነበር፤" አሉና

"አባታችንን ሸዋ ድረስ አስጠርቶ ‹እንዴት ብትደፍረኝ ነው ልጀንና ወንድሜን ያመነኰስካቸው› ቢላቸው አባታችንም ‹አንተም ልብ ገዝተህ፡ ይህን ዓለም ንቀህ፡ ዙፋንህን ትተህ ወደ እኔ ብትመጣ ባመነኰስኩህ ነበር› አሉት። በዚህ ተቆጥቶ አባታችንን የሚላስ የሚቀመስ በሌለበት በበረሃ ሰባት ዓመት ከተከታዮቻቸው ጋር በግዞት እንዲኖሩ ሰደዳቸው" አሉኝ ትክዝ ብለው።

"ከዚያስ?" አልኩኝ በመገረም።

"መንክራዊው አባታችንም ቅጣቱን በጸጋ ተቀብለው፤ በረሃውን አልምተው ወይን ተከሉ። ወይኑ ሲደርስ ለንጉሡ ‹እሸት ቅመስ› ብለው የወይን ዘለላ ላኩለት። ንጉሡም በድርጊታቸው ልቡ ተነክቶና በሥራው ተጸጽቶ ‹አባቴ ሆይ ይቅር በለኝ፤ ስለኃጢአቴም ጸልይልኝ› ብሎ በክብር ወደዚህ ወደ ደብረ አሮን መለሳቸው" አሉ ከሐዘን ስሜታቸው የወጡ እየመሰሉ።

በዚህ በተራራ አናት ላይ የተፈጸመውንና ተሰምቶ የማይሰለቸውን የቅዱሳኑን ገድል አባ እየነገሩኝ ቆይተን ወደ ዐሥራ አንድ ሰዓት አካባቢ ሲሆን "የሰርክ ጸሎት ሊደርስ ነው፤ እንተ በዚህ በኩል አረፍ ብለህ ቆየኝ" አሉና ከዋሻው ቤተ መቅደስ በስተምሥራቅ አቅጣጫ ወሰዱኝ። ወዲያው በእሰገራሚው ፍጥነታቸው ከዐይኔ ተሰወሩ።

የቤተ መቅደሱ ምሥራቃዊ አቅጣጫ የተራራው አንዳኛው ጫፍ ሲሆን ልክ እንደ ማማ ሆኖ ከርቀት የሳስታን ተራሮች ያስቃኛል። ደብረ አሮን ላይ ሆኖ ለሚያያቸው ሰው የላስታ ተራሮች በከፍታ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ እየተባባሉ ፉክክር የያዙ ይመስላሉ። አረንጓዴ ጸጋቸው ቢገፈፍም እይታን ለመማረክ የሚሆን ውበት አላጡም። ከጥግ ወደ ታች ሲመለከቱ ማለቂያ የሌለው የሚመስል ገደል አፋፍ ላይ እንደቆሙ ይረዳሉ። ሰውነት ያርዳል! የቅርብና የሩቅ መልክአ ምድራዊ ቅኝቴን እስኪታክተኝ ድረስ ካየሁ በኋላ ፊቴን ወደ መቅደሱ አዙሬ ከሆን ማውላ ላይ አረፍ አልኩና ጸሎት ቢጤ የአቅሜን አደረስኩ።

"አምላኬ ሆይ! አባክህ ለምን እንደ መጣሁ፤ ምን እንደምፈልግ ፍንጭ ስጠኝ። ተራ ቅኝት ከሆነ ደግሞ እንድረሳው አድርገኝ። ሰላሜንም መልስልኝ" በማለትም አምላክን ተማጸንኩ።

በሀሳብ እየተንገላታሁ ለበርካታ ደቂቃዎች ከቆየሁ በኋላ ድንገት ከሰመመን እንደሚነቃ ሰው እንደመባነን ብዬ፣ እግሮቼንና እጆቼን ዘርግቼ መንጠራራት ጀመርኩ። እንደተቀመጥኩ በእጆቼ የተቀመጥኩበትን እንጨት መዳሰስ ጀመርኩ። ጣውላ ነው። ከጎን ወደ ታች ሳንሸራትተው ማዕዘናዊ ጠርዝ አለው። ሀሳቤን ሰብስቤ የተቀመጥኩበትን ጣውላ አየሁት። ነጠላ ጣውላ ሳይሆን ሳጥን መሰል ነው። ወደ ቀኝና ወደ ግራ ርዝመቱንና ቅርፁን አስተዋልኩት። ሰውነቴ ባለሁበት ደርቆ የቀረ መሰለኝ። ድንገት "የሬሳ ሳጥን!" ብዬ ተሰፈንጥሬ ተነሳሁ"። በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ" ብዬ አማተብኩ። የተቀመጥኩበትን ደግሜ ቆሜ አየሁት። በትክክል የአስከሬን ሳጥን ነው። በጣም የሚሰቀጥጥ ስሜት ተሰማኝ። ደግሜ ደግሜ አማትብ ጀመር። ፍርሃት ወረረኝ። ድንገት ከየት መጡ ሳልል፤

" እንዴት ቆየህ?" እያሉ አባ መጡና "በል እንሂድ" አሉኝ።

ከድንጋጤዬ ስላልተመለስኩ መልስ አልሰጠኋቸውም።

"ምነው የለህም እንዴ፣ የት ሄድክ ?" አሉኝ፣

"እረ አለሁ አባ! እ.. ደንግጬ እኮ ነው" አልኩ።

"ምን አስደነገጠህ ልጄ? ድንገት መጣውብህ?" አሉኝ።

"እረ አይደለም። እ... ሳላየው እዚህ አስከሬን ሳጥን ላይ ተቀምጬ ነው እንጂ" አልኳቸው በፍርሃት በሚርድ አንደበት።

"እእእ.. አይዞህ የጻድቁ የአባ አድራል ሀፅም ነው። በረከቱ ያድርብሃል እንጅ ምን ትሆናለህ?" አሉና "ምእመናን በበረከቱ በቃል ኪዳኑ ተስፋ እንዲያገኙ እንዲሳለሙት ነው። ከዚህ ያስቀመጥነው" በማለት እያጽናኑኝ ወደ ገዳሙ ማረፊያ አቅጣጫ መሔድ ጀመሩ።

ከኋላቸው እየተከተልኩ።

"አባ አድራል ነው ያሉኝ?" አልኳቸው ።

"አዎን ሶርያዊው አባ አድራል!" ትንሽ ቆየት ብለው

"አባ መፍቀሬ በኩሳም ይባላል" አሉ።

"እንዲህ ያለ ስም ሰምቼም አላውቅም። የምን ቋንቋ ነው አልኳቸው?"

መልስ ሳይሰጡኝ ማረፊያችን ደረስን። ረዳቸውን ጠርተው ራት እንዲያቀርብ ጠየቁት። እርሳቸውም ጉድ ጉድ ማለት ጀመሩ። ከእኔ ጥያቄ ለመሸሽ የሚሞክሩ መሰለኝ። ራት ቀርቦ "ብላ እንጂ" እያሉ በአባታዊ ፍቅርና ልግስና ይጋብዙኝ ጀመር።

"እየውልህ! "አሉና መናገር ጀመሩ። "በወጣትነቱ በክርስቶስ ፍቅር ተነድፎ ከሶርያ ምድር ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘ። ከዚያም የሲና በረሃን አቋርጦ ምስር ገባ። ዐባይን ተከትሎ ወደ ኢትዮጵያ ተጓዘ"። ይኼን ሲነግሩኝ ቃላት የጠፉባቸው ይመስል እያማጡ ነበር። በመሐል አቋርጠው "ብላ እንጅ! ተውከው እንዴ?" አሉኝ።

"አዎን አባ፣ ጠገብኩ፣ እግዜር ይስጥልኝ፣ ማኅበሩን ያስፋልኝ" አልኩኝ።

ረዳቸውን "በል ና ልጄ ስብሐት በል" አሉት። ወጣቱ ዲያቆን እመስግና ሲያበቃ አባ አቡነ ዘበሰማያት ሰጥተው ማእዱ ተነሣ።

"ከዚያስ አባ ይጨርሱልኝ እንጅ?" አልኳቸው።

"ያው እንዳልኩህ በየሀገሩ ሲያሰለና ሲንከራተት ኑሮ በመጨረሻ የነብያን ምድር አቋርጦ ወደ ቅድስቲቱ አገር ወደ ኢትዮጵያ ዐባይን ተከትሎ መጣ። ዐሥራ ዐራት ዐመታትን በኢትዮጵያ ሲንከራተት ኖር በመጨረሻም ያሰበው ተሳክቶለት እግዚአብሔርን እመስግና አረፈ። በንባቤው መሠረት ዐፅሙ ወደዚህ ወደ አባታችን ወደ አቡነ አሮን ገዳም መጣ"።

እንዴት ወደ አቡነ አሮን ገዳም እንደመጣ ጠየኳቸው። ጥያቄው ለእኔ መሠረታዊ አልነበረም።

"ከጻድቁ አባታችን ከአቡነ አሮን ጋር ቀደም ሲል ይተዋወቁ ነበር። እና እርሳቸው እንዲጸልዩለት በረከታቸው እንዲደርሰው ነበር" አሉኝ።

ይህን ብለውኝ ወደ ማረፊያ መደባቸው ሂደው ቁጭ አሉ።

"ምንድን ነበር የሚፈለገው?" አልኳቸው ።

"ቅዱሱንና ተአምራዊውን ቅርስ ነዋ! ልጄ" አሉኝ።

"የምን ቅርስ? የትኛውን ቅዱስ ቅርስ?" አልኩኝ በጉጉት። መልስ የለም።

"ለመሆኑ ያገኘው የት ነው?" መልሰ የለም።

አባ አውቀው ይሁን ሰዓታቸው ደርሶ ጸሎት በለሆሳስ ማድረስ ጀመሩ።

"የመጠየቅ እድሌ አበቃ ማለት ነው?!" አልኩኝ ለራሴ። "ምን እንዲያው ጅራቱን እንጂ ራሱን የማያስጨብጡ ምሥጢራዊ ሰዎች። ልጉሞች !" አልኩኝ በምሬት። ሊሊቱን ሰገባበጥ አደርኩ።

"ቅዱስ ቅርስ? ሰንት ቅዱስ ቅርስ አለ?"

"ጽላተ ሙሴን ይሆን እንዴ?! አይ አይመስልም!" አልኩ።

እንዳይነጋ የለም እንቅልፍ ባይኔ ሳይዞር ነጋ። ከሌሊቱ ዐሥራ አንድ ሰዓት አባ ለኪዳን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄዱ እንደ ጅራት ተከትዬ ሄድኩ። ኪዳን አልቆ ወደ ውጭ ስንወጣ አባ ተጨማሪ ጥያቄ ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ተረዳሁ። ስለጉዞዬ ነበር የሚያወሩኝ።

"አየህ ልጄ! እንደዚህ በየጊዜው እየመጡ በረከት መቀበል ጥሩ ነው።እራስከን ከቅዱሳን አባቶች ጋር ማቀራረብ መልካም ነው።ያምም ስለሆነ አናስረፍድህም፣ ፀሐይ ሳይበረታ በቀዝቃዛው መንገድህን ብትጀምር ጥሩ ነው" አሉኝ።

"እሺ አልኩኝ" በቅሬታ።

ከዚያም እጃቸውን ትከሻዬ ላይ ጭነው ዝቅ ባለ ድምፅ "የእኔ ልጅ ከመሄድህ በፊት የአባ አድራሉን ዐፅም በጉዞህ ሁሉ እንዲረዳህ ተማፀነው" አሉኝና እየመሩ ወሰዱኝ።

"አትፍራ እጅህን ሳጥኑ ላይ አድርገህ ዙሪያውን እየዳሰስክ ጸሎት አድርስ" አሉኝ።

እስክሬንና የእስክሬን ሳጥን አልወድም። የሞተ ሰው በአጋጣሚ ካየሁ ብዙ ቀን እንቅልፍ አጣለሁ። ሞት ለምን ያን ያክል ግድግዳ እንደሚፈጥር ሁሌ ይደንቀኛል። የምንወደው፣ የምናቅፈው ሰው ከሞተ ከአምስት ደቂቃ በኋላ ያስፈራናል።

ያለኝን ጥንካሬ ሰብስቤ ከቅዱሱ ዐፅም ማስቀመጫ ሳጥን ፊት ተንበረከኩ። አባ መቅደሱን ተጠግተው ቆመዋል። የማደርገውን ማየት ባይችሉም በጥንቃቄ እንደሚከታተሉኝ ተረድቻለሁ።

ፍርሃቱን እንዲቀንስልኝ ዓይኖቼን ጨፍኜ አባ እንዳዘዙኝ ግራ የገባው ጸሎት እያደረስኩ በእጆቼ ሳጥኑን ዙሪያውን መዳሰስ ጀምርኩ።

ሦስቱን መዓዝን አዳርሼ አራተኛውን መዓዝን ስዳብስ በጎን በኩል የተሰጠፈ ነገር ያለ መሰለኝ። ቀና ብዬ ተጠግቼ ሳየው በትንሽ የብረት ሰሌዳ ላይ የተቀረፀ ጽሑፍ አለ። አቧራውን በለበስኩት ነጠላ ጫፍ ጠረግ ጠረግ አድርጌ ሳየው በግእዝ ፊደላት ቁልጭ ብሎ የተጻፈ አጭር መልእክት አለ።

የግእዝ እውቀቴ እንሥተኛ በመሆኑ ፊደላቱን እንዳለ በጥንቃቄ ገልብጬ ሳጥኑን ተሳልሜ ተነሣሁ። የአባ ዓላማ የእስክሬን ሳጥኑን እንድሳለመው ሳይሆን ይህን ጽሑፍ እንዳይ መሆኑ ታሰበኝ። እንዳች ጥንካሬ በውስጤ ሲያድር ተሰማኝ።

"ጨረስክ?" አሉኝ

"አዎን! አባታችን" አልኳቸው።

አባ እንደተለመደው እየመሩ ከገዳሙ መግቢያ በር ላይ አድረሰውኝ ሲያበቁ

"የማይታየውን ለማየት ሞክር። ሰው ሁሉ የሚያየውን ማየት አያስገርምም። እኔ ሰው ሁሉ የሚያየውን ማየት አልችልም፣ ሰው የማያየውን ግን አያለሁ" አሉኝና

"የቅዱሳን አምላክ ይርዳህ፣ መድረሻህን ያሳምርልህ !" ብለው መርቀው ጸሎት አደርገው አሰናበቱኝ።

የሆነ ኃይል ውስጤን እያበርታተው ቁልቁለቱን ወርጄ ዳገቱን ወጥቼ ወደ ገዳሙ ስሄድ ከነበረው ድካም ባነሰ ስሜት ደብረ ዘቢጥ ደረስኩ። መኪና ያቆምኩበትን ሰዎች አመስግኜ መኪናዬን አስነስቼ ወደ ባሕር ዳር ከነፍኩ።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

ከደብረ አርጎን እንደተመለስኩ በሥራ ተወጥሬ ሰነበትኩ። እንደ እውነቱ ከሆነ ፋታ አልነበረኝም። ያም ሆኖ ጋደም ለማለት ወደ አልጋዬ በሄድኩ ቁጥር ከእስክሬኑ ሳጥን ላይ ያገኘኋቸውን ቃላት ምሥጢር ማንሰላሰሌ አልቀረም። ጥሩ የግእዝ እውቀት ያለው ሰው ሳፈላልግ በቅርብ የማውቃቸው መምህር ቀጸላ ትዝ አሉኝ። መምህር ቀጸላ የቅኔ መምህር ሲሆኑ በባሕር ዳር ከተማ ካሉት አድባራት በአንዱ በርካታ ተማሪዎችን ያስተምራሉ። ቀና ሰው ናቸው። አንድ ቀን ቅዳሜ በጠዋት ከሚያስተምሩበት ደብር ሄጄ ከአገልግሎት በኋላ ከቤተክርስቲያን ሲወጡ ጠብቄ አገኘኋቸው።

የእግዜር ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ "ለአንድ ጉዳይ ፈልጌዎት ነበር" አልኳቸው፡

"ምነው በደህና?" አሉኝ።

"ኧረ ደኅና ነኝ፡ የምጠይቀዎት ነገር ኑሮኝ ነው" አልኳቸው።

"አንተ ደግሞ እኔን የምትጠይቀው ነገር ምን ተገኘ?!" አሉኝ በቀልድ መልክ።

ከቤተክርስቲያኑ ግቢ በአንድ ጥግ ወደተሰራው መኖሪያ ቤታቸው ወሰዱኝ። ቤት ገብተን ቁጭ እንዳልን፡

"ጊዜ እንዳልፈጅብዎት ጥያቄዬን ልንገርዎት" አልኩ፣

"ለእኔ ጊዜ አታስብ ብቻ ማወቅ የፈለከውን ንገረኝ" አሉኝ።

"የሆነ ቦታ ተጽፈው ያገኘኋቸው ቃላት ናቸው። የግእዝ ቃላት ስለሆኑ ትርጉማቸውን ነው ማወቅ የፈለኩ" አልኩና በቁራጭ ወረቀት የጻፍኩትን ሰጠኋቸው።

ፊታቸው ከስተር ፈታ እያለ ሲያስተውሉ ቆዩና፣

"እህ! ምንድን ነው?!" አሉና ቀና ብለው ማራ ማራውን ያዩ ጀመር። ይጠፋቸዋል ብዬ ስለማልጠብቅ ዝም ብዬ በትዕግሥት መጠበቅ ያዝኩኝ።

"እየውልህ ሲሳይ!" አሉና "ከነዚህ ቃላት ውስጥ የመጀመሪያው ሁለቱ ቃላት የግእዝ ቃላት አይደሉም" አሉኝ።

"በለው!" ፡ "ወይ ጣጣ!" አልኩኝ ለራሴ። ከአቡነ አሮን ገዳም ከአባ አድራል ሀፅም ሳጥን ላይ በጥንቃቄ ገልብጬ ያመጣኋቸው ቃላት የሚከተሉት ነበሩ.

*"ለኩሳዎ በኩሳ"*

*" ውስተ ክርሠ እመ እንል ሐቃላዊት ይሄሉ"*

"እርግጠኛ ነዎት?" አልኳቸው

"እርግጠኛ ነኝ። የቅኔ መምህርም አይደለሁ?!" አሉኝ በቀልድ መልክ በራስ መተማመናቸውን ለመግለጽ።

"እሺ፣ የሆነስ ሆነና የግእዝ ቃላት የሆኑት ትርጉምስ?" አልኳቸው።

"እነዚያ እንኳን " አሉና

*"ብቆለኛዋ የልጅ እናት ሆድ ውስጥ ይገኛል ወይም ይኖራል ማለት ነው" አሉኝ።*

ጭልጥ ብዬ ሃሳብ ውስጥ ገባሁ:: አባ ተወልደ መድኅን ስለ አባ አድራል የነገሩኝን ማስታወስ ጀመርኩ።

"ዘመኑን በሙሉ በክርስቶስ ፍቅር ተነድፎ በፍሊጋ ኖረ።"

"ምንድን ነበር የሚፈልገው ስላቸው ቅዱሱን ቅርስ ነዋ! ልጄ! ያሉኝ" ትዝ አለኝ።

ስለሆነም ከላይ ግእዝ ያልሆኑት ቃላት ሲፈልግው የነበረውን ቅርስ የሚያመላክቱ ሊሆኑ እንደሚችሉ ገመትኩ። "ብቆላማዋ የልጅ እናት ሆድ ውስጥ ይገኛል/ይኖራል" የሚለው ደግሞ ያገኘበትን ቦታ ያመላክታል ማለት ነው ብዬ አሰብኩ።

ስለዚህ የመጀመሪያው ሥራ የሚሆነው የመጀመሪያዎቹን ሁለት ቃላት የምን ቋንቋ ቃላት እንደሆኑ መለየትና ከዚያም ፍቻቸውን ማወቅ ነው። የምፈልገውን ነገር ካወቅሁ የሚገኝበት ቦታ በኋላ የሚመጣ ነው። ቢያንስ የምፈልገውን ነገር ማወቅ የፍሊጋዬን ሃምሳ በመቶ አቃለልኩ ማለት ነው ብዬ ራሴን አዘጋጀሁ።

"የት ነው ተጽፎ ያገኘኸው?" አሉኝ መምህር ቀጸላ።

እንደ መባነን ብዬ "እ... የሆነ ቦታ ነው" አልኩኝ።

መምህር ቀጸላን ለሰጡኝ ማብራሪያ አመስግኜ እየተጣደፍኩ ወደ ቢሮዬ ሄድኩ። ከሥራ ቀናት ውጭ ቢሮ አካባቢ ሰው ስለማይኖር ፀጥታው እንደልብ ለማሰብ ይመቻል። ቢሮ ደርሼ ወንበሬ ላይ በቁሜ ዘፍ አልኩ።

"የምን ቋንቋ ቃላት ሊሆኑ ይችላሉ?" አልኩ። ሊሆን የሚችለው ከጥንት ቋንቋዎች አንዱ ነው። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መጻሕፍት በአብዛኛው የተተረጎሙት ከአራት ጥንታዊ የመካከለኛው ምሥራቅ ቋንቋዎች ነው። ከዕብራይስጥ፣ ከአርማይክ ወይም ከአሁኑ ሱርስት፣ ከጽርዕና ከዐረብኛ ነው። እነዚህ ቃላት ከአራቱ የአንዱ ሊሆኑ እንደሚችሉ ገመትኩ። ወዲያው አንድ ሀሳብ ታወሰኝ። አባ አድረል ከሶሪያ የመጡ መሆናቸው።

ኮምፒውተሬን በችኮላ ከፈትኩና ከኢንተርኔት Syria + Chirstian + Language የሚል ጎግል ላይ ጻፍኩ። ካገኘሁት መረጃ የአባ አድረል ቋንቋ አረማይክ ወይም ሱርስት ሊሆን እንደሚችል ገመትኩ። ከዚህ በኋላ ከላይ የተጠቀሱትን ቋንቋዎች ላይ ጥናት ያደረገ ሰው ማግኘት እንዳለብኝ ወሰንኩ።

በዚህ መሠረት ነበር በዶ/ር ሻሮን አማካኝነት ወደ አሜሪካ በመምጣት ፕሮፌሰር ዴቪድ ራምስፌልድን ለማግኘትና የቃላቱን ትርጉም ለማወቅ የቻልኩት" አልኩኝና ለረጅም ሰዓት ሳልጠጣው በመቀመጡ የቀዘቀዘውን ቡና ለአስተናጋጁ መልሼ ወይን እንድትሰጠኝ ከይቅርታ ጋር ጠየኩ።

ሚ/ር እንድራውም ጣልቃ ገብተው፣

"ለኔ የሚገርም ታሪክ እየነገረኝ ምሳውንም በደንብ አልበላም። ቡናውንም ስላስረሳሁት ይቅርታውን የምጠይቅ እኔ ነኝ" አለ።

"ምንም ችግር የለም። ካስፈለገ ወይኑን ከምግብ ና ከትኩስ ቡናም ጭምር ላመጣ እችላለሁ" አለች።

"አመሰግናለሁ። ባይሆን ወይን ከትኩስ ቡና ጋር አምጭልኝ" አልኩኝ።

አስተናጋጇ እንደሄደች ወዲያው ሚ/ር እንድሪው በጉጉት

"መጨረሻ የቃላቱ ትርጉም ምን ሆነ?" አሉ።

በፕሮፌሰር ዴቪድ ኮምፒዩተር አማካኝነት ያገኘነው የቃላት ትረጉም፤

"ለካሳዋ በኩሳ"

"ቅዱስ ጽዋ ወይም ቅዱሱ ጽዋ" ማለት ነው የሚል ነበር።

በኮምፒውተሩ ስክሪን ላይ የታየው ማመሳከሪያ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስም ማቴ 26÷27ም ደግሞ እንዲህ ይላል፡

> "ጽዋውን አንሥቶ ይህ ስለብዙዎች የሚፈስሰው የሐዲስ ኪዳን ደሜ ነው። ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ።"

"ስለሆነም አባ አድሪል እድሜ ልኩን ሲፈልገው የነበረው በኋላም ተሳክቶለት ያገኘው የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ በጸሎተ ሐሙስ ለሐዋርያት የሐዲስ ኪዳን ደሜ ብሎ ወይኑን ሞልቶ ያሳያቸውን ጽዋ ነው" ብዬ በረጅሙ ተነፈስኩ።

"Jesus Christ" (የክርስቶስ ያለህ)! አሉ ሚስተር እንድሪው በአድናቆት በቀኝ እጃቸው አፋቸውን ይዘው።

"ይህ ነገር እውነት ይሆናል ብለህ ታምናለህ?" አሉኝ ቀጠሉና

"አባ አድራል ከሰርያ ምድር ተንሥቶ ሲፈለገው የነበረው በኋላም ተሳክቶለት ያገኘው ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ እጆቹ ከፍ አድርጎ ይዞት የነበረው ጽዋ ስለመሆኑ ቅንጣት ያክል ጥርጣሬ የለኝም። ገዳማውያኑ መንከሰትም ለመጠቆም የፈለጉት የዚህን ምሥጢር ማኅፍ ነው። እኔ ብቻ ሳልሆን እንጋፋው ፕሮፌሰር ዶ.ሲ.ድም በነበረን አጭር ቆይታ የምፈልገው ነገር ምን እንደሆነ ወዲያው ተረድተውት ነበር። "Take Care!" ካሉኝ በኋላ ከጀርመኑ ባለቅኔ ዎልፍራም ፓርዚቫል ጀምረው ጠፍቶ ቀርቷል ሰለሚባው ስለ ቅዱሱ ጽዋ ሰፊ "ማብራሪያ ሰጥተውኛል" አልኩኝና ድጋሚ የመጣልኝን ቡና መጠጣት ጀመርኩ።

ማ/ር እንድሪው በዝምታ ተውጠው ቆዩና፣

"ያችን ሀገር ካወቅሁበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ ምሥጢሮችን ደብቃ የያዘች ራሷም ለዓለም ምሥጢር የሆነች ሀገር እንደሆነች ይሰማኝ ነበር። እንደልቤ መውጣትና መውረድ የምችልበት እድሜዬ ላይ ብሆን ኖሮ አብሬ በፍለጋው ብሳተፍ ደስ ይለኝ ነበር" አሉና እጄን በእጃቸው በደንብ ጠበቅ አድርገው ይዘው

"በምንም ምክንያት ፍለጋህን እንዳታቋርጥ ቃል ግባልኝ" አሉ።

በአግራሞት ፈገግ አልኩና "የተቻለኝን አደርጋለሁ" አልኳቸው።

ወዲያው የአውሮፕላኑ ካፒቴን የሱዳንን የአየር ክልል ጨርሰን የኢትዮጵያ አየር ክልል ውስጥ በመግባታችን በአንድ ሰዓት ውስጥ አዲስ አበባ ቦሌ ዓለምአቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ እንደምንደርስ አበሰሩን። ካፒቴኑ መንገደኞችንም ሰላም መሆኑን የአዲስ አበባ የአየር ጠባይም ጥሩ መሆኑን ነግረው ሲሰናበቱን እኔም እርሳቸውን ተከትዬ የተጠራቀመ ድካሜን ተሸክሜ ወንበሬን አስተካክዬ ገደም ስል ወዲያው ሸለብ አደረገኝ።

# ምዕራፍ ዐሥር

ከአሜሪካ መልስ የምፈልገው ነገር ግልጽ ሆነልኝ። እጅግ የከበረ ነገር ለመፈለግና ለታላቅ በረከት እንደተጠራሁ አመንኩ። ምን እንደምፈለግ ሳላውቅ በጉጉት ስቃትት የነበረው አሁን ደግሞ ታላቅ ናፍቆትና የከበረ ቅርስ ፍለጋ ስሜት ውስጥ ገባሁ። ፍለጋዬ ከተራ ጉጉት ልቆ ታላቅ የሕይወት ጥሪዬ እንደሆን አድርጌ ተቀበልኩት። ይሁንና ለዚህ ፍለጋ የተገባሁ አለመሆኔን ሳስብ ኃፍረት የሚሰማኝ ቢሆንም ከእኔ ሕይወት ይልቅ የቅዱሱ ጽዋ የተሰፋ ብርሃን በለጠና እንዳች የሚያበረታ ኃይል ተሰማኝ። እናም ፍለጋዬን የምድር ዳርቻም ቢሆን ሳላቋርጥ በአባ አድሬል ስም ቃል ገባሁ።

ሆኖም "የት ብዬ ነው የምፈልገው?!" የሚለው ጥያቄ ገና አልተመለሰም ነበር። የምፈልገው ነገር መርፌ ቢሆን ከተደበቀበት የጭድ ክምር መሐል ለመፈለግ መጀመሪያ የጭዱ ክምር የት እንዳለ ማወቅ አለብኝ። የምፈልገውን ነገር ካወቅሁ የሚቀረው ቀላል ነው። ቢያንስ የእንቆቅልሹን ግማሽ መፍታት ይቻላል ብዬ ተስፋ አድርጌ ነበር። ነገር ግን ከየት እንደምጀምር እንኳን ፍንጭ የለኝም። ፍለጋውን በስህተት አቅልየ እንደተመለከትኩት በኋላ ገባኝ። በእጄ ያለው ነገር ቢኖር

"ውስተ ከርሠ እመ እጓል ሐቃላዊት ይሄሉ"

"በቆላኛዋ የልጅ እናት ሆድ ውስጥ ይኖራል"

የሚለውና መልእክቱ ገና በውል ያልተገለጸው ጽሑፋዊ ፍንጭ ብቻ ነበር።

ታዲያ "ቆለኛዋ የልጅ እናት ማንናት?" ብዬ ራሴን ከጠየቅሁ በኋላ የሆነ ነገር ትዝ አለኝ። ናዳ ማርያም በሄድኩበት ወቅት ገበሬው መንገድ እንዲያሳልፈኝ ኮድ መሳይ መልእክት የነገሩኝ መነኮሲት።

"---- ብለውሃል ቆለኛዋ እማሆይ" ያሉኝ ትዝ አለኝ። "እንዴ! ታዲያ እርሳቸው ሆድ ውስጥ እንዴት?" አልኩኝና ንግግሩ በምሳሌ የተነገረ እንጅ በቀጥታ የሚተረጎም አለመሆኑ እንደገና ታወቀኝ።

"ሂጂ ታዲያ ለምን አልጠይቃቸውም?" አልኩኝ። ሆኖም በሁለት ምክንያቶች ወደ ናዳ ማርያም መመለሰን ልቡናዬ አልቀበለው አለ። አንደኛ ነገር ቆለኛዋ እማሆይ አድራሻቸው ከገዳሙ ይሁን ወይም ከሌላ ቦታ የመጡ መናኝ ማረጋገጫ የለኝም። መልካቸውን እንኳን በአግባቡ አላየሁትም። "ቆለኛዋ እማሆይ" ተብሎ ደግሞ በምሥጢራዊው ገዳም ውስጥ መጠየቅና መፈለግ ሞኝነት መሆኑ ታወሰኝ። ሁለተኛ አባ መርሐ ጽድቅ "እርፍ ይዞ ወደ ኋላ የሚል የለም" ያሉኝ ደግሞ ትዝ አለኝ። አሁን ላይ ሆኜ ሳስበው ገዳማውያኑ የነገሩኝ ነገር አንድም መሬት ጠብ የማይልና በትክክል እንደተነገረኝ መፈጸም ብቻ ወደ ግቢ እንደሚያደርሰኝ አመንኩ።

በዚህ ሁኔታ የቆለኛዋን የልጅ እናት ፍንጭ እስካገኝ ድረስ ሌት ተቀን እያሰላሰልኩ ሥራዬን እየሠራሁ መቆዬት እንዳለብኝ አመንኩ። ይሁን እንጅ አእምሮዬ ሰላም እየራቀው፣ ውስጡ እየተረበሸ እንደሆነ ይገባኛል። እንቅልፌም ጨርሶ ጠፋ፣ ዝም ብሎ ከመገላበጥ በቀር ሰላም ራቀኝ። ባለቤቴም ሁኔታዬን እያየች፦

"ምን የሆንከው ነገር አለ?" ትለኛለች በተደጋጋሚ።

" ምንም!" እላታለሁ የግዴን ፈገግታ እያሳየሁ።

ቢሮ ውስጥ ወንበር ላይ ቁጭ እንዳልኩ በሀሳብና በትካዜ ጭልጥ ብዬ እንዛለሁ። አንዳንዴ ጸሐፊዬ ወረቀት አምጥታ ጠረጴዛ ላይ አስቀምጣልኝ ስትሄድ የማላስተውልበት ጊዜም ነበረ።

"ሰሞኑን ደኅና አይደለህም፣ በሀሳብ ጭልጥ ብለህ ትሔዳለህ፣

ምንድን ነው የሆንከው?" ትለኛለች።

"ምንም!" እላታለሁ።

"ለምን ዕረፍት አትወስድም?" ትለኛለች።

"እይ! አያስፈልገኝም ደኅና ነኝ" እላታለሁ።

እንደ እውነቱ ከሆነ የሥራ ፍላጐቴና ትዕግሥቴ ሁሉ ተሟጦ ነበር። ከሰው ጋር ቁጭ ብዬ፣ ከስብሰባ መካከል ሆኜ ፣ ለይስሙላ የሰማሁ ለመምሰል አንገቴን እነቀንቃለሁ እንጅ በሀሳብ አልኖርም ነበር።

አንድ በጣም የምወደው የቅርብ ጓደኛዬ ደግሞ አንድ ቀን ንፋስ እንቀበል ብለን ሀባይ ዳር ተቀምጠን እያለ ራሴን እያሻሸ "እዚህ ውስጥ ለብቻህ የምታጉላላው ሀሳብ ያለ ይመስለኛል! ለምን ተንፍሰኸው ወይም ጽፈኸው አትገላገልም" አለኝ። ሁሌም ከልብ በመነጨ ወዳጅነት ስለሚመክረኝ ሀሳቡን ተቀብዬ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የታሪክና የአንትሮፖሎጂ መምህር ወደ ሆነው ሊላኛው ወዳጄ ወደ ዶ/ር ከበበው ሄጄ የሚረዳኝ ነገር ካለ ብዬ ጉዳዩን በዝርዝር አስረዳሁት።

በጥሞና ካዳመጠኝ በኋላ፣

"ስማ ሲሳይ! እዚህ ሀገር ብዙ ምሥጢራዊ የሆኑ ቅርሶች እንዳሉ ይነገራል። እንዳቸውም ግን በግልጽ የሚታዩና የሚጨበጡ አይደሉም። ሳይንሳዊ በሆነ መልኩና ምክንያታዊ ሆኖ ለመረዳትም ሆነ ለማስረዳት በሩ ክፍት አይደለም። ‹ግዝት ነው ወይም ምሥጢር ነው› ተብለህ ትከለከላለህ። ምክንያቱም የሌለ ቅርስና ታሪክ ስለሆነ ነው። ስለዚህ ይህ ቅዱስ ጽዋም ወደ ኢትዮጵያ ሊመጣበት የሚችል የታሪክ አጋጣሚ ይኖራል ብዬ አላምንም። ከኖረም ሊኖር የሚችለው በጀስዊቶች ወይም በመስቀል ጦረኞች እጅ አውሮፓ ውስጥ የሆነ ምሥጢራዊ ቦታ ነው። ስለሆነም የሌለ ቅርስ ለመፈለግ እጅግ ቁልፍና ዝግ የሆኑ መነኵሳትን ልብ አስከፍታለሁ ብለህ ጊዜህን አታጥፋ" አለኝ።

የወዳጅ ምክር በአእምሮዬ ውስጥ ቦታ አግኝቶ ለመቀበልና ትዳዬን ለመርሳት ብሞክርም ልቡናዬ ግን አልፈቀደም። እናም "ቀለኛዋ የልጅ እናት ማን ናት?! እላለሁ ጠዋት ማታ። ሦስት የምጥ ወራት እየተንቀራፈፉ በግድ አለፉ።

አንድ ቀን ዐሥራ አንድ ሰዓት አካባቢ ከቢሮዬ ወጥቼ ወደ ቤቴ በጊዜ ገባሁ። ጭንቀቱም ስለረበሸኝ ሶፋ ላይ ጋደም ብዬ ቴሌቪዥን መከታተል ጀመርኩ። ሰዓቱ የአማራ ክልል ቴሌቪዥን ፕሮግራም የሚተላለፈበት ነበር ። የአማርኛ ባህላዊ ዘፈኖች ሲያቀርቡ ከቆዩ በኋላ የዜና እወጃ ሰዓት መድረሱን አስቀድመው ዜናውን ማንበብ ቀጠሉ። የዜና እወጃው ባይጠናቀቅም አዲስ ነገር ስላላገኘሁበት ትኩረት መስጠት ተሳነኝ ። ትንሽ ቆይቶ ግን አንድ ዜና ድንገት ደንግጥ አደረገኝ።

"በሰሜን ሸዋ ዞን በመንዝ ላሎ ማማ ምድር ወረዳ ማዳበሪያና ምርጥ ዘር በመጠቀማቸው ምርታቸው እንደጨመረ አርሶ አደሮች ገለፁ" የሚለው ዜና። ደንግጥ ያደረገኝ "መንዝ ላሎ ማማ ምድር" የሚለው ሐረግ ነበር። እናም ያ እየሰለቸሁት ከነበረው የዜና እወጃ ወጥቼ በሀሳቤ ወደ መንዝ ላሎ ማማ ምድር ከመቅጽበት ነጎድኩ።

የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርቴን ጨርሼ ከዩኒቨርሲቲ እንደወጣሁ ሥራ የጀመርኩት መንዝ ላሎ-ማማ ምድር ወረዳ ነበር። ሦስት ዓመት የተፍጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ባለሙያና ሐላፊ ሆኜ ሰርቻለሁ። እኔ ሥራ ስጀምር ሁለት ራሳቸውን የቻሉ ወረዳዎች ነበሩ። ላሎ ምድርና ማማ ምድር። መጀመሪያ ላሎ ምድር ሁለት ዓመት ሠራሁ። ከዚያም ሁለቱ ወረዳዎች ወደ አንድ ወረዳ ሲዋሐዱ ተጨማሪ አንድ ዓመት ሠርቻለሁ። የሕይወትን ምንነትና ውጣ ውረድ የተማርኩበት ስለሆነ ልዩ ትዝታ አለኝ። እናም ሁልጊዜ መንዝ ሲነሳ ሰውነቴ ስንጥቅ ይላል።

ያሳለፍኳቸውን ዓመታት ጓደኞቼን፣ ወዳጆቼን፣ ኑሮዬንና ጠቅላላ ሀገሩን እያስታወስኩ በሐዘንና በደስታ ትዝታ እናጥ ጀመር።

# ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

መንዝ ተብሎ የሚታወቀው ሀገር በወቅቱ በአራት ወረዳዎች የተከፈለ ነበር። ጊራ ምድር ዋና ከተማው መሃልሜዳ፣ ማማ ምድር ዋና ከተማው ሞላሌ፣ ላሎ ምድር ዋና ከተማው ወገሬ እና ቀያ ገብርኤል ዋና ከተማው ዘመሮ ነበሩ። መደበኛ አውቶብስ ከአዲስ አበባ ወይም ከደብረ ብርሃን ተነሥቶ በሞላሌ አድርጎ መሐልሜዳ የሚሄድ ቢኖርም መንገዱ አስቸጋሪ ስለሆነ አውቶብሶች ብዙ ጊዜ መስመራቸውን ይሰርዛሉ። ይህ ችግር ያስመረረው የመንዝ ሕዝብ ገንዘብ አዋጥቶ አንድ መለስተኛ አውቶብስ ገዝቶ ነበር። የአውቶብሷ ስም "የመንዝ ወርቅ" ትባል ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ መንዝ ከደብረ ብርሃን ተሳፍሬ የሄድኩት በየመንዝ ወርቅ አውቶብስ ነበር። በወቅቱ አዲስ ስለነበረች ደስ ትል ነበር። ከደብረ ብርሃን ተሳፍረን ሞላሌ እስክንደርስ ድረስ ሀገሩ በሙሉ በጉም ተሸፍኖ ስለነበር ሆዴ እየተሸበረ ነበር የሄድኩት። ሾፌሩ አንድ ባህላዊ ዘፈን ከፍቶ እርሷኑ ብቻ እየደጋገመ ያሰማን ነበር። ከዘፈኑ ዋና ግጥሞች ውስጥ፣

"ብወድህ ነው እንጅ የማንከሰው

እኔ እራሴን ችዬ ቁሜ እምሄድ ሰው" ይል ነበር።

አንዳንድ ተሳፋሪዎች በዘፈኑ በመሰላቸት "ለምን አይቀይርልንም?" ሲሉ አንዱ ቀልደኛ መንዜ

"አባካችሁ ተውት የሚያስነክስ ፍቅር ይዞት ይሆናል" ሲል እኔን ጨምሮ በሳቅ አጀብነው።

ከሞላሌ ከተማ ከአውቶብስ ወርጄ ከሁለት ቀን አዳር በኋላ ወደ ተመደብኩበት ላሎ ምድር ወረዳ ዋና ከተማ "ወገሬ" ስሄድ መደበኛ የሕዝብ ትራንስፖርት ስላልነበረ ሻንጣዬን በአህያ አስጭኜ በእግሬ እንደሄድኩ አስታውሳለሁ። ረትመት የተባለውን በገደል ውስጥ የሚያልፍ አስፈሪ ወንዝ ስሻገር ከዓለም ሁሉ ወደ ተገለለ ስፍራ ለግዞት የምሄድ መሰለኝ ልቤ በተስፋ መቁረጥ ተሰብሮ ነበር። ለነገሩ የቀድሞ ነገሥታት ተቀናቃኞቻቸውን በግዞት የሚያስቀምጡት በዚህ ወረዳ በሚገኝ አፍቀራ በተባለ ኮረብታማ ቀበሌ ነበር ሲሉ ሰምቻለሁ። ወገሬ እንደ ደረስኩ ጭራሽ ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር ገጠመኝ። ማረፊያ ሆቴል የለም፣ ምግብ ቤት የለም፣ በቃ! እዛ ቦታ አዲስ መጤ ሁነህ ገንዘብ ምንም አይፈይድልህም። በበጎነት የሚቸርህ መስተንግዶ እንጅ በገንዘብ የሚገዛ አገልግሎት ገና አልተለመደም ነበርና።

ቀደም ብሎ ተመድቦ የነበረ የግብርና ባለሙያ ተቀበለኝ። 80 ሳ.ሜ. ስፋት ባላት ታጣፊ አልጋ ላይ ለሁለት ተቃቅፈን ሳይሆን ተጣብቀን ተኛን። በበነጋታው ጓሳ ከተባለ ሳር ለችግኝ ጣቢያ ሠራተኞች ክፍያ በተላከ ሰንደ ጆንያ የራሴን ፍራሽ አሰፋሁ። የመጀመሪያዋ የግል ንብረቴ ማለት ነች። ከሳምንታት በኋላ ተጨማሪ ባለሙያዎች መጡና ጨዋታና ደስታ እየተፈጠረ መጣ።

መብራት የለ፣ ትራንስፖርት የለ፣ ሆቴል የለ፣ መዝናኛ ብሎ ነገር የለ፣ ብቻ ደስተኞች እንደነበርን ትዝ ይለኛል። እየተለማመድን ስንሔድ ደግሞ ድንበሬና መሳፍንት ደስታችንን እየጨመሩት ሔዱ። የግብርና ባለሙያዎች ናቸው። ማታ ራት ለመብላት የምንሰበሰበው ወደ ሁለት ሰዓት አካባቢ ነበር። ቤቱ ይጨልማል። ያው ያለው ኩራዝ በቂ ብርሃን አይሰጥም። ታዲያ ሁልጊዜ ማታ ማታ ያገኘነውን እራት በልተን ስናበቃ ድንበሬና መሳፍንት ያለምንም ዘፈን ወይም ሙዚቃ ተነሥተው እስክስታ መውረድ፣ ዳንኪራ መምታት ይጀምራሉ፤ በጨለማው ውስጥ።

"እላከሽ እናከሽ ... እላከሽ እናከሽ !"

"እንዴ! እናንተ ምን ሆናችኋል? አረቦቻችሁ አርፋችሁ ቁጭ በሉ!" ሲባሉ

"እንዴ! እኛ ታዲያ ስንጠግብ ምን እናደርጋ?!" ይላሉ። በቃ ሁልጊዜ ጥጋብ ነው በነሱ ቤት። እኛም በሳቅ ፍርስ እንላለን።

ሌላው የደስታ ምንጫችን ደግሞ ይታያል ነበር። ይታያል የትምህርት ጽሕፈት ቤት ባለሙያ ነበር። እንደ እርሱ ሥጋ የሚወድ ሰው አይቼ አላውቅም። ካለም ወይ የእንስሳ አልያም የሰው ዝርያ ያለበት መሆን አለበት። ከረቡዕና ከአርብ ውጭ ሁልጊዜ ከሥራ በፊት ጠዋትና ከሥራ ሰዓት በኋላ የሚታረድ ፍሪዳ ወይም አዙሬት የያዘው በግ መፈለግ ነበረበት። ቢያንስ በሳምንት ሦስት ቀን አዙሬት የያዘው በግ አያጣም ነበር።

መንዝ የበግ አገር ነው። ጠስኝ የሚባል ሳር መሰል ተክል ስለሚበሉ ሥጋቸው በጣም ይጣፍጣል። ታዲያ አዙሬት የሚባል የጭንቅላት በሽታ ያጠቃቸዋል። አዙሬት የያዘው በግ ቀጥ ብሎ መሄድ አይችልም፤ አንድ ቦታ ላይ እምቧለሌ (ክብ በሚመስል ሁኔታ) እየዞረ መዋል ነው። በዚህ በሽታ የተያዘ በግ ብዙ ጊዜ አይድንም። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በረሀብ ይሞታል። ስለዚህ ገበሬዎቹ ከመሞቱ በፊት ተሸቀዳድመው በርካሽ ይሸጧቸዋል። ይታያል ይሄኔ ተደራድሮ ዋጋ ጨርሶ በየቢሮው መጥቶ ይነግረናል። ብዙ ጊዜ ከ15 እስከ 20 ብር ይገዙቸዋል። በዚሁ መሠረት እኛም አንድ ብር ከሃምሳ እስከ ሁለት ብር ከሀምሳ እያንዳንዳችን መክፈል ይጠበቅብናል። ከሥራ መልስ በጉ ይታረዳል፤ በእርጄታ ዘይት ቀርቀሮ ተክትክቶ ሁለመናው ይቀቀላል። ሲበስል በትሪ ተገልብጦ ይበላል፤ አለቀ!።

የይታያል አስደሳችነት የሚጨምረው ግን ሥጋውን ከመብላታችን በፊት ስለ ሥጋው በሚያደርገው ተወዳጅ ስብከት ነበር። እንደ ይታያል ስብከት ከሆነ ከጤነኛው ሁሉ ይልቅ አዙሬት የያዘው በግ ሥጋው በጣም ጣፋጭ ነው። ሥጋም ደግሞ በጠቅላላው ለሰው ልጅ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ አዘውትሮ ይሰብካል። ከዚህ በኋላ ሥጋው ሲበላ ልዩ የሆነ አስቂኝ ጨዋታ ከየት እንደሚመጣ አይታወቅም። ብቻ እንባችን ጠብ እስኪል እንስቃለን። ተበልቶ እንዳለቀ እንደተለመደው ሁሉ የድንበሬና የመሳፍንት እስክስታ ይቀጥላል። በዚህ ጊዜ ሌሎችም ይጨምራሉ።

"እረ እባካችሁ ሰው እንረብሻለን?!" ሲባሉ "እንዴ! ታዲያ እኛ ስንጠግብ ምን እናድርግ?!" በማለት የተለመደ መልሳቸውን በአንድ ቃል ይሰጣሉ።

የአንደኛው ቀን ገጠመኞችን ግን ለየት ያለ ነበር። ይታያል በአካባቢው የፋሪዳ ሥጋ (ቅርጫ) መኖሩን ሰምቶ ኖሮ ሁለት መደብ ይዞ እንደተለመደው ከሥራ መልስ የሚደርስብንን አጥቀተን ሰብስብ ብለን ሥጋውን በጥሬው ለንበላ መሳፍንት ከመስክ ሥራው ተመልሶ ከተፍ አለ። ሲያይ ከብን እንደ አንበሳ ይዤን ጥሬ ሥጋ እሳቱን እናሳየዋለን።

"እንዴት ጥሬ ሥጋ ትበላላችሁ። አንትራክስ (ቁርባ) በስፋት ያለበት ሀገር ነው። እያንዳንዳችሁ ብትታመሙ መድኃኒት የምታገኙ መስሎሃል" ብሎ መብላት እንድናቆም ጮኸብን።

ይታያል ግን ለእንዲህ ያለ ሀሳብ በቀላሉ የሚንበረከክ አልነበረምና ፈጠን ብሎ "መምሬ ወርቁ ሥጋውን ሳመጣ ቁርባ የያዘው ከብት ሙሉ በሙሉ ሳያጸክመው ከታረደ ሥጋው እንዲያውም ለቁርባ መከላከያ ይሆናል ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ" አለና የሥጋ ጥብቅናውን ገለጸ።

መሳፍንት ከደብረ ዘይት እንስሳት ህክምና ኮሌጅ በዲፕሎማ የተመረቀ ረዳት የእንስሳት ሐኪም ስለነበረ ነው የተቆጣን። ማንም የሰማው ስለሌለ አኩርፎ ሂዶ በአሻንጉሬ ቁጭ አለ። እኛም እየተሳሳቅን መብላታችንን ቀጠልን። ትንሽ ቆይቶ እንዲህ አለ፦

"እያንዳንድሽ ተሰቃቅመሽ በአንትራክስ ፈንዳድተሽ መሞትሽ እንደማይቀር እወቂ። ታዲያ ሁልሽም ተሰቃቅመሽ ሙተሽ እኔ ብቻዬን ቀርቼ ምን እሠራለሁ" አለና ቢላዋውን ይዞ ቀረብ አለ ሊበላ። ሁላችንም በሳቅ ፍርስ አልን።

ብዙ ጊዜ ግብግቡን የሚያስተናብረው ደግሞ እስክቢያው የሚባለው ጓደኛችን ነበር። እስክቢያውን አሁን እዚህ አይተኸው ከሆነ ከመቼው ከዚያ እንደደረሰ አይታወቅም። የአንድ ኮንትራክተር ሳይት ፎርማን ሆኖ የወረዳውን መስተዳድር ጽ/ቤት ግንባታ

ለመቆጣጠር የመጣ የሚወደድ ከውካዋ ነበር። ታዲያ በተወዳጅነት ለመበላለጥ ሲሉ ከመሳፍንት ጋር የሚያደርጉት ብሽሽቅ ደግሞ ለእኛ ሲሳኛው የሳቅ ምንጭ ነበር።

አንድ ቀን ግን እንዲህ አለን፡

"ወደ አዲስ አበባ ሄጄ ትምህርት መቀጠል አለብኝ። ሲሆን ዲግሪ ካለዚያ ዲፕሎም መያዝ አለብኝ" አለን። እኛም ጥሩ ነው ተምረህ እራስክን ችለህ ኮንትራክተር ብትሆን ደስ ይለናል አልነው። የመሔዱ ነገር ቁርጥ ሲሆን እንደተለመደው አዙሪት የያዘው በግ ታርዶ፡ ተፈናፍሮ በመጨረሻም ተሳቅሰን ተለያየን። እስከዚያው ሆዬ ግን በሳምንቱ ተመልሶ ወገሬ ከች አለ።

በቃ ሳቅ ሆን። ለተበሻሸቂውና ተወዳዳሪው መሳፍንት ግን የእስከዚያው መመለስ ለብሽሽቅ ስለተመቸው ሁልጊዜ ይህችን እያነሣ ያበሳጨው ገባ።

መሳፍንት ብሽሽቁን አጉልቶ ሊያሰማ ሲፈልግ በልዩ ዜማው "ውይ" ይልና "እኛም አንተን ሰው ብለን በግ አርደን አልቅሰን መሸኘታችን።፡ተእንግዲህ አንተን ጥቁር ድመት አርድን ካልሸኘንህ በስተቀር ቀርጠህ ትሄዳለህ ማለት ዘበት ነው!" እያለ ያበግነው ነበር።

"ዱሮስ አዙሪት የያዘው በግ ታርዶ ሲሸኝ ዙሮ መምጣቱ ምን ያስገርማል?" ይልና አቶ ይታፈሩ እንኳ ሳይቀር በዚህ ላይ ይጨመርበታል።

ለነገሩ ሁልጊዜም የጨዋታው አጋጋይ አቶ ይታፈሩ ነበር። እድሜው በወቅቱ ከሃምሳ በላይ ነበር። እንደነገሩን ከሆነ በአብዮቱ ወቅት በኢህአፓ አባልነት ተጠርጥሮ ብዙ ተሰቃይቷል። ሕይወት ብዙ ያስተማረችው ሰው ስለሆነ ማግኘትንና ማጣትን፣ መክበርንና መዋረድን በደንብ ያውቀዋል። እናም ከእኛ ከታናናሾቹ ጋር ሲጫወት ለእኛም ልዩ ደስታ ይሰጠን ነበር። አቤት! ከእርሱ ጋር ማውራት እድርጎ ደስ ይለኝ የነበረው! በተለይ የጥንቱን እንሥቶ ሲያወራ አይጠገብም ነበር።

"የሀገራቱን የኢኮኖሚ መሠረትና ደረጃ፣ የሕዝቡንም ሃይማኖት፣ ባህልና፣ ሥነ ልቡና ሳናገናዝብ፣ ተግባራዊነቱን ገና ሳናየው፣ ከውጭ እንደ ወረደ በቀዳነው ርዕዮተ ዓለም ተጠምቀን፣ ለአፍታ እንኳን መደማመጥና መቻቻል ተስኖን የአንድ እናት ልጆች ገራፊና ተገራፊ፣ አጥፊና ጠፊ ሆነን ይህችን ሀገር እንደ ትውልድ ማሳጣታችን ሁሉ ይቆጨኛል። በጣት የሚቆጠሩና ከወፍራሙ ብዙም ከፍ ያላሉ ፋብሪካዎች በነበሩባት ሀገር፣ ሠራተኛ፣ ወዝ አደርና ላብ አደር የሚሉ ቃላቶችን የያዙ ቡድኖችን መሥርተን ወይም በእነርሱ አመካኝተን መጋደላችንን ሳስብ እስካሁን ድረስ በጣም አዝናለሁ" ይለን ነበር። የሚገርመው በጊዜው ከመደነቅ አልፈ አንድም ቀን የሚነግረንን አለመጻፌ ነው። ለንግሩ ስንበላና ስንጠጣ የተነገረ ነገር ከዚህ ውጭ ምን ሊጠቅመው ይችላል እሉና ሌላ ጊዜ ማስታወሻ መያዝ እንደነበረብኝ ኅሊናዬ ሲወቅሰኝ እንደገና እቆጫለሁ። እንዲያው እኛ ኢትዮጵያውያን ነገሮችን የመመዝገብና የመጻፍ ልምድ ለምን እንደሌለንም ይገርመኛል። ከአፍ ወደ ጆሮ፣ ከዚያም ወደ አፍ ነው፣ በቃ! ይኸው ነው የኛ ነገር።

ሌላው የመዝናኛችንና የደስታችን ምንጭ ደግሞ ሰርግና ድግስ ነበር። መንዝ አንድ ሰው ሰርግ ወይም ክርስትና ወይም የመሳሰሉት ጉዳይ ኖሮት ድግስ ሲደግስ ዘመዶቹናን ወዳጆቹን መጥራት አይጠበቅበትም። ይልቁንም ዘመድ ወይም ወዳጅ ነኝ የሚል ሰው ድግሱን ሰምቶ አውቆ ራሱን የግብዣው ታዳሚ ማድረግ ይጠበቅበታል። በዚህም ወዳጅነቱን ያረጋግጣል። ነገር ግን ለመስተንግዶው እንዲያግዝ ዘመድና ወዳጅ አህል ውሃ ይዞ ሊሄድ ይችላል ወይም ከመስተንግዶ በኋላ ሁሉም ሰው እንደ አቅሙና እንደቀረቤታው መጠን ገንዘብ ይደጉማል። ብዙ ጊዜ ሁለት ብርና ሦስት ብር ግፋ ቢል አምስት ብር ነው የሚሰጠው። እኛም የማኅበረሰቡ አካል ሆንናልና የምናውቃቸው ሰዎች ሲደግሱ እንታደም ነበር። ለደጋሾቹ የምንሰጠውን የገንዘብ መጠን የሚወስነው ደግሞ የወረዳው መስተዳድር ጽሕፈት ቤት ባልደረባ የነበረው መብራቱ የሚባለው ኮሚክ ጓደኛችን ነበር።

የድግሱን ጠላ ቀምሶ ካጣጣመ በኋላ በጣም ጥሩ ጠላ ከሆነ አራት ጣቱን ያሳየናል። የምንከፍለው ብር አራት ብር ነው ማለት ነው። ስለዚህ እንደጠላው ጣዕም ሦስትም ሁለትም እጣት ሊያሳየን ይችላል። የአንድ ቀኑ ድግስ ግን ጠላው በጣም ቀጠናና መብራቱ በጣም ተናዶ አንድ እጣቱን አሳየን። በድርጊቱ የተናደደው ሌላኛው ጓደኛችን ታዲያ፡

"አንተ እምብርትህ እስኪገለበጥ የስንዴ እንጀራ በልተህ አንድ ብር እንክፈል ስትል አታፍርም" አለው።

መብራቱም መልሶ፡

"በጠላ ላይ ያለኝ ፖሊሲ በምንም ምክንያት ለድርድር አይቀርብም" አለ።

ያው ጓደኛችን መልሶ "ይህን ቃለ ጉባኤ ስትይዝ የሸመደድከውን ንግግር ወዲያ ጣል" አለው። በሳቅ ፍርስ እንላለን።

አንዳንዴ ግን ከጨዋታ መለስ ብለን ቁም ነገርም እንመካከር ነበር። ነገር ግን ቁምነገሩ ሀሳብ ቢጤ ስለሚያስከትልብን ወደ ጨዋታው ማድላታችን የተለመደ ነበር። በተለይ የአንድ ጓደኛችን ጥያቄ ሁላችንንም አስደንግጦን ነበር። ከመካከላችን አንዱ በወቅቱ ከመንዝ ውጪ የምትኖር እጮኛ ነበረችው። ታዲያ የማግባት ሀሳብ ስለነበረው በየጊዜው አዙሪት ይዞት ለምናርደው በግ የሚጠየቀው መዋጮ አሳሰቦት ነው መሰል አንድ ቀን ለጥሎሽ፣ ለድግስ በአጠቃላይ ሰርግ ለማዘጋጀት ስንት ብር ያስፈልጋል? የሚል ጥያቄ ድንገት አቀረበ። ከመካከላችን ልምድ አለን፣ እናውቃለን ወይም ሰምተናል የሚሉት ሰርጉ ከፍለ ሀገር ከሆነ ቢያንስ ዐሥር ሺሕ ብር ይፈጃል አሉ። ሁላችንም በእውነት ደነገጥን፣ የማግባት ክብደቱም ደስታችን እቋርጦ ከፊታችን ተጋረጠብንና ተሰፋ አስቆረጠን። "ይህን ያክል የትየለሌ ብር ከየት ይመጣል?" ተባባልን። ሁሌም የሚያስከፋ ሀሳብ ሲመጣ በቀልድ መልክ ቀለል የሚያደርግልን አቶ ይታፈሩ

"ምን እስጨነቃችሁ ማግባት ስትፈለጉ ወደ ቀያ ገብርኤል ማቅናት ነው" እለና ፈገግ አሰኘን።

መንዝ ቀያ ገብርኤል ወረዳ ከዘመሮ ከተማ ወጣ ብሎ በዐመት አንድ ጊዜ ጳጉሜ ሦስት የቅዱስ ሩፋኤል ዕለት ብቻ የሚውል ገበያ አለ። ይህ ገበያ ለየት ያለ አስደናቂ ትዕይንት ይታይበታል። ልዩ ልዩ ሸቀጦችና የግብርና ውጤቶች የየራሳቸው ተራ ይዘው ሸያጭና ግዥ ከሚከናወንበት ውጪ አንድ ለላ አስገራሚ ተራ አለ። ወይዛዝርት አምረውና ተውበው እንደየችሎታቸው የሙያቸውን ልክና ደረጃ ያሳያል የሚሉትን እንዝርት፣ የጥጥ መንደፊያ ደጋን፣ መሶበ ወርቅ፣ ሰፌድ፣ ሙዳይ፣ ወይም ጥልፍ የመሳሰሉትን ይዘው መደዳውን ይቀመጣሉ። እነዚህ ወይዛዝርት ትዳር ፈላጊዎች ናቸው ማለት ነው። ትዳር ፈላጊ የሆነ ወንድ ደግሞ ዞር ዞር ብሎ ከታዘበ ካስተዋለ በኋላ ቀልቡ ያረፈባትን ጠጋ ብሎ ያነጋግራል። እርሷም ቀልቧ ከፈቀደው ሸማግሌ የለ፣ ጥሎሽ የለ ፣ ሰርግና ምላሽ ግርግር የለ ውሃ አጣጫቸውን በቀላሉ አገኙ ማለት ነው። በዚህ ገበያ ተገናኝተው ወልደው ከብደው የተሳካ ትዳር የመሠረቱትም ብዙዎች ናቸው። በዚያ ወግ አጥባቂ ተብሎ በሚገመትና በሚፈረጅ ኅብረተሰብ መካከል እንዲዚህ አይነት የሞራል ነጻነት መኖሩ ደግሞ በጣም ያስደምማል።

ሌላው አዲስና የደስታችን እካል የነበረው ደግሞ የማኅበረሰቡ የቁልምጫና የፍቅር አጠራር ነበር። መንዞች መውደዳቸውንና ማቅረባቸውን ከሚገልጹበት መንገድ አንዱ እድሜና የሥራ ማዕረግ ሳይለዩ ፆታን ቀይረው መጥራታቸው ነው። ወንዱን አንቺ ሴቷን ደግሞ አንተ ብለው ማለት ነው። ለምሳሌ እንዲህ ሊሉ ይችላሉ፡-

"መምህሬ ሰርጤ (ሰርፀ) በን አደርሽ፣ ይፍቱኝ ይባርኩኝ" ወይም ደግሞ

"እስናኸች ቤቴን እያየህ ውሃ ልኧዳ ሂጃለው" ወይም አባውራው የሚወዳትን የልጆቹን እናት እንዲህ ሊላት ይችላል፣

"የአጥላው እናት እስኪ እሚጠጣ ነገር ፈልግ" እርሷም መልሳ

"መጀመሪያ ትንሽ እህል ብትጎምሽ አይሻልም" ስትለው ከሰማሁ እገሩ መንዝ ንግግሩም የፍቅር መሆኑን ተረዳ። እገሩን እየለመድኩ፣ ከሕዝቡም ጋር እየተዋወኩ በሄድኩ ጊዜ "አንቺ" የሚለኝ ሰው እየበዛ መጣ። መጀመሪያ አካባቢ እየናቁኝ መሰሉኝ ይከፋኝ ነበር። እየገባኝ ሲመጣ ግን አንቺነቱን ወደድኩት። በጣም ብዙ ሰው በተለይ የገጠሩ አንቺ እያለ ይጠራኝ ነበር። "ጋሽ ሲሳይ፣ እባክሽ ችግኝ ማቢያ ዱይኝና ልሥራ" ይለኛል አንዱ። እኔም "በሚቀጥለው ወር እዶልሃለሁ" እለዋለሁ።

መቼም የማልረሳው ደግሞ አቶ አሸኔ ወልደሃና ነው። ላሎ ምድር 'ጣያት' የሚባል ቀበሌ የሚኖር አርሶ አደር ነው። እርሱ ለሚኖርበት ጎጥ የልማት አስተባባሪ ነበር። አንድ ቀን ሁለት ሆነን እርከን ለማሠራት ሄድን። ሥራው አብቅቶ ሕዝብ ከተበተነ በኋላ ወደ ቤት ካልሄድን ብሎ ግድ አለን። ተያይዘን ከቤት ስንደርስ ባለቤቱ በጣም ደነገጠች። ድንጋጤዋ እስከ አሁን ድረስ ከአእምሮዬ አልጠፋም። እርሱም ለምን እንደ ደነገጠች ስለገባው "አይዞህ ዝም ብለህ የማታውን አረኤ(ቄ) አእ(ቅ)ርብ መጣሁ" ብሏት እየተጣደፈ ወጣ። በወቅቱ ለሁለት ዓመታት የበልግ ዝናብ ጠፍቶ ስለነበረ በአካባቢው ከፍተኛ የምግብ እጥረት ተከስቶ የብዙ አርሶ አደሮች ቅስም ተሰብሮ ነበር። እና እዛ ቤት ለካ ምንም የሚበላ ዳቦም፣ እንጀራም፣ ጥሬም አልነበረም። ለዚህ ነው ሲትዮዋ የደነገጠች። ወዲያው አቶ አሸኔ የሸንብራ እሸት ከማሳው ነቅሎ ታቅፎ ገባና፤

"አይዞህ አትሳቭእ(ቀቅ)፤ ይህ ኧን ያልፋል። ግን እኒህን ወንድሞቻችን በጠራራ ጠሐይ ዝም ብለን ከምንሰዳቸው ቢያንስ አረፍ ብለው እሸት ጎምሰው ቢሄዱ ምን አለበት ብዬ ነው" አላት ለባለቤቱ በመንዝኛ። የርሱን የፍቅር ግብዣና ሰብአዊነት ሳየው የምዕራቡ ዓለም የራስ ወዳድነት ባህል እንደዛር የሰፈረብኝን እኔነቴን እሰቤ እራሴን ጠላሁት። እና በወቅቱ እንዲህ አልኩ "የሰማይ አምላክ ሆይ! እባክህ ይህ ቅዱስ ሕዝብ የሚወደውን መስጠትን እንደለበ ያከናውን ዘንድ የሰማይ መስኮትን ከፈትለትና ዝናብ ምሕረትን አውርድለት"። ሲላማ ምን አቅም አለኝ? ምንስ ላደርግ እችላለሁ።

የመንዝንማ ትዝታ ምን ተናግሮ ያልቃል? አሁን የኔታ ሰፈሩን እንደዉት ልረሳ እችላለሁ። የኔታ ላሎ ምድር ላይ ዘብር ቀበሌ በረትመት ወንዝ አረህ አፋፍ ላይ የሚገኘው የታላቁ የዘብር ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን አለቃና የአቋቋም መምህር ናቸው። የኔታ ዕፁብ አጭርና ደቃቃ ሰውነት ያላቸው በወቅቱ የሰማንያ ዐመት እባውንት ነበሩ ። ሊቅነታቸውንና አካላቸውን ለሚያወዳድር ሰው "የኔታ እኮ ጭንቅላትና ድምጽ እንጂ አካል የላቸውም" ያሰብላል። ቅኔ ማኅሌት ላይ ያን ሁሉ ተማሪ ግራና ቀኝ አሰልፈው በዝማሜ ሲመሰጡ ግን አካላቸው ይገዝፋል። የተማሩትን ቀለም ብዛት፣ በዘመናቸው ያስተዋሉትን የደረሰበትን የሕይወት ልምዳቸውን በንበረኝ ቅርበት ሳውቅ "በእኚህ እባውንት ሊቅና መናኝ አእምሮ ውስጥ ያለው እውቀትና ልምድ ቢጻፍ አንድ ቤተ መጻሕፍት ይወጣው ነበር" ማለቴም ትዝ ይለኛል። ከሰው የሰማሁት ይሁን ያነበብኩት አላስታውስም እንጂ በአፍሪካ ውስጥ አንድ እድሜ ጠገብ እባውንት ሲሞት አንድ ቤተ መጻሕፍት እንደተቃጠለ ይቆጠራል የሚል ነገርም አለ። የኔታ በወቅቱ ወደ ሦስት መቶ የሚደርሱ ተመሪዎች ነበሯቸው። ተማሪዎቹ ከፊደል ቆጠራ እስከ ማጠናቀቂያ የደረሱ አድራሾችን ያካትታል። በርካታዎቹ ተማሪዎች ቅኔና፣ ዜማ፣ አንዳንዶቹም የመጻሕፍት ትርጓሜ ሳይቀር ተምረው አጠናቅቀው አቋቋም ለመማር የሚመጡ ነበሩ። ያ ሁሉ ተማሪ ከበታቹ ያሉትን በዘርፉ እያስተማረ ከበላዩ ካለው እየተማረ ከንኑም ሌላ የትምህርት መስክ እየቀሰመ በስተመጨረሻ ወደ ሊቁ ወደ የኔታ ዕፁብ ይደርሳል። በዘመናዊው የትምህርት ሥርዓት አንጻር ለማስቀመጥ የየኔታ ትምህርት ቤት አንደኛ ደረጃም፣ ሁለተኛ ደረጃም፣ ዩኒቨርሲቲንም አጣምሮ የያዘ ነው። ለምሳሌ እርሳቸው የሚያስመርቁበት መስክ የሥነ ሙዚቃ (ዜማ) ቢሆን ይህን ለመማር ሌላ ቦታ ሂሳብ፣ ቋንቋ፣ የኅብረተሰብ ሳይንስ ተምረውና አጠናቅቀው ይመጣሉ። ስለዚህ የተማሩትን በነጻ እያስተማሩ እነርሱም በነጻ ይማራሉ ማለት ነው። በነ የኔታ የትምህርት ሥርዓት መሠረት ተማሪነትንና አስተማሪነትን በአንድ ላይ ትማራለህ። በዘመናዊው የትምህርት ሥርዓት ግን መምህራን ትምህራታቸውን ሊጨርሱ ትንሽ ሲቀራቸው ብቻ

ለልምምድ (Teaching Practice) ይወጣሉ። ይህ ፕሮግራም ዘግይቶ የሚመጣና አጭር በመሆኑ ደግሞ የመምህርነትን ሥነ ልቡናንና ፍቅርን ሙሉ በሙሉ የሚያጎናጽፍ አይመስለኝም። ምናልባት የሥነ ትምህርትና የሥነ ልቡና ባለሙያዎች ወደፊት ያጠኑት ይሆናል። ለማናቸውም የኔታ የቅርብ አጽናኜና አማካሪዬ ነበሩ። የኔታ ሥራ አዝዘው እንዳልተሠራ ካወቁ ለምን ብለው አይጠይቁም ነበር። አንድ ቀን ገርሞኝ ለምን እንደማይጠይቁ ስጠይቃቸው ፣ "የሰጠሁትን ሥራ ሳይሠራው ከቀረ በቂ ምክንያት እንዳዘጋጀ አውቃለሁ። ታዲያ የእርሱን ድርሰት ለምን እሰማለሁ? ወደፊት ሥራውን እንዴት ማሠራት እንዳለብኝ አስባለሁ እንጂ ለምንስ ጠይቄ የእርሱን ዲስኩር በመስማት ጊዜዬን አባክናለሁ" ብለውኝ ነበር። እስከ ዛሬ ድረስ ይህ ፍልስፍናቸው እኔም ላይ ተጽእኖ አሳድሮብኝ በግል ሕይወቴም ሆነ በሙያዬ ባለኝ ሃላፊነት ላልተሰራ ሥራ ለምን ብዬ አጥብቄ አልጠይቅም። "ወደፊት ለማሠራት አስባለሁ እንጂ" ብለዋልና የኔታ ዕውብ እያልኩ። ልቤ ሁሌም መንገደኛ ሆኖ እቃውን እንደቀረቀበ የሚኖር ስለነበር የኔታ "ዕውብን" ከመሰለ መምህር አንድ የትምህርት ዘርፍ እንኳን በነበረኝ ሰፊ ጊዜ ሳልማር መቅረቴን ሳስብ በሕይወት መንገድ ካጋጠሙኝ ወርቃማ እድሎች ውስጥ በእጅጉ ያባከንኩት መስሎ ይሰማኛል።

ቤት የተከራየሁባቸው ሰዎች አቶ አለምነውና ባለቤቱ ወ/ሮ አዲስ ዓለም ይባላሉ። መንግሥት ሠራተኛው እየበዛ ሲሄድ አንድ ምግብ ቤት ነገር ከፍተው ነበር። ከግቢው በአንድ አቅጣጫ ለሱቅና ለእርቢርን ተብለው ከተሠሩት አንዱን ክፍል በወር ሠላሳ ብር ተከራይቼ ነበር የምኖረው።

ኪራይ የምከፍል ተከራይ ብሆንም ከቅርርባችን የተነሳ እጠቃላይ የግቢው አባል ሆኜ ነበር። ወ/ሮ አዲስ ዓለም እጅግ ታታሪ ሴት ናት። አቶ አለምነው ደግሞ ጎበዝ ነጋዴ ቢሆንም ገንዘብ አባካኝ ነው። በተለይ መጠጥ ይወዳል። አንድ ቀን አምሽቶ መጣና ወደ አምስት ሰዓት አካባቢ የግቢውን በር አንኳኳ። ሁሉም ተኝተው ስለነበረ ተነሥቼ እርሱ መሆኑን ካረጋገጥኩ በኋላ ከፈትኩለት። የበሩን አንድ ጥግ ይዞ ቁሞ ቀረ።

"እንዴ! ግባ እንጂ፤ ምን ሆንክ?" አልኩት።

"ሂጂልኝና ልእልእ..ልግባ" አለ፤ እቶን ያዝ አድርጎታል።

"ግባና በሩን ዘግቼ ነው የምሄደው!" አልኩት ቆጣ ብዬ።

"ከዚህ ካልሄድሽ አልገገገገባም" አለኝ።

ፈገግ ብዬ የሄድኩ መስልኩና ጨለማው ውስጥ ቆምኩ። በሩን ሳይዘጋው እየተውተረተረ ወደ መኖሪያ ቤቱ ሄደ። በሳቅ ሞትኩ፤ በእርሱ ቤት መስከሩን እንዳላውቅና እንዳልቆጣው መጠንቀቁ ነበር። ሁልጊዜ ስለምመክረውና ስለምገሥፀው እንደታላቅ ወንድም ያከብረኝ ነበር። ሳስበው በገንዛ ቤቱ ላይ እኔ ተከራይ ሆኜ ማዘዜ፤ ያን ያክል መተሳሰባችንና እሱም እኔን መፍራቱ ይገርመኛል።

በቃ መንዝ ውስጥ የትም መወለድ ቋንቋ ነው። አብረህ ከኖርክ ቤተሰብ ትሆናለህ። ለነገሩ በሕዝብ አውቶብስ ውስጥ ስትጓዝ አብሮ የተቀመጠው ሰው ጨዋታ ይጀምርልሃል። ለምንና የት እንደሚሄድ ሳይደብቅ ያጫውትሃል። አንተም ትነግረዋለህ። ቆሎ፤ ሽንኩራ ተካፍለህ ትበላለህ። ስምህንና አድራሻህን እፈላልጐ የሌላ ጊዜ ደግንነትክንና ያኔ የሄድክበት ጉዳይ "እንዴት ሆነልህ?" ብሎ አስቦ ይጠይቅሃል። ሰው ነህና ከሰው መሐል መሆንህን ይነግርሃል።

በአንድ ወቅት ፈረንሳይ ሀገር ቦርዶ የምትባል ከተማ ለሥራ በሄድኩበት ወቅት በትውልድ ሊባኖሳዊ የሆነ አንድ ጥሩ ወዳጄ እንዲህ አለኝ፤

"It is not the humans who are bad here in west, it is the society!"

"በሰለጠነው በምዕራቡ ዓለም መጥፎው ግለሰቡ ሳይሆን ማኅበረሰቡ ነው ።"

"ራስ ወዳድና ብቸኛ እንድትሆን ያደርግሃል። እናም ለራስህ ብቻ ታስባለህ፣ ለራስህ ብቻ ትኖራለህ" ።

በእኔ እምነት ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ በተቃራኒው ማኅበረሰቡ ወይም መስተጋብራዊ ኑሮው ጥሩ ነው። በመሆኑም መንዝ የቆየሁባቸው ጊዜያት በብዙ ወዳጆችና ጓደኞች በመተሳሰብና በመፈቃቀር የተንሳ ቀላልና የደስታ ኑሮ ነበር።

ከሁለት ዓመት ቆይታ በኋላ ወረዳዎቹ ሲዋሐዱ ከወገሬ ወደ ሞላሌ ተዛወርን። ሞላሌ በሳምንት ሁለት ቀን መደበኛ አውቶብስ ከደብረ ብርሃን ይመጣላታል፤ እስከ ምሽቱ ሀራት ሰዓት ድረስ የጀኔሬተር መብራት አለ፣ በማዞሪያ የሚሠራ ስልክ አላት (ያኔ ሞባይል የሚባል ነበር የለም)፣ ሦስት አራት አሊቤርጎ፣ ምግብና መጠጥ ያላቸው ሆቴሎች አሏት። ከወገሬ ጋር ስትወደደር ትልቅ ከተማ ሆነችልን። ደመወዛችን በ127 ብር አካባቢ አደገልን፤ እጅግም ደስ አለንና "እድገት ማለት ይህ አይደለምን?!" አልን ።

መንዝ በቆየሁባቸው ዓመታት የከተማውና የገጠር ኑሮ ልዩነት ስላልነበረው ገጠር ለመውጣት እንስቀቅም ነበር። ስለሆነም ገጠሩን በደንብ የማወቅ እድል ገጥሞኛል። የሚገርመው እያንዳንዱን የተራራ፣ የወንዝ፣ የምንጭ፣ የደንና ልዩ ቦታ እንዲሁም የእያንዳንዱን ቀበሌ ስም በቃሌ አውቃቸው ነበር።

"እቤት! ከመንዝ ከወጣሁ በኋላ ስንቴ ቦታ/ሀገር ሄድኩ፤ ስንቱን አርከንና ዳገት ወጣሁት፤ ስንቱን ተዋወቅሁት!" አልኩ በመደመም።

"አሁን የቀበሌዎቹን ስም አስታውሳቸው ይሆን?" ብዬ ለራሴ ፈተና አቀረብኩ። እስኪ እየጠራሁ ልቁጠር አልኩና ከላሎ ምድር ጀመርኩ። ከደጋው ጀምሬ ወደ ቆላው ወረድኩ፡

"እንጀትላ፣ ሰቅላይ፣ ክለርቦ ----- እፍቀሬ በቀድሞው ዘመን ነገሥታቱ ተቃዋሚዎቻቸውን ወይም ተቀናቃኞቻቸውን በቁም እስር የሚያስቀምጡበት በገደል የተከበበ ቀበሌ ነው፡.....መረኸና ግንዳላ እና እንጀላና ሀገር መድፈያ ብዬ ሁሉንም ቀበሌዎች ጠራሁ። እስመርሳቱ ገርሞኝ እስኪ ደግሞ የማማ ምድርን ልቁጠር አልኩና አሁንም ከደጋው ወደ ቆላው ፡

"ደገም፣ ባሽ፣ እንጋዋ --- "እያልኩ አንድ ሰባት ቀበሌዎችን ጠርቼ ስምንተኛውን ቀበሌ ስም ስጠራ አእምሮዬ ውስጥ የትልቅ መረዋ ድምፅ የሚመስል የሚያባንን ጩኸት ተሰማኝ!

"እንዴ!" አልኩኝና ድንገት ተስፈንጥሬ ተነሳሁ።

" Yes! Yes!" አገኘሁት እያልኩ እቦርቅ ጀመር። እንደ ልጅ ነው ያደረገኝ። ከቤቴ ወጥቼ ግቢዬ ውስጥ እዘል ጀመር። በቃ ኳስ ተጫዋቾች ጎል ሲያስገቡ የሚሆኑት ነገር እለ አይደል? እንደዚያ ነበር የሆንኩት።

እንዴት ይሆን ያክል ጊዜ ስጨነቅና ሳስብ ሳይመጣልኝ ቀረ በማለት ተገረምኩ። "የሚያስጨንቀኝ እንቆቅልሽ ተፈታ፣ የተደበቀበትን ቦታ አገኘሁት፣ አወቅሁት!" አልኩኝ።

ተለጉሜ የሰነበትኩትን ያክል ማታ ፋሲካ ሆኖልኝ ፍስሐ ሆኜ አመሸሁ። ባለቤቴም፣

" ባሬ ምን ተገኘ?" አለችኝ ድንገተኛና ከመጠን ያለፈውን ደስታዬን አይታ፣

"ምንም!" አልኩኝ በፈገግታ።

"ለማንኛውም እንኳን ደብርትህ ለቀቀህ" አለችኝ።

እንቆቅልሹ ሲፈታ ከራት በኋላ ከተቀመጥኩበት ሶፋ ላይ እንዳለሁ የሰነበተው ድካም ተደማምሮ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወሰደኝ።

# ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት

ከቀዋቱ ሦስት ሰዓት ተኩል አካባቢ ደብረ ብርሃን ደረስን። ሾፌሩ ለቁርስ ሠላሳ ደቂቃ መስጠቱን ነገረን። ከተሳፈረው ዘግዬት ብዬ ወረድኩ። ከአዲስ አበባ ወደ መሐል ሜዳ በሚሄደው አውቶብስ ነበር የተሳፈርኩት። መሐል ሜዳ ከመድረሱ ሃምሳ ኪ/ሜ በፊት መንዝ ፣ የላሎ ማማ ምድር ወረዳ ዋና ከተማ ሞላሌ የጉዞ መዳረሻዬን አድርጌ ነው።

ወሩ ታኅሣሥ በመሆኑ የጠዋቱ ቅዝቃዜ አይጣል ነው። እንኳን ታኅሣሥ ሆኖ ደብረ ብርሃን ወትሮም ብርዳም ናት። ደብረ ብርሃን በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን የኢትዮጵያ ዋና መናገሻ የነበረች ዕድሜ ጠገብ ከተማ ብትሆንም ይህ ነው የሚባል እድገት ሳታሳይ እስከ ቆፈኗ ተኮራምታ የኖረች ከተማ ናት። ባለችኝ አጭር ጊዜ መሐል ከተማዋን ለመቃኘት ሞከርኩ። አሁን ሳያት ግን ከስሟ ብርሃንና ሙቀትን ወስዳ፣ ራሷን ከቆፈን አላቅቃ፣ ፊቷ ደመቅ እያለች መሆኑን ማንም ሰው በቀላሉ ይረዳል። ውብና ታላላቅ ሕንፃዎች፣ የአስፓልት መንገድ፣ የውስጥ ለውስጥ ኮብል ስቶን መንገድ፣ አልፎ አልፎ የተጀመሩ ፋብሪካዎችን ስመለከት፣

“ደብረ ብርሃን ሆይ! እንኳንም ድብርትሽና ቆፈንሽ ለቀቀሽ” አልኩ። ከተማ ሲለወጥ አገር ሲያድግ የልብ ተስፋ ነውና፣ ደስ ይላል።

የተሰጠን ሠዓት ስላለቀ እንደ ነገሩ ሻይና ብስኩት ቀማምሼ ወደ አውቶብሱ ተመለስኩ። ከአርባ ደቂቃ የደብረ ብርሃን ቆይታ በኋላ አውቶቡሱ ጉዞውን ወደ መንዝ ቀጠለ። ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ መንዝ ስጓዝ የነበረኝን ትውስታ እየቃኘሁ አሁን ያለውን የመልክአ

ምድራዊ ለውጥ፣ የከተሞችንና መንደሮችን እድገት እያንጸጸርኩ በዝምታ መንገዴን መረጥኩ። ያው እንደተለመደው የሀገራችን ሰው የሚተዋወቀውም የማይተዋወቀውም የሞቀ ጨዋታና ወሬ ይዟል።

ከደብረ ብርሃን አርባ ኪሎ ሜትር እንደተጓዝን አውቶብሱ የአዲስ አበባ ደሴ አስፋልት መንገድን ትቶ ወደ ቀኝ በመታጠፍ የጠጠር መንገድ ውስጥ ገባ። ይህ ቦታ ጣርማ በር ይባላል። ጣሊያኖች ደሴን ከአዲስ አበባ ጋር ለማገናኘት በተሰሩት መንገድ ማለፊያ፣ መሿለኪያ የሌለውን የጣርማ በር ሰንሰለታማና በሲታማ ተራራ ውስጡን ቦርቡረው ማለፊያ ቀዳ፣ የሰሩበት ቦታ ነው። በእውነቱ በዚያን ዘመን ያን መሥራት መቻል የወቅቱን የጣሊያኖች የምሕንድስና ጥበብ መጠንን በግልጽ ያሳያል። ሀገሪቱን ለመግዛት የነበራቸውንም ጉጉትና ቁርጠኝነትም ያመለክታል።

ወደ መንዝ የሚሄደው መንገድ በዋሻው አናት ባለው ቋጥኝ ላይ ከቀኝ ወደ ግራ ወይም ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ታጥፎ የተዘረጋ ነው። ከሰኔ እስከ ታኅሣሥ የጣርማ በር ሰንሰለታማ ተራሮችና ደጋማው መንዝ ሁሉም እንደ ግድግዳ የሚዳሰስ የሚመስል ጉም እንደለበሱ ነው። ለአዲስ መጪ ሰው ሆድ ያባባል። ከግራ ወደ ቀኝ ምንም የሚታይ ነገር የለም፣ ጉም የለበሰ ነጭ ሀገር!!!

አውቶብሳችን መብራት አብርቶ ፍጥነቱን እየተቆጣጠረ በመጓዝ ላይ ነው። በመንዝ መንገድ በፍጥነት መጓዝ በተለይ በዚህ ወቅት አደገኛ ነው። መንገዱ ጠመዝማዛ እና ጠባብ ሆኖ በተራራ አናትና ጥግ ላይ የሚያልፍ ሲሆን ከፊት ለፊት ያለው መንገድ በጉም ስለሚሸፈን ከሃምሳ ሜትር በላይ አይታይም። ስለሆነም ከፊት ለፊት የመጣ ተሽከርካሪም ሆነ እንስሳ ለአደጋ ሊያጋልጥ ይችላል።

አሁን ጉሙ እንደ መጀመሪያ ጉዞዬ ሆዴን አላባባውም። ይልቁንም ትዝታና ደስታ እንዲሁም ጉጉት ነበር የሚሰማኝ። መዘዞ፣ ቆብ አስጥል፣ ባሽ፣ መለያ የሚባሉ መንደሮችንና ከተሞችን አልፈን ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ተኩል ሞላሌ ከተማ ደረስን። በጀርባ የሚታዘሉና በእጅ የሚያዝ ቀለል ቀለል ያሉ ሁለት ሻንጣዎቼን ይዤ ሹፌሩንና ረዳቱን አመስግኜና ቀሪ መንገዳቸው ሰላም እንዲሆን ተመኝቼ ወደ ማውቀው ሆቴል ሄድኩ።

በዚህ ከተማ ከፉንና ደጉን አብረን ያሳለፍን ብዙ ወዳጆችና ጓደኞች ነበሩኝ። አሁን እነማን ይኑሩ፣ እነማን ከአካባቢው ለቅቀው ይሂዱ መረጃ የለኝም። የማግኘት ናፍቆት ቢኖርብኝም ለጊዜው ከመጣሁበት ዓላማዬ አንጻር ማንንም ማግኘት አልፈለኩም። ከዐሥራ ስምንት ዓመት በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ መንዝ ሲሄድ ያረፍኩበት ሆቴል ዘንድ ሂጄ አልጋ ጠየኩ። በፊት በ10 ብር የተከራየሁትን አልቤርጎ አሁን በ70 ብር ተከራየሁ። ሻንጣዬን አስቀምጬ የሚበላ ነገር አዝዤ እሱን እየቀማመስኩ ስለሚቀጥለው ተግባሬ ማሰብ ጀመርኩ።

የመጨረሻ መዳረሻዬ ከዚች ከተማ የሦስት ሰዓት የእግር ጉዞ ያስኬዳል። የቦታውን ስምና መሄጃ መንገዱን ከሞላ ጎደል አውቀዋለሁ። የዛሬን አይሁንና ብዙ ጊዜ ተመላልሼበታለሁ። እንዲህ እንዳሁኑ በከፍተኛ ጉጉት ሥራዬን ሁሉ እርግፍ አድርጌ በልዩ ዓላማ ባይሆንም ለመደበኛ ሥራዬም፣ ለመንፈሳዊ በረከትም አንድ ሁለት ሦስት ጊዜ ሂጄ ነበር።

የመጣሁበት ጉዳይ ምልከቶችንና ንግግሮችን በጥንቃቄ መመርመርና ማብሰልሰል የሚጠይቀኝ ነው ብዬ ስላሰብኩ ብቸኝነቱን መርጬዋለሁ። ስለሆነም ለጉዞዬና ለቆይታዬ የሚያስፈልጉኝን ነገሮች ለመግዛት ወደ ሱቅ ለመሄድ ስነሳ በተቻለ መጠን ሰዎች እንዳያውቁኝ ራሴን በኮፍያ፣ በካርፍና መነጽር ለመሸፈን ሞከርኩ። በዚህ ወቅት ማንም ወዳጄ ቢሆን ከሀሳቤ እንዲያናጥበኝ አልፈለኩም።

ከተማዋ ብዙ ተለውጣለች ባይባልም አንዳንድ ለውጦች ግን አሏት። ሌላው ቢቀር ሞባይል ስልክ ይሠራል። ወደ ሱቅ ሔጄ ባትሪ፣ ሻማ፣ ክብሪት፣ የተባይ ማጥፊያ ሞቢል፣ ስኳር፣ ሻይቅጠል፣ መኮረኒ፣ የታሸገ ዘይት፣ ዱቄት፣ ጨው ብቻ ለሁለት ሰው ለአንድ ሳምንት የሚያቆይ ምግብና አስፈላጊ ነገሮችን ገዛሁ። ምን ያክል ቀን ልቆይ እንደምችል ግምቱ የለኝም። ለማንኛውም ለጊዜው ይህን ከያዝኩ ወደፊት የሚሆነውን ሲደርስ አያለሁ አልኩኝ። ማረፊያ አይቸግረኝም። ምክንያቱም እማሆይ ዕሌተ ማርያም ይኖራሉ፣ የጥንቷ ወዳጄ!

ሞያሌ መሐል ከተማ ጫማ እየጠረጉ ከሚተዳደሩ ወጣቶች መካከል ጠንከር ያሉትን ሁለቱን መርጬው በበነጋታው በጠዋት ዕቃዬን ተሸክመውልኝ አብረውኝ እንዲሄዱ በክፍያ ተስማምተን ወደ ሆቴሌ ተመለስኩ። እንዳይነጋ የለም ነጋ። ውስጤ መረጋጋት አጥቶት ስቁነጠነጥ ወጣቶቹ ፊታቸውን እያሻሹ ከተነጋገርንበት ሠላሳ ደቂቃ አሳልፈው መጡ። ጓዜን ለሦስት ተከፋፍለን ከከተማዋ የደቡብ አቅጣጫን ይዘን ፊትና ኋላ ሆነን መጓዝ ጀመርን።

በጸጥታ እየተጓዝን እንዳለን አንደኛው ልጅ፡

"ጋሼ ምን ልታደርግ ነው የምትሄድ?" ሲል ጠየቀኝ።

በሆዴ "ምን ላደርግ እንደምሄድ እኔም አላውቀውም ልጄ!" እያልኩ ለእርሱ ግን

"ዘመድ አለኝ፣ ዘመድ ልጠይቅ ነው" አልኩትና ተጨማሪ ጥያቄ አለመፈለጌን ለማሳወቅ እንጉርጉር ወይም ዜማ ቢጤ ጀመር አደረግሁ። ከሞያሌ ከተነሳን ልክ ከሁለት ሰዓት በኋላ የመጣንበት ለጥ ያለ ሜዳማ መልክአ ምድር ጨርሰን መሬቱ ሙሉ ለሙሉ ተቆርጦ የሰጠመ የሚመስልበት ቆላማ አካባቢ ደረስን። አስተውሎ ለተመለከተው የጠረጴዛ ጫፍ ላይ የመድረስ ያክል ነው። ቆላማው መሬት ከደጋማው የመሬት ጫፍ ቢያንስ 200 ሜትር ዝቅታ አለው። ወደታች ቆላውን እያየሁ በተመስጦ ቆየሁ። ዐይኔ ላይ ብዥ አለብኝ። ለካ ዕንባ ዐይኖቼን ሞልቷቸው ነበር።

አንደኛው ልጅ "ጋሼ!" አለኝ"

ወዬ!" አልኩት፤

"እስከ አሁን የመጣንበት "እመኑ ደጋ" ይባላል፤ ከዚህ በታች ያለው ሀገር ደግሞ "እመኑ ቆላ" ይባላል" አለኝ በቀናነት።

" አዎን ልክ ነህ! አውቃለሁ" አልኩት በፈገግታ።

እጆቼን ወደ ላይ ዘርግቼና ጮኽ ብዬ፤

"እመኑ ቆላ!" አልኩኝ።

የአካባቢው ሽማግሌዎችና ሊቃውንት፣ "እመጓ" ማለት "እመ እጓል" ከሚለው የግእዝ ሐረግ አጥሮ የተገኘ ቃል ነው ይላሉ። ይህም "የልጅ እናት" ማለት ነው። በፊት መንዝ እያለሁ የማውቀው ነው። ታዲያ ደጋውን "እመጓ ደጋ" ቆላውን ደግሞ "እመጓ ቆላ" ይሉታል።

ይህንን ነው አባ አድራሉ፣

"ውስተ ክርሥ እመ እጓል ሐቃላዊት ይሄሉ"

በማለት በምሥጢር የጠቆመው።

" እመ እጓል ሐቃላዊት- እመጓ ቆላ- ቆለኛዋ የልጅ እናት "

ከደጋው ወደ ቆላው ለመውረድ ሁለት መንገድ አለው። አንደኛው ሰፊ በመሆኑ ሰውና እንስሳት እንደልብ የሚያስኬድ ቢሆንም ረጅም ጊዜ ይፈጃል። ሁለተኛው መንገድ አቋራጭ ሆኖ ነገር ግን እጅግ ጠባብ በሆነ የገደል ሠርጥ የሚወረድበት ነው። ረጅም ሰዓት ሲናውዞ ከመዋል በጥንቃቄ በገደሉ መውረድ ይሻላል አልኩና የገደሉን መውረጃ ተያያዝነው። ውሳኔዬ ስሕተት መሆኑን ያወቅሁት ከገደሉ መካከል ስደርስ ነው። ከዚህ በፊት በዚህ ገደል መውረዴ ትዝ ይለኛል። አሁን ግን ሰውነቴ ከብደትና ምቾት ስለጨመረ መሰለኝ በጣም ከበደኝና ፈራሁ።

ሰርጡን ለመውረድ በቁም መራመድ የማይታሰብ ነው። ግራና ቀኝ ቋጥ ያለው ገደል በስበት ሃይል ጎትቶ ሊወስድ ይችላል። ጀርባዬን ለገደሉ እየሰጠሁ ያገኘሁትን እየጨበጥሁ ነፍስና ሥጋዬ የተለያዩ እየመሰለኝ፣ በፍርሃት እየራድኩ አርባ አምስት ደቂቃ ያክል የእንኩትት (ተቀምጬ በመንፏቀቅ) እንደ ምንም ወረድኩ። ወጣቶቹ ብዙም አልተቸገሩም። እንዲውም እንደ መዝናኛ ቆጥረውት ይቀናጡ ጀመር። እነርሱን ሳይ በራሴ አፈርኩ።

ገደሉን ጨርሰን ረባዳው ላይ ስንደርስ እፎይ አልኩ። መልክአ ምድሩ ትንሽ በትንሽ ወደ ደልዳላነት እየተቀየረ መጣ። ከዚያም በሰሜንና ደቡብ አቅጣጫ ተራሮች የከለሉት በምዕራብና በምሥራቅ ደግሞ እንደገና ተገምሶ የወረደ መሬት የሚያዋስኑት ደልዳላ ሜዳ

/ፕላቶ/ የመሰለ መሬት ላይ ደረስን። ከተራሮቹ ጥግ መንደሮች ያሉ ሲሆን ከሜዳው መካከል ላይ ግን ጥንታዊው አመን ቆላ ቅዱስ ሁራኤል ቤተክርስቲያን በታላላቅና እድሜ ጠገብ የጽድ ዛፎች ተከቦ ጉብ ብሏል።

አገሩ በሙሉ ዝምታ የሰፈነበት ነው። አንዳች የሚያስፈራ ግርማ አለው። ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ገብቼ ተሳለምኩ። ለረጅም ጊዜ ከቤተክርስቲያኑ መግቢያ በር ላይ ተደፍቼ ቆየሁ። ተራራውን ከወረድኩ ጀምሮ የምረግጠው መሬት ሁሉ ያስፈራኝ ጀምሯል። የቤተ ክርስቲያኑ እቃ ቤት ከቤተክርስቲያኑ በስተደቡብ ይገኛል። በዚያ በኩል ሁለት ጎጆ ቤቶች አሉ። ወደዚያው አመራሁ።

አንዲት እናት በሰፌድ የመግበሪያ ስንዴ ይለቅማሉ። አንድ ሽምግል ያሉ ወንድ መነኩሴ ደግሞ ከወገባቸው በላይ ራቁታቸውን ሆነው ያረጀ ሱሪያቸው እንዲፍታታላቸው ጀርባቸውን ለፀሐዩ ሰጥተው አሮጌ ልብስ ይጠቅማሉ (በእጃቸው ይሰፋሉ) ።

ጠጋ ብዬ ትርርዬን ለመጠራረግ "እሁ.. እሆ" አልኩና "እንደምን አረፈዳችሁ?" አልኩኝ በትሕትና።

"እግዚአብሔር ይመስገን" አሉና ቀና ትኩር ብለው አዩኝ።

"እማሆይ ዕሴተ ማርያም ናቸው!"፣ አልኩኝ ለራሴ። ደስታ ተሰማኝ።

"ኃይለ ጊዮርጊስ! (የክርስትና ስሜ ነው)" ብለው ብድግ አሉና እጃቸውን ዘርግተው በእናትነት ፍቅር ወደ እኔ መጡ። የ1989 ዓ.ም. መልካቸው እንደ ፍዝ ሥዕል ሆኖ መጣልኝ።

# ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት

በ1989 ዓ.ም በወርኃ ግንቦት ዕለቱን በማላስታውሰው ቀን ከቢሮ የሥራ ሰዓት በኋላ ሁሌም እንደማደርገው ወደ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሄድኩ። ከቤተ ክርስቲያኑ ምሥራቅ በቤተልሔም አቅጣጫ ቆሜ ጸሎት ካደረስኩ በኋላ ወደ ቤቴ ለመሄድ ወደ ቅጽሩ በር ሳመራ አንድ በእድሜ ገፋ ያሉ ግርማ ሞገሳቸው ደስ የሚል መነኮሴ ከአራት ወጣት ሴቶች ጋር ከደጀ ሰላሙ ቁጭ ብለዋል። ወጣቶቹ የፊታቸውና የእጃቸው ቆዳ ልስላሴ፣ አለባበሳቸው ከትልቅ ከተማ የመጡ መሆናቸውን ያሳብቃል። ግራ የገባቸውና የተገረሙ ይመስላሉ። መንገዴን ገታ አድርጌ ወደ መነኮሴው አመራሁ፣ ካህን ስለነበሩ ተሳለምኩ።

"እንደምን ዋላችሁ? እንግዶች ትመስላላችሁ?" በማለትም ጥያቄ አስከተልኩ።

"እግዚአብሔር ይመስገን እንደምን ዋልክ ልጄ?" አሉና "አዎን! ከአዲስ አበባ ነው የመጣነው፣ አሉኝ።

"ምነው በደኅና?" አልኳቸው።

"አዎን ደኅና ነን። እዚህ ታች እመጓ ቆላ የቅዱስ ሁራኤልን ክብረ በዓል ልናከብር መጥተን ነው" አሉ።

"ወይ ጉድ! እኛ እዚሁ ተቀምጠን ከቁብ ሳንቆጥረው እናንተ ከአዲስ አበባ መጣችሁ!" ሰላቸው አባም ቀበል አድርገው፣

"የደጅ ጠበል የቆዳ መንከሪያ ነው ሲባል አልሰማህም" አሉኝ።

"ሆኖ ነው እንጂ!" አልኩና "ታዲያ ማረፊያ አግኝታችኋል?" ስል ጠየኳቸው።

"ልጆቼ አሊቢርጐ ይዘዋል። እኔ እንኳን እዚህ ደጃ ሰላሙ ቢሆን አድራለሁ። በጠዋት ወደ ቆላው እንወርዳለን" አሉኝ።

"እርስዎ ከእኔ ቤት ያድራሉ። ብቻዬን ነው የምኖረው። ለማንኛውም እንሂድ እራት ነገር ተማምሱ" ብዬ ሁል ጊዜ እንግዳ ወደምናስተናግድበት ምግብ ቤት ወሰድኳቸው። ጓደኞቼም መጡ። ከእራት በኋላ ወጣቶቹን አልቢርጐ ከያዙበት ሆቴል አድርሰን እኔና አባ ወደ እኔ ቤት ሄድን። ቤት እንደገባን መኝታቸውን አነጣጥፌላቸው ሲያበቃ፣

"አባ!" አልኳቸው፣ ልብሳቸውን ለመኝታ ሲያስተካክሉ፣

"ሁራኤል ቤተክርስቲያን እንደሆነ አዲስ አበባ አለ። እዚህ መንዝ እመን ቆላ ድረስ በዚህ ወቅት የመጣችሁ ቦታው የተለየ ታሪክ ይኖረው ይሆንን?" አልኳቸው።

"አለው እንጂ ልጄ! ታሪኩ እንዲሁ ተሸፋፍኖ ቀረ እንጂ ከእነግሸን ማርያም፣ ከእነጣና ቂርቆስ፣ ከእነአክሱም ጽዮን ያላነሰ ቃል ኪዳንና ታሪክ ያለው ቦታ እኮ ነው!" አሉኝ።

" እንዴት ያለ ታሪክ? " አልኳቸው ።

መቼም መመዝገብ አላውቅም እንጂ ታሪክ ሲነገር መስማት ነፍሴን ያስደስታታል። ስለማልጽፈው ግን ብዙ ጊዜ እረሳዋለሁ። አለመጻፍ ትልቅ በሽታ!

"አየህ አባቶቻችን እንደነገሩንና በድርሳነ ሁራኤልም እንደተጻፈው ጌታችንና መድኃኒታችን በዕለተ ዐርብ በመስቀል በተሰቀለ ጊዜ ከሰውነቱ የፈሰሰውን ደም በብርሃን ጽዋ መልአኩ ሁራኤል ተቀበለው። ደሙንም በመላው ዓለም ረጨው። የደሙ ንጣቢ ያረፈበት ቦታ ሁሉ የቤተክርስቲያን ሕንፃ ማረፊያ፣ የቅዱስ ቁርባን መፈፀሚያ እንዲሆን ታላቅ ቃል ኪዳን ለዓለም ተሰጠ።

እነሆ ዛሬ ሰዎች ተመካክረውና ፈቅደው በአካባቢያቸው ቤተክርስቲያን ቢያንፁም የሚሠሩበት ቦታ የክቡር ደሙ ንጣቢ ያረፈበት ቀድሞ በመንፈስ ቅዱስ የተለየ ቦታ ነው። የመድኃኔዓለም ምሥጢሩ ቸርነቱ ብዙ ነው ልጄ !" አሉ።

"ይደንቃል እንጅ!" አልኩና "ታዲያ እመጓ ቆላ ምን የተለየ ነገር አለ?" አልኳቸው።

"እንዳልኩህ መልአኩ ቅዱስ ዑራኤል ክቡር ደሙን በዐራቱም ማዕዘናት ከረጨ በኋላ ጽዋውን በመድኃኔዓለም ፈቃድ በቅድስት አገር ኢትዮጵያ መንዝ ውስጥ እመጓ ቆላ አምጥቶ ቀበረው። እንዲያውም እኮ ይህ ሀገር መንዝ የተባለው ለዚህ ነው"።

"እንዴት" አልኩ

"መንዝ ማለት ንዝሃ ከሚለው ግእዝ ቃል የተገኘ ነው። ይኸውም መርጨት ማለት ነው። የክርስትቶስ ደሙ የተረጨበት ጽዋ ማረፊያ ስለሆነ" አሉ።

"ወይ ግሩም" አልኩኝ።

"እና ልጄ  መንዝ እመጓ ቆላ ክቡርና ቅዱስ ቦታ ነው። አንተም ከበረከቱ በየጊዜው እየሄድክ ተካፈል!" አሉኝ።

"ይህን ታሪክ እንዴት መንዝ እየኖርኩ ሰምቼው አላውቅም?" ስል በመደነቅ

"ታሪኩ እንኳ በጥንታዊው ድርሳነ ዑራኤል ላይ ተጽፏል። በየጊዜው መጻሕፍቱ እየተቆነጸጸሉ ነገሩ ልብ ወለድ ታሪክ የመሰላቸው ደግሞ ከዛሬው ድርሳነ ዑራኤል ቀንሰው አጥፍተውታል ይባላል" አሉኝ።

"ድፍረት ባይሆንብኝ እርስዎ ከየት ነው የመጡት?" አልኳቸው። ለምን እንደሆነ እንጃ ከአዲስ አበባ ወይ ከትልቅ ከተማ ለሚኖር መነኩሴ ወይም ባህታዊ ብዙም ልቡናዬን አልሰጥም።

"እኔ እንኳን ደብረ ሊባኖስ ነው ያለሁት። ሠላሳ ዓመት በዚያው ገዳም ኖሬያለሁ። የመጽሐፍ መምህር ነኝ። ሁልጊዜ እዚህ ቦታ ቤተሰብ ጊዜም ይሁን ባልታሰበ ጊዜ ድንገት እመጣለሁ። እና አዲስ አበባ መጥቼ ከአንድ ክርስቲያን ቤት አረፍኩ። ወደዚህ እንደምመጣ ስናገር አብረውኝ ከመጡት እንደኛዋ ልጅ ያረፍኩባቸው ሰዎች ልጅ ናትና ታዲያ በበኩሏታው ጓደኞቿን ሰብስባ እኛም ከእርስዎ ጋር አብረን እንሄዳለን አለ። የኮሌጅ ተማሪዎች ናቸው።

እኔም ምንቸገረኝ ምናልባት የእግሩ መንገድ ከባድ እንዳይሆንባችሁ እንጂ አልኳቸው። ይሁን ግድየለም ብለው ያው አብረን መጣን አሉኝ።

የገዳም አባት ያውም ሊቅ መሆናቸውን ሳውቅ ልቤ ተከፈተ፡ እናም ታሪኩ እውነት እንደሚሆን ገመትኩ። እውነት ለመናገር ብዙም ለመመርመር ግን ፍላጎቱ አልነበረኝምና ገም ብሎ በልቤ ውስጥ የተቀበረ እውቀት ሆኖ ቀረና [illegible] ፈጽሞ እስከመርሳት ደረስኩ። በማግሥቱ ጠዋት መንገድ [illegible] እንደ መጣን ሰዎቹ ተሰናብበተን ተለያየን።

ይህ ከሆነ በግምት ከሁለት ሳምንት በኋላ አንድ የገጠር ሰው አንድ ደብዳቤ ከቢሮዬ አምጥቶ ሰጠኝ። የተጣለፈ [illegible] ደብዳቤ ነው።

*በመድኃኔዓለም ወንድሜ ለሆንከው ለአቶ ቢሳይ እንደምን ሰነበትክ? እኔ የአባቶቻችን አምላክ መድኃኔዓለም ይክበር ይመስገን ደኅና ነኝ። ልትረሳኝ ትችላለህ። ባለፈው ከአንድ አባት ጋር ከአዲስ አበባ ከመጡት ወጣቶች አንዷ ነኝ። ወደ አዲስ አበባ አልተመለስኩም። እዚሁ ለመኖር ወስኛለሁ እና እባክህ ትንሽ ወረቀትና ቀይ ቀለም እና ጥቁር ቀለም ያለው እስኪብሪቶ ለሚመጣ ሰው ላክልኝ ። እግዚአብሔር ዋጋህን ይከፍልሃል።*

*በመድኃኔዓለም እህትህ ሥርጉት ተሰፋዬ*

"የክርስቶስ ያለህ" አልኩኝ

በጣም ደነገጥኩ። ቆዳዋ የለሰለሰ ምግብ እንኳን ወርዶ የምታውቅ የማትመስል መሐል አዲስ አበባ ያደገች ወጣት ምንም በማታውቀው ኅብረተሰብ መካከል ተፈጥሮ ከነሰም የለየችው በሚመስል ቆላማ ቦታ ድንገት ስትመጣን በጣም ያስደነግጣል። አባ እንደ ነገሩኝ አመጣጣቸው ግብታዊ ነበር። ስለዚህ ግብታዊ ውሳኔ እንደወሰኑት ተሰማኝና ወደ ቤተሰቦቿ መመለስ እንዳለብኝ የሞራል ኃላፊነት አደረብኝ። መልእክቱን ያመጣልኝን ሰው ተመልሶ ይሄድ እንደሆነ ስጠይቀው ለዚሁ ጉዳይ እንደመጣና እባው እንደሚኖር ነገረኝ። ወደ ከተማ ሄጄ የጠየቀችውን ነገሮችና ሌሎች ምግብ ነክ ሸቀጦችን ገዝቼ ከደብዳቤ ጋር ለሰውየው አስይዤ ላኩኝ። ደብዳቤው አጭር ነበር።

"በሚቀጥለው ቅዳሜ እመጣለሁ" የሚል ነው።

በሚቀጥለው ቅዳሜ አራት ጓደኞቼን ይዤ በጠዋት አመን ቆላ ወረድን። በመንገድ በምናየውም ሆነ አባ ከደረስን በኋላ አካባቢው እንዳች ምሥጢር ያለው መሆኑን መገመት ይቻላል። ዝም ብሎ የሚከብድ ነገር አለው። ይሁን እንጂ በወቅቱ ትኩረቴ መንፈሳዊ ተጋድሎ ምን እደሚጠይቅ በወጉ ያልተረዳች ናት ብዩ ያሰብኳትን ያችን ወጣት ወደ ቤተሰቦቿ መመለስ ላይ ስለነበረ ስለአካባቢውም ሆነ አባ ስለነገሩኝ ታሪክ ትኩረት አልሰጠሁትም ነበር። አሁን ላይ ሆኜ ሳስበው ብቻ "ተጋርዶብኝ" ነበር።

አመን ቆላ ከቤተክርስቲያኑ ስንደርስ ቅዳሴ አልቆ ስርሆተ ሕዝብ ሲደረግ ደረስን። ተሳልመን ስናበቃ በዐይኔ መቃኘት ጀመርኩ። ሥርጉትን ከአካባቢው ሴት ምእመናን ጋር ተመሳስላ ቁጭ ብላለች። እኛም ከአንድ ጥግ ቁጭ አልን። ሰው ወደየቤቱ እየሄደ ነው። ሴቶች እየመጡ ለሥርጉት የሆነ ነገር እየሰጧት ይሄዳሉ። በኋላ ሳረጋግጥ ጥቂት ቂጣም እህል ነበር የሚሰጧት። አንጀቴ ስፍ ስፍ አለ። በእርሷ ውሳኔ፣ በሕዝቡ ደግነት፣ ብቻ፣ አልቅስ አልቅስ አለኝ።

ሰላምታ ከተሰጣጣን በኋላ ከቤተክርስቲያን በደቡብ አቅጣጫ ወደ አለች ትንሽ ጎጆ እየመራችን ሄድን። ውስጧ በደንብ በጭቃ ተለስናል። ጥሩ የገጠር ቤት ይመስላል።

በአንድ ጥግ ትልቅ መደብ ከዚያም የእህል ማስቀመጫ ጉስጓሻ (ከጭቃ የተሰራ በርሜል መሰል የዱቄት ማስቀመጫ)፣ የምግብ ማቅረቢያ ጥሬር፣ እርጌ ብረት ድስት፣ ዙሪያውን ጫፎቹ የተቆረማመመ ብረት ምጣድ፣ ጭልፋ፣ የሻይ ማፍያ እርጌ በራድ፣ የወየበ የፕላስቲክ ኩባያና ሳህን፣ ኩራዝ፣ አለቀ የቤቱ እቃ።

"እንዴት ነሽ?" አልኳት በምርመራ ዐይንት

"መድኃኔዓለም ይከበር ይመስገን በጣም ደኅና ነኝ!" አለች በሙሉ ፈገግታ።

ከሞላሌ ያመጣነውን ሳህን ከፍተን እንድንበላ ጠየቅናት።

"እናንተ ብሉ። ይልቅ ሻይ ላፍላላችሁ" ብላ ጉድ ጉድ ማለት ጀመረች።

እኛ የላመ የጣመውን እየበላን እርሷ ሲቶች የሰጧትን የሰንዴ እንጀራ ደረቁን ለቁመተ ሥጋ ያክል ብጥስ ብጥስ ታደርግ ጀመር።

በልተን እንደጨረስን ወደ ዋናው ጉዳይ መግባት ፈለግሁ። እትዱ ከሰዓት በኋላ ወይም በነገው ከቅዳሴ በኋላ እርሷን ይዘን ወደ ሞላሌ መመለስና ወደ አዲስ አበባ አሳፍረን መላክ ነበር።

"ይኸውልሽ ሥርጉት እዚህ መቅረትሽ ትክክል አይደለም። ቦታው የተቀደሰ እንደሆነ ሁላችንም ተረድተናል። ግን ለመመንኩስም ሆነ ለመመነን እንቺ ገና ልጅ ነሽ። ሁኔታሽ ግብታዊ ነው እና ዛሬ ወይም ነገ ከዚህ ወጥተሽ ከእኛ ጋር መሄድ አለብሽ። ከዚያም ወደ አዲስ አበባ አሳፍረን እንልክሻለን። ወደፊት ከፈለግሽ በየጎመቱ መምጣት ትችያለሽ። አሁን ግን የኮሌጅ ትምህርትሽን መጨረስ አለብሽ" አልኩ።

ጓደኞቼም ተረባረቡ። ዝም ብላ በፈገግታ ተውጣ ታዳምጠን ነበር፤ ሥርጉት ተሰፋፉ።

"ጨረሳችሁ? አለችን።

" እምንቦ፤ እልኩኝ ጓደኞቼንም ወክዬ።

"እንደ ታናሽ እህታችሁ ተጨንቃችሁ እዚህ ድረስ መጥታችሁ ስለሰጣችሁኝ ምክር መድኃኔዓለም ዋጋችሁን ይከፈላችሁ። እንዳላችሁት ምንም መንፈሳዊ እውቀት የሌለኝ ደካማ እንደሆንኩኝ አውቃለሁ። እዚህ ለመቅረት የወሰንኩት ለምንና ወይም ለምንዝሮስና አይደለም። ከዚህ ደግ ሕዝብ መሐል እየኖሩ መመንን የለምና። እኔ አሁን ብዙ ወዳጆች አሉኝ። አለያችኋቸውም ቢት? ለመመንኩሰም አልተዘጋጀሁም። ታዲያ ከዚህ ለምን ቀረሽ? ካላችሁ በታ ቀሪ ዘመኔን የምኖረው እዚህ ነው። ስለትምህርቱ መቋረጥ አትጨነቁ። ትምህርት የዓላማ መሳፈጸሚያ ነው እንጂ በራሱ ግብ አይደለምና የተማርኩት በቂዬ ነው። ከተማርኩት በላይ ያለውን አልፈልገውም። ለታላቁ ቃል ኪዳን የተገባሁ ባልሆንም የተመረጡትን እያገለገልኩ ለመኖር ወስኛለሁ። ጥልቅ ከሆነው ሰላሜ ለማውጣት አትድከሙ" ብላ እቅፌኔን ነገረችን።

ከጓደኞቼ መካከል አንዳንዶች እያለቀሱ ጭምር ብንመክርም፣ ብናስፈራራም የሚለወጥ ነገር እንደሌለ ተረዳን። እዚያው አድረን በማግስቱ ከቅዳሴ በኋላ የቤተክርስቲያኑን ዋና ዋና ቀሳውስት እና የአገር ሽማግሌዎችን ስለ ሥርጉት አመጣጥ፣ የእግዚአብሔር ጥሪ ስለመሆኑ እዛው መኖር ስለመወሰኗ ነግረን በተቻላቸው ሁሉ ፍቅር እንዲሰጧት ለመንናቸው። እነርሱም በአንድ ቃል

"የአምላካችን ጥሪ የሚቃወም ማነው? ይህች ልጅ ዛሬ ልጃችን ናት፣ ነገ በጸሎት የምታስበን እናታችን ትሆናለች። እስከፈቀደችው ጊዜ ብትኖር አትከብደንም። ሀገራችን ታላቅ የቃል ኪዳን ምድር እንደሆነ እናውቃለን። ገና ብዙዎች ይመጣሉ እያሉ ብዙ አባቶች ከቀድሞ ጀምሮ ይናገሩን የነበረው ትንቢት እየደረሰ ይመስላል፤ ስለዚህ አታስቡ !" አሉን።

በመጨረሻ ዕንባ በሁላችንም ዐይን እያቀረረ ሥርጉትን ተሰናብተን ወደ ዲጋው ወጣን፤ ወደ ከተማችን ወደ ሞላሌ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መንዝ በቆየሁባቸው ጊዜያት ሁሉ አልፎ አልፎ

የምንጠያየቅ የነበረ ቢሆንም መንዝን ከለቀቅሁ ከሀሥር ዓመት በኋላ ወጣቷና ከተሜዋ ሥርጉት ተሰፋዬ መንዝኖን እማዝዮይ ሰሴተ ማርያም ተብላ እዛው እመን ቆላ ጸንታ እንደቀረች ሰማሁ። ከሀሥራ ስምንት ዓመታት በኋላ እንደገና ወደ አካባቢው ስመለስ በአካል ያገኘኋቸውና በታላቅ ናፍቆት በአናትነት ፍቅር ስመው የተቀበሉኝ የእመን ቆላ ቅዱስ ሁራኤል አገልጋይ እማዝዮይ ሰሴተ ማርያም፣ ያን ጊዜ ወደ ቤቷ ልመልሳት ብዙ የለመንኳት የዛ ጊዜዋ ሥርጉት ተሰፋዬ ናቸው።

"አቤት! እንዴው እንዴት ነህ!" እያሉ ስለ ራሴ ስለ ቤተሰቤ ብዙ ሲጠይቁኝ ቆይተው፣

"እዚህ አገር ከሄድክ ስንት ጊዜ ሆነህ?" አሉኝ፣ ትንሽ እንደማሰብ አልኩና

"ዐሥራ ስምንት ዓመት ሆነ መሰለኝ እማዝዮይ" አልኳቸው።

" አቤት የዚህ ዓለም ነገር! አቤት የጊዜው መሮጥ...." አሉ በመደነቅ።

በእውነቱ እኔም በጣም ገረመኝ። መንዝን ከለቀቅሁ ዐሥራ ስምንት ዓመት መሆኑን ሳስብ እድሜዬ እንዴት እየሮጠ እንደሆነ ተገለጸልኝና፣

"አዲያ ! እንዲያው ዝም ብሎ መባከን፣ ምንም ሳይሞላ!" አልኳቸው።

"እስቲ ወደ ቤት ግባና ጓዝክን አኑረው። ምንድን ነው ይሀ ሁሉ ኮተት?" አሉ።

"እንዲያው አንዳንድ ነገር ነው" አልኳቸው።

"ለማንኛውም መጀመሪያ ድካሙ እንዲለቅህ እግርህን ታጠብ። ውሃ ሳሙቅልህ" ብለው እሳት ሊያያይዙ ወደ ምድጃው ሄዱ። ከሞላሌ አብረውኝ የመጡትን ወጣቶች እማዝዮይ እንዲቆዩ ቢጠይቋቸው እንቢ ስላሉ ለመንገዳቸው የሚሆን ዳቦ ሰጥተዋቸው እኔ ደግሞ ሂሳባቸውን ከፍዬና አመስግኜ ሸኘዋቸውና ከእማዝዮይ ጋር ወጋችንን ቀጠልን።

እማሆይ ውብዋ ሰውነታቸው በመንፈሳዊ ተጋድሎ በመጕሳቆሉ ትንሽ ጠቆር ያሉ ቢመስሉም ፈገግ ሲሉ ግን ሙሉ የደስታ ብርሃን ፊታቸው ላይ ይታያል። ውሳጣቸው በሰላምና በደስታ በእርጋታ የተሞላ ስለመሆኑ ነጋሪ አያሻም።

"እማሆይ!" አልኳቸው የሞቀውን ውሃ አቅርበው ካለጠብኩህ ብለው ስንከራከር ቆይተን እኔ አሸንፌ ውሃውን እግሬ ላይ እያፈሰስኩ።

"አቤት! ኃይለጊዮርጊስ" አሉኝ፤

"እንዲያው ይህን ያህል ዘመን ማን እየረዳዎት ኖሩ?" አልኳቸው።

"አይ ኃይለ ጊዮርጊስ! መድኃኔዓለምን ያመነ ምን ይቸግረው ብለህ፣ ሳለ ቅዱስ ዑራኤል!" አሉኝና በምስጋና ቃና ክትል አድርገው፦ "የአካባቢው ገበሬዎች ሁልጊዜ መኸር ሲሰበሰቡ ትንሽ ትንሽ እህል ይሰጡኛል። ዓቃቤት በመሆኔ ሰበካ ጉባኤው በወር ትንሽ ትንሽ ደመወዝ ይደጉሙኛል። ከዚያ በተረፈ አሁን አሁን ምእመናን በርከት ብለው ከአዲስ አበባ በዓመት አንዴ ስለሚመጡ የሚቸግረኝን ያሟሉልኛል። እንዲያውም ከእኔ አልፎ በአካባቢው ጧሪ የሌላቸውን አረጋውያን እረዳለሁ። ምንም ችግር የለብኝም" አሉኝ።

አቤት! ከፊታቸው ላይ የሚታየው የደስታ ስሜት፣ እምነታቸውና ደስታቸው ያስደንቃል።

በሥራ ስምንት ዓመት ሙሉ እኔ በሥጋዊው እርሳቸው በመንፈሳዊ ዓለም ያሳለፍነውን ውጣ ውረድ ስናወጋ ውለን ዕለቱ ፆም በመሆኑ ቅዳሴ ባይኖርም የቅዳሴ ማለቂያ ሰዓቱን ጠብቀን እኔ ተሸክሜ ከመጣሁት ከእርሳቸው ቤት ካለውም አድርገን ምሳ በላን።

ይህን ያክል ዓመት ሙሉ ራሱን ከዓለም ባገለለ ሩቅና ቆላማ ቦታ ውስጥ በአንድ ጎጆ ቤት ሳይናወፁ መኖር መቻላቸውን ሳስብ፣ የቦታውን ክቡርነትና ቃልኪዳን ዛሬ በዙሪያ ጥምጥም በገደምዳሜ ተረድቼ እኔ እራሴ ወድጄ ሳይሆን ጉጉት እየናጠኝ ተመልሼ መምጣቴን ሳውቅ እማሆይ ዕሴተ ማርያም ምን ያክል

በእግዚአብሔር የተመረጡ መሆናቸውን ተረዳሁ። ከላይ ያለው ሰውነታቸው እየተንሳቆለ ቢሆንም ውስጣቸው ግን ዕለት ከዕለት እየታደሰ ነው። የእኔ በእንፃሩ የውጪ ሰውነቴ እየሰለለ ውስጡ ግን እየሻገተና እየሻከረ እንደሄደ ይሰማኛል።

እመን ቆላ ቅዱስ ሁራኤል ቤተ ክርስቲያን ለመኖር ሲወስኑ ወሳኔያቸውን ለማስቀየር ያደረኩትን ጥረት አሁን ሳስበው "ልፈትናቸው የተላኩኝ ገብረ ሰይጣን ነበርኩ" እላለሁ።

ለማንኛውም የመጣሁበትን ጉዳይ ለእማሆይ ማታ ገልጽልጽ አድርጌ እነግራቸዋለሁ። የደረሱበት ምሥጢር እንዳለም አምኛለሁ። እለዚያማ ይህን ያህል ጊዜ ምን የሚያሥራቸው ኃይል ይኖራል? ለማንኛውም አካባቢውን በጥንቃቄ መቃኘት ፈለግሁና እማሆይን እግሬን ማፍታታት እንደምፈልግ ነግሬያቸው ከቤት ወጣሁ።

ወዘ ልውጥ በመሆኔ በአካባቢው ትኩረት እንዳልስብ መጠንቀቅ እንዳለብኝ ቀደም ብዬ አስቤዋለሁ። ቀለሙ ያልደመቀ እንዲያውም የወየበ ካኪ ጃኬትና ሱሪ፣ አሮጌ ኮፍያና አሮጌ ጫማ አድርጌያለሁ። ይህን እልፎ የሚጠይቀኝ ካለም የእማሆይ ዕሴተ ማርያም ዘመድ እንደሆንኩና እርሳቸውን ለመጠየቅ እንደመጣሁ እናገራለሁ ብዬ መላ ዘየድኩ።

ከእማሆይ ጎጆ ወጥቼ በስተደቡብ ወዳለው ተራራ ሄድኩና መሐል ዳገቱ ላይ ስደርስ ዙሪያ ገባው መልክአ ምድር ቁልጭ ብሎ ታየኝ። ከቤተክርስቲያኑ ትይዩ ካለ አንድ ድንጋይ ላይ ዐረፍ አልኩና ዙሪያውን መቃኘት ጀመርኩ።

ሳላስበው ሳነበንብ አገኘሁት፤

"ከሸክላ፣ ከብረት፣ ከነሐስ፣ ከብር፣ ከወርቅ ወይም ከሌላ ነገር ተሠርተህ ሊሆን ይችላል። ዕብራዊ ወይም ሮማዊ ወይም ግሪካዊ አንጥረኛ ሰርቶህም ይሆናል። ይህ ሁሉ ግን ለእኔ ትርጉም የለውም የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ እጆች ከፍ አድርገው የያዙህ ቅዱሱ ጽዋ ሆይ! በውስጥህ የሚያሰክር መጠጥ ሳይሆን የዘላለም ቤዛ የሚሆን ክቡር ደምን የተሞላህ ቅዱሱ ጽዋ ሆይ! የት ይሆን የተደበቅከው?!"

ባልዩ መንፈሳዊ ኃይልህ ልቤን እየሳብክ በገነት የምታቀልጠው ክቡር ንዋይ ሆይ የት ይሆን ያረፍከው?! የልቤ ንጽሕናና የእምነቴ ልክ አንተን ለማየት እንደማያስችለኝ ባውቅም ናፍቆቴ መጠን አልፎ እንቅልፍ ያሳጣኸኝ ቅዱሱ ቅርስ ሆይ የት ነህ? ከመቅደሱ ሥር ወይስ በእነዚህ ተራሮች እናት ወይስ ዋሻዎች ውስጥ? እባክህ ተገለጥልኝ!!" እያልኩ ስናገር ሳይታወቀኝ ድምጼ ከፍ እያለ መምጣቱን የተረዳሁት ዘግይቼ ነበር።

ጀርመናዊው ባለቅኔ ዎልፍራም "ወደ ቅዱሱ ጽዋ የሚቀርቡ የተመረጡ ናቸው። የሚጠብቁትም ቅዱሳን ናቸው" ብሎ የተቀኘውም ትዝ አለኝና እኔ ለዚያ የተገባሁ እንዳልሆንኩና ዝም ብዬ እንደምዳክርም ተሰማኝ። ይህን እያሰብኩ ዝም ብዬ በውስጤ ስነጋገርና ስደነቅ እንባዬ ድንገት መውረድ ጀመረ።

አካባቢው ለዐይን ያዝ ሲያደርግ ወደ ቤተክርስቲያኑ ወደ እማሆይ ጎጆ ተመለስኩ።

እማሆይ የሆነ ነገር ምድጃ ላይ ጥደዋል። ሲያዩኝ "መጣህ ኃይለ ጊዮርጊስ?" አሉና ጠዋት ፀሐይ ሲሞቁ የነበሩትን አባት ጠሯቸው። ከአባ ጋር ወንድሜ ነው ብለው ካስተዋወቁኝ በኋላ የሠሩትን እራት አቅርበው ሦስታችንም አብረን በላን። አባ የቤተ ክርስቲያኑ እቃ ቤት ጠባቂ ናቸው። እራት በልተን አመስግነን እንደጨረስን ወደ ማደሪያቸው ተሰናብተውን ሄዱ።

መኝታዬን አንጥፌ እንደተቀመጥኩ እማሆይ ለጸሎት እየተዘጋጁ እንደሆነ ስረዳ፥

" እማሆይ?" አልኳቸው፥

" አቤት" አሉኝ።

"አንድ የማማክረዎት ነገር ነበረኝ፥ ጸሎትዎን የማላስተጓጉል ከሆነ?" አልኳቸው።

"አይ! ይደርስ የለ። ይልቅ ምንድን ነው የምታማክረኝ?" አሉኝ። በሻማው ብርሃን ውስጥ ፈገግ ሲሉ አየኋቸው።

እንዴት ብዬ ነው መንገር ያለብኝ? ጥያቄዬ ያስከፋቸው ይሆን? እያልኩ ከራሴ ጋር ትግል ጀመርኩ። ዝምታዬ ሲበዛባቸው፣

"እሀ! ንገረኝ እንጂ?" ሲሉኝ

እንደመባነን አልኩኝና

"እ... እኔ የመጣሁት እኮ... ቅዱሱን ጸዋ ፍለጋ ነው" አልኳቸው። ከተናገርኩ በኋላ ግን ቦንብ ያፈነዳሁ ያክል ተሰማኝና የሚሉትን ለመስማማት በጉጉት መጠባበቅ ያዝኩ። ትንሽ ዝም ብለው በፈገግታ ውስጥ ቆዩና፣

"አውቃለሁ !" አሉኝ።

"ምን? እንዴት?" አልኩኝ። መብረቅ የወረደብኝ መሰለኝ።

"ቀኑን አላወኩትም ነበር እንጂ በመጨረሻ ወደ ዚህ እንደምትመጣ እጠብቅ ነበር" አሉኝ።

እማሆይ ዕሴተ ማርያም በናዳ ማርያምና አቡነ አሮን ገዳም በገጠመኝ ቅንብር መሳይ ነገር እሳቸውም እንዳሉበት ወለል ብሎ የታየኝ በዚች ቅጽበት ነበር። እማሆይ በእጃቸው ይዘውት የነበረውን ሻማ ጥግ ላይ በእንጨት ጉማጅ ላይ ተክለው ሲያበቁ እጅግ በረጋ አነጋገር፣

"አንተ ቅዱስ ጸዋ የምትለውን እኛ የቅዱስ ኪዳን ቅርስ እንለዋለን። እንደገመትከው በመድኃኔዓለም ፈቃድ በዚህ በመንዝ ይኖራል። ይህንን ቅዱስ ኪዳን የሚጠብቅ ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ከተለያዩ መካናትና ገዳማት የተውጣጡ አባቶች ያሉበት ጉባዔ አለ። ይህ ጉባዔ በዐሥር ዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰብና ሱባኤ ተገብቶ ጸሎት ተደርጎ ሲያበቃ የቅዱሱን ኪዳን ቅርስ የሚያጥኑና የሚጠብቁ ሦስት አባቶችን ለዐሥር ዓመት ይሰይማል። እነዚያ አባቶች ዐሥር ዓመታቸውን አድርሰው ወደየመጡበት መካናት ይመለሳሉ። እነዚህ ሦስት አባቶች ክህነት ያላቸው መነኩሳት ሲሆኑ በገዳማዊ ሕይወታቸው የተመሰከረላቸው ብቁ አባቶች ናቸው።

ቅዱሱ የኪዳን ቅርስ ያለበትን ቦታ በሚቀየርበት ጊዜ ከሚተኩት ሰሞነኛ አባቶች በቀር ለማንም መንገር አይፈቀድላቸውም። በአገልግሎት ዘመናቸውም የቅዱሱን ኪዳን ቅርስ የሚገኝበትን ቦታ መልቀቅ አይፈቀድላቸውም። ለቁመተ ሥጋ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ በቅዱስ ሁራኤል የወር በዓል እዚህ እመን ቆላ ቅዱስ ሁራኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ ምሥጢራዊ ቦታ ላይ በሥርዓት ይቀመጥላቸዋል። በሌሊት እንዳቸው መጥተው ይወስዳሉ። ይህንን የሚያቀናጅ የእርድእት ንዑስ ጉባኤ አለ። በዋና ዋና ምሥጢራት ግን አይካፈልም። ጉባኤ ሲካሄድ ገበያ ሄዶ እህል መሸመት፣ ማዕድ ማዘጋጀት እና የመሳሰለውን ተግባራት ማከናወን ነው። እኔም የመድኃኔዓለም ቸርነትና ጸጋ ብዙ ነውና ከእርድእቱ ውስጥ እንዷ ሆኜ አባቶቼን አገለግላለሁ" አለኝ።

"ይገርማል!" አልኩኝ በተመሰጦ ስሰማ ቆይቼ።

"ጉባኤው በየዐሥር ዓመቱ የት ነው የሚካሄደው?" አልኳቸው።

"ትኩረት ላለመሳብ ሲባል የተወሰነና የተለየ ቦታ የለውም። አባቶች ተመካክረው በአንድ ገዳም ያደርጉታል። ለምሳሌ የቅርቡ ጉባኤ የተካሄደው ጉጃም ውስጥ ናዳ ማርያም ነበር" አለኝ።

"ናዳ ማርያም?!" አልኩኝ ሳላስበው።

"አዎን! ናዳ ማርያም" አለ ። ቀጠሉና፣

"ጉባኤ በሚካሄድበት አካባቢ ያሉ የቤተክርስቲያን ፍቅር ያላቸው ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን አልፎ አልፎ እርድእቱን እንዲያግዙ ይጠራሉ። ሲጠሩም ጉባኤ አለ ሳይባል ያው ቀጥተኛ ባልሆነ ወይም ዘወር ባለ አነጋገር ነው"።

"እኔም እዛ መጥቼ ስለነበር፣ ባሕር ዳር እንደምትኖር ሰምቼ ስለነበረ እዚህም የኪዳኑን ቦታ በተደጋጋሚ የረገጥክ በመሆኑ አባ መርሐ ጽድቅም በአጋጣሚ ስለሚያውቁህ አንዳንድ ነገሮችን እንድታግዘን፣ በዛውም በረከት እንድታገኝ በማሰብ እንድትመጣ ላከንብህ"።

ይሁን እንጂ የመድኃኔዓለም ፈቃድ ሳይሆን ቀርቶ ጉባኤው አለቆ አባቶች ሁሉ ከተበተኑ በኋላ በሳምንቱ መጣህ" አሉኝ፤ ቀረብሁ ለማለት የእጃቸውን መዳፍ ወደ ላይ ገልብጠውና ዘርግተው በሐዘኔታ እያዩኝ ።

የሚያምሰለው አጥቶ እሳት ላይ ተጥዶ እንደተረረ የማሽላ እሸት በጸጸት እርር አልኩኝ። ሰንባ በዐይኔ መጥቶ ግጥም አለ። ራሴን ስረግምና እድሌን ሳማርር ቆየሁና፤

"ታዲያ ዘማይቼም ቢሆን መምጣቴን እንዴት አወቁ?" አልኳቸው።

"ከመጣህ አይቀር ብዬ ከአባ መርሐ ጽድቅ ለተወሰነ ጊዜ የምቀጽለው አንድ ትምህርት ነበረኝ። እና ማታ ጉባኤ ላይ አንድ ጥግ ተቀምጠህ አየሁህ። ወዲያው ከጉባኤው በኋላ ከአባ ጋር ተመካከርን። ዘማይተህ መምጣትክን ነግረን ተስፋ ማስቆረጥ አልፈለግንም። በዝርዝር ብንነግርህ ብዙም ክብደት ስለማትሰጠው አንዳንድ ምልክት ነግረንህ ወደዚህ ወደ ቅዱስ ኪዳን እንድትመጣ ለመገፋፋት ተስማማን። በበኔጊያው ስትመለስ እንጨት ለቀማ መስለን ጠበቅንህ። እንዳታውቀኝ አጠንቀቅ ነበር። አንተ ግን ጭራሽ በቁጣ ነደህ ስለነበር እንኳን ልትለየኝ በአግባቡ እንኳን ሳትናገረን መኪናህን እያከነፍክ ሄድክ" አሉኝ።

"ምን? እርስዎ ነበሩ ያናገሩኝ?" አልኩ በመደነቅ።

"አዎን! ቀለኛዋ እማሆይ!" አሉ።

በንዴት ከምሽሽ አልኩ። በርግጥ በወቅቱ ያደረኩት ነገር ወዲያው ጸጸተኝ እንደነበርም ትዝ አለኝ። አሁን ደግሞ ይባስ አሳፈረኝ። እግሬን ሰብስቤ ከርምት አልኩ።

"እኔ እምለው ጉባኤው በየዐመቱ ዓመቱ የሚካሄድ ከሆነ ከቆይታም አንጻር ሁለት ጉባኤዎችን ተካፍለዋል ማለት አይ ነው?" አልኳቸው።

"አዎን የመድኃኔዓለም ቸርነቱ ብዙ ነው" አሉ በደስታ።

"ታዲያ እርስዎ መጀመሪያ የተካፈሉበት ጉባኤ የት ነበር የተካሄደው?"

"እኔ ለመጀመሪያ ጊዜ የተካፈልኩበት በጎንደር ውስጥ አምስትያ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ሲሆን ከዚያ በፊት የነበረው ትግራይ ውስጥ እንደነበረ ሰምቻለሁ" አሉኝ።

ጉባኤው በአምስትያ ተክለ ሃይማኖት ገዳም የተካሄደበትን ወርና ዓመተ ምሕረት እማሆይ ሲነግሩኝ አእምሮዬ የሆነ ነገር እያሰላ ነበር። በጣም ይገርማል። በዚያው ወቅት የድህረ ምረቃ ጥናቴን ለማሟላት የገዳሙን ደን ለማጥናት ሄጄ ስለነበር ብዙ ነገር ወደ አእምሮዬ ተግተልትሎ መጣ።

አምስትያ ተክለሃይማኖት ገዳም በደቡብ ጎንደር ዞን በዕብናት ወረዳ ከወረዳው ዋና ከተማ በስምንት ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ከትልቅ ጋራ ስር በማራኪ የተፈጥሮ ደን ተሸፍኖ የሚገኝ ገዳም ነው። በ1260 ዓ.ም በዐፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት በጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖት ተባርኮ በኋላ በአቡነ ሀላዊ እንደተመሰረተ ገዳምያውኑ ይናገራሉ። ገዳሙን እኔ በጎበኘሁበት ወቅት 23 ሄክታር ጥቅጥቅ ያለ የተፈጥሮ ደን ነበረው። ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ፣ ከሰሜን ወደ ደቡብ የሁላብ መስመር እያሰመርኩ የደኑን ይዘት፣ የዕፅዋቱን ስብጥር በደንብ አድርጌ እንዳጠናሁት አስታውሳለሁ። እድሜ ጠገብ የሆኑ የጽድ፣ የወይራ፣ የቋጥኝ፣ የብርብራ፣ የዶንጋና የኮሶ ዛፎች ከእጋምና ከቀጋው ሽታ ጋር ተዳምረው አካባቢውን የገነት በር ያስመስሉት ገዳም ነው። ጥቅጥቅ ካለው የገዳሙ ደን ውስጥ ሁነው ሲያስቡ የተፈጥሮ ዕፅዋቱ ተጨፍጭፎ መልክአ ምድሩ ከተራቆተው ዕብናት ወረዳ ውስጥ መሆንዎን ይዘነጋሉ። ታዲያ በጥናቱ ወቅት ዳስ መሳይ ነገር ከሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ በስተ ሰሜን በኩል አይቼ

"ንግሥ ወይም ድግስ ነበር እንዴ?" ብዬ ብጠይቅ ገደማውያኑ በፈገግታ ከማየት በስተቀር መልስ አልሰጡኝም ነበር። ጥናቴን አጠናቅቄ ከመመለሴ በፊት የገዳሙን አበምኔት ለማመስገንና ለመሰናበት ሳገኛቸው

"በሰላም ጨረስክ?" አለኝ

"አዎን አባታችን" አልኩ

"የደኑ ይዞታው እንዴት ነው?" አለኝ

"በጣም ጥሩ ነው ብቻ ወደ ዳር አከባቢ ድንበሩ እየተገፋ ስለሆነ ትኩረት ብትሰጡት መልካም ነው" አልኳቸው።

"ደኅና የተቻለንን ያክል እናደርጋለን" ካሉኝ በኋላ

"ከሳምንት በፊት መጥተህ ቢሆን ኖሮ ከዕፅዋቱ በተጨማሪ ሕያው ቅርሶችን ማየት ትችል ነበር" ብለው ፈገግ አሉ።

"ምን ዓይነት ቅርስ? አሁንስ እንዳላይ ምን ያግደኛል?" አልኩኝ በችኮላ። ልክ አባ መርሐ ጽድቅ ናዳ ማርያም ሲያሰናብቱኝ እንዳሳዩኝ ዓይነት ለልጅና ለጅል የሚሰጥ ፈገግታ አሳይተው ትከሻዬን ስመው ጸሎት አድርገው ወደ በዓታቸው እንደተመለሱ ትዝ አለኝ።

አሁን ግን ያን ያደረጉት ለምን እንደነበረ ግልጽ ሆነልኝ። ቅዱሱን ጉባኤ በቅርብ ርቀት የሳትኩት ለሁለተኛ ጊዜ መሆኑን ተረዳሁ። ገጣሚ ጌትነት እንየው ‹ባዶዬን መጣሁኝ› በሚል ርእስ የጻፈው ግጥም ትዝ አለኝና ወደ መጨረሻ ያሉትን ስንኞች በልቤ አነበነብኩ፡

"...........

ሰባተኛው ችሎት ይሆን ፍርድ አግኝቼ

ሥጋዬን ለሲኦል ነፍሴን ገነት ትቼ

ዘላለም እንድኖር እግዚያር ፈርዶልኝ

እሰ ሥጋ- እሰ ነፍስ፡ እንድኖር ፈቅዶልኝ

‹ባዶህን ሂድ› ብሎኝ ባዶዬን መጣሁኝ።"

ብዙ ገዳማትንና አድባራትን የመጎብኘት እድል ገጥሞኛል። ነገር

ግን ባዶዬን እየሄድኩ ባዶዬን ስመለስ ነበር የኖርኩት፡ አልኩና በትካዜ ባሕር ውስጥ ሰጠምኩ።

ትንሽ ቆይቼ እንደመባነን አልኩና

"እማሆይ እርስዎ ግን ቅዱሱን ጽዋ በአካል አይተውታል አይደል? ምን ይመስላል? እንዴት ነው የተቀመጠው?" አልኳቸው።

"አላየሁትም!" አሉኝ ፍርጥም ብለው።

"እንዴት? ከነዚህ አባቶች ጋር ከሀምሣ ስምንት ዓመታት በላይ ኑረው? እያገለገሏቸው እንዴት እስከ ዛሬ ሳያዩት ቀሩ?" አልኳቸው ጥርጣሬዬን በሚገልጽ ሁኔታ።

"ማየት ስለማያስፈልገኝ ለማየት አልሞከርኩም" አሉ።

"እንዴ ከዚህ በላይ የከበረ ነገር ማገኛ የትኛ ተአምር ምን አለ?!" አልኳቸው።

"ሰማህ ኃይለ ጊዮርጊስ ቅዱሱ የኪዳን ቅርስ በእውነት ተራሮች በአንዱ ወይም በዋሻው ውስጥ ሊኖር ይችላል። ለእኔ ትልቁ ነገር ይህ ክቡር ኪዳን በአለበት ቦታ መኖሬ ነው። ይህ ብቻ በቂዬ ነው። የጥንት ነገሥታት ይጠጡበት ነበር ተብሎ በየሙዚየሙ በመስታወት ከተቀመጡ በወርቅ ከተንቆጠቆጡ ጽዋዎች በቅርፁ አይለይ ይሆናል። ለእኔ ተስፋዬ ግዙፍ ቅርስነቱ ሳይሆን ቃል ኪዳኑ ነው ። ይህን የቃል ኪዳን ቅርስ የሚያጥኑና የሚጠብቁ የተመረጡ አባቶችን ማገልገሌ ብቻ ነፍሴን ያረካታል" አሉና ትንሽ እንደማሰብ ብለው፦

"በወንጌል ላይ ታሪኳ የተጻፈውን ደም ይፈስሳት የነበረች ሴት ታሪክ ታስታውስ የለ?" አሉና፣" ሰዎች ሁሉ ክርስቶስን ለማየት፣ ለመናገር፣ ለመዳሰስ፣ ቤታቸው ለመጋበዝ ሲጋፉ፣ እንዲህ አለች ለእኔ ግን የልብሱን ጫፍ ብቻ የዳሰስኩ እንደሆን እድናለሁ ብላ የለበሰውን የቀሚስ ጫፍ ከኋላ ሂዳ ነካች። ከሕመሟም ወዲያውኑ ተፈወሰች።

ወደ ቅዱሱ ኪዳን ወዳለበት ስፍራ መጠራቱን ያወቅሁት ቀን ነፍሴ ሰላምና ዕረፍት አግኝታለች። ከዚህ በላይ አያስፈልገኝም" አለኝ።

"እኔ ግን ማየት ማለት በአካል ላየው እፈልጋለሁ !" አልኳቸው በልመናና በጉጉት፡

"አዎን! ብዙዎች ሊያዩት ይጓጓሉ" አሉ እማሆይ።

"እኔ እምነቱ ተንጠፍጥፎ አልቆ ባዶ የሆንኩ ሰው ነኝ። ቅዱሱን ጽዋ አይቼ መፈወስ እፈልጋለሁ። ተአምራቱን ለዓለም መናገር እፈልጋለሁ። እባክዎን የመንገዱን ቁልፍ ይንገሩኝ። ከተራራው አናት ወደ አዘቅት ውስጥም ቢሆን ግድ የለኝም። የትም ቦታ የሚገኝበትን ፈተና ተጋፍጬ ከፊቱ ልንበረከክ እሻለሁ" አልኳቸው።

"የት እንዳለ የመናገር ዕውቀቱም ሥልጣኑም የለኝም። ልደብቅህ ፈልጌ አይደለም!" አለኝ በማስተዛዘን።

"እይ ግድየለም ይተውት። የቅዱስ ዑራኤልን የወር በዓልን ጠብቄ ቅዱሳኑ የተቀመጠላቸውን ዕቃ ሊወስዱ በሌሊት ሲመጡ ከኋላቸው ተከትዬ ወደ ሚሄዱበት እሄዳለሁ። የፈጀውን ጊዜ ይፍጅ እንጂ እነዚያን ቅዱሳን አባቶች እዚሁ ቤተ ክርስቲያን ጓሮ ሆኜ እጠብቃቸዋለሁ" አልኩ ፈርጠም ብዬ።

"እይ ያንተ ነገር!" ብለው ፈገግ አሉና

"በመንፈስ ጀምረህ በሥጋ ልትጨርስ ነው? ቅዱሱ የኪዳን ቅርስ የተሰወረው እኮ በመንፈስ ነው። በሥጋ ድካም የምታገኘው አይደለም!" አሉና

"ይልቁንስ..." ብለው ዝም አሉ። ሊነግሩኝ የፈለጉት ነገር እንዳለ ግን እያወላወሉ እንደሆነ ገባኝ እና ድንገት ብድግ ብዬ ከሥራቸው ተንበርክኬ

"ይልቁንስ ምንን?" አልኳቸው፣

"ኧረ በፈጠረህ ተነስ፤ ልንግርህም አይደል?" አሉ። ተነሳሁና ቁም አልኩ፡

"ወደ አንድ ቦታ እልክሀለሁ። እዛ ሄደህ አባ አከሊሉ የሚባሉ አባት ታገኛለህ። እርሳቸው ጉጉትህንና ቅንነትክን አይተው አንድ ፍንጭ ይሰጡህ ይሆናል" አሉኝ።

"እርስዎ የሚያውቁኝ የደበቁኝን እርሳቸው ምን ብለው ይረዱኛል?" አልኩ በቅሬታ።

"ግድ የለም ይረዱሀል። በዚህ አካባቢ ያሉ ትልቅ አባታችን እርሳቸው ናቸው። ቦታው ልዩ ቃል ኪዳን ያለው ነውና በዚያውም በረከት ታገኛለህ። እኔ ማስታወሻ ጽፌ እሰጥሀና እሱን ታሳያቸዋለህ" አሉኝ።

"የት ነው ቦታው? እሩቅ ነው?" አልኳቸው።

"የትም ቢሆን እሄዳለሁ ብለኸኝ አልነበር? አሁን ምን ርቀት አስጠየቀህ?" አሉ ፈገግ ብለው።

መቼም ሲያወሩኝ ሕፃን ልጅ እንደሚያወሩ ዓይነት ነው።

"እሱስ ግድ የለኝም እንዲው ዝም ብዬ ነው" አልኳኙ፤ መቀላመዱ ታውቆኝ።

"እዚሁ መንዝ ግግ ምድር ነው። ቦታውን በፊትም ሳታውቀው አትቀርም። ይገም አርባ ሃራ መድኃኔዓለም ነው" አሉኝ።

" ይገም አርባሃራ፤ አዎን! ትዝ አለኝ። በደጋው በኩል ዋሻ ያለው ቤተክርስቲያን አይደል?" አልኳቸው።

"አዎን፤ እዛ ነገ ትሄዳለህ" አሉኝና ወረቀትና እስክብሪቶ እንድሰጣቸው ጠየቁኝ። ከማስታወሻዬ ቀድጄ ከእስክብሪቶ ጋር ሰጠኋቸው። ወደ ሻማው ተጠግተው ሲጽፉ ቆዩና ወረቀቱን ከአራት አጥፈው ከትራሳቸው ሥር አስቀመጡት።

" በል እንግዲህ ሀረፍ በል፤ በጠዋት ትሄዳለህ" ብለው ጸሎታቸውን ጀመሩ።

እኔም እንደነገሩ ጸሎት ቢጤ አደረግሁና ከመደቡ ላይ ተጋደምኩ። እማሆይ በእሻጋሪ ቁመው ጸሎት እያደረጉ እኔ መደብ ላይ ተሸፋፍኜና ተጋድሜ ለሚያይ ሞቼ ጸሎተ ፍትሐት እየተደረገልኝ ይመስላል።

"ወይ ማማ። ወደ ግቤ ተቃረብኩ ስል እንደገና ወደ ሌላ በታ መንከራተት። እንዲያው እነዚህ ምሥጢራቸው የማይፈታ ልጉሞች። በቃ እንደ ኳስ እየተቀባበሉ ከአንዱ ገዳም ወደ ሌላኛው ይጠልዙኛል" አልኩና ለምን ቁርጥ አድርጌ እንደማልተወው ሳስብ "ሲያንሰኝ ነው" ብዬ ለመተኛት ሞከርኩ። ሌሊት እማሆይ ለጸሎት እንደገና ተነሡ። እኔም ተነሣሁና ሰዓቱን ሳይ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ይላል።

"ደኅና አደርክ? ኃይለጊዮርጊስ " አሉኝ

"ደኅና እግዜር ይመስገን፤ እረስዎ እንደምን አደሩ" አልኩና መደቡን ለቅቄ ቁሜ ልብሴን ስፈልግ አዩና፡

"ተኛ እንጂ፤ ገና እኮ አልነጋም" አሉኝ ።

"እይ! እንግዲህ ምን ቀረው? በጠዋት ብሄድ ይሻላል ብዬ ነው" አልኩ።

"እንዴ! የእመጓ ቆላ መውጫ እንኳን በጨለማ በብርሃንም ችግር ነው። ወይ ጉድ! ምንድን ነው ጥድፊያው?" አሉ ቆጣ ብለው ። ዳገቱን ሳስብ እንደገና ሀሞቴ ፍስስ አለና ቁጭ አልኩ።

"ወይ ኃይለጊዮርጊስ! አውንትም ታመሐል? እንዲያው ያ ሁሉ ትዕግሥትህ ወዴት ጠፋ። በል ዐርፈህ ተኛ" አሉና ጸሎታቸውን ቀጠሉ።

እንዳይነጋ የሰም ኑጋና ሁለቱን ሻንጣዎቼን ይዤ ለመሄድ ተነሳሁ። እማሆይ ዕሴተ ማርያም ከትራሳቸው ስር ያስቀመጧትን ወረቀት አነሱና።

“ለአባ አክሊሉ በእጃቸው ስጣቸው። ገልጠህ እንዳታነብ ዋ!” አሉኝ።

ፈገግ ብዬ “እሺ” አልኩና ወረቀቷን ተቀብዬ ከደረቴ ኪስ ሸጎጥኳት።

“እየሙልህ ኃይሌዬ! እባክህ ትዕግሥት ይኑርህ። ይሄ በየሀገሩ እየዞርክ የቃረምከው እውቀት መንፈሳዊነትክን ሳይጎዳው አልቀረም። አትቸኩል፤ ምንም ምን ቢያጋጥምህ አትናደድ፤ የቅዱሱ ኪዳን በረከት አይለይህ፤ መልአኩ ሁራኤል ይከተልህ” አሉኝና ተሰናበቱኝ።

“እሺ እማሆይ እግዜር ቢረዳኝ ቶሎ እመለሳለሁ” አልኳቸውና መንገዴን ጀመርኩ።

የእመጓ ቆላን ዳገት በደረቴ እየታከኩና እንደ ዝንጀሮ እየቧጠጥኩ እንደምንም ወጣሁት። ወደ ላይ መውጣት ያደክማል እንጂ አያስፈራም። ዳገቱን ጨርሼ ደልዳላ ሜዳው ላይ ስደርስ ፊቴን ወደ ቆላው አዙሬ ድንጋይ ላይ ዐረፍ አልኩኝ። ድንገት አንድ መጥፎ ሀሳብ ብልጭ አለብኝ።

“እንዴ! እማሆይ ሁኔታዬ ስላላማራቸው በዘዴ ከቅዱሱ ስፍራ እንድርቅ ይሆን እንዴ ወደ ደብሩ የላኩኝ?” አልኩና የሰጡኝን ደብዳቤ ደረት ኪሴ ውስጥ ላጥ አድርጌ አወጣሁት።

“ምን ብለው ይሆን የጻፉት?” አልኩ ጀመር። ደብዳቤውን የማንበብ ከፍተኛ ጉጉት አደረብኝ። “ገልጠህ እንዳታነብ ዋ!” ያሉኝ ቃል ሞገተኝ። ይህን ያክል ሞራለቢስ መሆንማ የለብኝም አልኩና ደብዳቤውን መልሼ ኪሴ ከተትኩና ጉዞዬን ወደ ሞላሌ ተያያዝኩት።

# ምዕራፍ ዐሥራ ዐራት

ይገም አርባሃራ መድኃኔዓለም ከሞላሌ ከተማ ሃያ ሰባት ኪሎ ሜትር ላይ ወደ መሐል ሜዳ በሚወስደው የመኪና መንገድ በስተቀኝ አንድ ኪ.ሜ. ገባ ብሎ የሚገኝ ጥንታዊ ደብር ነው። ወደ መሐል ሜዳ የሚወስድ መኪና ሳጠያይቅ ከአዲስ አበባ በሞላሌ አድርጎ ወደ መሐል ሜዳ የሚሄደው አውቶብስ ካልሆነ በቀር ለጊዜው እንደማላገኝ ሰዎች ጠቆሙኝ። ከአዲስ አበባ የሚመጣውን አውቶብስ ለዕለት የሚያስፈልጉኝን ደረቅ ብስኩትና ውሃ ገዝቼ ከአንድ ሆቴል ጥግ ቁጭ ብዬ መጠበቅ ጀመርኩ።

ከቀኑ ዐሥር ሰዓት ላይ አንድ አውቶብስ መጣ። የሞላሌ መንገደኞች ከወረዱ በኋላ ‹ይገም ነው የምሄደው› ብዬ ተሳፈርኩ። ትኬት ቆራጩ መጣና

"መሐል ሜዳ እንጅ መንገድ ወራጅ አንጭንም" አለኝ።

"ግዴየለም በመሐል ሜዳ ሂሳብ እከፍላለሁ፤ ስለምቸኩል ነው" አልኩኝ። ያው የተለመደ ገንዘብ ማስጨማሪያ ዘዴ ነው። በአዲስ አበባ ሂሳብ ክፈል ቢሉኝም መክፈሌ አይቀርም ነበር።

ይገም የቀበሌ ንዑስ ጣቢያ በመሆኗ እዚህና እዚያ የተሰሩ ሻይ ቤቶች፣ የመምህራንና የግብርና ባለሙያዎች መኖሪያ ቤቶች አሉባት። በጣም ብርዳምና ድብርታም መንደር ናት። ከአውቶብሱ ወረድኩ። እንደ እኔ ያለ ወዘ ልውጥ ሰው ምሽት ሲቃረብ ደብር መሄድ ለአካባቢው ሰው ጥሩ ስሜት ላይፈጥር ይችላል ብዬ ስላሰብኩ በዚያ ሰዓት ወደ ቤተክርስቲያኑ መሄድ እንደሌለብኝ ወሰንኩ።

የተወሰኑ ሰዎች ከተቀመጡበት ሻይ ቤት ነገር ገባሁና ሰላምታ አቀረብኩ። ሁሉም ከመቀመጫቸው ተነሥተው እንደሚያውቁት ሰው አድርገው ተቀበሉኝ። "እረ በእግዜር አይገባም!" ብዬ በአንድ ጥግ ሄጄ ቁጭ አልኩ። ያለ ሰዓት የመጣሁ እንግዳ መሆኔን አይተው ግር እንዳላቸው ገባኝና

"እ... ከዩኒቨርሲቲ የመጣሁ አጥኚ ነኝ። እዚህ ጓሳው ስላሉት ቀይ ቀበሮች የማጠና ነኝ" አልኳቸው።

ከይግም ትንሽ እለፍ ብሎ "መንዝ ጓሳ" የሚባል ስፍራ አለ። እናም እዛ ብርቅዬ የሆኑት ቀይ ቀበሮዎች መኖሪያ እንዲሆን የማኅበረሰብ ፓርክ እየተቋቋመ እንደሆነ ስለማውቅና እነሱም እንግዳ አይሆንባቸውም ብዬ አስቤ ነው።

"አይይይ! ታዲያ ከወዲያ ነበር የምትወርድ እኮ!" አለኝ እንደኛው ለእኔ በማዘን ስሜት።

"አውቂያለሁ ስለመሸ በዚያውም በወዲህ በኩል ለመጀመር ብዬ ነው" አልኩኝ።

"እንዲያ ከሆነ ደኅና ነው" አሉኝና ተረጋጉ።

የቤቱ ባለቤት ብስል ቀይ ደረበብ ያሉ ግርማ ሞገስ ያላቸው እናት ናቸው።

"እናቱ ካላስቸገርኩ የዛሬን እዚች እመደቧ ላይ ቢያሳድሩኝ? ሂሳብ የጠየቁኝን እከፍላለሁ" አልኩኝ።

"እንዴ! ቤት የእግዜርም አይደል? አይመችህ እንደሆንይ እኔማ ምን ችግሮኝ ልጄ?" አሉኝ

እዛ ያሉት ሁሉ፡ "ደሞ ለመደብ ምን ችግር አለው?" አሉና ጥያቄዬን አቃለሉት።

ተረጋግቼ ቁጭ አልኩ።

"ለብርድ አረሌ /አረቄ ማለታቸው ነው/ ጥሩ ነው፤ አትሞክርም?" አሉኝ።

"እሺ ጥሩ ነው" አልኩና አንድ መለኪያ አስቀዳሁ። የቅዝቃዜው ኃይል አረቄውን እንደ ውሃ ያስጠጣል። መሸቶ ሰዎቹ ተሰናብተው ሲነሱ የመጠጥ ሂሳባቸውን እኔ እንደምከፍል ተናግሬ ተመሰጋግነን ወደ ቤታቸው ሄዱ ።

ቅዝቃዜው ከጨለማው ጋር ተዳምሮ አካባቢውን ሲኦል አስመሰለው። ብርዱን እንዴት ችዬ እንደማድር ሳስበው በጣም ጨነቀኝ። ቅጥል ያለ በርሃ ብሄድ ይሻለኛል ከቀዝቃዛ ቤት። ባለቤቷ ወደ አንድ ጥግ ሄደው ታስሮ የተቀመጠ የሚመስል ጓዝ ይፈቱ ጀመር። ዝተት ነው። ዝተት ወይም ባና ከበግ ፀጉር የሚሰራ የመንዞች ብርድ ልብስ ነው።

"ነጋዴዎች አስቸምጠውት ነው። ይከለከስህ እንደሆነይ ለብርዱ መድኃኒት ነው" አሉና ምስቱን ሰጡኝ። ሁለቱን ከሥር አንጥፌ ከላይ ስልፒንግ ባግ ዘረጋሁና ውስጥ ገባሁ። ከላይ ነጣ ያለውን ዝተት ደርቤ ጋደም አልኩ። ትንሽ ጠረኑ በግ በግ ይሸታል እንጂ ምቾቱና ሙቀቱ በጣም ተስማማኝ። እንዲያ በነጭ ዝተት ተጠቅልዬ ስታይ ትልቅ ቀንድ አውጣ እመስላለሁ።

ሌሊቱ ተመችቶኝ ጥሩ እንቅልፍ ተኝቼ አደርኩ። ጠዋት ስነቃ አንድ ሰዓት ተኩል ሆኗል። አንገቴን ቀና አድርጌና እጄን አውጥቼ ቅዝቃዜውን ስፈትሽ አካባቢው በረዶ የተደፋበት መስሏል። መልሼ ዝተቴ ውስጥ ጥልቅ አልኩ። ከዝተቴ ቀስ ብዬ ብቅ ካልኩ በኋላ መልሼ መግባቴን በዓይነ ኅሊናዩ እየሳልኩ "አሁንስ በደንብ ቀንድ አውጣ መሰልኩ" ብዬ በራሴ ላይ ፈገግ አልኩ። ሦስት ሰዓት አካባቢ ብርዱ ባይለቅም ትንሽ ፈካ በማለቱ ከመኝታዬ ተነስቼ እቃዬን ያዝኩና ባለቤቷን አመስግኜና ትንሽ ገንዘብ ሰጥቼ ወደ አርባ ሃሬ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን አቀናሁ።

እርባ ሃራ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያንን ቀደም ብዬ አውቀዋለሁ። ከገደል አፋፍ ላይ የተሠራ ቤተክርስቲያን ነው። ከቤተክርስቲያኑ ጀርባ በግምት አንድ መቶ ሜትር ላይ ቀጥ ያለ ገደል ነው። በበጋ ወራት የደፋት ሜዳዎች ቁልቁ ብለው ይታያሉ። ልክ ፎቅ ቤት ላይ ሁነው በመስኮት አሻግሮ የማየት ያክል ነው።

የጣርማ በር ሰንሰለታማ ተራሮች ወደ ምሥራቅ እየተጅመሰመሰ ከዚያም ወደ ደቡብ ታጥፈው እስከ አንኮበር ይዘረጋሉ። በምሥራቁ አቅጣጫ የደፋትና የአፋር ረባዳማ ቦታዎች ይገኛሉ። ከደግሞ በስተምዕራብ አቅጣጫ ደግሞ እነዚሁ ተራሮች እስከ መሐል ሜዳ ተዘርግተው በሰሜን ግሸ ራቤልን እየተው ወደ ምዕራብ ደግሞ መርሐ ቤቴንና የደቡብ ወሎ ወርኢሉን ጃማንና ደላንታን አሻግረው ያሳያሉ። እቤት መልክአ ምድር! መቼም የተፈጥሮ ዕፅዋቱ ተሟጦ ባያልቅ የምድር ገነት ይሆን ነበር። ከቤተክርስቲያኑ ሥር ካለው ገደል ሃያ ሜትር ወረድ ብሎ የተፈጥሮ ዋሻ አለ።

ከቤተ ክርስቲያኑ ደርሼ አጭር ጸሎት ካደረስኩ በኋላ ወደ ዕቃ ቤት አቅጣጫዬ ስሄድ አንድ ንቁ መነኮሴ ጓሳ ከተባለው ሳር ገመድ እየፈተሉ፣ የተወሰኑ ተማሪዎች እዚህም እዛም ቁጭ ብለው ሲቀጽሉ (ሲማሩ) አገኘኋቸው።

"አባ አክሊሉ መሆን አለባቸው" አልኩ።

ሰላምታ ሰጥቼ በመስቀላቸው ከተባረክሁ በኋላ እፊት ለፊታቸው ካለው የተጋደመ ደረቅ ግንድ ላይ እንድቀመጥ ጋበዙኝ።

"እህሳ ልጄ! ከወዴት መጣህ?" አሉኝ በአባታዊ ቃና። ድምፃቸው እንዳች ከብደት አለው።

"የመጣሁት እንኳን ከሩቅ አገር ነው። ዛሬ ግን..." አልኩና ንግግሬን ገታ አድርጌ

"አባ አክሊሉ እርስዎ ነዎት አባቴ?" አልኩኝ። መፍተላቸውን ተወት አድርገው ቀና አሉና

"አዎን፤ እኔ ነኝ። የኔ ልጅ ደኅናም አይደለህ?" ሲሉ ጠየቁኝ።

"ኧረ ደኅና ነኝ። ለእርስዎ የሚሰጥ መልእክት ይዤ ነው" አልኩኝ።

"ከወዴት? ከማን?" አሉኝ፤

"እዚሁ ታች እመጓ ቆላ ከእማሆይ ዕሌኒ ማርያም ነው" አልኩኝና ወረቀቷን ከኪሴ ለማውጣት ስዳብስ አጣኋት። እመይ ሁን አለ።

"ምን የተረገምኩ ሰው ነኝ! አልኩ ለራሴ፤

"በደኅና ነው እመጓ ቆላ የወረድከ?" አሉኝ አባ ተረጋጋ ለማለት በሚያስመስል አነጋገር።

በሀሳቤ "ምን ደኅንነት አለ!" እያልኩ ቁሜ ኪሴን እዳብስ ጀመር።

"እ… በደኅና ነው" አልኩ በደመ ነፍስ

"እማሆይ ደኅና ናቸው?" አሉኝ፤

"ደኅና ናቸው" አልኩ።

አባ ወረቀቱ እንደጠፋብኝ ገባቸውና ወደ ገመድ ፈትላቸው አቀረቀሩ። እራሴን መርገሙን ትቼ ተረጋግቼ ማሰብ ጀመርኩ። ማታ ስተኛ ልብሴን ሳላወልቅ ስለነበር ወረቀቷ እንዳትቀደድ ብዬ ከማስታወሻ ደብተሬ ማኅደሬ ትዝ አለኝና ሻንጣዬን ከፍቼ መዥረጥ አደረኳት። ሎተሪ የወጣልኝ ያክል ደስ አለኝ።

"አባታችን እማሆይ ለእርስዎ የላኩት ደብዳቤ ይኸው" አልኩ ቀረብ ብዬ። ልክ የሹመት ደብዳቤውን ለርእሰ ብሔር እንደሚሰጥ አምባሳደር የሆንኩ መሰለኝ።

ተቀብለው ሳያነቡ ከዳዊታቸው ገጽ ወሸቅ አደረጓትና ሥራቸውን ቀጠሉ። እርር አልኩ።

"ከወዴት ነበር መጣሁ ያልከኝ?" አሉኝ፤

"አሁን ከእመን ቆላ ነው። ከዚያ በፊት ግን ከባሕርዳር ነው" አልኩ።

"እረ እረ ተሩቅ አገር ነውሳ የመጣህ " አሉኝና

"ስንት ቀን ፈጀብህ?" አሉኝ።

"እይ! እርስዎ ራስዎ ጉጃም ናዳ "ማርያም" አልነበሩም? ምን ያክል እንደፈጀ አጥተውት ነው ? እንዲያው መቼም አላዋቂ ለመምሰል የማያደርጉት ጥረት ይገርማል!" አልኩ በልቤ።

ከባሕር ዳር አዲስ አበባ አንድ ቀን ሙሉ፣ ከአዲስ አበባ መንዝ አንድ ቀን፣ ያው መንገድ ብቻ ሁለት ቀን ማለት ነው። ትኬት ለመቁረጥ አንድ ቀን አዲስ አበባ ውያለሁ። በጠቅላላ ሦስት ቀን ፈጀብኝ ማለት ነው" አልኩ።

እንዲያዝኑልኝ ብዬ ነው እንጂ እንደ እውነቱ ከሆነ ከባሕር ዳር አዲስ አበባ በአውሮፕላን 45 ደቂቃ ፈጅቶብኝ ነው የመጣሁት።

"እረ እረ አያሌ ተጉዘሀል ደክምሃል እንጅ!" አሉኝ። ያዘኑልኝ መሰለኝና ተስፋ አሳደርኩ።

"ምንድን ትሰራለህ?" አባ ጥያቄያቸውን ቀጠሉ።

" ዩኒቨርሲቲ መምህር ነኝ"።

" እሃ የተማርክ ትልቅ ሰው ነህና!" አሉና

"ታዲያ ተማሪዎቻችሁን አስጨርሳችሁ መሰማሪያ ለምን አትሰጧቸውም? ድሀ ገበሬ ልጁ ኮሌጅ ገባ ሲባል በሬውን እየሸጠ ይልካል። ተአራት ፀመት በኋላ ወላጆቹን ይረዳል ሲባል ሥራ አልጠጣለትም ተብሎ እዚሁ ገበር መቶ መኖር ሆነ እንጅ" አሉ።

"እውን መቼስ ተመራቂውም በዛ። የመንግሥት ሥራ ደግሞ በዚያው ልክ አላድግ አለና ለጊዜው ችግር ሆነ እንጅ ወደፊት ተስፋ ይኖራል። ቢሆንም መማር በራሱ ጥሩ ነው" አልኩኝ።

"እሱስ እውነትክን ነው" አሉና

"ምንድን ነው እምታስተምር?" አሉኝ

"ጉድ ፈላ!" አልኩ ለራሴ

ዩኒቨርሲቲ አካባቢም ሆነ በሌላ ሥራ መስክ ላይ ላለን ባለሞያዎች በጣም አስቸጋሪው ነገር ሙያችንን ላልተማረው ኅብረተሰብ በተለይም መደበኛ ትምህርት ለሌለው ሰው መንገርና ማስረዳት ነው። በውጭ ቋንቋ እዋንተን፣ የውጭ ምሳሌ እየተሰጠን፣ የውጭ መጻሕፍትን እያነበብን ነው ወደ ላይ የምንወጣው። ወደ ህገረኛና አካባቢ ለመለወጥ ግር ይላል።

"በእንግሊዝኛ ኢኮሎጂ በአማርኛ የሥነ ምህዳር ሳይንስ ይባላል" አልኳቸው።

"ምን ማለት ይሆን?" አሉኝ

እማሆይ ዕሌተ ማርያም "ትዕግሥት ይኑርህ" ያሉኝ ትዝ አለኝ።

"በአንድ በተወሰነ አካባቢ ያለውን የዕፅዋት፣ የእንስሳት ስብጥር፣ ከአፈሩ፣ ከውሃው፣ ከአየር ንብረቱ ጋር ያለውን መስተጋብር የሚያጠና ሳይንስ ነው" አልኩና

"ለምሳሌ ዳጋ ስንል የአየሩ ቅዝቃዜ፣ እርጥበቱ፣ ተራራማ መሆኑ፣ የዕፅዋቱን ዓይነት የሚበቅለውን እዝርዕት፣ የእንስሳቱን፣ የተባዩን ፣ የነፍሳት ዓይነቱን የተለየ ያደርገዋል። በለዚህ ደጋ፣ ወይና ደጋ፣ ቆላ እያልን ብዙ ሥነ ምህዳር ማውጣት ይቻላል" አልኳቸው።

"ግሩም! ግሩም!" አሉ አንገታቸውን እየነቀነቁ።

"ውጭ አገር ተምርሃል? የፈረንጅ ልሳንስ?"

"አዎን ተምሬያለሁ። ከውጭ ቋንቋ እንግሊዝኛ ብቻ ነው የማውቅ" አልኩ።

"አሜሪካን ነው?" አሉኝ።

"በተወሰነ ደረጃ አሜሪካ የቆየሁ ቢሆንም ረዘም ላለ ጊዜ የተማርኩት ግን አውሮፓ ውስጥ ነው"።

"ግሩም ነው፤ ብዙ ነገር አይተሃል፤ ብዙ ጥበብም ገብይተሃል ማለት ነው"።

እምን አሜሪካ ስንት ጊዜ ሳተላይት ወደ ህዋ እንዳመጠቀች፣ የፓናማ ካናል መቼ እንደተከፈተ ፣ የዘንድሮውን የአካዳሚ አዋርድ ያሸነፈው ፊልም ዳይሬክተርና ተዋናይ እነማን እንደሆኑ ማወቅ ብቻ ሳይሆን ተዋናዮቹ ስንት ጊዜ አግብተው እንደፈቱ እንደማውቅ፣ ሩሲያዊው ባለሀብት የእንግሊዙን የእግር ኳስ ክለብን ቼልሲን እንደገዙት መረጃው እንዳለኝ በዚህም በጣም ተናድጄ እንደነበር፣ ኒውዮርክ ስቴት ኢምፓየር ሕንፃ ጫፍ፣ እንዲሁም ፓሪስ አይፍል ታዎር ላይ እንደወጣሁ፣ የብራስልስንና የእስቶኮልምን ከተሞች ጽዳትና ውበት በዐይኔ በብረቱ እንዳየሁ፣ የሼክስፒርን ተውኔቶች በለንደን ቲያትር ቤቶች መታደሜን፣ ልዩ የሙዚቃ ቅንብር በቬዬና ማዳመጤን ባወራላቸው እንደማይደነቁ እገምታለሁ። የቻርልስ ዳርዊንን ኦሪጅን ኦፍ ስፒስስ (Origin of Species) እንዲሁም የአልበርት እንስታይንን ሬላቲቭ ቲዮሪ እንደ ሸመደድኩ ብነግራቸው ልባቸው አይከፈትልኝም። ለእነርሱ እውቀትና ጥበብ ከማንነትህ የሚጀምር ተግባር ነው። ከያሬድ ዜማ አንዱን መዝሀ ካላዜምክ ወይም ከተዋናይ ቅኔ አንዱን ፍልስፍና መርጠህ ካልተቀኘህ፣ ወይም ከገዳሙ ሥር የሚፈልቀውን ውሃ ስድስት ሜትር ወደ ላይ የሚገፋ ዘዴ ካላመጣህ፣ ወይም እንደ ሰው የሚቆጥሩትን ዕድሜ ጠገብ የጽድ ዛፍ በቁሙ የሚያደርቀውን በሽታ ለይተህ ካላዳንክ፣ ወይም የተልባ ቆሎ የመሰለ እባብ ቢነድፍህ የትኛውን ቅጠል በጥሰህ ወይም ሥር ምሰህ እራስክን ማዳን እንዳለብህ ካላወክ በእነርሱ ዘንድ ገሌቱ ነህ። በማረሻ ታርሶ የተመረተ እህል ተሸጦ የተገዛ ላፕቶፕ እንግተህ የምዕራቡን ዓለም ጥበብ በጥራዝ ነጠቅ ብታነበንብ አንተ ለእነርሱ ሃዲዱን የሳተ ባቡር ነህ ብዬ ለራሴ ነገርኩትና

"ብዙ የሚባል ዕውቀት እንኳን የለኝም አባ" አልኩ፣

"ባለ ትሕትና ነህ። ለመሆኑ የኛንስ የቤተ ክህነቱን ተምረሃል?" አሉ

"እርፍ! አላልኩህም" አልኩ በልቤ።

"አይ... አልተማርኩም። ብቻ አሁን አሁን እየቆጨኝና ፍቅሩ እያደረብኝ ወደ አማርኛ የተተረጎሙ ድርሳናትን፣ ገድላትንና ሊቃውንት የጻፏቸውን የታሪክና የተግሣጽ መጻሕፍት ማንበብ ጀምሬያለሁ" አልኩኝ።

"ደግና ነው" አሉና "ታዲያ እመኔ ቆላ ምን እግር ጣለህ?" አሉኝ።

"ከፀሎታው በረከት ለማግኘትና ...." አልኩና ሀሳቤን ጎታ አደረኩ፡ የቸኮልኩ መሰለኝ"። እማሆይ ለማንኛውም ጽፌውለዎታል" አልኳቸው።

"አይ የኔ ነገር ከመድረስህ አደከምኩህ ልጄ" አሉና ዳዊታቸውን አንስተው መጣሁ ብለው ሄዱ። የእማሆይን ደብዳቤ ሊያነቡ እንደሆነ ገመትኩ።

አባ አክሊሉ ተጣጥፈው ቁጭ ካሉበት ሲነሱ ረዘም ያለው ተክለ ቁመናቸው ከኋላ ሲታይ ፆምና ስግደት በፍጹም እንዳላዛለው ይናገራል። የመጉበጥም ሆነ የመጎሳቆል ነገር አይታይበትም። ሲሄዱ ቀጥ ብለው ነው። ፊታቸው ቀይ የሚባል ሲሆን ከዐይናቸው አካባቢ ቆዳቸው በመጠኑ የተሸበሸበ ከመሆኑ በስተቀር የጠንካራ ጎልማሳ ፊት ነው። ፀጉራቸው ከምንዝሩና ቆባቸው ተርፎ ሲታይ አልፎ አልፎ ከሚታይ ሽበት በስተቀር የሚያብረቀርቅ ሉጫ ጥቁር ነው። ዓይኖቻቸው ሳም ያሉ ሲሆን ንቃታቸውን ይመሰክራሉ። ሲናገሩ ቃላትን እንደዋዛ ጣል የሚያደርጉ ሲሆን ሰስ ከንፈሮቻቸው ብዙም አይላቀቁም።

አባ አክሊሉ እስኪመለሱ ከተማሪዎቹ ጋር እያወራሁ ብቻ ጥልቅ እያለች የምትሽከረመመውን ፀሐይ መሞቅ ጀመርኩ። አባ ቆይተው እያዜሙ መጡና

“የእኔ ልጅ ዋሻውን ላሳይህ እንሂድ” አሉኝ፡

“እሺ አባቴ!” ብዬ ቀልጠፍ ብዬ ተነሳሁ።

“ንዙን ልጆቹ ያስጠጉታል ተወው” አሉና ተማሪዎቹን የትም እንዳይሄዱ አስጠንቅቀው ወደ ገደሉ ወረድን።

ገደሉ ለወትሮው የይፋት ሜዳን ወለል አድረጎ የሚያሳየው ዛሬ ግን ጥቅጥቅ ባለ ጉም ተሸፍኖ ቢወድቁበት የሚመች ይመስላል። ትንሽ እንደወረድን በእንጨት አጥር የተዘጋ ዋሻ ጋ ደረስን። አባ የእንጨቱን በር ከፈቱና እንድገባ ጋበዙኝ። የሚከብድ ስሜት አለው። ወደ ውስጥ ሲዘልቁ በሰማን ጢስ የጠቆረው በለታማ ጣራና ግድግዳ እንደማንጸባረቅ ይላል። የመታፈን ሽታ እንጅ መጥፎ ጠረን የለውም። ወደ ውስጥ በጣም እየዘለቁ ሲሄዱ የቆሙና የተጋደሙ ያልፈረሱ በርካታ አስከሬኖች ይታያሉ።

ፍርሃቴ መጣ! አባ ግን ከፊቴ አሉ።

“ይኸውልህ የመድኃኔዓለም ተአምር ብዙ ነው። ሰው ሞቶ ሳይፈርስ ሳይበላሽ በቃል ኪዳኑ እንዲህ ይኖራል” አሉና የአንደኛውን ያልፈረሰ ዐፅም ፀጉሩን እየነካኩ ጠጋ ብዬ እንዳየው ጋበዙኝ።

ያለ የሌለ ድፍረቴን አሰባስቤ ጠጋ ብዬ ማየት ጀመርኩ። ግማሾቹ አስከሬኖች በሸራ የተከተቱና ከላይና ከታች የተቋጠሩ ናቸው። እንደዚህ ያለ የፋብሪካ ሸራ በአካባቢው ለአስከሬን መግነዣ አይውልም። በአካባቢው ለመግነዣ የሚጠቀሙት ከላይ ቆዳ ወይም ሰሌን ሆኖ ከውስጥ ሸማ ወይም አቡጀዲ ነው።

“ይህ ጠንካራ የመኪና ሸራ የሚመስል መግነዣ ከየት መጣ?” አልኳቸው ሰራሴ። ጥቂት አስከሬኖች ደግሞ መግነዣቸው ተፈቶ ግድግዳውን ተደግፈው እንዲቆሙ ተደርገዋል።

ከዚህ በፊት መጥቼ የነበር ቢሆንም በፍርሃት ከበር ሆኜ በርቀት ነው ያየሁት። ታዲያ ያን ጊዜ ያስጐበኙኝን ቄስ

"የንማን አስክሬን ነው?" ስላቸው፣

"እይ አናውቅም። ብቻ እልፎ እልፎ ትልቅ ነጭ ገዴ እሞራ መጥቶ ያርፋል። ገበሬዎችም ያዩታል። በበነጋው መጥተን ስናይ አዲስ አስክሬን እናገኛለን" ነበር ያሉን።

እንደገና አስክሬኖቹን ለማየት ሞከርኩ። ተመጣጣኝ ቁመት፣ ወርድና መጠን ያላቸው ናቸው። ነገር ግን የአንድ ዘመን አለመሆናቸውን ከተገነዙበት ሸራ መረዳት ይቻላል። በመደነቅና በመገረም ላይ ቆይቼ ወደ አባ እክሊሉ ዘወር አልኩና

"የንማን አስክሬን ነው? ከየት ነው የሚመጣው? ማን ነውስ የሚያመጣው?" አልኳቸው አከታትዬ።

"የመድኃኒዓለም ጥበብና ቸርነቱ ብዙ ነው" አሉኝና ወደ ዋሻው በር ሄደው ከውጭ በኩል ያለ ለስላሳ ድንጋይ ላይ ተቀመጡ።

እኔም ተከተልኳቸውና ድንጋይ ፈልጌ ከፊት ለፊታቸው ተቀመጥኩ። ከዚህ ሆኖ ወደ ገደሉ ሲመለከቱ ልክ 60ኛ ፎቅ በረንዳ ላይ እንደመቀመጥ ያለ ነው። ከተቀመጥንበት ቦታ ወደታች መውረጃ የምትመስል ቀጭን መንገድ ያየሁ መሰለኝና

"ወደታች መውረድ ይቻላል እንዴ?" አልኳቸው

"እይ አያስወርድም" አሉኝ።

በጣቴ እያመለከትኩ" መንገድ መሰሎኝ እኮ ነው?" አልኳቸው።

ፈገግ አሉና፦ " ከዚህ ትንሽ ወረድ ብሎ ወደ ጐን ሌላ ዋሻ አለ" አሉኝ።

"እንደዚህ አስክሬን ያለበት ነው?" አልኳቸው በመደነቅ

"አይ አይደለም። ያ እንኳን የዋሻ ውስጥ መንገድ ነው" አሉ ዐይን ዐይኔን እያዩ፣

"ወዴት የሚወስድ?!" መቼም ችኩሏ፣ " ለምንድን ነው እራሴን የማልቆጣጠር?" አልኩኝ::

"ወደ ዚህ ዋሻ ጠዋት ጠዋት ሁልጊዜ እመጣለሁ። ከኪዳን በኋላ እየመጣሁ እጥናዋለሁ። ዳዊትም እደግማለሁ። በሥጋ ሙታን ቢመስሉህም ቅዱሳን ሕያዋን ናቸው። ወደ እነሱ እስክሄድ ድረስ እናፍቃለሁ" አሉኝ።

ጥያቄዬን ለመሸሽ የፈለጉ ስለመሰለኝ ተጨማሪ ጥያቄ መጠየቅ አልፈለኩም።

"ማታ ተማሪዎቼን ካስቀፀልኩ በኋላ ሁሉንም እንጫወታለን" አሉኝ።

ፊቴ ወገግ ብሎ "እሺ አባቴ!" አልኩኝ።

ተያይዘን ወደ እቃቤቱ ሄድንና በር ላይ ተቀመጥኩ። ወደ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ሆኗል።

"ትናንት ፍትሐት ነበር እና ትንሽ የተረፈ ነገር ይኖራል" ብለው ወደ ደጀ ሰላሙ ሄድን። ድስት፣ የተከደነ ወራንታ፣ የተዘነበለ እንሥራና የሸክላ ዕቃዎች አሉ። አባ ቀልጠፍ ብለው የእንጀራ ማስቀመጫውን ሲከፍቱ እንጀራ አገኙ፤ ከድስቱ ውስጥ ግን ወጥ አልነበረም። እንሥራውን ሲያዩ ደግሞ ጠላ አለው።

"እንግዲህ ደረቁንም ቢሆን በጠላ እያማግህ ሞክር። ደጀ ሰላም የተገኘ ሁሉም ነገር ይጣፍጣል" ብለው ጸሎት ካደረሱ በኋላ ግማሽ እንጀራ አጥፈው ሰጡኝ። አንድ ተማሪ ደግሞ ጠላ ቀድቶ ሰጠኝ። ሁሉም የድርሻ የድርሻውን ይዞ ተቀመጥን።

አባ ስለ ዓለሙ አስተዳደር ብዙ ብዙ ነገር እየጠየቁኝ እኔ እየመለስኩ መሸና የቅጸላ ሰዓት ደረሰ። አባ ማረፊያየን አሳዩኝና ከመንበራቸው ላይ ባናቸውን ለብሰው ቆሞ አሉ።

እቃ ቤቱ በጭቃና በማገብ ተሰርቶ ጣራው በቆርቆሮ የተከደነ ነው። ጣራው ዙሪያውን ከግድግዳው በእያሊው ሰፋ ያለ ተዛንብ (በረንዳ) አለው። ተዛናቡ በእንጨት ተገርግሮ አንዳንድ እቃዎች ተቀምጠውበታል። ከዚህ ተዛንብ ከእቃ ቤቱ ዋና መግቢያ በር በግራና በቀኝ በጎላ የተደለደሉ ሁለት ቆጦች ማዶ ለማዶ አሉ። አንደኛው የአባ መኝታ ሲሆን ማዶ ያለው ግን ለእንግዳ የተዘጋጀ ነበር መሰል ለእኔ ተሰጠኝ። በመሐሉ ያለው እርቀት የበሩ ስፋት ብቻ ስለሆነ ለመነጋገርና ለመደማመጥ ይቻላል።

ሻንጣዬን እቃው ላይ ሰቅዬ የተማሪዎችን ቅጸላ እከታተል ጀመር። ከምሽቱ ሦስት ሰዓት አካባቢ አባ ሲተነፍሱ የሕመም ድምፅ ያሰሙ ጀመር። አልፎ አልፎ "እሁሁሁ" ይላሉ። ሕመማቸውን የሚታገሉ ይመስላሉ። በእድሜ ከፍ ያለው አንደኛው ተማሪ ቅጸላውን አቁሞ

"የኔታ! ደኅና አይደሉም?" አላቸው። ሁሉም ተማሪ ጸጥ አለ።

"ያ ጠንከኛ ቁርጤ ጀመረኝ" አሉና በረጅሙ አሁንም "እሁሁሁ" አሉ።

ንባቡም ወዲያው ተበተኑና ተማሪዎቹ ወደየማደሪያቸው ሄዱ። አባም ወደ አልጋቸው ወጥተው ቁጭ አሉ። ነገር ግን ሕመማቸው እየበረታ፥ ሲቃቸው እየጨመረ ሄደ እንጂ አልተሻላቸውም።

አልፎ አልፎ ደግሞ "አወይ ሰው መሆን!" ይላሉ። ይወድቁ ይነሱ ጀመር። ላደርግው የምችለው ምንም ነገር አልነበረም። ወዲህ የርሳቸውን ስቃይ ስሰማ ወዲያ ደግሞ ብርዱ፣ ብቻ ምሽቱ ምድራዊ ገሃነም ሆነብኝ። ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት አካባቢ ግን አባ አክሊሉ ወደ እኔ በቀስታ ተጣሩና

"ባትሪ አለህ የኔ ልጅ?" አሉኝ ።

"አዎን! አባ ልስጠዎት?"

"እስኪ አቀብለኝ፤ ልሂድና የሆነ ሥር አምጥቼ ልያዝበት እንጂ ዛሬስ የሚያሳድረኝም አልሆነም" አሉ።

በፍጥነት ወረድኩና ባትሪውን አብርቼ ሰጠኋቸው። እየተንሰፈሰፉ ካሊጋው ወረዱና ባትሪውን ይዘው በሌላ እጃቸው ማግድ ይዘው ወደ ውጭ ሲያመሩ

"ልከተልዎት አባ?" አልኳቸው፤

"ግድ የለም፤ እዚሁ ቆይ" አሉኝ።

"ጅል! የመድኃኒት ሥር ለመማስ እየተሄደ ልከተልዎት ይባላል እንዴ?" አልኩ ራሴን። ትንሽ ቆይተው የሆነ ነገር እያኘኩ ተመለሱ።

"ትንሽ በረድ አለልዎት አባታችን?" አልኳቸው።

"አሁን ትንሽ በረድ አለልኝ። ብቻ መልሶ መነሣቱ አይቀርም እንጅ" አሉ።

"ታዲያ እስከ አሁን መድኃኒቱ እያለ ለምን በስቃይ ቆዩ አባ?" አልኩ።

መልስ የለም። እኔ መቀላመድ አልተው። ብቻ ስቃዩን በጸጋ የተቀበሉት ይመስላል። ፈጣሪን ሲያማርሩም ሆነ እድላቸውን ሲረግሙ አልሰማሁም። አልፎ አልፎ ብቻ ፡- "አወይ ሰው መሆን" ይላሉ።

ሊነጋ ሲል የብርዱን ስቃይ ተቋቁሜ እንቅልፍ ሸለብ አደረገኝ። ሰነቃ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ከሩብ ሆኗል፤ አባ የሉም። እየተጨማደድኩ ተነስቼ ወደ ቤተክርሲያን ስሄድ አባ ኪዳን እያደረሱ አገኘኋቸው። በጣም ተደነቅሁ። "ወይ የሰው ልጅ ጥንካሬ!" አልኩ።

ኪዳን ሲያልቅ አንድ ዲያቆን አስከትለው ወደ ዋሻው ሲወርዱ ሲሉ ጠብቄ

"አባ እንዴት አደሩ?" አልኳቸው፤

"መድኃኔዓለም ከብሩ ይስፋ ደኅና ነኝ" አሉ። ፊታቸው ግን አበጥ ብሏል።

"አባ ዘላቂ ህክምና ካላገኙ በዚህ ሁኔታ የሚቀጥሉ አይመስለኝም" አልኳቸው።

"አስወልቄው ካላረፍኩ መቼ ይሆናል ብለህ ነው" አሉ ።

"እኮ! ሐኪም ዘንድ እንሂድና ዛሬ ቢያስወልቁት ጥሩ ነው። ምክንያቱም እንደታመመ ሲሆን ይሻላል" አልኳቸው።

"እይ ልጄ! ቤተ ክርስቲያኑን ለማን ትቼ? ተማሪዎቼንስ ትቼ እንዴት እሄዳለሁ?" አሉ።

"እንዴ! ከሁለት ከሦስት ቀን በላይ አይፈጅም፤ ወይ መሐል ሜዳ አለዚያ ደብረ ብርሃን ብንሔድ ነው፤ እሩቅ አይሄዱም። እኔም የመድኃኔዓለም ፈቃድ ሆኖ ነው የመጣሁትና ሁሉንም የሚያስፈልገውን እኔ አዘጋጃለሁ" አልኳቸው።

"ተባረክ ልጄ! እስቲ ለማንኛውም ታች ወርጄ ልምጣ" ብለው ወደ ቀሻው አመሩ።

ዲያቆኑ ወደ ኋላ ቀረት አለና፡

"አለቃውን ይንገሯቸው እንጂ፤ እሳቸው እንኳ በጄ አይሉም" አለኝ

"ማናቸው አለቃው? የት አገኛቸዋለሁ?" አልኩት

"ርእሰ ደብር ዲበኩሉ ይባላሉ፤ ተቅኔ ማኅሌቱ ጸሎት እያደረጉ ያገኙቸዋል" አለኝ

"እመሰግናለሁ" ብዬ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ዘለቅሁ።

ርዕሰ ደብር ዲበኩሉ ጸሎታቸውን እስኪጨርሱ ጠብቄ ተሳለምኩና ጓሳ አካባቢ ለምርምር እንደመጣሁ፡ እዚህ ቤተክርስቲያን ግን ለመሳለምና በረከት ለማግኘት ትናንት መጥቼ አባ አክሊሉ ዘንድ እንዳደርኩ ባጭሩ ነግሬ

"አባታችን ትናንት በጣም ታምመው ነው ያደሩት። ምን እንደ ማለኝ ብዬ እኔም እብሬ ስስቃይ አደርኩ" አልኳቸው።

"እይይይ! ያው ጠንከኛ ጥርስ ቁርጥማት ይሆናል!? መቼም አንድ ቀን ጉድ ሳይሠራን አይቀርም። አባቴን! አባቴን!" አለ። የልብ ሐዘን ይመስላል።

"እንዳስተዋልኩት ጥርሳቸው መውለቅ አለበት። እና ደብረ ብርሃን ቢሄዱ ሆስፒታል ወይም የግል ደንና ሕክምና አይጠፋም። አስወልቀው በዚያውም ሴላም ምርመራ አድርገው ቢመጡ ጥሩ ነው" አልኳቸው።

"አረ እሱማ ማለፊያ ነገር ነበር እንጅ፣ ብቻ..." ሲሉ

"ግድየለም። ይህ ለእኔ ፈጣሪ በረከት እንዳገኝበት ያመቻቸው ይሆናል። ሙሉ ወጪቸውን ችዬ አሳክሜ መልሼ እዚሁ ቦታቸው ድረስ እመልሳቸዋለሁ" አልኩ።

"የመጣህበት ሥራህስ ልጂ?" አለ

"ግድየለም ይደርሳል፤ ቀስ ብዬ የምሠራው ነው። ብቻ አባታችን አግባብተው እንዲሄዱ ያድርጉ። በዚህ ሁላችን ከጸጸት እንድናለን" አልኩ።

ርእሰ ደብር ዲበኩሉ እጂግ ቀና ሰው ነበሩና "ይኸማ ማለፊያ ነገር ነው እንጅ ልጂ" ብለው አባ አክሊሉ እንዲመጡ ተማሪ ላኩ። አባ አክሊሉ ከዋሻው ሲመለሱ በጣም ተዳክመው ነበር። ከርእሰ ደብር ጋር ስላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ርእሰ ደብር እንዲህ አሉ፥

"አባታችን ይኸ በሽታ እያሰቃየ አንድ ነገር ቢሆኑ በኋላ ጸጸቱ ለእኛ ነው። ይህ ወንድማችን ደብረ ብርሃን ወስጂ አሳክማችዋለሁ ብሏልና እበጡ ሳይጉድል ዛሬ መሄድ አለብዎት" አሉ ጠንከር ብለው።

"እንዲሁ ተነሥቶ ይኬዳል?" አሉ አባ አክሊሉ፥

ሻእቃ ቤቱ ቁልፍ ከእርስዎ ጋር ይሁን። እዚህ ለጥበቃው ገዘሁን ልኬበታለሁ እርሱ ይጠላል ያድራል። እኔም ብቅ እያልኩ እጎበኘዋለሁ። ደግሞስ ምን ያክል ቀን እንዳልቆዩ ነው?" አለ ርእሰ ደብር።

"እንዲያው እስቲ ትንሽ ቀን ልየው?" አሉ፤አባ አክሊሉ መልሰው።

"አባታችን በመድኃኔዓለም ይዥዎታለሁ። የትናንቱን አዳርዎን ረስተው እንዲህ ይላሉ። ሁሉ ነገር እኮ ቀላል ነው። ለእኔም አሚቸግረኝ ነገር የለም እና እባክዎት እሽ ይበሉ" አልኩ።

አባ ብዙ ከአንገራገሩ በኋላ ርእሰ ደብርም፣ ገበዙም፣ ጠና ያሉ ተማሪዎችም ሲለምኗቸው ሀሳቡን መቀበላቸውን በሚያመላክት አነጋገር "ታዲያ ነገ ጠዋት አይሻልም?" አሉ።

"የለም፤ መኪና ካገኘን ዛሬ እንሞክር። ለለበለዚያ ያው ነገ ይሆናል። ለማንኛውም መኪናው መንገድ ዳር ቆሎ እንውጣ" አልኩና በትኩሱ ገፋፋሁ።

አባ ጫናው ሲበዛባቸው ትንሽ ቦርሳ መሳይ አዘጋጅተው ከወይባቸው ሥር እንጠልጥለው በርእሰ ደብርና በተማሪዎቻቸው ታጅበን ወደ መንገድ ዳር ወጣን። ግማሽ ሰዓት ያህል ቆመን እንደጠበቅን የሰሜን ሸዋ ዞን ግብርና መምሪያ ደብል ካቢን ቶዮታ መኪና ጸረ ሰብል ተባይ መድኃኒት መሳል ሜዳ አድርሶ ባዶውን ሲመለስ ሁላችንም እጆቻችንን ጭራር እስመስለን በንለምነው ጊዜ አቁሞ አሳፈረን።

ከዚህ በኋላ ይህን ሁሉ ማድረጌና የእርሳቸውም እሽ ብሎ መሔድ ለዓላማዬ ያለውን አስተዋጽዖ ባሰብም በመንገድም ይሁን በቆይታችን ስለመጣሁበት ጉዳይ አባን ማነጋገርም ሆነ ርዕሱን እንስቼ መጠየቅ እንደሌለብኝ ግን ወሰንኩ። ምክንያቱም ላላከም ብሎ እምቀቼ የሞራል ጫና ሊፈጥርባቸው አይገባምና።

የተባረከው ሹፌር ምንም ገንዘብ ሳይጠይቅ አባፍሮ ከወሰደን በኋላ ደብረ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን በር ላይ አወረደን።

እኔም አመስግኜ እባም መርቀውት ወደ ቤተክርስቲያን ዘልቀን ቀኀሉመን ሰናበቃ አንድ ጥግ ላይ ዐረፍ እንዳልን

'አቢታችን ሰው የማይደፍጠበት ስል በረጉ ፈልጌ ከዛ ብናድርስ' አልኳቸው።

'የኔ ልጅ እኔ እዚህ አንድ ጥግ ከቤተክርስቲያኑ አድራለሁ። ባይሆን ለአንተ ሳይመሽ ፈልግ' አሉኝ። የጠበኩት መልስ ነበር። መጣሁ ብዬ ወደ ዐውደ ምሕረቱ ዘለቅሁ። አባቶችም፣ እናቶችም፣ ወጣቶችም የግል ጸሎት ለማድረስና ሰዓምታ ለመሰጣጣት ውር ውር ይላሉ። በዐይኔ ትንሽ አማተርኩና በሴቶቹ መግቢያ በኩል ቆሞ ካሉት ታላላቅ እናቶች መካከል አንዳቸው ላይ ዐይኔ ዐረፈ። አለባበሳቸውና ሁሉ ነገራቸው ደግና ነዋሪ ይመስላሉ።

ጠጋ ብዬ፣ "ጤና ይስጥልኝ እሚይቴ፣ እንደምን ዋሉ?" አልኩ

"እግዚር ይመስገን። ማነህ?" አሉኝ የቀኝ እጃቸውን ቅንድቦቻቸው ላይ ጋረድ አድርገውና ዐይናቸውን እኔ ላይ ተክለው ለመለየት እየሞከሩ።

"አይ እንግዳ ነኝ አያውቁኝም። አንድ ነገር ቸግሮኝ ላማክረዎት ነበር?" አልኩ።

"ምንድን ነው የኔ ልጅ? ደኅናም አደለህ?" አሉ በእናትነት ለዛ ።

"አንድ ትልቅ የገዳም አባት ከመንዝ ለሕክምና ይዤ መጥቼ ነበር። ያው ገዳማዊ በመሆናቸው አሊቤርጎ ልያዝልዎት ብል አይሆንም እዚህ ቤተክርስቲያን ግቢ ነው የማድር አሉ። ደግሞ ሕመማቸው ጥርስ ቁርጥማት ስለሆነ ብርዱን አይችሉትም እና..." አልኩና

"ትልቅ ሰው መሆንዎን አይቼ ነውና፣ እንዲያው የማይቸገሩ ከሆነ እርስዎ ቤት ወስደው ቢያሳድሩልኝ? ጠዋት መጥቼ እወስዳቸው ነበር" አልኩ እየተቅለሰለስኩ።

"አረ ምን ክፉ ሰው ነህ ልጄ፣ ቤት የአግቤርም አዶሉ። ያውም የገዳም አባት ተገኝቶ ነው። በረከት ነው እንጅ ደግሞ የምን ችግር? የት ነው ያሉትን" ብለው ምርኩዛቸውን ይዘው ብድግ አሉ።

ከአባ ጋር አስተዋውቂያቸው በመስቀል ከተባረኩ በኋላ፦ "አባታችን እኔ ቤት ያድራሉ። የትልቅ ሰው ቤት ነው" አሉ እማማ።

አባ ትንሽ አቅማምተው እሺ ስላሉን ሴትዮዋን ተከትለን ወደ ቤታቸው ሄድን። እንደገመትኩት ሰፊ ግቢ ከኋላ ሰርቪስ ያለው የጭር ቪላ ነው። ሳሎን ገብተን እንደተቀመጥን ወይዘሮዋ አንድ ክፍል ሰብቻቸው እንዲዘጋጅላቸው፣ ለእግራቸው ውሃ እንዲሞቅ፣ ምግብም እንዲቀርብ ቤተሰቡን ያጣድፉት ጀመር።

"እመይቴ የአባን ማረፊያ ካገኘሁ፣ እኔ ልሂድና አሲቤርጐ ልያዝ፣ ሕክምናውንም ላመቻች" ብዬ ብድግ ስል

"አይሆንም። እራት መብላት አለብህ፣ መኝታህም ቢሆን እዚህ ይዘጋጃል" አሉ።

በመጨረሻ ባይሆን "እራት ልብላ፣ መኝታውን ግን አልቤርጎ እይዛለሁ። በዚያውም ሕክምናውን ለማመቻቸትም ይመቸኛል" ብዬ እራት በልቼ ጠዋት እንደምመጣ ለአባ ነግሬ ወጣሁ። በፍጥነት አልቤርጎ ከያዝኩ በኋላ የግል የጥርስ ሕክምና ስለመኖሩና ስለሕክምናው ጥራት መረጃ እየተዘዋወርኩ ሰበሰብኩ። በማግስቱ ጠዋት የተጠቆምኩት ዶክተር መግቢቱን እረጋግጬ ማታ ወደ መረጥኩት የግል የጥርስ ሕክምና ክሊኒክ አባን በኮንትራት ባጃጅ ወሰድኳቸው።

ካርድ ስናወጣ ነርሷ፦

"ስም ማን ልበል?"

"አባ አክሊሉ" አልኩ እኔ ተሽቀዳድሜ።

"የአባት ስም?" አለች

"አባ አክሊሉ ይበቃል የኔ ልጅ፣" አሉ አባ።

የአባታቸው ስም ምናልባት የመጡበትን ቦታና አካባቢ ሊጠቁም ስለሚችል ይሆናል። መናኙ የመጣበትን ማሳወቅ አይፈልግም። ወደፊት እንጅ ወደ ኋላ መመልከት የለም። ነርሷም ፈገግ አለችና "ግድየለም" ብላ እድሜና አድራሻ ከጠየቀች በኋላ አረፍ እንድንል ጠይቃን ካርዱን ይዛ ወደ ዶክተሩ ገባች።

የቀደመን ሰው ስላልነበረ በሩን ከፍታ "ግቡ" አለች። ዶክተሩ ሰላምታ ሰጥቶ አንድ አንድ መሠረታዊ ጥያቄ ከጠየቃቸው በኋላ አፋቸውን ከፍቶ ማየት ጀመረ።

"Oh! already decayed!" አለ በእንግሊዝኛ፤ ወንበሩ ላይ ቁጭ እያለ።

"በስብሰማ ነው ስቃዬን የሚያሳየኝ። እንዲያው እባክህ ልጄ ነቅለህ ገላግለኝ!" አሉ አባ።

ዶክተሩና እኔ በአግራሞት ተያየን።

"አባ! እንግሊዝኛ ያውቃሉ እንዴ?" አለ ዶክተሩ በትሕትናና በአድናቆት።

"እና ቢወልቅልኝ አይሻልም?" አሉ አባ ማወቃቸውን ለመደበቅና ጥያቄውን ለመሸሽ በሚያስመስል አነጋገር።

ዶክተሩ ፈገግ ብሎ

"ችግር የለም በቀላሉ ይነቀላል። ኢንፌክሽን እንዳይፍጥር ደግሞ ተገቢውን መድኃኒት እዛለሁ። በሦስት ቀን ሙሉ ጤነኛ ይሆናሉ" ብሎ አረጋጋቸው።

ከመነቀሉ በፊት ስኳርና የደም ግፊታቸው ተለካ። ሁሉም ነገር ሙያዊ በሆነ መልኩ ቅድመ ዝግጅት ተደርጐ ጥርሳቸው ተነቀለ። ዶክተሩን አመስግኜ ቢት ቃል ባስገቡኝ መሠረት ያሳደጉቸው እናት ዘንድ ወሰድኳቸው። ሾርባ ሰርተው ጠበቁን። በዚህ ሁኔታ ደብረ ብርሃን ከአባ ጋር አራት ቀን ቆየን።

አንድ ቀን ከተማ ቆይቼ አባ ከተኙበት ክፍል ድንገት ዘው ብዬ ስገባ ከታዘዘላቸው መድኃኒት ጋር ውስጥ በእንግሊዝኛ የተጻፈውንና የመድኃኒቱን ሥሪትና ማስገንዘቢያ የያዘውን ወረቀት የንባብ መነጽራቸውን አድርገው በሥነ ሥርዓት ሲያነቡ ደረስኩ። ድንገት ስለነበረ የደረስኩት እያነበቡ ማየቴን ማስተባበል እንደማይችሉና የእኔንም መደነቅ ሲያዩ ቀና አሉና ፈገግ ብለው

"እኔም እንዳንተ አውሮፓ ውስጥ ተምሬያለሁ እኮ" አሉ ቀልድ በሚመስል ሁኔታ።

"ምን?" አልኩኝ የበለጠ በመገርም

"አዎን። ጀርመን ሀገር ሀምቡርግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት የኬሚካል ምሕንድስና ተማሪ ነበርኩ" አሉ ፈገግ እንዳሉ።

ጭራሽ ግራ ገባኝና "ታዲያ እንዴት ነው...?" የምለው ሁሉ ጠፋብኝ።

"የጀስዊቶች ማኅበር አባል የነበረ አንድ ጀርመናዊ ጓደኛ ነበረኝ። በአጋጣሚ ትምህርቴን ወደ ማጠናቀቅ ስደረስ ከዚሁ ጀርመናዊ ጋር በነበረኝ ቅርርብ የሕይወቴን አቅጣጫ የሚያስቀይር ምሥጢር ማወቅ ቻልኩ። እናም የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆነና ወደ ሀገሬ ተመለስኩ" ብለው በሃሳብ ጭልጥ አሉ።

"ምንድን ነበር የደረሱበት ምሥጢር?" አልኳቸው በውትወታ መልክ። የእኔን ውትወታ ዝሽሽ አድርገው በትዝታ ባሕር ሰጥመው ቆዩ።

በደብረ ብረሃን ቆይታችን የአባ አክሊሉን ግለ ታሪክ በከፊል ማወቁ ተጨማሪ የአእምሮ ሥራ ሆኖብኝ ሰነበተ። "መቼም ልፋ ያለው በሕልሙ ዳውላ ይሸከማል" የሚሉት ዓይነት ሆነና "ምን ምሥጢር ቢያውቁ ይሆን እንደዚህ ያለ ቆራጥ ውሳኔ ላይ የደረሱት። መቼም የቅዱሱን ጽዋ ምሥጢር መሆን አለበት" እያልኩ ሳስብ ሰነበትኩ።

ለዘመናት በምሥጢር ጠባቂነት ተቆልፎ የኖረውን የአባ አክሊሉን ልብ ለማስከፈት መሞከር ሞኝነት መሆኑን ተረድቼ ወደ ራሴ ሕይወት ተመለስኩ።

"አባ አክሊሉን ከአውሮፓ ሕይዎት ከምሕንድስና ሙያ አስወጥቶ ያስመነኑ ምን ዓይነት የሕይወት ግብና ዓላማ ይሆን? ይህንንስ ለመቀበል የተዘጋጀ ሰብእና እንዴት ይገነባ ይሆን? ለመሆኑ እኔ እንዲህ ሁሉን እርግፍ አድርጌ የምተውለት ሲጸናም መሥዋዕትነት የምከፍልለት የሕይዎት ግብና ተልዕኮ (Life Purpose and Mission) አለኝን? ንበዝ መሐንዲስ ሳይ እሱን መሆን ያምረኛል፤ ታታሪ ሐኪም ሳይ በሱ እቀናለሁ፤ ሀብት ያካበተ ኢንቨስተር ሳይ በእርሱ እማልላለሁ፤ ጥሩ ድርሰት ሳነብ ደራሲ መሆን ያሰኘኛል፤ የሳይንስ ምርምር ግኝት ስሰማ ምነው እኔ በሆንኩ እላለሁ፤ በርቱዕ አንደበቱና በዲስኩሩ የብዙዎችን ቀልብ የሚገዛ ፖለቲከኛ ሲያጋጥመኝ በእርሱ ደስ ይለኛል። እንደ አባ አክሊሉ ያለ መናኝ ሳይም ምና አባቱ ዓለም ብዬ እማረካለሁ። ያም ሆኖ የማውቀው ሃይማኖታዊ ወይም ፖለቲካዊ ወይም ሙያዊ የሆነ የምኖርለት ክፍ ሲልም መሥዋዕትነት የምከፍልለት የሕይዎት ጥሪ እንዳላዳበርኩ ተሰማኝ። በጥቅሉ ሕይዎቴን ባስበው ነፋስ ወደላይ አንስቶ ወደፈለገበት አቅጣጫ እንደሚገፋት ብጫቂ ወረቀት ሁና ታየችኝና ልንባ ሀይኖቼን ሲሞላቸው ታወቀኝ።

አባ አክሊሉን ያስመነነውን ምሥጢር ለማወቅ ያደረኩት ተደጋጋሚ ሙከራ ባይሳካም በቆይታችን በተዘዋዋሪ መንገድ በርከት ያሉ የሙያ ቋንቋዎችን እንደሚያውቁ እንዲሁም ዝቋላ አቦ ገዳም አገልግለው እንዳደጉና በኋላ በጊምድር አምበትያ ተክለሃይማኖት ገዳም ምንኩስና ተቀብለው ዐሥራ ስድስት ዓመት እንደቆዩ፤ ከዚያም በአባቶች ትእዛዝ ወደ ደንም እርባ ሄራ መድኃኔዓለም ከመጡ ሃያ ሁለት ዓመታቸው እንደሆነ ለማወቅ ቻልኩ። በእምስተኛ ቀናችን ተሰናብተናቸው ወደ መንዝ በደግና ተመለስን።

# ምዕራፍ ዐሥራ አምስት

ከአባ አክሊሉ ጋር ወደ መንዝ አርባ ሃራ መድኃኒዓለም እንደተመለስን ወዲያውኑ የመጣሁበትን ጉዳይ እንስቼ መወያየቱ አልታደለህ አለኝ። አባ አክሊሉ በሕመም ምክንያት ወደ ደብረ ብርሃን እንደሄዱ ስለሚታወቅ በርካታ ምእመናን እንኳን ደኅና መጡ ለማለት መጉረፋቸው አይቀርም። በዚህ መሐል ትኩረት መሳብና እሳቸውንም ማጨናነቅ አልፈለግሁም። ስለዚህ አንድ ሁለት ቀን በአቅራቢያው ወደ ሚገኘው ጓሳ መገራ ፓርክ ለማሳለፍ ሄድኩ።

ጓሳ መገራ ከአዲስ አበባ 288 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ በመንዝ ጌራ ምድር ወረዳ ውስጥ የሚገኝ ለዘመናት በኅብረተሰቡ ሲጠበቅ የኖረ የተራራ ሥነ ምሕዳር ያለው ስፍራ ነው።

"አገሬ ጓሳ መገራ አገሬ ጓሳ መገራ፤

ምነው አልሰማ አለች ብጣራ ብጣራ"

ተብሎ የተዘፈነለት አካባቢ ነው። የዘፈኑ መልእክትም መንዜዎች ኩሩ ስለሆኑ ጠርተሃት የምትመጣልህ አይደለችም፤ ምናልባት ሄደህ ደጅ ጠንተህ ልታገኛት ብትችል እንጂ ለማለት ይሆናል።

አጠቃላይ የፓርኩ ስፋት 10000 ሄክታር አካባቢ ሲሆን ከፍታው ከባህር ጠለል በላይ ከ3200 እስከ 3600 ሜትር ላይ ይገኛል። አካባቢው ጓሳ በሚባል ሳር በተፈጥሮ የተሸፈነ በመሆኑ መሬቱ እንደስፖንጅ ሲረግጡት ይመቻል።

የሣሩ ባሕርይ በዓመት ከ1400 ሚሜ በላይ የሚዘንበውን ዝናብ ወደ ውስጥ በማስረግና እንደ ስፖንጅ መጥጦ መያዝ ስለሚያስችለው ከአካባቢው እርጥበት እንዳይጠፋ ከማድረጉም በላይ እንደ ደፋትና ሸዋ ሮቢት ላሉት የአካባቢው ዝቅተኛ ቦታዎች ዓመቱን በሙሉ የማያቋርጥ የምንጭና ወንዞች ፍሰት እንዲኖር ያደረጋል። ለከ ከተሞች በቤታቸው ጣራ ላይ የውሃ ማጠራቀሚያ ጋን ሰቅለው በቂ የውሃ ግፊት ባለበት ሰዓት ይሞሉና ግፊቱ በሚቀንስበት ወቅት ከጋናቸው እየቀዱ እንደሚጠቀሙ ሁሉ ጉና መገራም ተራራ ላይ ያለ የተፈጥሮ የውሃ ጋን ነው። መንዞች ለዘመናት ይህንን ምሥጢሩን ስለሚያውቁ ጉናውን ጠብቀው ተንከባክበው እስከአሁን አቆይተውታል። ሌሎች እንደዚህ ዓይነት ሥነ ምሕዳሮች ያሏቸው እንደ ጉና ተራራ፣ የባሌ ተራሮችና ራስ ዳሽን የመሳሰሉት በዙሪያቸው ያሉትን አካባቢዎች በዚሁ መንገድ ይጠብቃሉ። ያለ ጉና ተራራ ጣናን ማሰብ ያለ ጣና ደግሞ ዐባይንም ማሰብ ያዳግታል፤ አካባቢውም እንዳለ በረሃማ ይሆን ነበርና።

ፓርኩ የበርካታ ብዝሃ ሕይወት መገኛ ሲሆን ከዕፅዋት መካከል በተጠንቀቅ የቆሙ የእንግሊዝ ቤተ መንግሥት የክብር ዘቦችን የሚመስለው ጅብራ (Giant Lobelia) በብዛት የሚገኝበት ሲሆን ከእንስሳት መካከል ደግሞ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙት ብርቅዬዎቹ ቀይ ቀበሮዎችና ጭላዳ ዝንጀሮዎች እንዲሁም ታይተው የማይጠገቡ በርካታ አዕዋፍ ይኖሩበታል።

በፓርኩ ውስጥ ማኅበረሰቡ ተደራጅቶ የሚያስተዳድረው ውብ ባህላዊ ማረፊያ ሎጅ አለ። ምግብም አሰናድተው ከሚጣፍጠው አማርኛቸው ጋር ፤

"ምን ሆንህ? ብላይ ። ምሳህም አዶል?" እያሉ ያስተናግዳሉ።

ካሉት ማረፊያ ክፍሎች አንዱን ተከራይቼ ሻንጣዬን ካስቀመጥኩ በኋላ ወደ ውጭ ወጥቼ አካባቢውን ስቃኝ አንድ ጎልማሳ ሰውና አምስት ወጣቶች ቁጭ ብለው ግማሾቹ እየጻፉ ቀሪዎቹ ደግሞ ቀጫጭን ቱቦ መሳይ ጠርሙሶችን እያደራጁ (የምርምር ናሙና መውሰጃ ይመስላሉ) ተመለከትኩ። ጎልማሳው ሀበሻ ሲሆን ከወጣቶቹ መካከል ሦስቱ ፈረንጆችና ሁለቱ ደግሞ ሀበሾች ናቸው።

ጠጋ ብዬ ሰላምታ አቅርቤ ራሴን አስተዋወቅሁ። ጎልማሳው ሰውዬ ከመቀመጫቸው ተነሥተው በፈገግታ ዶክተር ዘመድኩን እባላለሁ ከአስትራሊያ ሲዲና ዩኒቨርሲቲ ነው የመጣነው። እነዚህ ተማሪዎቼ ናቸው ብለው አንድ በአንድ አስተዋወቁኝና

"ከዚህ የመጣነው የምርምር ሥራ ለመሥራት ነው" አለ።

"በምን መስክ ነው ምርምራችሁ?" አልኩ።

"እኔ የባዮሎጂ ፕሮፌሰር ነኝ። ከዚህ የመጣነው ቀይ ቀበሮዎች ላይ ጥናት ለማድረግ ነው" አለ

"እው! ደስ ይላል። ታዲያ ቀይ ቀበሮዎች ላይ ምንድን ነው የምታጠኑት?" አልኩ ቀጥዬ።

"ምን መሰለህ። አልፎ አልፎ ቀበሮዎች ሞተው ይገኛሉ። እንዳንዴ መደዳውን በብዛት ይሞታሉ። የሞታቸው መንሥኤ ደግሞ መርዝ ነው።" አሉ።

"መርዝ ማለት  እንዴት?" አልኩኝ ፈጠን ብዬ።

"የተመረዘ ሥጋ ወይም እንስሳ በልተዋል ማለት ነው" አሉ።

"እንዴ ማነው የሚመርዛቸው። የአካባቢው ሕዝብ ደግሞ ለዘመናት ጋርኩንም እነርሱንም ጠብቆ እንደኖረ ነው የሰማሁት "አልኩኝ።

"ልክ ነው። የኛም የጥናት ነጥብ የሞታቸው መንሥኤ መርዝ ከሆነ እንዴትና በማን ተመረዙ የሚለውን ማወቅ ነበር"።

"እና  አወቃችሁት?"

"ወደ ማወቁ ተቃርበናል"።

"ምን ሆነ ምክንያቱ ማለቴ መነሻው?" አልኩኝ መላ አካሌን ወደ እርሳቸው አዙሬ፣

"ከፓርኩ አቅራቢያ የሚኖሩ አርሶ አደሮች የሰንደል የገብስ ሰብላቸውን ከአይጥ ለመከላከል በማሳቸው ዳር መርዝ ያስቀምጣሉ። አይጦቹ መርዙን ይበሉና ወደ ጉድጓዳቸው ከመግባታቸው በፊት ሜዳ ላይ ይሞታሉ። ይሄኔ ሥጋ በል የሆኑት አሞራዎችና ጭልፊቶች ተናጥቀው ይዘው ወደ ፓርኩ ይመጡና ይበላሉ። በመርዙ ምክንያት እነርሱም ወዲው ይሞታሉ። ቀበሮዎቹ የሞቱትን አሞራዎች ወዲያው ይመገባሉ። ልብ በል። አርሶ አደሮቹ ለአይጦቹ የሚያስቀምጡት የመርዝ መጠን በጣም ትንሽ ነው። ይሁን እንጅ አይጦቹ ሲመገቡት የመርዙ መጠን በአይጦቹ አካል ልክ ያድጋል። ከአንዲት የተመረዘች አይጥ ክፍል ውስጥ ትንሽም ቢሆን የቀመሰ አሞራ ይመረዛል። እንዲሁ አሞራው መርዙን ከተመገበ በኋላ የመርዝ መጠኑ በአሞራው አካል ልክ ይሆናል ማለት ነው። ይህ መርዝ በምግብ ሰንሰለት ውስጥ ሲያልፍ የመግዘፍ ሂደት ‹ባዮሎጅካል ማግኒፊኬሽን› እንለዋለን። በዚህ የተነሣ ጥቂት ሆኖ ከአረሶ አደሩ ማሳ የተነሳው መርዝ ገዝፎና ተራብቶ ከፓርኩ መከከል ይደርስና ለብዙ ብርቅዬ ቀይ ቀበሮዎችና ሌሎች እንስሳት ሞት ምክንያት ይሆናል" አለኝ።

"በጣም ይደንቃል። በቲዎሪ የምናውቀው በተግባር መከሰቱ ያሳዝናል። ትንሽ ነው እያልን በየቦታው የምንጥለው ቆሻሻና ፍሳሽ በንቱን ይሆን የሚያዳርሰው ? በዚህ ዓይነትማ በእኛ ግዴለሽነት ወደፊት ብዙ መከራ ይጠብቀናል ማለት ነው?" አልኩኝ ከልብ በመነጨ ቁጭት።

"አዎን! የአካባቢ ብክለት መነሻውን እንጅ መድረሻውን መገመት ከባድ ነው። የመርዝና የቆሻሻ ትንሽ የለውም" አሉ ጠንከር ብለው ራሳቸውን እየነቀነቁ፡

"ይህንን ግኝታችሁን ለአካባቢው ማኅበረሰብና ግብርና ጽ/ቤት ብታሳውቁ መልካም ነው" የሚል ሀሳብ ሰነዘርኩ።

"አዎን ጥናታችንን እንዳጠናቀቅን የአንድ ቀን ስሚናር እናዘጋጃለን" አሉኝ።

ዶክተሩንና ተማሪዎቹን አመሰግኜ ብቻዬን ፓርኩን እየተዘዋወርኩ ለመጎብኘት ሄድኩ። ንፋሱ ጓሳውን ሲያስተኛውና ሲያቃናው ከሚሰማው ለስላሳ ፉጨትና አልፎ አልፎ ከሚሰማው የዝንጀሮዎችና የአዕዋፍ እንዲሁም ወደ ማታና ሌሊት ከሚሰማው የቀበሮዎች ጩኸት በስተቀር ሰላም በጸጥታ ታጅባ ነግሳበታለች። የከተማ ውዥንብር፣ ንትርክ፣ ውካታና ግርግር ያሰለቸው ሰው መንፈሱን ጸጥታ ለመመገብ ከፈለገ ስፍራው መንዝ ጓሳ መገራ ፓርክ ነው። ይህ ቦታ ዓለም በየሴኮንዱ ከምትናጥበት ውስብስብ ጉዳዮች ቀልቧን ገዝታ ወደ ልቦናዋ ተመልሳ ከምትረጋጋባቸው ቦታዎች አንዱ ነው።

እጅግ አስደሳች የሁለት ቀን የጸጥታ ጊዜ በፓርኩ ካሳለፍኩ በኋላ ከአባ አክሊሉ ጋር የሀሳብ ፍልሚያ አድርጌ ፍንጭ ለማግኘት እንደገና ወደ አርባ ሃራ ቤተክርስቲያን ተመለስኩ። ከሰዓት በኋላ ወደ ስምንት ሰዓት አካባቢ ከቤተክርስቲያኑ ደረስኩ። እንደተለመደው አባን ከተማሪዎቻቸው ጋር ከዕቃ ቤቱ በር ላይ አገኘኋቸው። ትልቅና ዕድሜ ጠገብ የሚመስል የብራና መጽሐፍ ከአትሮንስ ላይ አድርገው እያነበቡ ነበርና ቀና ብለው በፈገግታ ተቀበሉኝ። ተማሪዎቹ በሙሉ ሞቅ ያለ አቀባበል አደረጉልኝ። አባም ፍጹም ተሽሏቸው ነበር።

ተማሪዎቻቸው መምህራቸውን ወስጄ በማሳከሜ ይመስላል ፍጹም በቤተሰባዊ ፍቅርና እንክብካቤ ይመግቡኝ ጀመር። ከአባ ጋር የአባትና የልጅ ዓይነት ወጋችንን ስንሰልቅ አምሽተን የጉባኤ ሰዓት ደረሰና ትምህርት ተጀመረ። ሁሉንም በትዕግሥት መያዝ እንዳለብኝ ስለተረዳሁ ጉባኤውን ስከታተል አምሽቼ ወደ መኝታችን ስንሄድ ጉዳዩ ከአባ ከራሳቸው ይምጣ በማለት በዝምታ የሚጠይቁኝን ብቻ እየመለስኩ አምሽተን ወደ እኩለ ሌሊት ደኅና እደር ብለውኝ ወደ ተለመደው የንዋም ጸሎታቸው ገቡ።

ጠዋት ለኪዳን ሲነሱ አብሬ ተነስቼ ወደ ቤተክርስቲያን ሄድኩ። እንደተለመደው ኪዳኑ ሲያልቅ አባ ማዕጠንታቸውን ይዘው ወደ ዋሻው ወረዱ። እኔም ተከትዬ ሄድኩ። አጥነው እንደጨረሱ ከዋሻው በር በስተውጭ ካለች ጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ ሄደው ዐረፍ አሉ። እኔም ከፊት ለፊታቸው ሄጄ ቁጭ አልኩ።

ፈገግ ብለው ካዩኝ በኋላ

"ይህ ቦታው ከ፱ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት እንደተመሠረተና በኋላም ከግብጽ በመጡና አቡነ ሐራ በተባሉ ጻድቅ እንደተስፋፋ ይነገራል። ስለዚህ በስንክሳር ላይ የተገለጹት የዐርባው ሰማዕታት መታሰቢያ ሆኖ ተመሥርቶ ሊሆን ይችላል፤ ለአንተ ይኸው ሊበቃህ ይችላል።"

"ከጊዜ በኋላ ቦታው የቅዱሳን ዐፅም ማረፊያ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ምስካበ ቅዱሳን አርባ ሃራ መድኃኔዓለም ተብሎ ተጠራ። ምስካበ ቅዱሳን ማለት የቅዱሳን ማረፊያ ማለት ነው" አሉና ትንሽ ዐረፍ ብለው እንደገና ቀጠሉ።

"እና ባለፈው ጀምሬልህ እንደነበረው ሁልጊዜ ወደ ዚህ ዋሻ በመጣሁ ቁጥር እጅግ ደስ ይለኛል። ሙታን ቢመስሉህም ቅዱሳን ሕያዋ ናቸው" አሉ።

"አባ! እንዲያው ድፍረት ባይሆንብኝ እነማን ናቸው?" አልኩኝ።

"እነዚህ የቅዱሱ ኪዳን ቅርስ ጠባቂዎች የነበሩ ባለ ቃል ኪዳን ናቸው!" አሉኝ ከፍተኛ መንፈሳዊ ክብር የሚሰጣቸው እንደሆኑ በገጽታቸው ቍምር እያስገነዘቡኝ።

"የቅዱሱ ጽዋ ማለትዎ ነው?" አልኩኝ።

"አዎን! የቅዱሱ ጽዋ" አሉና፤ "ለዚህ ቃል ኪዳን የታመኑና የተገቡ በመሆናቸው የነፍሳቸውን ጽድቅ ብቻ ሳይሆን እስከ ዳግም ምጽአት ድረስ የከበረ ሥጋቸው እንዳይበሰብስ ዐፅማቸው እንዳይፈርስ በመድኃኔዓለም ቃል የተገባላቸው ናቸው" አሉ።

"እወይ መመረጥ!" አልኩኝ ከልቤ።

"ነው እንጅ ልጄ!" አሉ አባ።

"አባታችን! ቅዱሱ ጽዋ እዚህ አርባ ሃራ ነው እንዴ ያለው?" አልኩ ስፈራ ስቸር

"እይ፣ አይደለም!" አሉ።

"ታዲያ እንዴት ነው ነገሩ?" አልኩኝ ግራ በመጋባት።

"የቅዱሱን ጽዋ አገልግሎት ሲጨርሱ የተመረጡትናቸው ዕለት ስትደርስ በቅዱሱ ጽዋ በተሰዋ መሥዋዕት ቁርበው ያርፋሉ። ከዚያ በኋላ ቅዱሱ ጽዋ ካለበት ለዕረፍታቸው ወደ ተመረጡትው ወደዚህች ዋሻ የከበረ ሥጋቸው ይመጣል" አሉ።

"እንዴት ነው አስከሬናቸው የሚመጣው?" አልኩኝ

"ከዚህ በታች ባለው ዋሻ አድርጐ እንዲመጣ ይደረጋል" አሉ

"የፈጣሪ ያለህ" አልኩኝ።

"አዎን ልጄ! ይህች አገር ብዙ ያልተነገሩ አስደናቂ ገቢር ተአምራት ይሰራባታል" አሉ።

"አባታችን ቅዱሱ ጽዋ ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደመጣ አባክዎት ያስረዱኝ?" አልኳቸው።

በጸጥታ ብዙ ከቆዩ በኋላ

"ሁለት ዓይነት ታሪኮች አሉ። አንደኛው ጌታችን በተሰቀለ ጊዜ ለንጊኖስ የሚባል ሰው ጎኑን በጦር ወጋው። ደምና ውሃም ተቀላቅሎ ፈሰሰ። በዚህ ጊዜ ሊቀ መላዕክት ቅዱስ ሁራኤል በብርሃን ጽዋ ተቀብሎ ዓለሙን በዓራቱም ማዕዘናት ረጨው። የደሙ ንጣቢ ያረፈበት ቦታ ሁሉ የቤተክርስቲያን መትከያ ቦታ እንዲሆን በመንፈስ ቅዱስ ተለየ። ከዚህ በኋላ ቅዱስ ሁራኤል የብርሃኑን ጽዋ በቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ በማዕከላዊ ምድር አመጣ ቆላ ተራሮች ውስጥ እስከ ዓለም ፍጻሜ እናረፈው የሚል ነው። በድርሳነ ሁራኤል የተገለጸውና በብዙ ኢትዮጵያውያን ሊታወቅት የሚታወቀውና የሚታመነው ታሪክ ይህ ነው። ይሁን እንጅ ሌላ ግዘፍ የነሳው የቅዱሱ ጽዋ ታሪክ እና እውነትም አለን" ብለው ዝም አሉ። እኔም በጸጥታ መጠበቅ ያዝኩ።

"በወንጌል እንደምናነበው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የፋሲካ በዓልን ለማክበር ባለ አንድ ደርብ ቤት ላይ እንዲያዘጋጁለት ደቀመዛሙርቱን አዘዛቸው። ራትም ከበሉ በኋላ ጽዋውን አንስቶ ይህ ስለብዙዎች የሚፈሰው የሐዲስ ኪዳን ደሜ ነው። ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ አላቸው። በዚያውም ስለሞቱና ስለትንሣኤው ነገራቸው። ከከበረው የጌታ ራት ምሽት በኋላ ሦስቱን ደቀ መዛሙርት ይዞ ወደ ጌቴሴማኒ ለጸሎት ሄደ። ሐዋርያት እሞታለሁ ስላለ ተረብሸው ነበርና ስለ ቅዱሱ ጽዋ ትኩረት የሰጠ ከመካከላቸው አልነበረም። ይሁን እንጂ ሁልጊዜ በምሽት እየመጣ ከጌታ ዘንድ ይማርና ከቃሉ በረከት ይቀበል የነበረ የአይሁድ ሸንጎ አባል የሆነ የአርማትያሱ ዮሴፍ የሚባል ደግ ሰው ነበር። እንደተለመደው በዚህ ምሽትም ከሐዋርያት ተርታ ባይቀመጥም ተገኝቶ ነበር። እናም ከቅዱሱ እራት በኋላ በጌታ የተመረጠውን ቅዱስ ጽዋ አንስቶ ወደ ቤቱ ወሰደ"።

"የሚገርመው ጌታ በመስቀል ላይ ሲሰቀል ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ሸሽተው ስለነበረ ወደ ጲላጦስ ቀርቦ የጌታን ሥጋ በክብር ለመቅበር የለመነ ይህ ታማኝ ቅዱስ ሰው ነበር። ኒቆዲሞስ ከተባለ ሰው ጋር ከመስቀል አውርደው በንጹሕ በፍታና በአዲስ ከተልባ እግር በተሠራ ጨርቅ በሽቱና በከርቤ ቀብተው ሲገንዙት ከጎድኑና ከመዳፎቹ የተነሣ ከሥጋው የፈሰሰውን ደም በቅዱሱ ጽዋ ተቀበለ። በዚህም ጌታ የተናገረውን ትንቢት መፈጸሙን አከበረ። ከዚህ በኋላ ለራሱ ባዘጋጀውና ከዓለት ተፈልፍሎ በተሰናዳው መቃብር የጌታን ሥጋ በክብር አሳረፈ"።

"አይሁድም መጀመሪያም ለክርስቶስ በጎ ሃሳብ በማሳየቱና በምሥጢር እየሄደ በመማሩ፣ ከዚያም ክርስቶስን አሳልፎ ስለመስጠት ክፉ ምክራቸው አለመተባበሩ ሳያንሰው የክርስቶስን ሥጋ ከመስቀሉ አውርዶ በራሱ መቃብር በክብር በማሳረፉ እምርረው ተጣሉት። ሊገድሉትም ዛቱበት። በዚህ የተነሳ ኢየሩሳሌምን ለቅቆ ወደ ትውልድ ስፍራው ወደ አርማትያስ (ኬብሮንም ትባላለች) ቅዱሱን ጽዋ ይዞ ሸሸ። በዚያም ስለ ክርስቶስ እየመሰከረና

እያስተማረ መኖር ጀመረ። ከቅዱሱ ጽዋ በሚወጣው ኃይልና ፈውስም ብዙዎች የክርስቶስ አማኝ ሁነው ተጠመቁ" ብለው በረጅሙ ተነፈሱ።

"ክዚያስ ወደ ኢትዮጵያ እንዴት ሊመጣ ቻለ?" አልኩ በጉጉት።

"ጌታ በተወለደ በ34ኛው ዓመት የኢትዮጵያ ንግሥት ባለሥልጣን የነበረው ጃንደረባ ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የተለመደ አምልኮትና ስግደት ለመፈጸም ተጓዘ። በመጽሐፍ ቅዱስ በሐዋርያት ሥራ እንደተገለጸው በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ፊልጶስ በተባለው ሐዋርያ አማካኝነት በትንቢተ ኢሳይያስ እንደተጻፈው ነገረ ክርስቶስን ተረድቶ አምኖ በጋዛ ሰርጥ ተጠመቀ። ይህ ቅዱስ ኢትዮጵያዊ ወደ ሀገሩ ተመልሶ የምሥራቹን በመንገር ክርስትናን ለኢትዮጵያ አስተዋወቀ። ይህ ሰው በክርስቶስ ነገረ ስቅለት በመመሰጡና ራሱን ለክርስቲያናዊ ተልእኮ መለየት በመፈለጉ ከሥልጣኑ እንዲሰናበት ጥያቄ አቀረበ። ንግሥቲቱም ጥያቄውን ተቀብላ እንዲህ አለችው፣

> "አንተ የተባረክ አገልጋዬ ሆይ አሁንም ወደ ኢየሩሳሌም ሂድ። በዚያም ለሀገራችን በረከት ለሕዝባችን ምስክር የሚሆን የክርስቶስ የመወለዱ፣ የማስተማሩ፣ የመሞቱና የመነሣቱ ምልክት የሚሆን አንዳች ነገር ይዘህ ተመለስ። በብሉይ ኪዳን ታቦተ ጽዮንን እንድንጠብቅ የመረጠንና የፈቀደልን አምላክ በሐዲስ ኪዳን ዘመንም በረከት አይነሳንምና" አለችው።

ጃንደረባውም የንግሥቲቱን ልብ የሚነካ ትእዛዝ ተቀብሎ ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘ። ነገረ ክርስቶስንና ምሥጢረ ሥጋዌን በአግባቡ ተማረ። በዚያውም የቅዱሱን ጽዋ ተአምራት ሰማና ወደ ኪብሮን አቀና። ይሁን እንጂ አይሁድ ተአምራቱን ሰምተው በመቆጣታቸው ዮሴፍ ኪብሮንን ለቆ ወደ ሶርያ ተሰዶ ነበርና ከብዙ ድካም በኋላ በሶርያ ታላቁን ሰው ማግኘት ቻለ።

ታላቁን ሰው ዮሴፍን ለአምስት ዓመታት ያክል በአገልግሎት እያገዘ ቆየ። በቆይታው ዓለም ጠፍታ ቀርታለች ብሎ ያመነውን ታቦተ ጽዮንን (ጽላተ ሙሴን) በእምነትና በምሥጢር ጠብቃ ከምትኖር ሀገር እንደመጣ፣ እርሱም በክርስቶስ እንዴት አምኖ እንደተጠመቀ፣ ከዚያም አልፎ የሀገሩ ሰዎች ያለምንም ሁከትና ማመንታት ክርስቶስን አምነው መቀበላቸውንና አሁንም ወደዚህ የመጣው በንግሥቲቱ መልካም ፈቃድ ለላቀ የክርስቶስ በረከት እንደሆነ ስለገለጸለት በዮሴፍ ዘንድ ከፍተኛ ሞገስና መታመንን አተረፈ። ታላቁ ሰው ዮሴፍ እድሜው እየገፋና የአይሁድም የማሳደድ እጅ እየረዘመ ሲሄድ ለኢትዮጵያው ጃንደረባ እንዲህ አለው።

"ሕዝብህ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው ብሎ ክርስቶስ የተናገረለት ታላቅ ሕዝብ ነው። ለእሥራኤል አምላክ የታመነ የተስፋውን ቃልም ከአምሳል እስከ መርገፉ የጠበቀ ነው። አንተም የልብህ ንጽሕናና እምነትህ በመንፈስ ቅዱስ የተመሰከረልህ ነህ። ከአንተና ከሕዝብህ በስተቀር ይህንን ቅዱስ ቅርስ ለመቀበልና ለመጠበቅ ማን የተገባ ይሆናል?! የጌታዬ የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅርና ሰላም ይብዛልህ። ይህንን የከበረ ቅዱስ ቅርስ ለሕዝብህ የእምነት ውጤት የጸጋ ምልክት የሐዲስ ኪዳን ምስክር ይሆን ዘንድ ወደ ሀገርህ ይዘህ እንድትሄድ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኗል!"

ካለ በኋላ መርቆና ጸልዮ ጽዋውንም በምሥጢር አስይዞ ሰደደው" ብለው በረጅሙ ተነፈሱ።

የአባ አድራልን ቃላት ትርጉም ለማወቅ ፕሮፌሰር ዴቪድን በአገኘኋቸው ጊዜ ስለ ቅዱሱ ጽዋ ታሪክና አጠፋፍ በዝርዝር ነግረውኝ ነበር። በእርሳቸው ገለጻ መሠረት ከዮሴፍ ጋር የተያያዘውና እስከ ኬብሮን/ አርማትያስ ያለው ታሪክ ከሞላ ጎደል አባ አክሊሉ ከተረኩልኝ ጋር በጣም ተመሳሳይ ነው።

ይሁን እንጂ ከኬብሮን በኋላ የአይሁድ ተጽዕኖ ሲበዛ በወቅቱ የዮሴፍ ሀገረ ስብከት ተብላ ወደ ምትታወቀው ወደ እንግሊዝ በተከታዮቹ አማካኝነት በምሥጢር በጀልባ እንደላከውና ከዚያ በኋላ የት እንደደረሰ እንደማይታወቅ፤ እንዲሁም በሌላ መላምት ደግሞ ፈረንሳይ ማርሴል አካባቢ በአንድ ወቅት እንደታየና ከዚያ በኋላ እንደተሰወረ እንጂ ወደ አፍሪካ ኢትዮጵያ ሄዷል የሚል እምነትና መላምት እንደሌለ ፕሮፌሰሩ የነገሩኝንና ምልክቱ በኢትዮጵያ መታየቱ እንዳስደነቃቸው የገለጹልኝ ትዝ አለኝ።

"አባታችን! በውጪው ዓለም ያሉ የታሪክ ምሁራን ቅዱሱን ጽዋ ዮሴፍ ከኬብሮን ወደ እንግሊዝ እንደላከውና በዚያው ጠፍቶ እንደቀረ ነው የሚያምኑት። ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱ በፍጹም አይታወቅም። የሚታመንም አይመስልም" አልኳቸው።

አባ ፈገግ በለው በተረጋጋ ስሜት እንዲህ አሉ፤

"ታሪኩን የነገርኩህ ስለጠየቅኸኝ እንጅ አንተንም ሆነ ሌሎችን ለማሳመን አይደለም። ኅሊናህ የፈቀደውን መቀበል ያንተ ፋንታ ነው" አሉኝ።

"ይቅር ይበሉኝ አባ! እንዲያው በዓለሙ የሚታመነውን ለመናገር ነው እንጅ ተጠራጥሬ አይደለም። ይልቁንስ ከዚያ በኋላ ምን ሆነ?"

"እንደነገርኩህ ጃንደረባውም በታላቅ ሃይማኖት ቅዱሱን ቅርስ ተረክቦ ወደ ሀገሩ ወደ ኢትዮጵያ አክሱም መጣ። ከዚያም ወደ ጣና ሃይቅ መጥቶ ቆየ። ከብዙ ጊዜ ቆይታ በኋላ አባቶች የቅዱስ ዑራኤልን ፍኖት በራእይ በመረዳታቸው ጉባኤ ተሠርቶ የቅዱሱ ቅርስ ማረፊያ ማዕከላዊ ምድር ወደ ሆነችው መንዝ እንዲሆን ወሰኑ። መንዝ ማለት ‹ነዝሃ› ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ‹ረጨ› ማለት ነው። ስም ሲሆን ደግሞ ‹መንዝሀ› ወይም ‹መርጨት› ይሆናል። በሂደት ‹ሀ›ን አስቀርቶ ‹መንዝ› የተባለ ለዚህ ነው።

ይህ እንግዲህ ሲጠቃለል ደሙ የተረጨበት ምድር ማለት ነው። በዚሁ መሠረት ከማና ዳር በስተሰሜን ከሚኖሩ ነዋሪዎች ተመርጠው በሦስት ወገን ተከፍለው የቅዱሱ ቅርስ ጠባቂ ይሆኑ ዘንድ አጅበው ወደ ዚህ መጡ ። የሦስቱ ወገን መሪዎችም ወንድማማቾቹ ሳሎ፣ ማማና ጌራ ይባሉ ስለነበር በአሰፋፈራቸው እንዳር ሳሎ ምድር፣ ማማ ምድርና ጌራ ምድር ተብሎ መንዝንም አቅንተው ቅዱሱን ቅርስም ጠብቀው እስከአሁን አቆዩ"። ብለው ሲጨርሱ፦

"አባ የዚህ ታላቅ ሰው ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ታሪክ ግን በቤተክርስቲያንም ሆነ በሀገር ደረጃ በሚገባው መጠን ተመዝግቦ ክብር ተሰጥቶታል ብለው ያምናሉ?" አልኳቸው በቁጭት።

"አየህ የኔ ልጅ ይህ ሰው የሐዲስ ኪዳን የእምነታችን ታሪክ የማዕዘን ድንጋይ ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ ባለው ታሪካችን ደግሞ የአጥቢያ ኮከብ ነው። ትልቁ ችግራችን የኋለኛውን ለማግዘፍ ስንል የፊተኛውን ስለምንረሳ ነው። ለምን የእርሱን እውነት በ 300 ዐመት ጎትተን ኢትዮጵያ ክርስትናን የተቀበለችው በዐራተኛው ክፍለ ዘመን ነው እንደሚባል አይገባኝም። የሆነው ሆኖ ይህ ሰው ከመሠረቶቻችን መካከል ዋናው ሆኖ ገድሉ ተጽፎለታል" አሉ።

"ስለ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የተጻፈ ገድል በቤተክርስቲያን ሰምቼም አጋጥሞኝ አያውቅም" አልኳቸው።

"አዎን ልክ ነህ። በብዙ ቦታ የለም። አንተ ግን ስለዚህ ቅዱስ ሰው የበለጠ ማወቅ ከፈለክ ቦታውን ልነግርህ እችላለሁ" ብለው ፈገግ አሉ።

"አሁን ባይሆንም በሌላ ጊዜ ሄጄ ታሪኩን በደንብ ማጥናት እፍለጋለሁና እባክዎትን ይንገሩኝ?" አልኳቸው፤

"ቦታው እ.. እሉና በጌምድር ውስጥ እንዳቤት ከሚባል ሀገር ግሼና ተክለ ሃይማኖት ከሚባል ደብር ታገኘዋለህ። በዚያውም የምትደነቅባቸውን ሌሎች ቅርሶችንም ታያለህ" አሉኝ።

ታላቁን ሰው ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ በአእምሮዬ እያመላለስኩ በሀሳብ ጭልጥ አልኩና በምናቤ፡

"በሀገር ሀብት ላይ ታምኖ የተሾመ በጅሮንድ፤

ሊሎችን ለማገልገል ጃንደረባ የሆነ፤

ለማመን ቅርብ የሆነ ንጹሕ ልብ የታደለ!

ከመቅታዊው የዓለም እውነት ጋር ቀድሞ ወገኑን ያስተዋወቀ አንጋፋ ዲፕሎማት፣በታላቁ መጽሐፍ የሀገሩንና የራሱን ስም መትከል የቻለ የማይደበዝዝ ታሪክ ባለቤት ሆኖ ሳለ ምነው በወገኖቹ ዘንድ ታሪኩ የተረሳ ሆነ? የሚል ቁጭት አደረብኝ።

"አባታችን አሁን ለምንና እንዴት ሶርያዊው አባ አድራል ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣ እንዲሁም ግብጻዊው ጻድቅ አቡነ ሃራ ለምን ይህን ቦታ እንደመረጡ ግልጽ ሆነልኝ። እነዚህ ሰዎች ስለ ቅዱሱ ጽዋ በቂ መረጃ የነበራቸው ናቸው" አልኳቸው።

"ታሪክን በትዕግሥት ከመረመሩት እንደ መስታዎት ሁሉን በግልፅ ያሳያል" አሉኝና በመካከላችን ዝምታ ሰፈነ።

እንግሊዛዊው ጋዜጠኛና ደራሲ ግራሃም ሐንኮክ "The Sign and The Seal" (ታቦተ ጽዮንን ፍለጋ ተብሎ በአማርኛ የተተረጎመው) በሚል ያሳታመው መጽሐፍ ታወሰኝና የሆነ ቦታ ላይ እርሱ በተሳሳተ ትርጉም የወሰደው ቢሆንም  አባ አክሊሉ የገለጹት ቅዱሱ ጽዋ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ታሪክ ግሩም ማስረጃ እንደነበረ አመንኩ። ግራሃም ሐንኮክ በመጽሐፉ ፈረንሳይ ውስጥ ሻርተር በምትባል ከተማ በ12ኛውና በ13ኛው ሙቶ ክፍለ ዘመን በአዲስ መልክ በታደሰና በቅድስት ድንግል ማርያም ስም የታነጸ ካቴድራልን እንደጎበኘ ይገልጻል።

በዚህ ቤተ መቅደስ ውስጣዊ ክፍል በሁለት አቅጣጫ የንግሥተ ሳባን ሃውልት እንደተመለከተና በተለይ አንደኛው ሃውልት ላይ "ከእግር ጀርባ የሚታይ አፍሪካዊ መሰል ሰው ነበር" ይልና በንብኝዎች መመሪያ ላይ ደግሞ "አፍሪካዊ አገልጋይ ወይም ኢትዮጵያዊ ባርያ ይለዋል" ይላል። ከዚህ ሃውልት በአሻጋሪ "መልከ ጼዴቅ ከተኝ እጁ በታች ጽንሐሕ በግራ እጁ ደግሞ መያዣው ቀጠን ረዘም ያለ ጽዋ ይዞ ተሥሏል። በውስጡ ግን ፈሳሽ ሳይሆን እምድ ይዟል" ይልና "በመልከ ጼዴቅ ሃውልትና በንግሥተ ሳባ ሃውልት መካከል ስረገላ ወደ ንግሥት ሳባ አቅጣጫ ሲጓዝ ይታያል" ይላል። ግርሃም ሐንኩክ ይህን አገጣጥሞና ከክብረ ነገሥት ጋር እያይዞ ጽላተ ሙሴ ከእስራኤል ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣቱ የመነሻ መላምት አድርጎ በመጽሐፉ ላይ አቅርቦታል። ታቦተ ጽዮን (ጽላተ ሙሴ ) በኢትዮጵያ ለመገኘቷ ጠንካራ ማረጋገጫ እንዳለ ቢታመንም ከላይ የቀረበው ማስረጃ ግን ቅዱሱ ጽዋ ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱን በግልጽ የሚያስረዳ እንጅ ግራሃም ሐንኩክ እንደተረዳው ለታቦተ ጽዮን የሚሆን አይመስልም። መልከ ጼዴቅ የሚታወቀው ከስንዴና ከወይን መሥዋዕትን በማቅረብ የክርስቶስ ምሳሌ ሆኖ ነው። በመሆኑም መልከ ጼዴቅ የያዘው ጽዋ ከታቦተ ጽዮን ይልቅ በቀጥታ ለሐዲስ ኪዳኑ ጽዋ የቀረበ ይመስላል። የሚገርመው ሐውልቱን ከሚያሳየው ፎቶ ሥር ደግሞ " መልከ ጼዴቅ ጽዋውን ጨብጧል። በውስጡም ድንጋይ አለው። ከዚህም ጋር የዎልፍራም ቮንን ግጥም ማገናኘት ይቻላል።እርሱም ቅዱስ ጽዋ የተባለው ድንጋይ ነው" ተብሎ የተጻፈ የሥዕሉ መግለጫ መኖሩ ነው። በብዙ ምሁራን የሚታመነው የዎልፍራም ፓረዚቫል ድርሰት ስለ ቅዱስ ጽዋ እንጅ ስለ ታቦተ ጽዮን ይናገራል ተብሎ አይታምንም። በሌላ በኩል "አፍሪካዊ አገልጋይ ወይም ኢትዮጵያዊ ባሪያ" ተብሎ በዚያን ዘመን ሊጠቀስ የሚችል ከኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ውጭ ማን ሊሆን ይችላል? በእኔ ግምት ግራሃም ሐንኩክ ስለ ቅዱሱ ጽዋ በኢትዮጵያ መገኘት ፍንጭ ኖሮት ቢሆን ኖሮ ማስረጃዎቹና ጉዞዎቹ በሙሉ በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ያስመቱት ነበር። ሁለቱም እስደናቂ የዓለም ቅርሶች በኢትዮጵያ መገኘታቸውን ማወቅ!

በመሆኑም ፕሮፌሰር ዴቪድ ‹ፓርዚቫል› ስለሚባለው የዎልፍራም ሥራ የገለጹልኝና እኔም ያነበብኩት ትዝ አለኝና አፌን ከፍቼ ቀረሁ።

ዎልፍራም ቮን ኤስከንባህ በ12ኛው ክ.ዘ. የነበረ ጀርመናዊ ባለቅኔ ሲሆን ‹ፓርዚቫል› የተባለ ዓለም አቀፍ እውቅናን ያተረፈ ምሥጢራዊ ድርሰት አለው። የድርሰቱ ማዕከላዊ ጭብጥ ደግሞ ‹ስለ ቅዱሱ ጽዋ› ኃይልና እሱን ፈልጎ ስለማግኘት ነበር። አንድ አውሮፓዊ መስፍን ከጥቁር ንግሥትና ከአንድ ነጭ ሴት የተወለዱ ልጆች እንዳሉትና ከሁለቱ ልጆች መካከል ከአውሮፓዊ ሴት የተወለደው ፓርዚቫል ‹ቅዱሱን ጽዋ› እንዳገኘው ይተርካል።

ይህን በተመለከተ ፕሮፌሰር ዴቪድ እንዲህ ብለውኝ ነበር፡

"በዚህ ቅኔ ውስጥ ያለው ቁም ነገር ከአውሮፓዊው መስፍንና ከጥቁር ንግሥት የተወለደው ወጣት የፍለጋው ተካፋይ መሆኑ ነው እንጅ ነጩ ፓርዚቫል ‹ቅዱሱን ጽዋ› እንዳገኘ መተረኩ የዘመኑን የአውሮፓ መሳፍንትንና የሃይማኖት መሪዎችን ለማስደሰት ብቻ ይሆናል በማለት ብዙዎች ይጠራጠሩታል።"

እኔን ያስደነቀኝ ግን በዎልፍራም ቅኔ ውስጥ እንዲህ የሚል መኖሩ ነው፤

> "ቅዱሱን ጽዋ ለመመልከት የታደለ ሰው ታሞም ቢሆን ይድናል። በዛች ሳምንት አይሞትምና.....የቻለውን ያክል ዘመን ጽዋዋን ቢመለከታት የፊቱ ጸዳል ሳይቀየር እንደልጅነቱ እንደለመለመ ይኖራል.."ይልና"፤ ድንጋይ የተባለው ቅዱሱ ጽዋ የሰውን ልጅ አጥንትና ሥጋ ከመበስበስ ታደጎ ለዘለዓለም ያደርገዋል" ይላል።

"የፈጣሪ ያለህ! በዋሻው ውስጥ የተከማቹት ያልፈረሱ አስከሬኖች ምሥጢርም ከቅዱሱ ጽዋ በሚወጣው ሃይል ነው ማለት ነው" አልኩኝና

"አባ!" አልኩኝ በሙሉ ስሜት ወደ እርሳቸው በእንብርክኬ ቀርቤ እጆቼን ጉልበታቸው ላይ አሳርፌ

"ምን ሆንክ? አሉኝ በመገረም።

"ይህ ግዘፍ የነሣው ቅዱስ ጽዋ እመን ቆላ ነው እይደል ያለው?" አልኳቸው

ፈገግ አሉና "በል ተነሥ ወደ ላይ እንውጣና እህል መሳይ ቅመስ" ብለውኝ ብድግ አሉ። እንደተለመደው ጥያቄዬን መሸሻቸው ነበር። አንዳንዴ ከትዕግሥቴ በላይ ይሆኑብኛል። ሆኖም ውስጤ በጣም እየተነጫነጨ ተከተልኳቸው።

ምእመናን ልጆቻቸው የሚባላ ነገር በየዕለቱ እያመጡላቸው ስለነበረ እህል ውሃ ሞልቷል። እሱን ከተመገብን በኋላ አባ ሀባብ በማስቀየስ ስልት የባጥ የቆጡን ያወሩኝ ጀመር። በናወራ ውስን መሸቶ ጉባኤ ተጀመረ። ጉባኤ አልቆ ወደ መኝታ ስናመራ እንደተለመደው ጥያቄዬን ለመሸሽ በጸሎት ከመጠመዳቸው በፊት ፍላጎቴን በግልጽ ነግሬ ሊጋፈጣቸው ወሰንኩ።

"አባታችን እኔ እኮ ....." ብዬ እንደማቅማማት ካልኩ በኋላ "እኔ እኮ በእናንተ በአባቶቼ እነሳሽነት በአገኘኋቸው ምልክቶች በመመራት ቅዱሱን ጽዋ ፍለጋ ነው የመጣሁት" አልኳቸው።

ትንሽ ዝም ብለው ከቆዩ በኋላ "አዎን ተረድቻለሁ" አሉ።

"እንግዲያውስ አባቴ ቅዱሱን ጽዋ ማየት እፈልጋለሁ!"

"አዎን! ብዙዎች ሊያዩት ይፈልጋሉ"

"እባክዎትን አባቴ ያረፈበት ቦታ ይውሰዱኝ ወይም ቦታውን እንዳውቅ ያግዙኝ"

"ያንን እንኳን ላደርግ አልችልም" አሉኝ ፍርጥም ብለው

"ለምን?"

"ስለማይቻለኝ ነው ልጄ። አትቀየመኝ!"

"ለምን አልቀየምም? ከመቀየምም በላይ አዝንበታለሁ እንጂ! ተረጋግቼ የምኖረውን ሰው ትንት በሚፈጥር ግራ አማርኛ የእርስዎ ባለንጀሮች በሆኑ አባቶች ተጠራሁ። ምንም ቢሆን የገዳም አባቶች ናቸው ብዬ አክብሬ ሄድኩ። ያገኘሁት ግን ትንሽ ፍንጭ እየተሰጠሁ በምሥጢር ቁልፍ ፍለጋ መዳከርን ነው። ከጎጃም እስከ ወሎ ተንከራተትኩ። አሁን ደግሞ ሸዋ መጣሁ። በመሐሉም ትርጉም ፍለጋ አሜሪካ ድረስ ሄድኩ። ምን አለባት እንዳጠፋው ፈልጋችሁ ከሆነ በግልጽ ቢነግሩኝ ቅጣት ከሆነም ወደ ኑሮዬ ብመለስ" አልኳቸው መረር ብዬ።

"እውነት ነው የጠራንህ በረከትን በእምነት እንድትቀበል ወዲህም የትውልዱን ሕመም እንድታውቅ ነው። አንተ ደግሞ ሁሉን የማወቅ ጉጉትና ወረት የሚንጠው የዚህ ትውልድ ናሙና ነህና ትጠራና ትማር ዘንድ ይገባ ነበር" አሉኝ።

"ፍላጎታችሁ ትምህርት መሥጠት ከሆነ ታዲያ ይህን ያክል ምሥጢራዊ ማድረግ ለምን አስፈለገ? ሁሉን ነገር ትውልዱ ቢያውቀው ምን አለ? ታሪኩን ምሥጢር፣ መድኃኒቱን ምሥጢር፣ ቅርሱን ሁሉ ምሥጢር ማድረግ ምን ይጠቅማል?! እኛስ የክርስቶስ ፍቅር የለንምን? የቃል ኪዳኑ በረከት አይገባንምን? እጅግ ምሥጢራዊ ከመሆናችሁ የተነሣ ከትውልዱ ጋር የሚያገናኝ የትብብር ድልድይ መሥራት አልቻላችሁም። እንደ እኔ ያለውም በከተማችን በቅርብ ካሉት ካህናትና አገልጋዮች ጋር ብቻ እየተጋጨና እየተፋጨ፣ እያማና እየናቀ እንዲኖር ፈረዳችሁበት። እውነት ከሆነ ይህ ብቻ እንኳን እናንተን አያስጠይቃችሁም" አልኩ በምሬት።

"እዮሀ!" አሉ ሲቃ በተሞላበት ድምፀት። የንግግራቸውን የአጀማመር ሁኔታ ስሰማ ግን የተኛን አንበሳ የመቀስቀስ ያክል ቀይ መስመር እንዳለፍኩ ገባኝ። ቢሆንም ምርጫ አልነበረኝም።

"ስማህ!" አሉ፣

ባእፍላ ትጀምራላችሁ። በወረት ትተውታላችሁ። ያወቃችሁትን ትረሳላችሁ፤ ያላወቃችሁትን ለማወቅ ትጥራላችሁ፤ የያዛችሁትን ትረግጣላችሁ፤ የረገጣችሁትን ትይዛላችሁ። ምኞታችሁ ልክ የለውም፤ እምሮታችሁ ብዙ ነው። የእማራችሁን ሲታገኙ ወዲያው ይሰላቹችኋል። ተው የተባላችሁትን ትሸራላችሁ፤ የተከለከላችሁትን ትደፍራላችሁ፤ የተፈቀደላችሁን ችላ ትሉታላችሁ። ቤተ መቅደስ እንዳትገቡ ብትከለከሉ ወደ ፊት ቤተ መቅደሱን በመሰታዎት ሠርታችሁ መቅደስ ባትገቡም እንኳን ሁሉን ከውጪ ሆናችሁ ማየት ትፈልጋላችሁ። ሁሉን ማወቅ ትፈልጋላችሁ፤ በአንዱም ግን አትጠቀሙበትም። ሁሉ አላችሁ፤ ግን ባዷችሁን ናችሁ። ሃይማኖት እንጅ እምነት የላችሁም!" ቀጠሉ አባ። ሰውነታቸው እንደ ቅኔ ዘራፊ በስሜት ይናጣል።

"መድኃኒት ነው ያልከው ?! መቀመሚያውን ነግሬህ ማርከሻውን ሳልገልጥልህ መጀመሪያውን ብቻ ሞጭልፈህ ትተኸኝ ትሄዳለህ። ጥበብን "ሀ ግእዝ" ብዬ ሳስተምርህ ብሞክር፤ መንደር ውስጥ በቃረምካት ዕውቀት ተመኩተህ በመሰልቸት "ሆ ሳብዕ" ብለህ ቀድመህ ትዘጋዋለህ። የግል ታሪካችሁ ቢታይ ወጥነት የጎደለው ከዚህም ከዚያም የተለከፈከፈ የተማሪ ከፋዳ ውስጥ ያለ እህል ይመስላል። ተምራችሁ እውቀት ሲታገኙ፤ ሰርታችሁ ሀብት ሲታፈሩ፤ ከላይ የሆናችሁበትን ሀገር ለቃችሁ፤ ሰፋ ወዳለው እንሂድ ብላችሁ እንደገና ከታች ትጀምራላችሁ። ትቀጥላላችሁ፤ በመጨረሻ ከጀመራችሁበት ትገኛላችሁ። ቸኩላችሁ ትወሰናላችሁ ወዲያው ትጸጸታላችሁ። በጽኑ ታማችኋል!"

ከታሪክ ፍቅርንና ልማትን ሳይሆን ጥላቻንና ጥፋትን ለይታችሁ ትቆፍራላችሁ። ከዚያም ቀጥላችሁ የከበረ ማዕድን እንዳወጣችሁ ሁሉ በኩራት ደረታችሁን ነፍታችሁ ሳትመርጡ ሁሉን በአደባባይ ትዘሩታላችሁ፤ እናም ወደ ኋላ ስለታሪካችሁና ስለ ቅርሳችሁ ባሰባችሁ ቁጥር ፍርሃትና ሃፍረት ይሰማችኋል። ስለሆነም ከኋላ ታሪካችሁና ከብራችሁ እየራቃችሁ መጣችሁ። የአሸናፊነትንና የተሸናፊነትን ትርጉም በአንድ ላይ የያዙ ሃውልቶችን ታቆማላችሁ።

ለማልጽንትና ለነጻነት እያላችሁ በምታደርጉት ሽኩቻ ዕርቃን ወደ መሆን ወረዳችሁ።

ቅቤ ሳይወጣችሁ ትናጣላችሁ። በዚህ ዓለም ጥድፊያ ታማችኋል። ሀገራችሁን ትንቃላችሁ፤ ጥላችሁ ለመሄድ ትፈልጋላችሁ፤ ከሄዳችሁ በኋላ ደግሞ አፍታ ሳትቆዩ አገሬ ናፈቀኝ ትላላችሁ። በቁማችሁ የናቃችሁትን የሀገራችሁን አፈር በሞታችሁ ልትለብሱት ትናፍቃላችሁ። ለሀገሬ አፈር አብቃኝ ብላችሁ በድናችሁን ልካችሁ የወገኖቻችሁን ልብ ትሰብራላችሁ። ግብዝነታችሁ መጠን የለውም። ሁለት ሀገር እንዲኖራችሁ ትፈልጋላችሁ፤ አንዱን በደም ሌላኛውን በመታወቂያ ታስባላችሁ። ከአንዱም ግን በአግባቡ አትኖሩም። ዘመናችሁም በምልልስና በመዋተት ያልቃል። ምን እንደምትፈልጉ አታውቁም እናም ፍለጋችሁ አያልቅም!"

በዚህ የተነጣ ምሥጢር ለመካፈል ቅርስ ለመረከብ የሚያስችል ሰብእና አልነበራችሁም። እኛ የመገናኛውን ድልድይ ስላልሠራንና ከእናንተ ስለራቅን ሳይሆን ስለማታዩት ወይም ማየት ስለማትፈልጉ አለበለዚያም እንደ ልቦለድ ገጸ ባሕርይ የራሳችሁን ያሸበረቀ አስረካቢ ፈጥራችሁ እውነቱን ሳይሆን ምናባችሁን መረከብ ፈልጋችሁ ስለምታጡት ነው። እኛ ደግሞ እናንተ ታዩን ዘንድ አላሸበረቅንም፤ ማሸብረቅም አንፈልግም። በዚህ ምክንያት ለእናንተ ምሥጢር ለመንገር፣ ቅርስ ለማውረስ እጅግ ከባድ ሆኗል። እኛ አባቶቻችንን እናምናለን። በእነርሱም ደስ ይለናል። የነገሩንን ተቀብለን ቃል ኪዳናቸውን ጠብቀን እንኖራለን።

> "ጽላተ ሙሴ አክሱም ጽዮን እንዳለች ሲነግሩን መጋረጃ ገልጠን፣ ሳጥን ከፍተን እንይ አላልንም፤
>
> ጌታ የተሰቀለበት የግማደ መስቀሉ ክፋይ ግሼን ማርያም አለ ሲሉን ቆፍረን አውጥተን እንመልከት አላልንም፤
>
> ቅዱሱ ጽዋ መንዝ ውስጥ አለ ሲሉንም ዋሻ እናስስ አላልንም።"

"አባቶቻችንን እምነን፣ ሀገራችን የበረከት ምድር መሆኗን ተረድተን፣ የጌታችንን የጸጋ ስጦታ ተቀብለን በእምነት እንኖራለን። ምንም የለንም፤ ሁሉ ግን የኛ ነው። ደሆች ብንባልም ባለጸጎችም ነን። የተራቆትን ብንመስልም የጸጋ ልብስ አለን። ሐዘንተኞች ብንመስልም ደስተኞች ነን። ስለ ሀገራችን መባረክ፣ ቅድስት ሀገር መሆን፣ ቅዱስ ቅርስ በእጃችን እንዳለ ዓለም እንዲያረጋግጥልን አንፈልግም። የሌለንን አለን፣ ያልተሰጠንን ተቀበልን ብለን የምንኩራራ ግብዞችም አይደለንምና። የሌለን ነገር ለመጠበቅናለመታመን ስንል ሥጋችንን እየጎሰምን በገዳም ለመኖር የምንወስን ጅሎችም አይደለንምና"።

በንግግሩ ብርታት የእርሳቸውን ኅሊና አሸንፌ የምፈልገውን ለማግኘት ብዬ በተናገርኩት መልስ ምክንያት ሳላስበው ከእርሳቸው የወጣው የንግግር ጎራዴ አእምሮዬን ይሸረካክተው ጀመር። የሚናገሩት ነገር በሙሉ እውነት በመሆኑ የምሟገትበት አቅም አልነበረኝም። ነባራዊ ሀቅ ነውና። በራስ መተማመኑን ተላብሰን ድህነታችንን አሸንፈን በዓለም አደባባይ ላይ ቀና ብለን የሀገራችንን ቅርሶች በአግባቡ ጠብቀን የውጭውን ዓለም አማልለን ወደ ሀገራችን መሳብ አልቻልንም። ብርቅዬዋን ቅርስ ሉሲን እንኳን አሜሪካ ድረስ የወሰድን፣ ጎብኚ ወደ ቅርስ ይመጣል እንጂ ቅርስ ወደ ጎብኚ ሄዶ የማያውቀውን አዲስ ደካማ ልምድ ያስመዘገብን ሆነናል። ስለግል ኑሮአችን ብቻ የምንኳትን ምስኪኖች ነን። የእኔ የራሴ ሕይወት ምስክር ነው። ቀዳዳ በርሚል የመሙላት ጥድፊያ መሆኑን አውቃለሁና።

የእኔ ኅሊና የኀፍረት ካባውን ለብሶ ሲመለሰም አባ ግን ንግራቸውን ቀጥለዋል።

"አንተ ደግሞ ፍለጋው የማያልቀው የዚህ ትውልድ ናሙና ነህና እምነህ ሄድ ብልህ አትቀበለኝም። እንደ ቶማስ በዐይንህ ካላየህ፣ በእጅህ ካልዳሰስከው አትረካም። የትውልዱ ሕመም ይህ ነው። አንተም የዚህ ሕመም ተጠቂ ትውልድ ምሳሌ ነህና ጫፉን ንገረንህ በእምነት እንድትኖር ችላ ብንልህ እንኳን ፈልፍለህ ለማወቅ ትዳክራለህ። ያወቅከውን ደግሞ ትዘራጥለህ። አንተ የትውልዱ ጥሩ ናሙና ነህ።

አንተን ሊያቆምህ የሚችለው የመንገዱ ማለቅ ብቻ ነው። ሩቅ መንገደኛ የሚያቆመው አንድም መንገዱ ሲያልቅ አለበለዚያ መንገደኛው ራሱ ሲያልቅ ነውና።"

አባ በአጭሩ የሚመለሱ አይመስልም፤ እንደ ጥሩ ተኳሽ ኢላማቸውን እያጠበቡ ይቀጠቅጡኝ ይዘዋል።

"አንተ የተጓዝከውን ገና ብዙዎች ይጓዙታል። ያወቅከውንና የደረስክበትንም መጻፍህ ስለማይቀር ያንን ተከትለው ብዙዎች ይጓዛሉ። ግን ልብ በል! ብታገኙትም አታምኑም። እርሱ ራሱ ለመሆኑ ምን ማረጋገጫ አለ? ትላላችሁ። አንተ በነገርካቸው መሠረት ሌሎች ካላመኑልህ ደግሞ አንተም እምነትህ ይከዳሃል። ራሳችሁንና የራሳችሁን እውነት የምታረጋግጡት በምዕራቡ ዓለም መለኪያ ብቻ ነውና"።

"አዎን! አንተ እንደገመትከው ቅዱሱ ጽዋ በእመጓ ቆላ ውስጥ ይኖራል። በመንፈስ ቅዱስ የተመረጠችውን የቅዱሱን ጽዋ ማረፊያ ቅድስት ቦታ የት እንደሆነች ባውቅም አንተን መርቼ ለመውሰድ ሥልጣንም ፈቃድም የለኝም። መንገድህን ልዘጋብህ ግን ፈቃዴ አይደለም። እንደ ቅዱስ አድራል በድካምህና በመሻትህ ትደርስበት ይሆናል ወይም አትደርስበትም ይሆናል። ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ ይሆናልና"።

"በጠዋት ተነሥተህ ወደ ዋሻው ውረድ። ከዋሻው ውስጥ ካሉት ቅዱሳን በድኖች መካከል ፍለጋህን የሚረዳ ምልክት ታገኝ ይሆናል። እርሱን ይዘህ ወደ እመጓ ቆላ ውረድ። ድፍረት ካለህም ከቅዱሳኑ መካን በታች ባለው በዋሻ ውስጥ መንገድ መጓዝ ትችላለህ። ደኅና እደር!" አሉኝ።

ሳላውቀው እንባዬ እንደ ሐምሌ ዝናብ ጉንጬን አልፎ ደረቴ ላይ ፈስሶ ነበር።

# ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት

በማግሥቱ በጥዋት ለመነሳት አልቻልኩም። እንዳች የሚጫን ስሜት ተሰማኝ። ጭራሽ የሰመመን እንቅልፍም ወሰደኝ። ስነቃ ፀሐይ በደንብ ወጥታለች። ድንገት ከመኝታዬ ተስፈንጥሬ ተነሣሁና ልብሴን ለባበስኩ። ለብሼ ሳበቃ ምን ማድረግ አለብኝ ብዬ በቆምኩበት ሀሳብ ውስጥ ገባሁ። አባ ያወረዱብኝን መዓት ልረሳው አልቻልኩም። የንግግራቸው ምት ክፉኛ ቢያቆስለኝም የሆነ ወኔ ውስጤን ሲገፋው ተሰማኝ።

እንዲህ አልኩ፡-

"የየትኛውም ትውልድ አባል ለመሆን ምርጫ የለም። በቃ! ዘመን ከአንዱ ትውልድ ላይ ይጥልሃል። በዚያ ትውልድ ውስጥ ትውልዱን መስለህ ከትውልዱ ጋር እየተፋለምክና እየተፋቀርክ ትቀጥላለህ። እኔ የዚህ ፍሲጋው የማያልቀው ትውልድ አካል ነኝ። የእነ አባ አክሊሉ ትውልድ ለመሆን ጎትቶ ወደዚያኛው ዘመን የሚወስደኝ ኃይል የለኝም። ፍልጎቱ ቢኖረኝም የመገናኛውን ድልድይ የማውቀው አይመስለኝም። ለዚህም ተጠያቂው ማነው ብል የሚመልስልኝም አላገኝ ይሆናል። እንደ አብዛኛው የዚህ ዘመን ትውልድ ሰው ልቤን ያጓጓውን እየተከተልኩ እኖራለሁ። አዎን ፍሲጋው የማያልቀው ትውልድ አባል ነኝና!" አልኩና ወደ ዋሻው በስሜት እየተንደረደርኩ ወረድኩ።

ከዋሻው ስደርስ አባ ከተለመደው በታቸው ላይ ቁጭ ብለው ዳዊት ይደግማሉ። ጸሎታቸውን ሳለማቋረጥ ዝም ብዬ ቆምኩ። "እንደምን አደርክ?" ብለው መስቀላቸውን ዘረጉልኝ።" እግዜር ይመስገን" ብዬ ተሳልሜ ሳበቃ ፊቴን ወደ ዋሻው በር አዙሬ ቆምኩ። አባ ጸሎታቸውን ቀጠሉ። ወደ ዋሻው እንድገባ የፈቀዱ መሰለኝና ወደ በሩ አመራሁ።

"መቼም ምን ልበ ደንዳና ነው!" ሳይሉኝ አይቀርም።

የዋሻውን በር አልፌ ወደ ውስጥ ስዘልቅ የዋሻው ውስጥ ቅዝቃዜ ከጥልቅ ዝምታው ጋር ተዳምሮ በአስከሬኖች መሐል መቆሜን አረዳኝ። ድንገት መጠን የሌለው ፍርሃት መጣብኝና ሚዛኔን እስክስት ድረስ ተሸበርኩ።

"በዚህ በገደል አፋፍ ላይ በጉም ተሸፍኖ፣ በበርካታ ያልፈረሱ አስከሬኖች ተሞልቶ፣ በዝምታ በተከበበ የጓለት ዋሻ ውስጥ ምን እሠራለሁ? እንዴትስ ምንስ ነው የምፈልገው?" የሚል የገደል ማሚቶ የሚመስል ሃሳብ በላይ በላዩ በአእምሮዬ ይመላለስ ጀመር። ሳላስበው አስከሬኖቹን ፊት ለፊት እያየሁ ወደ ኋላ ወደ በሩ ሸሸሁ። ድንገት ደግሞ አባ የነገሩኝ ከሌላኛው የአእምሮዬ ክፍል አቃጨለ።

"ሙታን ቢመስሉህም ቅዱሳን ሕያዋን ናቸው። ሁሌ ወደዚህ ዋሻ ስመጣ ደስታ ይሰማኛል!"

"አዎን! እነዚህ አስከሬኖች ብቻ አይደሉም፣ ሕያዋን ቅዱሳን ናቸው፤ ምን ያስፈራኛል? ባለማመን የአስከሬን ፍርሃትና በማመን ቅዱሳን ቅርስ ፍለጋ እንዴት ሰው ያንክሳል? ወይ ፍርሃትን አለበለዚያም ድፍረትን መምረጥ ግድ ነው" አልኩና ወደ ዋሻው ገብቼ አንዱን አስከሬን ብድግ አድርጌ አቀፍኩትና ዝም ጭጭ አልኩ!።

ከዚህ በኋላ የጠፋውን ዕቃ ሳሎን ውስጥ እንደሚፈልግ አባወራ አንዱን አስከሬን አንስቼ ሌላውን እያጋደምኩ በጥንቃቄ ከመግነዛቸው ጋር የታሰረ ወይም በመካከላቸው የተጣለ ጥቅል ወይም መጽሐፍ ወይም ክታብ ነገር እፈልግ ጀመር። ብቻ አልፎ አልፎ አስከሬን እያነሳሁ እየጣልኩ እንደሆነ ሳስብ ፍርሃቴ ድንገት ብቅ ይላል። እንደገና ተረጋግቼ ፍለጋዬን እቀጥላለሁ።ምንም የተገኘ ነገር የለም።

ተስፋ ቆርጬ ወደ አንድ ጥግ ሄጄ ቁጭ አልኩ። በታችኛው ዋሻ ውስጥ መንገድ ልሂድ ይሆን? ብዬ አሰብኩ። ነገር ግን ከደገም አርባ ሃራ እስከ እመን ቆላ ያለው ርቀት ወደ 35 ኪሎሜትር ይጠጋል። ይህን ያክል ርቀት በዋሻ ውስጥ ብቻዬን መጓዝ አደገኛነቱ ታየኝ። ቢያንስ አሁን የማስበው አይደለም አልኩና የቅዱሳኖቹን አስከሬኖች በእርጋታ አስተውላቸው ጀመር።

ግማሾቹ አስከሬኖች መግነዛቸው ተፈቶ መልካቸው በግልጽ በሕይወት እንዳለ ሰው ሆኖ ጠውልጎ የሚታይ ሲሆን ሌሎቹ ግን መግነዛቸው ሳይፈታ በጠንካራ ሽራ ከላይና ከታች ተቋጥሮ የተቀመጡ ናቸው። መግነዛቸው ያልተፈቱትን የበሰበሰ አተኩሬ ሳይ የአንደኛው አስከሬን ቅርጽና ይዘት ለየት አለብኝ። ከመቀመጫዬ ተነስቼ ከሌሎቹ አስከሬኖች በጥንቃቄ ለይቼ አወጣሁት። በእጄ ስዳብሰው የሰው ቅርጽ የለውም ይልቁንም ቁሳቁስ መሰለኝ።በአንድ በኩል ያለውን መቋጠሪያ ፈታሁት።

"አሁን ሰው ከውጭ ቢመጣ ምን ይላል? አባስ ቢያዩ ምን ይላሉ?" አልኩ ለራሴ። "ተራ ሰው እንደሆነ አይመጣም፣ እባም እንደ ሕመምተኛ ቆጥረው ፈቅደውልኛል። ከአሁን ወዲያ ወደ ኋላ ማለት የለም" አልኩ ለራሴ።

ቋጠሮውን ፈትቼ ሳይ አብረቅራቂ ጨርቅ ታየኝ። እጄን ሰድጄ አወጣሁት። ያረጀ ልብሰ ተክህኖ ነው። ቀጥዬ ስሰድ እንዲሁ ያረጀ አብድል ከኒ የሚባለው ቀሚስ ነው። በመጨረሻ ሽራውን ዘቅዝቄ በሙሉ ዘረገፍኩት። ሁሉም የአንድ መነኮሴ አልባሳት፣

መታጠቂያና መቁጠሪያ ነገሮች ናቸው። ከመሐል ግን አንድ ጥቅል ብራና አየሁ። ብራናውን ብድግ አድርጌ ጥቅሉን ፈታሁና ለማንበብ ስሞክር አልታይህ አለኝ። ወደ ዋሻው በር ጠጋ ብዬ አጧራውን አራግፌ ለማየት ስሞክር ሥዕል መሳይ ነገር ታየኝ። መጀመሪያ ጠልሰም መስሎኝ ነበር። በጥንቃቄ የበለጠ አጧራውን አራግፌ ሳየው ግን ጠልሰም ሳይሆን የሸረሪት ድር የመሰለ ሥዕል ነው። እንደገና ቀለም እንዳላስለቅቅ እየተጠነቀቅሁ አጧራውን መጥረግ ጀመርኩ።

በሸረሪት ድር መሳይ ሥዕሉ ላይ ቁጥሮች፣ ፊደሎችና ምልክቶች ተንቅሰውበታል። አንዳቸው አንዳቸውን በመከበብና ሌሎቹ ደግሞ ከመሐል ወደ ውጭ እንደ ጨረር በሚወጡ ቀጥታ መስመሮች የተሠራ ሥዕል ነው። ወደ ጠርዝ ያለውን ክፍል እንደገና አጽድቼ ስመለከተው አንድ ጽሑፍ ያለ መሰለኝ። ወደ ውጭ ወጥቼ ደብዛዛውን ፊደላት ሳስተውል የግእዝ ናቸው። ከብዙ የጥንቃቄ ጠረጋ በኋላ ፊደሎችን አጥርቼ በማየቴ እንግጣጥሚ ሳነብባቸው ድንገት በደስታ ይሁን በድንጋጤ ሰውነቴ ባለበት ደርቆ ቀረ። "አገኘሁት!" አልኩኝ።

ብራናውን በጥንቃቄ ከዘረጋሁ በኋላ በያዝኩት አይ ፎን ካሜራ ደጋግሜ አነሳሁት። ይህም አልበቃኝም፤ በወረቀት በተቻለኝ መጠን ሥዕሉንና ምልክቶቹን ገለበጥኩ። "ይህ ድንቅ ነገር ለእኔ ብቻ ይሆን ዘንድ ያን ያክል ራስ ወዳድ አይደለሁም" አልኩኝና ሁሉንም እንደ ነበር አድርጌ ወደ ሸራው ከተትኩና ቋጥሬ ከአገኘሁበት መለስኩት።

ከደስታዬ ብዛት እንዴን አስከሬን አንሣሁና አቅፌ ሳምኩት። በተስፋ ከዋሻው ወጣሁ። አባ የሉም። ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ወደ እቃ ቤቱም በጥድፊያ ስሔድም የሉም። ተመልሼ ወደ ዋሻው ሄድኩ። ከታችኛው ዋሻ ወጥተው ሲመጡ አገኘኋቸው። ፊቴ በደስታ ተሞልቶ ቢያዩም ብዙ አልተደነቁም።

"ጨረስክ?" አሉኝ።

"አዎን አባ አሁን መሄድ አለብኝ!" አልኳቸው።

"አላልኩህም? እንዲሁ በጥድፊያ የተሞላችሁ ናችሁ!" ያሉ መሰለኝ።

"አሁን ልትሄድ?" አሉኝ

"አዎን አባታችን። ጸሎት ያድርጉልኝና ልሂድ" አልኳቸው።

"ወደ እቃ ቤቱ ሄድን። ከግንድ ላይ ዐረፍ አሉና።

" የዛሬን እንኳ አታድርም?" አሉኝ።

"አይ አባታችን ብዙ ቀን እኮ ቆየሁ፤ ግዴለም ልሂድ" አልኳቸው።

"በል እንግዲህ ካልክ" አሉና ተነስተው ጸሎት አድርገው ሲያበቁ ትካሻዬን ሳም አደረጉና ትኩር ብለው አዩኝ። ፊታቸው ላይ የሐዘን ስሜት አየሁ።

"ጥበብና እምነት ከፊትህ ቢቀርቡ ቢቻልህ እምነትን ምረጥ፣ ባይቻልህ ደግሞ እምነትን አስቀድም" አሉና "የመድኃኔዓለም ፈቃድ ይሁንልህ" አሉኝ፡

"አሜን" አልኩ።

ከቤተ ክርስቲያኑ ወጥቼ ከአውራ ጐዳናው ስደርስ አንድ አይሱዙ የጭነት መኪና እህል ጭና ወደ ሞላሌ ከተማ ሊሄድ ሲነሳ ደረስኩ።

"ጋቢና ቦታ የለንም ከላይ ደግሞ ነፋስና አቧራውን አትችለውም" አለኝ ሹፌሩ። "ግዴለም እንዳውም ከላይ መሆን ነው የምፈልገው" አልኩና ገብስና ስንዴ ሞልቶ ከተጫነው መኪና ላይ ወጣሁ። መኪናው ፍጥነቱን እየጨመረ በሄደ ቁጥር የመንዝ ቅዝቃዛ ነፋስ እንደ ጂፌ (ባልጩት) ድንጋይ ፊቴን ይሸረካክተው ጀመር። አቧራው ወደ ሰማይ ተጥመልምሎ ከወጣ በኋላ ከላዬ ላይ ይመረግ ጀመር።

በጣም ደስ አለኝ። ለጊዜውም ቢሆን በሥጋዬ ላይ የሰለጠንኩ መሰለኝ።

"እኔ እምሰው እምነት ግን ምንድን ነው?" አልኩ ለራሴ። እምነት የምትፈልገውን ነገር እንደምታገኝ አምነህ መትጋት ነው ወይስ የምትፈልገውን እንደምታገኝ አምነህ እንደተደረገልህ ቆጥረህ በእርካታ መኖር? የመጀመሪያውን ትርጉም ከሰጠነው ለትጋቱ ጥበብ ሊያስፈልግ ነው።

አባ "ቢቻልህ እምነትን ምረጥ" ሲሉስ ምን ማለታቸው ይሆን? በዚሁ ጥያቄ ራሴን እያደፕኘ ሳሟግት ሞባሴ ከተማ ደርሰናል ወረድ አለኝ ረዳቱ።

ሞባሴ ከተማ ስንደርስ ወፍሮ ቤት የዋለ ሰው መስዬ ከመኪናው ወረድኩ። ለአፒራው ግድ ባይኖረኝም አልቤርቶ ለመያዝ አፒራዬን በመጠን አረጋግፌ ወደ ሆቴል ሄጄ አልጋ ያዝኩ። በነጋታው ትልቅ ሥራ ይጠብቀኛል፤ የሥዕሉን ትርጉም ማወቅ።

ስለዚህ ከሰዓት በኋላ ያለውን ጊዜና ምሽቱን ዘና ብዬ ለማሳለፍ ፈለግሁ። ከሀሥራ ስምንት ዓመታት በፊት ለእኔ ሞባሴ ትልቅ ከተማ ነበረች። አሁን ባለኝ የኑሮና የእስተሳሰብ መጠን ግን ዘና ማድረግ ቀርቶ እንደነገሩ ለማሳደር እንኳ የማትመቸኝ መሆኑን ሳውቅ "በዚህ ዓለም የሰው ልጅ ብዙ በማየቱና በማወቁ የሚያገኘው ነገር ቢኖር በቀላሉ መደሰትን ማጣት ነው" አልኩኝ። ይገርማል ለመደሰት ብዙ ነገር ማወቅና ማግኘት አያስፈልግም ነበር።

ምሽቱን በቀዝቃዛ ስሜት እሳልፌ ለመተኛት ሞከርኩ። በጠዋት ተነሥቼ በሞባይል ካሜራ ካነሳሁትና በወረቀት ከነደፍኩት ሥዕል መሳይ የመስመሮች ጥንቅር ጋር ተፋጠጥኩ። ወደ ሥራዬ ስገባ ግና ርእሱን በርጋታ ማንበብ ስጀምር ታላቅ ተስፋ አገኘሁ።

"እሰረ ፍኖቱ ለአባ አድራል" ይላል

"የአባ አድራል የጉዛ መስመር" እንደማለት ነው

የአባ አድራሉን ማንነትና የነበረውን ዓላማ ስላወቅሁ ያለጥርጥር ቅዱሱን ጽዋ ለመፈለግ የተጓዘበትን መስመር የሚያመላክት ካርታ መሆኑን ገመትኩ። ይህ ሰው የቅዱሱን ጽዋ መገኛ ምልክት ሆን ብሎ መተው የፈለገ ይመስላል። በሸራው ቀረጢት የተከተቱት እቃዎችም የእርሱ መሆን አለባቸው ብዬ ገመትኩ። ታዲያ የአባ አድራል አስክሬን ከአርባ ሃራ ወደ ደብረ አሮን ለምን ሄደ? የሚል ጥያቄ መጣብኝ። ምን አልባት ቅዱሱን ጽዋ ለመጠበቅ በጉባኤ ያልተመረጠ ድንገት ዘው ብሎ የገባ መንገደኛ ስለሆነ ይሆናል። ለጊዜው ግን መሠረታዊ ጥያቄዬ አልነበረም። እናም ሥዕሉን ማጥናት ጀመርኩ።

ክቦቹ መስመሮች በእኩል እርቀት ከውስጥ ወደ ውጭ ትልቁ ትንሹን እየከበቡና እየሰፉ ይወጣሉ። በተለይ በካሜራው ያነሳሁትን ሳይ በጥንቃቄ በሁሉም አቅጣጫ እኩል እርቀት ያላቸው ክቦች ናቸው። በጠቅላላ ስድስት ክቦች ናቸው። ቀጥታ መስመሮቹ ደግሞ አሁንም በመካከላቸው እኩል ርቀት ይዘው ከመሐል ተነሥተው ወደ ውጭ እንደ ጨረር የሚወጡ ሲሆን በጥቅላላ ብዛታቸው ዐሥራ ሁለት ነው። የሁሉም ቀጥታ መስመሮች መጨረሻ ከውጨኛው ክብ መስመር አለፍ ብሎ የቆመ ሲሆን በአራቱ ተቃራኒ አቅጣጫ በሚወጡ አራቱ የጨረር መስመሮች መጨረሻ ላይ አንዳንድ የግእዝ ፊደላት ተቀምጠውበታል።

የግእዝ ፊደላቱም ሰ፣ ጽ፣ ደ፣ ም ናቸው። ፊደላቱ የቃል መነሻ መሆናቸውን ገምቼ ቃሉን ስፈልግ ወዲያውኑ ይህ ሥዕል በእርግጥም ካርታ ነው ብዬ ፈነደቅኩ።

ሰ = ሰሜን

ጽ = ጽባሀ (ምሥራቅ)

ደ = ደቡብ

ም = ምዕራብ የሚል መሆኑ ነው።

ቀጥሎ ክቦቹን በጥልቀት መመልከት ጀመርኩ የመጨረሻውና የውጨኛው ክብ መስመር ላይ ጸየ የሚል የግዕዝ ቁጥር ተጽፏል።

ይህ ማለት ርቀት ይሆን? አልኩ። በእርግጥ በክቦቹ ቁጥር መካከል ያለው ርቀት እኩል ስለሆነ ርቀቱን አቀናንሶ በማካፋፈል በየክቦቹ መካከል ያለውን ርቀት ማግኘት ይቻላል። ነገር ግን እነዚህ ቁጥሮች ርቀትን የሚያሳዩ ከሆነ መለኪያቸው ምንድን ነው? ሜትር ወይስ ክንድ ወይስ ሌላ? ምንም ተጨማሪ ምልክት የላቸውምና። ቁጥር ብቻ ነው። ቁጥር ወይም ፊደላት ያልሆኑ ምልክቶችን ደግሞ ማስተዋል ጀመርኩ። በዚህ ጊዜ የሞባይሉን ፎቶ ወደ ላፕቶፕ ገልብጬ በደንብ ማጥናት ጀመርኩ። ሦስት ምልክቶችን በግልጽ ማየት ቻልኩ።

> የመጀመሪያው የመስቀል ምልክት ሲሆን ከውስጠኛው ክብ መካከል ላይ በአጠቃላይ የሥዕሉ (የካርታው) ማዕከላዊ ነጥብ ላይ ተቀምጧል።
>
> ሁለተኛው የዘንዶ ምስል ሲሆን ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ ከተሰመሩት ጨረሮች በአንደኛውና በሦስተኛው ክብ መገናኛ ላይ ራሱ አርፏል።
>
> ሦስተኛው ደግሞ ሁለት የእንግሊዝኛውን ቪ የመሰሉ ምልክቶች አንደኛው ከታች ወደ ላይ ተፈጥሮውን ጠብቆ ሲቀመጥ ሁለተኛው ደግሞ ተገልብጦ የመጀመሪያው ላይ ተደፍቶበት የሚያሳይ ነው። ይህን ምልክት ላይ ልቤ ቀለጠ። ምክንያቱም ይህ ምልክት በብዙ ሥነ ጽሑፎች የቅዱሱ ጽዋ ምልክት ተደርጎ እንደሚወሰድ አንብቤ ነበርና። አባ አድሪልያም ፍሊጋውን ከመጀመሩ በፊት ስለቅዱሱ ጽዋ በአግባቡ እንዳጠና ግልጽ ነው። የበለጠ የኮምፒውተር ስክሪኑን ሰፋ እያደረኩ ላይ ይህ ምልክት የተቀመጠባቸው ሁለቱ መስመሮች ማለትም ክቡና ቀጥታው በተቆራረጠ መስመር የተሳሉና ከሌሎች መስመሮች የተለዩ መሆናቸውን ተረዳሁ።

አሁን ይህ ካርታ እንዴት ወደ መስከና ተግባራዊ ምልከታ ይወስደኛል? ብዬ ግራ ተጋባሁ። እዛው ደግሞ አርባ ሃራ ቆይቼ አባ አክሊሉን ባላያቸውና ትንሽ ፍንጭ ባገኝ ኖሮ ምን ነበረበት? ምን ይሆን እንዲህ የሚያጣድፈኝ ብዬ ተጸጸትኩ። ለመመለስ አሰብኩና ኀፍረት ተሰምቶኝ ተውኩት። በተለይ እርሳቸው "የዛሬን እንኳ አታድርም?" ያሉትን ሳስብ የበለጠ ችኮላየ ተሰማኝ፤ ውጤቱም አሳፈረኝ።

ምሥሉ ላይ አፍጥጬ ብዙ ከቆየሁ በኋላ አእምሮዬ መረጋጋት ሲጀመር የራሴን መልክአ ምድራዊ መላምት መስጠት ጀመርኩ። መስቀሉ የካርታው መነሻ ነጥብ ሆኖ ተቀምጧል። አባ አክሊሉ "ከዋሻው ውስጥ ካሉት ቅዱሳን ዐጽሞች መካከል ፍለጋህን የሚረዳ ምልክት ታገኝ ይሆናል። እርሱን ይዘህ ወደ አመጓ ቆላ ሂድ" ያሉኝ ትዝ አለኝና መስቀሉ የአመጓ ቆላ ሁራኤል ቤተክርስቲያን ሊሆን ይችላል ብዬ ወሰድኩ። ከመስቀሉ ተነሥተው ወደ ውጭ የሚወጡት መስመሮች ብዛት 12 በመሆኑ በሁለት ቀጥታ መስመሮች መካከል የ 30 ዲግሪ ልዩነት አለ ማለት ነው። ስለዚህ የሰሜኑን መስመር 0° ብለን ብንቆጥር የቅዱስ ጽዋ ምልክት ያለበት መስመር ከምሥራቅና ከደቡብ አቅጣጫ መካከል ከተሰመሩት ሁለት መስመሮች ወደ ደቡብ አቅጣጫ ላይ ካለው ነው። ስለዚህ የቅዱሱ ጽዋ የሚገኝበት ስፍራ ከቤተክርስቲያኑ በደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫ በ150 ዲግሪ ላይ ነው ማለት ነው። ምን ያክል ርቀት ላይ ነው ለሚለው በአምስተኛው ክብ መስመር ላይ ነው። ነገር ግን ይህ መስመር ከቤተክርስቲያኑ በምን ያክል ርቀት እንደተቀመጠ የሚገልጽ መረጃ በግልጽ የለም።

በመጨረሻው ክብ መስመር የተቀመጠው ቁጥር ፮፼ ( በግእዝ ስድስ እልፍ በአማርኛ ስድሳ ሺ.ሕ) የሚለው ርቀትን የሚያመላክት ይሆናል ብዬ ወሰድኩ። በዚህ መሠረት እያንዳንዱ ክብ መስመር ከማዕከላዊው ነጥብ አሥር ሺ.ሕ እየጨመረ ይሄዳል ማለት ነው። በዚህ ስሌት መሠረት ቅዱሱ ጽዋ በአምስተኛው ክብ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ከቤተ ክርስቲያኑ በ50000 ርቀት ላይ ይገኛል ማለት ነው።

ይሁን እንጅ 50000 የሚለው ቁጥር ብቻ እንጅ መለኪያ ስላልተቀመጠለት ሜትር ይሁን ክንድ አለበለዚያ ሌላ የሚታወቅ ነገር የለውም። ስለሆነም በዚህ መላምት የቅዱስ ጽዋ መገኛ ከቤተክርስቲያኑ በየት አቅጣጫ እንደሆነ እንጅ በምን ያክል ርቀት እንደሚገኝ አሁንም ፍንጭ የለውም። በመሆኑም እባ እድሪል ሊጠቀም የሚችለው የርቀት መለኪያ ምን ሊሆን ይችላል? ብዬ ማሰብ ጀመርኩ።

በመካከል ግን ሌላ ጥያቄ ብልጭ አለብኝ። የዘንዶው ምልክት ምንድን ነው? በካርታው ላይ ካላይ በተገለጸው ስሌት መሠረት የዘንዶው ራስ ያለበት ስፍራ ከቤተርክስቲያኑ በ$240^0$ በ30000 ርቀት ላይ ይገኛል ማለት ነው። በብዙ የኢትዮጵያ ክፍል ከዘንዶ ጋር የሚገናኙ አፈ ታሪክ የሚመስሉ ትረካዎች አሉ። ይህ ከሆነ የሚታወቅ ምልክት ተገኘ ማለት ነው። ስለዚህ አሁን ወደ እመጓ ቆላ የምመለሰበት ጊዜ ደረሰ ማለት ነው አልኩ።

# ምዕራፍ ዐሥራ ሰባት

በማግሥቱ እርፈድፈድ ብዬ ባለፊው አብረውኝ የተጓዙትን ወጣቶች አስከትዬ ወደ እመጓ ቆላ ወረድኩ። ደጋውን ጨርሼ ወደ ቆላው መውረጃ ስደርስ ልዩ ስሜት ተሰማኝና በተመስጦ ቁልቁል እያየሁ እንዲህ አልኩ፤

" እመጓ ቆላ ሆይ!"

"አንቺ የተባረክሽ ምሥጢራዊ ምድር!

ሶርያው አባ አድራል ቅዱሱን ቅርሰና ቃል ኪዳን በሆዷ ይዛለች ብሎ የተቀኘልሽ፣

አንቺ የቅርብ ሩቅ ማዕከላዊ ምድር ስትሆኚ ጠረፍ የሆንሽ፤

አንቺ የአደራ ማማ ስትሆኚ በተራሮች የተከለልሽ አዘቅት፤

አንቺ መላእክት የሚረብበብሽ ስትሆኚ ሰዎች ግን የናቁሽ፤

አንቺ ዓለምን የሚያስቀና ግሩም ቃል ኪዳን ያለሽ ስትሆኚ ራስሽን ደብቀሽ ተራ ሆነሽ የኖርሽ መናኝ፤

አንቺ ሁሉም ስለራሱ ሲያወራ፣ ለዘመናት ዝም ያልሽ ልጉም ሙዳይ፤

ቫቲካን ስታቅራሪ፣ ቀጵርስ ስትሮሁ፣ እስክንድርያ ስታመሰጥር፣ ኢየሩሳሌም በጸጸት ስትቃትት፣ ለንደን ያለስጠታዋ ስትቦተልክ፣ ፈረንሳይዋ ማርሴይ በምኞት ስትቃዥ ምንም የማይመስልሽ ፤ እርምጃን የመረጥሽ አሳቻ ታዛቢ፣

የእንቶቾችሽን የአክሱምን፣ የግሸንን፣ የላሊበላን፣ የጣና ቂርቆስን ያክል እንኳን ፊትሽ የማይፈታ የተቋጠርሽ ሽማ! ዓለም ሁሉ ወደ እነርሱ ሲጉርፍ ቅናት የለሌብሽ ልዝብ ደርባባ፡" እያልኩ በለሆሳስ አነበነብኩ።

ገደሉን ወርደን ከቤተክርስቲያኑ ስንደርስ እማሆይ ዕሴተ ማርያም በፈገግታ ተቀበሉኝ። ቀኑን ሙሉ ስለአባ እክሊሉ ጨንነትና ስለ ደብረ ብርሃን ጉዞአችን እያወራኋቸው አሳለፍን። በመሐል እንደዋዛ

"አባ ስለፍሊጋህ ምን አሉህ?" አሉኝ

"ምንም የሚጨበጥ ነገር አልነገሩኝም" አልኩ። በተራዬ ምሥጢር ጠባቂ ለመምሰል ሞከርኩ።

"አያይ! አባ እክሊሉ እንኳን የሚናገሩት ነገር መሬት ጠብ የሚል የለውም። ምናልባት በደንብ አልተረዳሃቸው ይሆና" አሉ።

"ይሆናል" አልኩና ርእሱ መነሳቱ ጥሩ አጋጣሚ ስለፈጠረልኝ፡

"እማሆይ! እዚህ አካባቢ ስለ ዘንዶ የሚነገር አፈታሪክ ወይም የተጻፈ ታሪክ ይኖር ይሆን?" አልኳቸው።

"አለ እንጅ! ያውም እውነተኛ ታሪክ" አሉ

"እውነትምን ነው?!" አልኩ በጉጉት።

"በዘመነ አሪት እዚህ አካባቢ የሰይጣን መንፈስ ያደረበት የሚገመስስ ዘንዶ ነበር። እናም ሕዝቡ ተራ ገብቶ ዘወትር ጊደር እየታረደ ደሙ በገቢታ ይደርግና ይቀርብለት ነበር" አሉ። ይህን ሲነግሩኝ የእቃ ቤት ጠባቂው መነኩሲ መጡና በላምታ ሰጥተውን ጨዋታችን ተቀላቀሉ።

"እናልህ ለብዙ ዘመን በዚህ መልክ ሲመለክ ኖሮ በመጨረሻ መልአኩ ቅዱስ ዑራኤል መጥቶ ዘንዶውን ገድሎ ህገሩንም ባረከው ይባላል" አሉ።

"ስለዘንዶው እየነገሩት ነው?" አሉ አባ በመሐል አቋርጠው።

"አዎን ስለ ዘንዶው ታሪክ" አሉ እማሆይ

"አዎን ምስጋና ይግባው ለመዳኒያለም። በአዱስ ዑራኤል ተረዳይነት አገሩ ነጣ ወጣ። እንዲያውም እኮ መላኩ ዑራዔል ከዘንዶው ላይ ያረፈውን አጋንንትና ቁፈራውን በሙሉ ሰብስቦ በብርሃን መስኸል በአማተበባቸው ጊዜ ሁሉም ወደ ጥኡር ድንጋይ ተኸየሩ። እስተ ዛሬ ድረስ ድንጋዮቹ እንደተሰበሰቡ አሉ። ለታሪክ ብታየው ግሩም ትላለህ" አሉ።

"በእውነት ለዘንዶው የሚሰዋበት ዛሬም ድረስ ተለይቶ የሚታወቅ ቦታ አለ?" አልኩ፤

"አዎን! ድንጋዮቹ ብቻ ሳይሆን ለዘንዶው የጊደር ደም ይኸርብበት የነበረው ጉድጓዳ ድንጋይም አለ። 'የዘንዶ ገበታ' ይባላል" አሉ

የደስታ ስሜቴን ተቆጣጥሬው ነው እንጅ መቼም ውስጤ ተፍነከነኳል።

"የዘንዶ ገበታ ከሚባለውና ከድንጋዩ ሰብሰብ መሄድ ይቻል ይሆን" ስል ጠየቅሁ።

"አዎን! በልጅነት ኸብት የምናግድበት የነበረ ቦታ እኮ ነው። ከዚህ ብዙም ሩእ አይደለም" አሉ።

ሰዓቱ ወደ ዐሥራ አንድ ከሃያ አካባቢ ነው። እንዲያው ይታዘቡኛል ብዬ ነው እንጅ ያኔውኑ ወደ ቦታው መሄድ አሰኝቶኝ ነበር። እራሴን አረጋጋሁና

"እማሆይ ብየ ተማርቼ ዘወር ሲሉ ቦታውን ማየት እፈልጋለሁ ሊረዱኝ ይችላሉ?" አልኳቸው።

"ምን ችግር አለው! ጠዋት ከአንድ ልጅ ጋር እልክሃለሁ" አሉኝ በፈገግታ።

እንዳይነጋ የለም ሌሊቱ ነጋልኝ። በጠዋት ተነስቼ በያዝኩት ጅፒኤስ (GPS) የእመጓ ቀላ ቅዱስ ዑራኤል ቤተክርስቲያንን ሉላዊ ቦታ መዘገብኩ። እኔ ይህን ሳደርግ እማሆይ ከሰፈሩ አንድ የሀሥራ ሀራት ዓመት የሚሆን አዳጊ ወጣት አመጡልኝ።

"ጎይልዬ እሱ ይወስድሃል። ታዲያ በዚያው እንዳትውሉ" አሉኝ።

"ቶሎ እንመለሳለን" ብዬ ልጁን አስቀድሜ መንገዝ ጀመርኩ። አርባ ደቂቃ ያክል አቀበት ቁልቁለት የበዛበት መንገድ የደቡብን አቅጣጫ ይዘን ከተጓዝን በኋላ

"ጋሽ ይኸውልህ ድንጋይ የሆኑት አጋንንቶች" አለኝ።

ዐይኔን ማመን አቃተው። ቁጥራቸው ከመቶ በላይ የሚሆን መጠናቸው ትልቅ ሰው የሚያክሉ ጥቋቁር ዐለታማ ድንጋዮች አንድ ቦታ ለስብሰባ የተጠሩ መስለው ተቀምጠዋል። ታሪኩን መቀበል አለመቀበል ሌላ ነገር ሆኖ የድንጋዮቹ አቀማመጥ በራሱ ግን በአግራሞት አፍ ያስከፍታል። "ወይ ጉድ!" አልኩ በአድናቆት። ጥቂት ቆየሁና "የዘንዶ ገበታ የሚባለውስ የት ነው?" አልኩት። ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በከፍታ የተገተረ ኮረብታ እያሳየ

"ተዚያ ላይ ነው" አለኝ።

"እባክህ ወደዚያው መሄድ እፈልጋለሁ" አልኩት። "ምን ችግር?" አለና በልጅ እግሩ ፈጠን ፈጠን እያለ ወደ ኮረብታው መራኝ። ከሃያ ደቂቃ እድካሚ የዳገት ጉዞ በኋላ ጠበብ ያለ ደልዳላ አምባ ላይ ደረሰን።

አምባው በምዕራብ አቅጣጫ ከሌላ ከፍታ ካለው ተራራ ጋር የተያየዘ ነው። ከተራራው ሥር ትልቅ ጥቁር ድንጋይ አለ። ልጁ ወደዚያው አመራና

"ይኼ ነው የዘንዶ ገበታ የሚባለው" አለኝ።

ሽበት የወረረው ወጥ ከብ መሳይ ድንጋይ ሆኖ ቁመቱ ዘጠና ሳ.ሜ. ሲሆን መሐል ላይ ስፋቱ ሰባ ሳ.ሜ. በ ሃምሳ ሳ.ሜ. ሲሆን ጥልቀቱ ደግሞ በሥሩ አምስት ሳ.ሜ. የሚሆን ጉድጓድ አለው። ገበታ ያሰኘው ይሄ ነው። እንደ ታሪኩ ከሆነ እዚህ ላይ ነው ለዘመናት ለዘንዶው የሚደርር ደም ይሰዋለት የነበረው።

ትንሽ ዕረፍት ካደረግሁ በኋላ ጂፒኤስ አውጥቼ ሉላዊ ቦታ ያለበትን ትክክለኛ ነጥብ ወሰድኩ። ከዚያም ከቤተክርስቲያኑ ላይ ከወሰድኩት ነጥብ ጋር አስተያየሁ። የዘንዶው ገበታ ከቤተክርስቲያኑ በ245° አቅጣጫውን ዲግሪ ላይ መገኘቱን አወቅኩ። በጣም ይገርማል! ከአባ አድራል ካርታ በመነሣት ያወጣሁት መላምት ጋር እጅግ ተቀራራቢ ሆነ ማለት ነው። የአባ አድራል ካርታ በትክክል የተሠራ መሆኑን አረጋገጠልኝ። ይህ ማለት የቅዱሱ ጽዋ መገኛም እንደገመትኩት በካርታው ላይ በተሳለው ዲግሪ መሠረት ይሆናል ማለት ነው። አባ አድራል በቂ የካርታና የመልክአ ምድር እውቀት ሲኖረው እንደሚችል መገመት ይቻላል። እስከዚያ ይህን የመሰለ ጉዞ ለማድረግ መጀመሪያውኑ አይሞክርም ነበርና።

በጂፒኤስ ርቀት መለኪያ መሠረት የዘንዶው ገበታ ከቤተክርስቲያኑ በ3.6 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ይገኛል። ይሁን እንጂ ከቤተ ክርስቲያኑ ወደ ዘንዶው ገበታ በመሬት ላይ የተጓዝነው ግን 4.7 ኪ.ሜ. ነው። ይህም የጂፒኤስ ርቀት ስሌት በቀጥታ መስመር ርቀት መለኪያ ስለሆነ ነው። ሁለቱም ቁጥሮች ከአባ አድራል ካርታ ላይ ከተመለከተው ቁጥር ጋር ፈጽሞ አይገናኙም።

ይህ ማለት አባ አድራል የተጠቀመበትን የርቀት መለኪያ እስከሳወቁት ድረስ ቅዱስ ጽዋ ከቤተክርስቲያኑ በየት አቅጣጫ እንደተደበቀ እንጀ በምን ያክል ርቀት እንደተቀመጠ ፍንጭ የሚሰጥ አለመሆኑን ተረዳሁ።

መልክአ ምድሩን ሳየው በዘንዶው ገበታ ግርጌ ትልቅ ሸለቆ ያለ ሲሆን በምሥራቅ አቅጣጫ ደግሞ ከፍታ እየጨመረ የሚሄድ የተራራ ሰንሰለት እንዳለ ተረዳሁ። ግዶ ካለው ተራራ ላይ የተለየ ነገር ወይ ቤት ካለ ብዬ አሻግሬ ማማተር ያዝኩ። ምንም የተለየ ፍንጭ የለም። በተስፋ መቁረጥ ስሜት ከአንድ ድንጋይ ላይ ሄጄ ቁጭ አልኩ። በሀሳብ ሰንገላታ ከቆየሁ በኋላ ድንገት አንድ ሀሳብ ብልጭ አለልኝ። ወጣቱን "ወደ ቤተክርስቲያን በፍጥነት እንመለስ" አልኩት።

የተከሰተልኝ ሀሳብና መላምት ቀላል የሥነ መሬት አመክንዮዋዊ ስሌት ነበር። የቅዱሱን ጽዋ ማረፊያ በሁለት መንገድ በንጽጽር ልኬት ማስላት ነው።

አንደኛው ዘዴ በአባ አድራል ካርታ መሠረት የዘንዶው ገበታ ከቤተክርስቲያኑ በ30000 (መለኪያው አይታወቅም) ርቀት ላይ ሲገኝ ቅዱሳ ጽዋ ደግሞ በ50000 ላይ ይገኛል። በእኔ ጂፒኤስ ደግሞ የዘንዶው ገበታ በቀጥታ ርቀት 3.6 ኪ.ሜ. ላይ ይገኛል። ስለዚህ 30000 3.6 ኪ/ሜ ከሆነ 50000 ምን ያክል ይሆናል ብሎ ማስላት ነው።

ሁለተኛው ዘዴ ደግሞ ምናልባት 30000 የርቀት መለኪያ ካልሆነ ካርታውን በፎቶ አንስቼ ወደ ኮምፒውተር ስለገለበጥኩት ስክሪኑ ላይ የካርታ ርቀቱን መመልከት ነው። በዚህ መሠረት የዘንዶው ገበታ 3.5 ሳ.ሜ. ከቤተ ክርስቲያኑ የሚርቅ ሲሆን የቅዱስ ጽዋ ምልክት ደግሞ 5.8 ሳ.ሜ. ላይ ይገኛል። ስለዚህ 3.5 ሳ.ሜ. 3.6 ኪ.ሜ. ከሆነ 5.5 ሳ.ሜ. ስንት ኪሎ ሜትር ይሆናል ብሎ ማስላት ነው።

በሁለቱም ስሌት በጣም የተቀራረበ ቁጥር አገኘሁ። በመጀመሪያው 6 ኪ.ሜ.፣ በሁለተኛው ደግሞ 5.96 ኪ.ሜ.። አሁንም አባ አድሪል ካርታውን መለኪያው በማይታወቅ ነገር ግን ሎጂካል በሆነ ነገር እንደሰራሁ አመንኩ።

ስለዚህ ቅዱሱ ጽዋ ከቤተክርስቲያኑ በ150° ዲግሪ በ6 ኪ.ሜ. ቀጥታ ርቀት ላይ ይገኛል ማለት ነው አልኩ። ድንገት ብድግ ብዬ በደስታ ወደ ላይ ዘለልኩ። “ደረስኩበት!” አልኩ።

ከዚህ በኋላ ጊዜ ማጥፋት አያስፈልግም። መሪ ወይም ተከታይም አያሻኝም። አሁን ብቻዬን መሄድ እችላለሁ። የሆነ ልበ ሙሉነት ተሰማኝ።

ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሄድኩና ከሕንፃው ተጠግቼ ጂፒኤሱን 150° አቅጣጫ 6 ኪ.ሜ. ርቀት ሞላሁና እንዲመራኝ አስተካክዬ ጉዞ ጀመርኩ። ይህ ዘመናዊ የናቪጌሽን ዘዴ አቅጣጫን ከርቀት ጋር አጣምሮ አንድን ቦታ ለማወቅ ወይም የመጡበትን ወደ ኋላ ፈልጎ ለማግኘትና ለመመለስ የሚያስችል ነው። ትንሽ እንደተጓዝኩ ጂፒኤሱ የሚያመለክተው አቅጣጫ ለእግር ጉዞ የማያመች መሆኑን በረዳ ከርቀት ተራራው ላይ ምልክት ይገፍ በደንናው መንገድ መጓዝ ጀመርኩ።

በመሐል የሆነ ሀሳብ ይፈታተነኝ ጀመር። “አሁን እኔ ቅዱሱን ጽዋ ለማየት የተገባሁ ነኝ?” ድንገት ፍርሃት ተሰማኝ። “ይህ የቅድስና ወይም የንጽሕና ጉዳይ አይደለም። ይህ የታሪክና የፍቅር ጉዳይ ነው። በሕይወቴ እጅግ ክብር የምሰጠው ጉዳይ ቢኖር የክርስቶስ በዚህ ምድር መመላለስ ነው። ከሁሉ የሚበልጠው ደግሞ ለሰው ልጅ ሲል መሞቱ ነው። ታዲያ ይህ ክቡር የመሥዋእትነት ደም የፈሰሰበትና የተቀዳበትን ጽዋ ከማየት በላይ ምን የሚገባኝ ነገር አለ?!” ስል ራሴን አደፋፈርኩት።

"ማን ምንድን ነው የማደርገው? መጀመሪያ በታላቅ አክብሮት በማንባሬ ተደፍቼ እሰግድለታለሁ። ከዚያም በታላቅ ፍቅር እስመዋለሁ። ከዚያም ሰላምን እጕናፀፋለሁ። ለካ መንካት አልችልም። ምክንያቱም ከሀት የለኝም። እምን ፎቶ ግራፍ እነሳዋለሁ። እጽፍለታለሁ። ከዚያም ለሀገር ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ፣ በእርሳቸው አማካኝነት ለፓትርያርኩ አገኙት ብዬ እበሰራቸዋለሁ። ከዚያስ!"

"ከዚያ ደግሞ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ጋዜጠኞች ቦታውን እንዲያዩት፣ ኢትዮጵያ ቅዱሱን ጽዋ በእደራ ይዛ የምትኖር ቅድስት ሀገር ብለው በዓለም እንዲናኙላት እነግራቸዋለሁ። ቫቲካንም፣ ለንደንም፣ ማርሴይም፣ ቆጵሮስም፣ ደማስቆም፣ ኬብሮንም ዝም ይበሉ።"

እንዲህ በሀሳብ እየቃኘሁ ማዶ ጋራ ላይ ምልክት ካደረኩት ስፍራ ደረስኩ። ጂፒኤሱን ሳየው አቅጣጫዬን በመጠኑ እንደሳትኩ አወቅሁ። አቅጣጫዬን አስተካክዬ ርቀቱን ስመለከት 5 ኪ.ሜ አካባቢ እንደደረስኩ አመላከተኝ። ፊት ለፊት ዳገቱ እየጨመረ ይሄዳል። አሁን ቀጥ ብዬ መሄድ አለብኝ አልኩና ፊት ለፊት መጓዝ ጀመርኩ። ፊታኝ አቀበት ከወጣሁ በኋላ ጸጥታ የሞላበት አልፎ አልፎ ዛፍ ያለበት ስፍራ ደረስኩ። ጂፒኤሱ ጢን..ጢን የሚል ድምጽ አሰምቶ ከምፈልገው ስፍራ እንደደረስኩ አሳወቀኝ። ዙሪያውን ቃኘሁት። ከጸጥታና ከአስፈሪ ግርማ በስተቀር ምንም የተለየ ነገር በአካባቢው የለም። ትልልቅ ቋጥኝ፣ እድሜ ጠገብ የወይራ ዛፎችና ቁጥቋጦ በቃ። አካባቢው ለእርሻም፣ ለእንስሳት ግጦሽም አይሆንም። በጣም ተራራና ተዳፋታማ በመሆኑ እራሱን ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ነጻ አድርጓል።

ለአንድ ሰዓት ያክል አካባቢውን አሰስኩት። ምንም ዋሻ ወይም ሰው ሠራሽ መጠለያ የሚባል ነገር የለም። እንደገና ደግሜ ጂፒኤሱን አየሁት። አቅጣጫውም ርቀቱም ትክክል ነው። ድካምና ረሀብ ተጋግዘው ተስፋ አስቆረጡኝ። ቀኑም እየመሸ ስለነበረ በማግስቱ ፍለጋዬን ለመቀጠል ወስኜ ወደ እማሆይ ዕሴተ ማርያም ጉጆ ተመለስኩ።

ከጉጆው ስደርስ መሸትሸት ብሎ ነበር። እማሆይ ሲያዩኝ "መጣህ ኃይለ ጊዮርጊስ ሳስብ ነበር። በዚያው እኮ ጠፍተህ ቀልክ!" አሉ።

"ከአንዱ ወደ አንዱ ስንከራተት ሳላስበው መሸ አልኳቸው"።

በጣም ደክሞኝ ስለነበረ እግሬን በቀዝቃዛ ውሃ ታጥቤ መደብ ላይ ጋደም አልኩ። ማታ እራት በልተን እማሆይ ለጸሎት ከመነሣታቸው በፊት እንዲህ አሉኝ፣

"እንዳው ምናለበት ባትንከራተት። ቅዱሱ የኪዳን ቅርስ እንደሆን እዚህ ለመኖሩ እርግጠኛ የሆንክ ይመስለኛል። ታዲያ ለምን ደስ ብሎህ በዚህ ረክተህ ወደ ቤትህ አትሄድም" አሉኝ።

"እማሆይ ነግሬዎታለሁ። እዚህ ድረስ መጥቼ ሳላየው አልሄድም። በቃ! ማየቱ ያንጻኛል ብዬ አምኛለሁ። ካዘኑልኝ በታውን ያሳዩኝ" አልኳቸው ፈረጠም ብዬ።

"በል እንዳሻህ" አሉና "ለመሆኑ ዛሬ የት ሄድክ?" አሉኝ።

"ጠዋት ከዘንዶው ገበታና ጥቋቁር የአጋንንት ድንጋዮች የሚባሉት ካሉበት ሄድኩ። ከዚያ ተመልሼ ወደ ቤተክርስቲያኑ መጣሁ። ከዚያ ከሰዓት በኋላ ደግሞ አልኩና" ዝም አልኩ

"ከዚያ ከሰዓት የት ሄድክ?" አሉ እማሆይ፣

"ከሰዓት በኋላ ከዘንዶው ገበታ ባሻገር ካለው ተራራ ነው የዋልኩ" አልኳቸው።

"ምን?!" አሉ እማሆይ በታላቅ ድንጋጤ ጮኸው።

"ምነው እዚያ አካባቢ አይኬድም እንዴ?" አልኩኝ። እማሆይ ሳያስቡት እንደጮሁና ድንጋጤያቸው እንዳጋለጣቸው ሲረዱ እንደመረጋጋት ብለው

"ኧረ እሱስ ችግር የለውም። እንዲያው እዚያ ድረስ ምን ወሰደህ ብዬ ነው እንጂ" አሉ።

"የማርያም ፈረስ አልኳቸው" ፈገግ ብዬ። ድንጋጤያቸው በትክክል ከቅዱሱ ስፍራ እንደ ደረስኩ አረጋገጠልኝ። ስለዚህ ቀደም ብዬ በጥዋት ለመሄድ ኃይል አገኘሁ።

እማሆይ እስከ ድንጋጤያቸው ለጸሎታቸው ቆሙ። ከሌሊቱ ዐሥራ አንድ ሰዓት እማሆይ ኪዳን ለማድረስ ሲነሱ የተኛሁ መስዬ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ እስኪሄዱ ጠብቄ በፍጥነት ለባብሼ ወጣሁና ወደ ቅዱስ ተራራ አመራሁ። ትንናት ከዋልኩበት ስደርስ በደንብ ነግቶ ነበር። ተራራው ጭራሽ ጸጥ ረጭ ብሏል። ከዚያ ከአንድ ጥግ ጀምሬ በጥንቃቄ አካባቢውን አሰስ ጀመር። ትላልቅ ቋጥኞች እርስ በርሳቸው ተቆላልፈው ለሚያያቸው ልዩ መስህብ አላቸው። አንድ የወይራ ዛፍ አካባቢ ስደርስ ልዩ የሆነ መዓዛ አወደኝ። ደጋግሜ ማግ አደረኩት። "የአምላክ ያለህ የዕጣን ሽታ!" አልኩ።

በአራቱም አቅጣጫ እየተዘዋወርኩ አየሩን በማም ወደ አፍንጫዬ እየሳብኩ የዕጣኑ ሽታ የሚመጣበትን አቅጣጫ ለመለየት ሞከርኩ። ከደቡብ አቅጣጫ ነው የሚመጣው። ወደ ዚያው ሄድኩ። የዛፎች ቁጥር እየበዛ ግርማው እየጨመረ መጣ።

ወደ ጫካው ውስጥ እየገባሁ ተራራውንም ወደ ላይ እየወጣሁ በመጠኑ እየበረከኩት በሄድኩ ቁጥር የዕጣኑ መዓዛ የበለጠ ያውደኝ ጀመር። በመጨረሻ በሐረግ ሥር የተተበተበ ዋሻ የሚመስል ስፍራ ደርስኩ። በጸጥታ አካባቢውን ቃኘሁት። የሐረጉን ሥር ከግራ ወደ ቀኝ ተጠግቼ ሳየው ጠንካራውን ዓለት ሸፍኖታል። ወደ መሐል አካባቢ ጥቁሩ ዐለት ወደ ግራጫ ነገር ተቀየረ። የሐረጉን ሥር ገለጥ አድርጌ ሳየው እንጨት ነው። ሐረጉን አሁንም በደንብ ገለጥ ሳደርገው በር መሆኑን አወኩ። ሰገፉው ተዘግቷል። በደንብ ተጠግቼና ጆሮዬን ለጥፌ ሳዳምጥ ከዕጣኑ መዓዛ ተጨማሪ ዜማ የሰማሁ መሰለኝ። በሩን በደንብ ገፋሁት፤ ንቅንቅ አልል አለ።

ከውስጥ በኩል ለመቀርቀሩ እርግጠኛ ሆንኩ። ከበሩ ግራና ቀኝ ለመዘዋወር ስሞክር ጭራሽ ሰው የማያሳልፍ ገደል ሆነብኝ ተመልሼ በሩ ሥር ሄጄ ቆሞ አልኩ።

ለምን ያክል ጊዜ እንደሚሆን ባላውቅም በሩ እስኪከፈት እዛው ለመቆየት፣ ለማደር ፣ ለመክረምም ልቤ የወሰነ መሰለኝ። "እርድእቱ ለቅዱሱ ቅርጽ ጠባቂዎች የሚያስፈልጋቸውን ቁሳቁስ ወይም ቀለብ በየወሩ በቅዱስ ዑራኤል በዓል ቀን በምሥጢራዊ ቦታ ያስቀመጡላቸዋል" በማለት እማሆይ ዕሌተ ማርያም የነገሩኝ ቦታ ይህ መሆን አለበት አልኩ።

መቀመጥ ሲሰለቸኝ ተነሥቼ በሩንና አካባቢውን በደንብ ማጥናት ያዝኩ። ቀደም ሲል ያላስተዋልኩት ከበሩ ከላይኛው ጠርዝ በቀኝ በኩል ትንሽ ወረድ ብሎ ከጥቁሩ ዐለት ላይ ትንሽ ቀዳዳ አየሁ። እጅ ታስገባለች፣ የሆነ ነገር አእምሮዬ ውስጥ ተገለባብጦ ጠፋ። ቀዳዳውንና አካባቢውን የበለጠ ስፈትሽ ከሐረጉ ሥር ጋር ተመሳስላ የተቀመጠች አንድ ክንድ የምትሆን የብረት ዘንግ ያላት የጠፍር አለንጋ አገኘሁ። ወዲያውኑ ዋሻ እንድርያስ ቤተክርስቲያን ያየሁት ነገር ትዝ አለኝና ልቤ ረገጥኩ።

ዋሻ እንድርያስ ደቡብ ጎንደር ሊቦ ከምከም ወረዳ ውስጥ ከጣና ሃይቅ በስተምሥራቅ በሊቦ በንሰለታማ ተራሮች ውስጥ ከባሕር ዳር ወደ ጎንደር በሚወስደው መንገድ ከጣራ ገዳም በስተ ምዕራብ በግምት በዐሥር ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ ጥንታዊ የዋሻ ውስጥ ቤተክርስቲያን ነው። ዋሻ እንድርያስ በ13ኛው መ.ክ.ዘ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ደቀ መዝሙር በነበሩት በአቡነ እንድርያስ ዘመርሐ ቤቴ እንደታነጸ ገድላቸው ይናገራል። ይህ በተፈጥሮ ደንና በእድሜ ጠገብ ዛፎች ተከልሎ የሚኖርና በተፈጥሮ ዋሻ ውስጥ የታነፀ ቤተክርስቲያን በርካታ ቅርሶች ያሉት ሲሆን በተለይ የአራት መሠዊያው፣ ከእንጨት የተሠራ ቃጭል፣ የድንጋይ ደወሎች፣ ጥንታዊ የገበጣ መጫወቻ፣ የቀድሞ ነጋሪቶች፣ ግርምትን የሚፈጥሩ ናቸው።

አጠቃላይ ኪነ ሕንፃውና አሠራሩ ከአከባቢው ይልቅ ከላስታ ቀደምት አብያተክርስቲያናት ጋራ ተቀራራቢነት አለው።

ይህን ቦታ የጎበኘሁበት ጊዜና ሁኔታ የሚገርም ነው። አንድ ረቡዕ ቀን ጎንደር ከተማ ለስብሰባ ሄድኩ። ስብሰባው የአንድ ቀን ተኩል ነበርና በበነጋው ሐሙስ ዕለት ወደ አምስት ሰዓት አካባቢ ተጠናቀቀ። በስብሰባው ደስተኛ አልነበርኩም። እናም ከአዳራሹ እንደወጣሁ ሾፌሬን

"እባክህ አሁኑኑ ወደ ባሕር ዳር  እንሂድ" አልኩት።

"ምነው በደኅና?" አለኝ።

"አዎን ደኅና ነኝ። በቃ መሄድ ፈልጌ ነው" አልኩት። ጥንቁቁና ትሑቱ  ሾፌር መኪናውን ከጎንደር ወደ ባሕር ዳር ያግለበልበው ጀመር። ከኋላ ወንበር ቁጭ አልኩና እንደ ማሸለብ አድርጎ እንቅልፍ ወሰደኝ። ለምን ያክል ሰዓት እንደተኛሁ ባላውቅም ስነቃ የጣራ ገዳም ተራራን እየወጣን መሆኑን አየሁ። ዳገቱን ጨርሰን ከደልዳላው ላይና ከገዳሙ መግቢያ ፊት ለፊት ስንደርስ ከመንገዱ በስተቀኝ "ዋሻ እንድርያስ" የሚል ታፔላ ተመለከትኩ። ምን እንደገፋፋኝ አላውቅም

"እባክህ ወደ ዋሻ እንድርያስ እንሂድ" አልኩት

"ምነው አልደከመህም እንዴ?" አለኝ

"ስለደከመኝማ ነው " አልኩት በፈገግታ

መኪናውን ወደ ቀኝ አዙሮ ኮረኮንች መንገድ ውስጥ አስገባና አቁሞ ወረደ። ስለመንገዱ ሊጠይቅ እንደሆነ ገብቶኛል። ሰዎችን ጠይቶ ተመለሰና "መኪና ያስገባል ብለውኛል" አለኝ። "በጣም ጥሩ" አልኩት። መንገዱ ዳገት ቢኖረውም ብዙም ሩቅ አይደለምና ደረስን። መኪናውን አፋፉ ላይ በዛፎች መካከል አቁመን ወደ ዋሻው ቁልቁል ወረድን።

ስንደርስ ቅዳሴ ገብቶው ኖሮ ፍሬ ቅዳሴ ከሚባለው ላይ ደረስን። ግራ ገባኝ። ምክንያቱም ዕለቱ ሐሙስ ሲሆን ወራቱም የፊቅድም የሕግም ጾም ጊዜ አልነበረምና። ለማንኛውም ቅዳሴ እስኪያልቅ ከአንድ ዛፍ ስር ቆምኩና የቅዳሴውን ዜማ ከወፎች ዝማሬ ጋር መንፈሴን መመገብ ጀመርኩ። ቅዳሴው ወደ ዘጠኝ ሰዓት ተኩል አካባቢ አለቀ። ልዑካኑና አስቀዳሾ ሁሉ ተሰባስበው ወደ ደጀ ሰላም ገቡ። ደጀ ሰላሙ ከቅጥሩ ውጪ በደቡብ ምሥራቅ በኩል ግድግዳው በባሕር ዛፍ ፍልጥ ጣራው ደግሞ በቆርቆሮ የተሰራ ነው። እኛም እንግዶች መሆናችን ስለታወቀ ተጋብዘን ከቀዳሾቹ ጎን ከፍ ያለ ቦታ ላይ እንድንቀመጥ ተደረገ። "እንግዳ ክቡር ነው" አሉ። ኋላ ላይ እንደተረዳሁት ክርስትና የሚነሳ ሕፃን ስለነበረ ነው በአዘቦት ቀን ቅዳሴ የገቡት። ክርስትና የሚያስነሱት ቤተሰቦች ያሰናዱት እንጀራ በሽንብራ ክክ ወጥ ከጠላ ጋር በታላቅ ልግስና ቀረበ።

ከዚናቱ ከድቶማቸው እንዳረፉ ግምቼ ሲከበከቡኝ የቆየውን ጥያቄ ሰነዘርኩ።

"ዕለቱ ጾም አይደለም። አዘቦት ቀንም ነው። በብሉት ቀን በከተማ በጠዋት ነው የሚቀደስ። ለምንድን ነው ውላችሁ የቀደሳችሁ?" አልኩኝ በትሕትና፣

"እውነት ነው። ደኅና አስተውለሃል" አሉ በፈገግታ ከመካከላቸው በዕድሜ ከፍ ያሉት መነኩሴ። ከአየኋቸው ጀምሮ ከሁሉም ጋር በፈገግታ በጨዋታ የሚነጋገሩ ፍስሐ የሆኑ ሰው ናቸው። "አባ ብርሃን መስቀል እባላለሁ" ብለውኝ ነበር።

"እውነት ነው። በገዳማትና በገጠር አብያተክርስቲያናት ሁልጊዜም ከእሑድና ከቅዳሜ እንዲሁም ከልደትና ከጥምቀት ቀናት በስተቀር ውሎ ነው የሚቀደስ። ይሄ እንግዲህ ከአባቶቻችን ጀምሮ የቆየ ሥርዓት ነው። ዋናው ምክንያት እ..." አሉና

"የገጠር ነዘን ገበሬም ጭምር በመሆኑ ነው። ልጅ ያሳድጋል፣ እንግዳ ይቀበላል፣ ለመንግሥት ይገብራል። እና ከቀደሰና ከቆረበ በስተኋላ እስከሚቀጥለው ቀን ድረስ ሥራ መሥራት አይፈቀድለትም።

ስለዚህ አስተሰዓት ድረስ በሬ ጠምዶ ሲያረስ እንዲውል፣ አረምም፣ አጨዳም፣ እንዳለው እንዳይቦዝን ነው። እየሀ የገጠር ካህን ይችን ቀድሰን ውለን ከምንቀምሳት እህል ውሃ ውጪ ኑሮ የሚደጉም በቂ ደመወዝ የለንም። ሌሊት ሰዓታት ቢቆም፣ ማኅሌት ቢቆም፣ ኪዳን ቢያደርስ፣ ቅዳሴ ቢቀድስ፣ አጥምቆ ቢያቆርብ፣ አጥቦ ገንዞ ውሎ ፍታት ፈትቶ ቢቀብር እንደማንኛውም ገበሬ ጥሮ ግሮ ነው የሚኖር። ከምእመናን ተሰብስቦ በዐመት የሚሰጠው ገንዘብ የሚጠመጠመው ሻሽ ይገዛለት እንደሆን እንጅ ልጅ አያሳድግበትም። የገጠር ካህን እውነተኛ የክርስቶስ ባሪያ ነው። ልጄ" አሉ እየተፍለቀለቁ ፤

"እሁን በደንብ ገብቶኛል" አልኳቸው።

አባ ብርሃኑ መስቀል ቀጠሉና "ለማንኛውም ን ቤተክርስቲያኑን ላስጎብኛችሁ" አሉና ተነሱ።

ሁሉም ሰው ወደ ደጀ ሰላሙ ሲገባ የሞቫው መግቢያ በር ተቆልፎ ስለነበር በስተውጭ ያለው ሰረገላ ቁልፍ ከተከፈተ በኋላ እንደገና ከላይ በኩል ባለች ትንሽ ቀዳዳ አለንጋ መሳይ ቁልፍ ሰደው አባ በሩን በድጋሚ ከውጭ ሆነው በስተውስጥ በኩል ሲከፍቱት በሩ ወለል ብሎ ተከፈተ።

በጥንታዊ የዋሻ አብያተክርስቲያናትና ቤተ መዘክሮች የእንጨት በር ከውስጥ በኩል ተወርዋሪ ጠንካራ እንጨት ወይም መሎጊያ በልዩ ጥበብ ይሰራሉታል። በሩ በተዘጋ ቁጥር ተወርዋሪው እንጨት በራሱ ጊዜ ተወርውሮ በሩን ከዋሻው ዐለት ጋር አጣብቆ ይይዘዋል። ስለዚህ በሩ ወደ ውስጥ አይከፈትም ማለት ነው። ታዲያ አለንጋዋ በቀዳዳዋ በስሏት ስትገባ ከመወርወሪያው አጀታ ላይ ትገባና ወደ ውጭ ስትሳብ መወርወሪያውን ወደ ጎን ትስበዋለች ። ያኔ በሩ ይከፈታል። ስለዚህ አለንጋዋ እንደ ማስተር ኪ (ዋና ቁልፍ) ሆና በጠባቂዎች ምሥጢራዊ ቦታ ትቀመጣለች። እንደ እውነቱ ከሆነ የዚህ ዓይነት የበር መዝጊያ መሠረታዊ አሰራር ከዚህ እንደተገለጸው ቀላል ሳይሆን ረቀቅ ያለ ቴክኖሎጂ በመሆኑ በወቅቱ በጣም ነበር የተደነቅሁት።

በሩ ተከፍቶ ጫማችንን አውልቀን ወደ ውስጥ ዘለቅን። በርካታ ቅርሶችን ከተመለከትን በኋላ ከዋሻው የውስጠኛውና በስተሰሜን ባለው ግድግዳ በኩል ወሰዱንና ጨለማ ክፍል አሳዩን።

"ምንድን ነው? " አልኳቸው

"የዋሻ ውስጥ መንገድ ነው" አሉና "በተለምዶ ዋሻ ተክለ ሃይማኖትንና ዜና ማርያምን የሚያገናኝ ነው ይባላል። ነገር ግን ከዚያም በላይ አልፎ ይሄዳል" አሉ።

"ወደ የት?" አልኳቸው፡

"ያንማ ገብቶ ማየትና መመርመር ነው እንጅ" አሉ ፍክት ብለው። መቼም የአምስት ዓመት ሕፃን ነው የሚመስሉት። "እንዲህ ያሉ መነኩሴ ገጥመውኝ አያውቅም" አልኩ በልቤ።

"ገብቼ ልየው ብል በእውነት ተፈቅዱልኛላችሁ?" አልኳቸው

"አንተ ለማየት ድፈር እንጂ መፍቀድ ብቻ አይደለም አብሬህም እንዛለሁ" አሉ አባ ብርሃነ መስቀል። ለመጀመሪያ ጊዜ ኮስተር አሉ።

"እውነተዎን ነው?" አልኩኝ በመደነቅ

"ወላዲቴን" አሉ። ከዚህ በላይ ማረጋገጫ የለም አልኩና

"ታዲያ አሁን ነው?" አልኳችው።

"ያንተ ነገር ። ነገ በጠዋት ነው እንጂ" አሉ።

በዚህ ተስማምተን በበነጋው በጠዋት ለመድረስ እንድችል በአቅራቢያ ወዳለችሁ ከተማ ወደ አዲስ ዘመን ሂደን ለማደር ወሰንኩ። ወደ አዲስ ዘመን ስንሄድ ሾፌሬ

"ጋሽ ሲሳይ ይሄ ነገር አደገኛ አይመስልህም?" ብሎ በቅንነት ስጋቱን ገለጸልኝ።

"አይ ምንም ችግር አይኖርም። በዚያ ላይ አባ አሉ" ብዬ አረጋጋሁት። ያለምንም ዕቅድ አዲስ ዘመን አድረን በጠዋት ወደ ዋሻ እንድርያስ ተመለስን። አባ በእጭር ታጥቀው ጠበቁኝ። ኪዳን ሲያደርሱ የነበሩት ካህናት "እውነት ደፍራችሁ ልትገቡ ነው? ከዚህ በፊት እኮ አንድ ካህንና ዲያቆን ሞክረውት አቅቶአቸው ነው የተመለሱት" አሉ። የሚገርመው ግን ማንም የሚቃወም አልነበረም።

ከአዲስ ዘመን የገዛሁትን ደካማ ባትሪ ይዤ ወደ ዋሻው መግቢያ ጠጋ አልኩኝ። አባ "ቆይ እኔ ከፊት ልሁን" አሉና ቆርጠው ብለው እግራቸውን በደድ አደረጉ። ተከተልኩ። ቁልቁል የሚያስወርድ ነው። አንድ አምስት ሜትር እንደወረድን ፊት ለፊት የሚያስኬድ መንገድ አገኘን። ባትሪውን አጥፍቼ ባይ እጅግ ድቅድቅ ጨለማ ነው። "በስመ አብ" አልኩ። አባ የፈራሁ መሰላቸውና "አይዞህ" አሉ።

"ችግር የለም ይሂዱ" አልኩና ባትሪውን አበራሁት። አንድ ሃያ ሜትር እንደተጓዝን ውሃ የቆመበት ስፍራ ደረስን።

"ይህ ጸበል ነው። አልፎ አልፎ ጠንካራ ካህናት እየመጡ ይቀዱና አራብተው ሕሙማንን ያጠምቁበታል። ብዙ ሰው ፈውሷል" አሉ።

በእጄ ጨለፌ ራቴንና ልቤ አካባቢ ደረቴን ቀባሁት። አባ ጸበሉን ሳለመርገጥ በዳር በኩል ቋጥኙን ታከው አለፉ። እካላቸው ሲተጣጠፍና ሲራመዱ ንቃታቸው እባውንት አይመስሉም። ዕድሜያቸውን ስገምት ወደ ሰባ ይሆናል። እኔም ጸበሉን ሳልረግጥ ቋጥኙን ታክኬው አለፍኩ። ጸበሉን እንዳለፍን ዋሻው እየሰፋ መጣ። ዙሪያውን ሳየው ጣራው ከፍ ያለና ግድግዳው መደዳውን እንደ ስቴዲየም መቀመጫ ደረጃ ያለው ነው። በግምት ስፋቱ ሰሥር ሜትር ይሆናል።

"ይህ ስፍራ ቅዱሳን የሚሰበሰቡበት የነበረ ነው" አሉ አባ

"በዚህ ድቅድቅ ጨለማ?" አልኩኝ

"መብራት ይቸግራቸው ብለህ ነው የኔ ልጅ?" አሉ

ዋሻው ከመግቢያው አቅጣጫ በአሻገር ወይም ትይዩ የሚቀጥል መሆኑን ተረዳንና ወደዚያው ቀጠልን። አንድ አራት እርምጃ እንደተራመድን መንገዱ ወደ ምሥራቅ ታጠፈ። በግምት ሀሥራ አምስት ሜትር እንደተጓዝን የምንተነፍሰው የአየር ጠረንና መጠን እየተቀየረ መጣ። በጣም ከባድና የሚያቅለሸልሽ ስሜት ተሰማኝ። "አባ ይቆዩ አንድ ጊዜ" አልኩኝና ቀደምኳቸው። አንድ ሁለት እርምጃ እንደተራመድን እየሳብን ያለው አየር ንጹሕ እንዳልሆነ ገባኝ። ቆም ብዬ አእምሮዬን በደንብ ሳሰራው እየሳብን ያለው አየር በ‹ሚቴን› ጋዝ የተበከለ እንደሆነ ገባኝ። እንደዚህ ለዘመናት የተዘጉ ዋሻዎችና እዘቅቶች ከፍተኛ የዕፅዋትና የእንስሳት ብስባሽ ይከማችባቸዋል። ሚቴን ይህ ብስባሽ እርጥበትና ከፍተኛ ሙቀት ሲያገኝና ሲታፈን በዓይን የማይታዩ ነፍሳት በከፊል ሲያብላሉት የሚፈጠር ነዳጅ ጋዝ ነው። ስለዚህ ወደ ፊት መሄድ አደገኛነቱ ታየኝ።

"አባ ከዚህ በላይ መሄድ እንችልም" አልኳቸው።

"ለምን?" አሉ

"ለሕይወታችን አደገኛ ነው" አልኳቸው።

"አንተ ተመለስ። እኔ ግን ሳላገኛቸው አልመለስም" አሉኝ

"እነ ማንን?" አልኩኝ

ባትሪውን ዋሻው ግድግዳ ላይ ስላበራሁት ፊታቸውን ማየት አልቻልኩም። ዝም አሉ። "አባ ፈርቼ ሳይሆን ወደየትም ቦታ ከመድረሳችን በፊት በጋዝ ታፍነን እንሞታለን" አልኳቸው ፈርጠም ብዬ።

ዝም ብለው አልፈውኝ ሊሄዱ ሲሞክሩ

"አባታችን እንኳን መሄድ እዚህ ካለንበት ከቆዬን ሳንባችን ይቆስላል። ቆይቶም መተንፈስ እንቸገራለን። ለማንኛውም ከመሰብሰቢያው እንሂድና እንመካከር ብዬ" አስቆምኳቸው። አቅም የማነስና የመዘለፍለፍ ምልክት በሰውነቴ እየመጣ እንደሆነ ተሰማኝና አቧን እየገፋሁ ወደ ኋላ ተመለስን። ከመሰብሰቢያው ሰፍራ ቀጭ ብለን በዝምታ ቆየን።

"በቃ ለሁለተኛ ጊዜ ተመለስኩ ማለት ነው?" አሉ በሐዘን ስሜት። ከተገናኘን ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ሐዘን እንደተሰማቸው በንግግራቸው ተረዳሁ።

"ከዚህ በፊት ሞክረው ነበር?" አልኳቸው መልስ የለም። እርሳቸውን በዚህ ወቅት የሚያስደስታቸው ወደፊት በመጓዝ ብቻ እንደሆነ ገብቶኛል። ይሁንና አደገኛነቱ ለመሞከር እድል እንደማይሰጥ ስላመንኩ ሌላ ዘዴ አሰብኩና

"እየውልዎት አባታችን። በእንደዚህ ዓይነት ለዘመናት በተዘጋ ስፍራ ለመጓዝ መጠባበቂያ ኦክስጅን የተሞላ መተንፈሻና የመርዝ ማጣሪያ ጭንብል ያስፈልጋል። ይህንን እኔ ውጭ ሀገር በቅርቡ ስለምሄድ ለእኔም ለእርስዎም ይዤ እመጣና እንደገና እስከ መጨረሻው እንዘልቃለን" ብዬ አባበልኳቸው።

"የኔ ልጅ ዕድሜዬ እየገፋ ያለ ሽማግሌ እኮ ነኝ። እኔ ዛሬን እንጂ ነገን ብዙም ተስፋ አላደርገውም" አሉኝ።

"እግዜር ቸር ነው። ደግሞ እኮ ብዙ ጊዜ አልቆይም ቶሎ እመለሳለሁ" አልኳቸውና ተረጋጉ።

በመካከላችን ጸጥታ ሰፈነ። ለምን እንደሆነ እንጃ ለረጅም ጊዜ እኔም ሆንኩ እርሳቸው ጨለማ ውስጥ ጸጥ ብለን መቆየትን የመረጥን መሰለኝ። ዝምታችን ከድቅድቅ ጨለማው ጋር ተዳምሮ እንዳች ደስ የሚል ድባብ ፈጠረ። ለመጀመሪያ ጊዜ ጨለማ ውበት እንዳለው ዋሻ እንድርያስ ውስጥ አረጋገጥኩ። በጣም ደስ ይል ነበር። ልጅ ሆነን ጨለማን ቀን የሚከለክለው ያለ ይመስል

ከጋኔልና ከአስፈሪ አውሬ ጋር በማያያዝ እየተነገረን ስላደግን ሁልጊዜ ጨለማን በእንቅልፍ ብቻ እንድናሳልፈው አእምሮአችን ተቀርጾበታል። ጨለማ ጸጥታ ነው። ጨለማ ሰላም ነው። ትኩረትህን የሚሰብ ምንም የምታየው ውጫዊ ነገር የለም። የምታየው ነገር ቢኖር የውስጥህን እንተንትነን ነው። በብርሃን ሌሎችን እናያለን፤ በጨለማ ግን ራሳችንን እናያለን። ለሰው ራሱን እንደማየትና እንደማወቅ ያለ ኃይል የለውም። ጨለማ ደግሞ ይህን ኃይል ያጎናጽፍሃል። በሀሳቤ "እግዚአብሔር ብርሃንና ጨለማን ከመፍጠሩ በፊት እንዴት ባለ ሁኔታ ኑሮ ይሆን?" ብዬ አደነቅሁ።

ለረጅም ጊዜ በጸጥታ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ በቅዱሳኖቹ መሰብሰቢያ ቆየን። በመጨረሻ አባ "እንግዲህ እንኳን ሰዎቻችን እንዳይጨነቁ እንውጣ' አሉኝ። ብቆይ በወደድኩ። ግን እንዳሉት ሰው ማስጨነቅ ነው ብዬ ለመውጣት ተነሣሁ።

ከጸበሉ ስፍራ ስንደርስ አንድ ሌሊት ሲከነክነኝ የነበረ ጥያቄ ስለነበር

'አባ ' አልኩኝ

'አቤት የኔ ልጅ" አሉ

'በዚህ ለዘመናት ተጠብቆ በቆየና ከመቅደስ ጥግ በሚገኝ ምሥጢራዊ ዋሻ ድንገት የመጣሁትን እኔን እንድገባ እንዲያውም አብረውኝ ለመምጣት የወሰኑት እንዴት ነው" አልኳቸው።

'ቅድም የነገርከኝን ስቃዮች ይዘህ ከመጣህ ምክንያቱን እነግርሃለሁ። ሌላም ብዙ ብዙ ነገር፣" አሉ። ጨለማው ስለማያስተያየን የፊታቸውንና የእጃቸቸውን መልእክት አላየሁም። ንግግራቸው ግን ፈርጠም ያለ ነበር።

ከዋሻው መንገድ ስንወጣ ከቀኑ ሰባት ሰዓት ሆኖ ነበር። ከአባ ብርሃነ መስቀል ጋር በዚህ ሁኔታ ከተለያየን በኋላ ሁለት ዓመት ሞላኝ። በዚህ ጊዜ ውስጥ አምስት ጊዜ አውሮፓና አሜሪካ ሄጃለሁ።

ቃል የገባሁላቸውን መሣሪያዎች ሳላመጣ፣ ከአባም ሳልገናኝ ዛሬ በዋሻዋ ቁልፍ ሰበብ ትገዛ አሉኝ። "አቤት እኔ!። ሞልቶልኝ ተመልሼ በሄድ አባ ብርሃኔ መስቀልን በሕይወት ያላገኘኋቸው እንደሆን የምከፍለው የሞራል ዕዳ ምን ያክል ይሆን?!" አልኩ በሐዘን።

ዋሻ እንድርያስ ባየሁት ስልት መሠረት የአለንጋዋን ታጣፊ ጠፍር በቀዳዳው ወደ ውስጥ ላኩና ለመክፈት ሞከርኩ። አልተሳካልኝም። ተስፋ ሳልቆርጥ በተለያየ አቅጣጫና ርዝመት እየላኩ ሞከርኩ። ከብዙ ሙከራ በኋላ መወርወሪያው ሲለቅ ተሰማኝ። በሩን ገፋ ሳደርገው ወለል ብሎ ተከፈተልኝ። ወደ ውስጥ ለመግባት እንደ እግሬን በደጁ ሳደረግ ድንገት መልካቸው የጠቆሩ ፍጥረታት ግር ብለው ፊቴን ራሴን እየበጫጨሩኝ ወደ ወጪ ወጡ። በድንጋጤው ጭምር ሚዛኔን ስቼ ወደ ኋላዬ ወደቅሁ። እንዲያ ቀሊዬን የገፈፉት የሌሊት ወፎች መሆናቸውን ሳውቅ ተረጋግቼ በፍጥነት ገባሁና በሩን ዘጋሁት። አስፈሪ ድቅድቅ ጨለማ ዋጠኝ። የዋሻው ከፍታ በቁመቴ እንፃር ሳየው አንድ ሜትር ከሰማንያ ሳንቲ ሜትር አካባቢ ይሆናል። ወደ ጎን ስፋቱ ሁለት ሜትር ይሆናል። ትንሽ ወደፊት እንደተጓዝኩና ዐይኔ ጨለማውን እየለመደው ሲመጣ ከበሩ በተቃራኒ የብርሃን ወጋገን አየሁ።

በብርሃኑ አቅጣጫ ከውስጥ የሰማሁት ዜማ በጉልህ ይሰማኝ ጀመር። "እንዴ በቃ የቅዱሱ ጽዋ መቀመጫ ዋሻ ገባሁ ማለት ነው!" አልኩ። "እንዴት እንዲህ በቀላሉ ሊከፈት በሚችል በር ይዘጋል" እያልኩ በጥርጣሬ በቀስታ ወደፊት ተጓዝኩ። የጨለማ ዋሻው ወዴት እንደሚወስደኝ ሳላውቅ ወደፊት መሄዴን ሳስብ "ምን አይነት የአብደት ሥራ እየሠራሁ ነው?" ብዬ ለራሴ ተገረምኩ።

በግምት 50 ሜትር እየዳበስኩ እንደተጓዝኩ የብርሃኑ መጠን እየጨመረ መጣ። እይታ ውስጥ እንዳልገባ በደረቴ ተኛሁና ወደፊት በደንብ ለማየት ሞከርኩ። ከፊት ለፊቴ በግምት ዐሥራ አምስት ሜትር አካባቢ ላይ በቂ ብርሃን ያለው የዋሻ ውስጥ አዳራሽ እንዳለ ተረዳሁ። በቂ ብርሃን ላይ ያለ ሰው ጨለማ ውስጥ

ያለን በቀላሉ ማየት እንደማይችል ገመትኩና በደረቱ እየተሳብኩ ወደፊት ለመጠጋት ሞከርኩ። ትንሽ እንደተሳብኩ ከፊት ለፊቴ አስፈሪ ጨለማ የለበሰ ጉድጓድ አገኘሁ። እኔ ካለሁበት እስከ አዳራሹ ያለው ጉድጓድ ስፋት በግምት አራት ሜትር ይሆናል። የጉድጓዱ ጥልቀት አይታወቅም። ብርሃን የተሞላው የዋሻ ውስጥ አዳራሽ እኔ ከመጣሁበት አቅጣጫ ጋር በፍፁም የተለያዩ ነው። ይህ ጠንካራ መከላከያ መሆኑ ገባኝ። በጣም ገረመኝ። የውጪ በር ሲከፈት በቀጥታ መሄድ የምችል መስሎኝ እንዴት እንዲህ በቀላሉ የሚገባበት ሆነ ብዬ ያሰብኩት ስሕተት መሆኑን ተረዳሁ። ወደ ጉድጓዱ ጠርዝ ተጠግቼ ሳዳምጥ ጽሙ፣ ሲጠጥ፣ ቀረጨጭ የሚል ድምጽ ጉድጓዱን ሞልቶታል። "ተናካሽ ነፍሳት ወይም ጊንጥ ሊኖር ይችላል። አገሩ ቆላ ነው፤ መርዛማ እባቦችም ሊኖሩ ይችላሉ። እዚህ ጉድጓድ ውስጥ መውደቅ በቁም ሲያል መግባት ነው" አልኩና ወደ ኋላ ተሰቤ ቀና ስል ከዋሻው መተላለፊያ ጣሪያ ስንጥቅ ላይ አንድ እርና፣ የሚያክል እባብ ቁልቁል ይመለከተኛል። ከመቅፅበት ሰውነቴ በላብ ተዘፈቀ። በዚህ ወቅት የኢኮሎጂ ሙያዬን ከመጠቀም ውጪ አማራጭ የለኝም። እባብ እንቅስቃሴን እንጂ ረግቶ የቆመን ነገር አያይም። ስለዚህ ፍርሃቴን ተቋቁሜ እንደ እንጨት ባለሁበት ደርቄ ቀረሁ። ከደቂቃዎች በኋላ ሽሽ እያለ ወደ መጣሁበት አቅጣጫ ወደ በሩ ጣራውን እየታከከ ሄደልኝ።

ከድንጋጤዬ ተመልሼ የበለጠ ሳስተውል ከተኛሁበት በስተቀኝ በኩል ሌላ ዋሻ አለ። ወደዚያው ጠጋ አልኩና ቆምኩ። የእጣት ሽታ ለጉድ ነው። የሰማሁት ዜማ አሁን ግልጽ ሆነልኝ ። ከዳን እያደረሱ ነበር። ዜማው ከዋሻው የገደል ማሚቶ እና ከእጣን ጋር ተዳምሮ ልዩ ስሜት ይፈጥራል። ዐይኔን ለጨለማው አለማመድኩና ድሃኛውን ዋሻ መፈተሽ ጀመርኩ። ደግሞ ከዚህ ምን አውሬ ይኖር ይሆን ብዬ ተጨንቅሁ። ዙሪያውን ቃኘሁት። መውጫ የሌለው ዝግ ዋሻ ሲሆን የእህልና ሌሎች ቁሳቁሶች መቀመጫ መሆኑን ተረዳሁ።

"አሁን እዚህ እንደ ገበር እደተ በእህል ከተሞሉ ጆንያዎች መሀል ብገኝ ምን ይባላል?" ብዬ አሰብኩና ጨነቀኝ። ማፈግፈግ የማልችልበት ደረጃ ላይ ደርሻለሁ ብዬ እራሴን አበረታታሁ።

ከመታላለፊያው ቀሻ መገናኛ ላይ ቆሜ አንገቴን ወጣ አድርጌ ወደ አዳራሹ ስመለከት ወለል ብሎ ታየኝ። የአዳራሹ ወለል በቀይ ምንጣፍ ተሸፍኗል። እኔ ከቆምኩበት በአሻገርና በስተሰሜን በልዩ ሀምራዊ መጋረጃ የተሸፈነ በር አየሁ። በወርቃማ ክር የተጠለፉና ሁለቱ ከላይ ጎን ለጎን አንደኛው ከታች የሆኑ ሥዕሎች አሉ። ቅዱስ ዑራኤል ከሥነ ስቅለቱ ላይ ክቡር ደሙን በጽዋ ሲቀበልና ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ጌታን ሲገንዙት ዮሴፍም በአንድ እጁ ጽዋ ይዞ የሚያሳዩት ከላይ ሲሆን ከታች ደግሞ አንድ የተንበረከከ ሰው ከቆመ አዛውንት ፅዋ ሲቀበል ያሳያል።

"ኦ አምላኬ! እዛ ውስጥ ነው የተቀመጠው!" አልኩኝ በለሆሳስ። እንባ በዐይኔ መጥቶ ግጥም አለ። ልቤ ፍስስ አለች፤ ድንገት ተብረከረኩ፤ አቅም አልነበረኝምና ከተደገፍኩት ግለት ሸርተት ብዬ መሬት ላይ ሚዛኔን ስቼ ዝርፍጥ አልኩ።

በዝምታው የኪዳን ጸሎት እንዳበቃ ተረዳሁ። ከሐምራዊ ግምጃ ከተሸፈነው በር ማዕዘኑን አልፎ በስተምሥራቅ ሌላ ክፍት ቀሻ በር ደግሞ አየሁ። ለእኔ ትይዩ ነው ግን ጨለማ ነው። ሦስተኛው በር ደግሞ ከሐምራዊ በር ትይዩ በስተደቡብ ያለ ሲሆን ሙሉ ብርሃን የሚገባበት መውጫ በር መሆኑን ተረዳሁ። ከዚሩ ውጭ የሚታይ ነገር የለም ስለዚህ በዚያ በኩል ገደል ነው ማለት ነው።

ትንሽ ቆይቶ አንድ ልብሰ ተክህኖ የለበሱ መነኮስ መጋረጃውን ገልጠው ወጡ። መስቀል ይዘዋል። እኔ በቆምኩበት ቀሻ ግድግዳ ለሌሎች ሁለት ወይባ የለበሱ መነኮሳት ሄዱና በመስቀል አንዳቸው ሌላኛውን ባረኩ። ሁለቱ ክህነት ያላቸው መነኩሳት ናቸው ማለት ነው አልኩ።

አቤት እርጋታቸውና የፊታቸው ጸዳል!። ሰው ሳይሆን መልአክ የማይ መሰለኝ። ከመጋረጃው የወጡት መነኮሴ አሳልመው ሲያበቁ ማዶ ወደ አለው ጨለማ ዋሻ ገቡና ልብሰ ተክህኖውን አውልቀው ወይባቸውን ለብሰው ወጡ። በመጨረሻ ሁሉም ተያይዘው የፀሐይ ጨረርና ብርሃን ወደሚያስገበው በር አመሩ።

አሁን አዳራሹ ባዶ ነው። እኔ ከአለሁበት እስከ ሐምራዊው መጋረጃ ድረስ ያለው ርቀት ከሀ/ሥር ሜትር በላይ አይሆንም። ችግሩ ግን ሀራት ሜትር ስፋት ያለው ጉድጓድ ከመካከል አለ። "ስንት ሜትር መዝለል እችላለሁ?" አልኩ። አራት ሜትር መዝለል አልችልም። ልዝለል ብል እንኳን መንደርደር እና ወደ ላይ መነሳት ከዚያም ወደፊት መወርወር ያስፈልጋል። 1.8 ሜትር ቁመት ያለው ዋሻ ይህን ለማድረግ አያስችለኝም። የባሰ ውስጡ ምን እንዳለና ርቀቱ ወደማይታወቅ ጉድጓድ ገብቶ ከመሰባበር በቀር ውጤት የለውም። መንጠላጠያ ገመድ ሆነ ሌላ መሸጋገሪያ የለም። ቅዱሳኖቹን መጠየቅ የሚታሰብ አይደለም። ሌላው ቀርቶ እዚህ መኖሬን ቢያውቁ ምን ሊከተል እንደሚችል አላውቅም። እምነት የጎደለኝና ለዚህ ቦታ የተገባሁ አለመሆኔ ብቻ ሳይሆን ከዓለም ተሰውሮ በተቀመጠ የተከበረ ቅዱስ ቅርስ መጠበቂያ ስፍራ ያለፈቃድ የገባሁ ወንጀለኛ ነኝና። የሆነው ሁኖ ሐምራዊውን መጋረጃና ወርቃማውን ጥልፍ ባየሁ ቁጥር ተወርወር፣ ተወርወር የሚለኝ ስሜት መጣ።

በመሐሉ የሰው ኮቴ የሰማሁ መሰለኝና አንገቴን ትንሽ ብቅ አድርጌ ሳይ ሁለት መነኮሳት ረጅም ሳንቃ(ጣውላ) ከፊትና ከኋላ ሆነው ከውጭው በር ወደ እኔ አቅጣጫ ሲመጡ አየሁ። ራሴን ጨለማው ውስጥ ሰውሬ የሚያደርጉትን በትኩረት እከታተል ጀመር። ከፊት የነበሩት መነኮሴ የሳንቃውን ጠርዝ ከአዳራሹ በኩል ካለው የጉድጓዱ ጠርዝ ላይ አስቀመጡና ወደ ማዶ ይገፉት ጀመር።

"የእምላክ ያለህ መሸገሪያ ነው! ወደ እኔ ሊመጡ ነው!" አልኩና በድንጋጤ ደርቄ ቀረሁ። ሳንቃውን በደንብ ገፍተው በዚህም በዚያም በኩል ከጉድጓዱ ጫፍ በደንብ እንዲቆነጥጥ አድርገው ካስቀመጡ በኋላ ተከታትለው መጡ። በደመ ነፍስ ዋሻው ውስጥ ከተደረደሩት ጆንያዎች መካከል ተወሸቅኩ። ወደ ውጭ ሊወጡ ይሆን ብዬ ሳስብ እኔ ወደ ተደበቅሁበት ጨለማ ዋሻ ታጥፈው ገቡና ተጋግዘው በዳር በኩል አንዱን ጆንያ አንስተው ፊትና ኋላ ተሸክመው ተመልሰው በሳንቃው ላይ ተሻገሩ። በፍጥነት ተከተልኩና አዳራሹን ስቃኝ ሦስተኛው መነኩሴ የሉም ሁለቱ ደግሞ ፊታቸውን ወደ በሩ አዙረው እየወጡ ነው።

"ሰዓቱ አሁን ነው!" አልኩ። ተመልሰው መጥተው ሳንቃውን ከማንሳታቸው በፊት ይህን እድል መጠቀም አለብኝ አልኩና ጫማዬን በፍጥነት አውልቄ በጣውላው ተሻግሬ አዳራሹን አቋርጬ በትይዩ ካለው ጨለማ ዋሻ ውስጥ ዘልዬ ገባሁ። በአጠቃላይ ከዐሥር ሴኮንዶች በላይ አልፈጀብኝም። ትንፋሼን ቀጥ አድርጌ ታይቼ እንደሆን ብዬ ለማዳመጥ ሞከርኩ። ከልቤ ትርታ በስተቀር ሁሉም ነገር ጸጥ እንዳለ ነው። እኔ ዋሻው ውስጥ ገብቼ አፍታ ሳልቆይ እንደገመትኩት አንደኛው ቅዱስ መጥተው ሳንቃውን አንስተው ወደ ውጭ ይዘውት ወጡ።

"እፎይ!" አልኩ። አሁን በወርቃማው ሥዕል በአሸበረቀው ሐምራዊ መጋረጃና በእኔ መካከል ያለው ርቀት ከሦስት ሜትር በላይ አይሆንም። "ምንድን ነው ማድረግ ያለብኝ? እንደዚህኛው ዋሻ መቼም ዘልዬ አልገባ። ምክንያቱም ታቦት ሊኖር ይችላል። ምንም ቢሆን እንጥፍጣፊ እምነት ሊኖረኝ ይችላልና መቅደስ አልደፍርም። ሳላየው መመለስ ግን የሚታሰብ አይደለም። ለምን ይህን ያክል ደከምኩ?!"

"አዎን! ልክ በአሁኑ ፍጥነት ተወርውሬ ሐምራዊውን መጋረጃ መግለጥ፤ ከውጭ የሚገባው ብርሃን ደግሞ ሙሉ ለሙሉ ማየት ያስችለኛል። ከዚያም ይህን ውብ ሐምራዊ መጋረጃ ገልጬ የማየው ቅዱስ ጽዋ ሁሉን ያስችለኛል። ከማየቱ የሚመነጭ ማርፊትም፣ መታሰርም፣ ሌላ

ቅጣትም፣ እርካታዬን አያስቀሩትም፣ ደስታዬንም አያደበዝዙትም። መጋረጃውን ሳልገልጥ ብቀር ግን ቀሪ ሕይወቴ ታማሚ እንደሚሆን አውቀዋለሁ። ስለዚህ አሁን መሆን ወይም አለመሆን እንዳለው ሼክስፒር ማየት ወይም አለማየት ነው" ብዬ በራሴ ላይ ፈረድኩ።

"ጊዜ መግዛት ደግሞ አለማየትን ሊያመጣ ይችላል" አልኩና " አ አምላኬ! ይህን ሁሉ የደከምኩት ቅዱሱን ጽዋ ለማየት ነው። ቅዱሱን ጽዋ ለማየት ይህን ያክል የተጓዝኩት ደግሞ ለአንተ ባለኝ ፍቅር ነው። እናም ፈቃድህ ይሁን!" ብዬ ባለሁበት ሆንኩና በስሜት ፊቴን ወደ ሐምራዊ መጋረጃ አዙሬ መሬት ላይ ለሴኮንዶች በግንባሬ ተደፋሁ።

በዚሁ ቅጽበት የእግር ኮቴ ከሆነ ዜማ ጋር ወደ እኔ አቅጣጫ ሲመጣ ተሰማኝና ሆዌ ፍስስ አለ። አንደኛው ቅዱስ እኔ ወዳለሁበት ክፍል እየመጡ እንደሆነ ስረዳ በደመነፍስ ወደ ግድግዳው ማዕዘን ሄጄ ኩርምት ብዬ ቁጭ አልኩ። ክፍሉ ጨለማ ስለሆነ ሙሉ በሙሉ ባያስተያይም የሆነ ነገር የሚፈልጉ ይመስላሉ። ሁሉንም አካባቢ አዳርሰው ወደ እኔ አቅጣጫ መጡ።

'አሁን አይቻው አልነበረም?' አሉ ለራሳቸው።

"አባቴ ይቅር ይበሉኝ!" ብዬ ልማጸናቸው ዳዳኝና ድምፄ ጨርሶ ከዳኝ። የእግሮቼን እጣቶች በእግራቸው ረግጠውኝ አለፉና 'ይኸውና' ብለው የሆነ ነገር አንስተው ተመልሰው ወደ ውጭ ወጡ። ዝልፍልፍ ብዬ መሬት ላይ ተጋደምኩ። ድንጋጤዬ አእምሮዬን ስላደነዘዘው ሰውነቴ አልታዘዝህ አለኝ። ደጋግሜ አየር ወደ ሳንባዬ እየሳብኩ ሰውነቴን ለማፍታታትና ለመቆጣጠር ጥረት አደርግሁ።

ከደቂቃዎች በኋላ ብድግ አልኩና በእግሬ እጣቶች እየቆምኩ ከሽታ ሳላሰማ በሚያስገርም ፍጥነት መጋረጃው ላይ ደረስኩ። ልቤ ድው... ድው... እያለ ከታች ወደ ላይ ከፍ ወደ ግራ በፍጥነት ለመግለጥና ቅዱሱን ጽዋ ለማየትና ለመሳለም እየተንሰፍሰፍኩ የመጋረጃዎቹን ጫፍ በድፍረት ጥርሴን ነክሼ ያዝኩት።

# ምዕራፍ ዐሥራ ስምንት

ራሴን ለማንቃንቅ ብሞክር በጣም ከበደኝ። እጅግ ከባድ ራስ ምታት ተሰማኝ። እጅና እግሬ የእኔ አልመሰለህ አለኝ። እንደምንም ዐይኔን ስገልጥ ነጭ ክፍል ውስጥ ተኝቻለሁ። በሰመመን ውስጥ እንደቆየሁ ገመትኩ። እንደምንም ከንፈሬን አላቅቄ እያማጥኩ

" የት ነው ያለሁት?" አልኩ።

"ንቃህ ኃይለ ጊዮርጊስ? ተመስገን ተመስገን ተመስገን ችሩ መድኃኔዓለም!" በደንብ ዐይኔን ገልጬ ሳይ እማሆይ ዕሌት ማርያም እጆቼን በጭንቀት ይዘዋቸዋል። የግሊክስ መስሚ መርፌ ክንዴ ላይ ተተክሏል።

"የት ነው ያለሁት እማሆይ?" አልኳቸው

"ሞላሊ ጤና ጣቢያ "

"እንዴት መጣሁ? ምንድን ነው የሆንኩት?"

"ጀመረህ እንግዲህ። ይሄ የማያልቀው ጥያቄህ ነው ችግር ያመጣብህ። አሁን ዝም ብለህ ዐረፍ በል" አሉና እርሳቸው ምስጋና ለፈጣሪ ማቅረባቸውን ቀጠሉ።

ዐይኔን እደገና ጨፍኜ በጸጥታ ቆየሁ።ራሴን ለማንቃት በጣርኩ ቁጥር ከፍተኛ የሕመም ስቃይ መላ አካሌን ይወርረዋል። ያም ሆኖ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ራሴን እስከስት ድረስ የሆነውን ሁሉ ማስታወስ ጀመርኩና አለቀስኩ።

በማግስቱ ከራስ ምታት በስተቀር ተሻለኝና ተደግፌ መንቀሳቀስ ቻልኩ።ሆኖም እማሆይን እንዴት ጤና ማቢያ እንደመጣሁ ጠየኳቸው።

"ካኪዳን መልስ አቡት ስሄድ የለህም። ብዙ ስትቆይ ወደ ቅዱሱ ተራራ እንደሄድክ ገመትኩ። በጣም ተጨነኩ። በመጨረሻ ሊደርስብህ የሚችለውን ገምቼ ወደ ተራራው ስወጣ መገናኛው ስፍራ ላይ አባቶች አስተኝተው ጸሎት ሲያደርሱልህ ደረስኩ። እንደ ምንም ሸለቆው ድረስ እነሱ አደረሱልኝና ከዚያ በኋላ ሀገሬውን ለምኜ በቃሬዛ ወደዚህ አመጣሁህ" አሉ።

"እዚህ ስንት ቀን ቆየሁ? ዛሬ ቀኑ ማነው?" አልኳቸው። ቀኑን ሲነግሩኝ ሁለት ቀን ሳልነቃ እንደቆየሁ ገባኝ።

እያለቀስኩ "እማሆይ ይቅር ይበሉኝ። እዚህ ሁሉ ችግር ስለከተትኩዎት" አልኩ።

"የኔን ድካምና ችግር ተወው። እንኳን መድኃኔዓለም ምሕረት ላከልህ እንጅ" አሉ እርሳቸውም እያለቀሱ።

በቅዱሱ ጥሻ ውስጥ ምን እንደደረሰብኝ ቁልጭ ብሎ ታወሰኝ። ከጨለማው ክፍል በፍጥነት ወጥቼ በወርቃማ ጥልፍ ሥዕል ያማረውን ሐምራዊ መጋረጃ ጫፉን በእጄ አጥብቄ ይዤ ከታች ወደ ላይ ከቀኝ ወደ ግራ በፍጥነት ገለጥ ሳደርገው ድንገት ምንነቱን ያላወቅሁት የብርሃን ጎርፍ ከአስደንጋጭ መብረቃዊ ኃይል ጋር ተጣምሮ ወደ ላይ አንሥቶ ማዶ ካለው የዋሻ ቋጥኝ ጋር አላተመኝ። ድንጋጤና ከባድ ሕመም ተዳምረው ወዲያው ራሴን አሳቱኝ። ከዚያ በኋላ የሆነውን የማስታውሰው ነገር አይደለም። በመጨረሻ አሁን በእማሆይ ዕሌተ ማርያም አስታማሚነት ራሴን ሞላሊ ጤና ማቢያ አገኘሁት። "አለመሞቴ ተመስገን ነው!" አልኩና እንባዬን መጠራረግ ጀመርሁ።

በሚቀጥለው ሌሊት በጣም ጥሩ እንቅልፍ ተኛሁ። ሕመሙም ከጥላ ኃይል ለቀቀኝ። ሆኖም የሆነው ነገር በኅሊናዬ እየመጣ ማስቃዠቱ አልቀረልኝም ነበር። ጠዋት ከእንቅልፌ ስነቃ አባ አክሊሉ ከእማሆይ ዕሴተ ማርያም ጋር ቆመው አየኋቸው።

"እንደምን አደርክ የኔ ልጅ?" አሉኝ አባ አክሊሉ በሐዘኔታ ገጽ ሆነው።

"እግዚር ይመስገን አባታችን!" አልኩኝ እንደማፈር ብዬ። ጠጋ አሉና በመስቀል እሸት እሸት አድርገው አሳለሙኝ።

"አባቴ ይፍቱኝ!" አልኩ። ይህንን ቃል ከልጅነት እስከ እውቀት ለበርካታ ጊዜያት ብየዋለሁ። እንዲዚህ ሰዓት ግን ከልቤ በመነጨ ስሜት ብየው አላውቅም።

"እግዚአብሔር ይፍታህ" አሉኝና ነርሷ መውጣቷን ጠብቀው እራሴን እሸት እሸት አደረጉት

"አሁንም ቅዱሱን የኪዳን ቅርስ ማየት ትፈልጋለህ?" አሉኝ

የብርሃን ኃረፉ ከመብረቃዊው ኃይል ጋር ድንገት በአእምሮዬ ብልጭ ያለ መሰለኝ።

እርሳቸው ሆን ብለዉ የጋፊጡኝ ይመስል ደንገጥ ብዬ "አባታችን አልፈልግም!" አልኳቸው

"አሁን ከሕመምህ ተፈወስክ፣ ወደ ልብህም ተመለስክ" አሉና መስቀላቸውን ግንባሬ ላይ ደገፍ አደርገው ሲያቡቱ

"እንደዚህ ልቡና ከገዛህና ማስተዋልን ጥንዘብ ካደረክ፣ ከዋድራዴና በወረት ከመናዋ ራስክን ካቀብክ ቅዱሱን የኪዳን ቅርስ ማየት ትችል ይሆናል" አሉ።

"አባታችን እግዚር ይስጥልኝ። ነገር ግን መቼም ቢሆን ለማየት አልሻም" አልኳቸው

"እንዴ ለምን?" አለ፡ እማሆይ በመገረም

"ወደዚህ ክቡር ቅርስ ወደ ቅዱሱ ጽዋ ለመቅረብም ሆነ ለማየት እንደማይገባኝ አሁን ገብቶኛልና፤" አልኳቸው ፈርጠም ብዬ።

"እየሀ የኔ ልጅ! የተገባሀ ባለመሆንህ ሳይሆን በጥበብና በዘዴ ለወሬ ፍጆታ ለማየት በመሞከርህ ነው። አሁን ግን በትሕትና በእምነት ስለእምነት ታየዋለህ!" አሉኝ።

"ግድየለም አባታችን ለዚህ ታላቅ ጸጋ የበቃሁ ብሆን ኖሮ በፈትም በእምነት መቀበል እችል ነበር። እምነትን በእምነት ባላገኘውም አሁን ግን እምነትን በኃይል አገኘቸዋለሁ። በኃይል የሚያምን ኃይል ይገዛዋል ተብሏልና። ከእንግዲህ በዚች ምሥጢራዊ ቅድስት ሀገር ቀሪ ዘመኔን በሰላምና ከትጋት በሚገኝ እርካታ ብቻ ለማሳለፍ እሞክራለሁ።"

"እንደኔ በኃይልም ይሁን እንደ እናንተ በእምነት መቀበል ለሚፈቅዱት ግን እላችኋለሁ፦

"በካሰዋ በኮሳ"

"ውስተ ከርሠ ሰመ ሰንበ ሐቃባዊት ደሄሱ"

[illegible] ተቀብዬ ግን [illegible] ያህል ብቻ ድንገት የጀመርኩት ገረፍ ገረፍ ዓይነት (scanning) ሳላስበው እንደ ውኃ መላት ጎትቶ ለሰነብቶኝ በዚያው ሲያሳድረኝ ይህ የመጀመሪያዬ ነበር፡፡ ንባቤን ከጨረስኩ በኋላ የመጀመሪያው ጥያቄዬ "እንዴት ሊጽፈው ቻለ?" የሚል ነበር፡፡ ምክንያቱም እኔ የማውቀው ዓለማየሁ ዋሴ (PhD) በተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት ዘርፍ የሥነ ምህዳር ባለሙያ (Ecologist) ነው፡፡ በርግጥ በምርምር ሥራው እንቁ የተባለ፣ ዓለም አቀፍ የሥነ ሕይወት ምርምር ላይ ባስመዘገበው አዲስ ግኝትም ATBC (Association for Tropical Biological Conservation - የትሮፒካል አካባቢ ሥነ ሕይወት ጥበቃ ማኅበር) በየዓመቱ የሚያዘጋጀውን የ2007 (እ. ኤ. አ.) የአልወን ጀንትሪ ሽልማት (Alwyn Gentry Award) ያገኘ፣ በአሁኑ ጊዜም ከአሜሪካ የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በምርምር የሚሠራና በዚያው ያሉ የሁለተኛ ዲግሪና የሦስተኛ ዲግሪ ተማሪዎችን ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ የሚያማክር፣ በየጊዜው የምርምር ሥራዎቹን በመስኩ ከፍተኛ ዕውቅና ባላቸው ጆርናሎች ላይ የሚያሳትም፣ በአጭሩ በራሱ የሙያ መስክ ስመ ገናና ከሆኑት ተመራማሪዎች አንዱ እንደሆነ በደንብ አውቃለሁ፡፡ አንዳንድ ሥራዎቹን ለማንበብ፣ ሌሎች ተመራማሪዎች ስለእርሱ ከጻፏቸውም ጥቂቶቹን ለማየት ዕድሉን አግኝቻለሁ፡፡ ሆኖም በዚህ መልኩ ሥራ ይዞ ብቅ ይላል የሚል ግምት አልነበረኝም፡፡ ጥያቄዬ የተፈጠረው እንዲህ ዓይነት ባለሞያ ወደ ሥነ ጽሑፍ ድንገት ለምን ብቅ አለ ከሚል አልነበረም፡፡ እንደ [illegible] የሥነ ጽሑፍ [illegible] ብዙ ጸሐፍት የሥነ ጽሑፍ ባለሞያዎች እንዳልሆኑ አውቃለሁና፡፡ ጥያቄና መደነቅ የፈጠሩብኝ ሁለት ጉዳዮች ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ይቶት የተነሣው ጉዳይ ሲሆን ሁለተኛውና ዋናው ግን እንደ በምርምር ሥራ እንቁ የተባለ ሰው፣ ብዙ ሥራዎችን ከማሳተም የተነሣም ያገን በምርምር ዘዴና በመርህ አብዝቶ የታሰረ የምርምር ጽሑፍ ቀጥብነትን ድንበር ተሻግሮ እንዲህ ዓይነት የትረካ ችሎታም በመጎናጸፉ ነው፡፡ ምንም እንኳ የትረካ ችሎታው ጥያቄም መደነቅም ቢፈጥርብኝም የምርምር ችሎታውና ከዚሁ ሥራው ጋር በተገናኘ ያደረጋቸው ዓለም አቀፍ ጉዞዎች፣ የመስክ ሥራዎች፣ ገጠመኞችና ሌሎቹም ሁነቶች መጽሐፉን ከዋናውና አስደናቂው ታሪክ ባሻገር ብዙ አጫጭር ታሪኮችን እንዲያዋሕድ፣ የተለየ ጭብጥ እንዲያገኝ፣ የሰላ ሂስ እንዲያቀርብና ተወዳጅ አቀራረብ እንዲኖረው ያስቻለው ይመስለኛል፡፡ ስለዚህም ጥብቅ ሥራ ባቀዱ ቀን ንባቡን እንዳይጀምሩ እመክረዎታለሁ፣ ሥራዎን ረስተው ተመስጠው ከቀሩ በኋላ ሣልሠራ ቀረሁ እንዳይሉ አስጋለሁና፡፡

ብርሃኑ አድማስ (ዲያቆን፣ በፊሎሎጂ ሁለተኛ ዲግሪ)

ዋጋ 65.00 ብር

ረቂቁን ተቀብለው ግዢ [illegible] ያህል ገፆ ድንገት የጀመርኩት ገረፍ ገረፍ [illegible] (scanning) ሳላስበው እንደ ውኃ ሙላት ጎትቶ ለጠንቦቶቹ በዚያው ሊያሳድረኝ ይህ የመጀመሪያዬ ነበር። ንባቤን ከጨረስኩ በኋላ የመጀመሪያው ጥያቄዬ "እንዴት ሊጽፈው ቻለ?" የሚል ነበር። ምክንያቱም እኔ የማውቀው ዓለማየሁ ዋሴ (PhD) በተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት ዘርፍ የሥነ ምህዳር ባለሙያ (Ecologist) ነው። በርግጥ በምርምር ሥራው እንቱ የተባለ፣ ዓለም አቀፍ የሥነ ሕይወት ምርምር ላይ ባስመዘገበው አዲስ ግኝትም ATBC (Association for Tropical Biological Conservation - የትሮፒካ አካባቢ ሥነ ሕይወት ጥበቃ ማኅበር) በየዓመቱ የሚያዘጋጀውን የ2007 (እ. ኤ. አ.) የአልዊን ጀንትሪ ሽልማት (Alwyn Gentry Award) ያገኘ፣ በአሁኑ ጊዜም ከአሜሪካ የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በምርምር የሚሠራና በዚያው ያሉ የሁለተኛ ዲግሪና የሦስተኛ ዲግሪ ተማሪዎችን ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ የሚያማክር፣ በየጊዜው የምርምር ሥራዎቹን በመስኩ ከፍተኛ ዕውቅና ባላቸው ጆርናሎች ላይ የሚያሳትም፣ በአጭሩ በራሱ የሙያ መስክ ስመ ገናና ከሆኑት ተመራማሪዎች አንዱ እንደሆነ በደንብ አውቃለሁ። አንዳንድ ሥራዎቹን ለማንበብ፣ ሌሎች ተመራማሪዎች ስለእርሱ ከጻፏቸውም ጥቂቶቹን ለማየት ዕድሉን አግኝቻለሁ። ሆኖም በዚህ መልኩ ሥራ ይዞ ብቅ ይላል የሚል ግምት አልነበረኝም። ጥያቄዬ የተፈጠረው እንዲህ ዓይነት ባለሙያ ወደ ሥነ ጽሑፍ ድንገት ለምን ብቅ አለ ከሚል [illegible] አልነበረም። እንደ [illegible] ብዙ ጸሐፍት የሥነ ጽሑፍ ባለሞያዎች እንዳልሆኑ አውቃለሁና። የመጀመሪያው ጥያቄና መደነቅ የፈጠሩብኝ ሁለት ጉዳዮች ናቸው። የመጀመሪያው ይዘት የተነካው ጉዳይ ሲሆን ሁለተኛውና ዋናው ግን እንደ በምርምር ሥራ እንቱ የተባለ ሰው፣ ብዙ ሥራዎችን ከማሳተም የተነካም ያንን በምርምር ዘዴና በመርህ አብዝቶ የታሰረ የምርምር ጽሑፍ ቁጥብነትን ድንበር ተሻግሮ እንዲህ ዓይነት የትረካ ችሎታም በመጎናጸፉ ነው። ምንም እንኳ የትረካ ችሎታው ጥያቄም መደነቅም ቢፈጥርብኝም የምርምር ችሎታውና ከዚሁ ሥራው ጋር በተገናኘ ያደረጋቸው ዓለም አቀፍ ጉዞዎች፣ የመስክ ሥራዎች፣ ገጠመኞቹና ሌሎቹም ሁነቶች መጽሐፉን ከዋናውና አስደናቂው ታሪክ ባሻገር ብዙ አጫጭር ታሪኮችን እንዲያዋሕድ፣ የተለየ ጭብጥ እንዲያነሳ፣ የሰላ ሂስ እንዲያቀርብና ተወዳጅ አቀራረብ እንዲኖረው ያስቻለው ይመስለኛል። ስለዚህም ጥበቃ ሥራዎን ሥራ ባቀዱ ቀን ንባቡን እንዳይጀምሩ እመክረዎታለሁ፣ ሥራዎን ረስተው ተመስጠው ከቆዩ በኋላ ማለቂያ ቀረሁ እንዳይሉ እሰጋለሁና።

ብርሃኑ አድማስ (ዲያቆን፣ በፊሎሎጂ ሁለተኛ ዲግሪ)

ዋጋ 65.00 ብር